# መግቢያ

## ‹‹ከትውልድ ስለ ትውልድ››

መደመር በለውጥ መንገድ ላይ የተወለደ የአተያይ ፓራዳይም ነው። ቁስሎች እንዲጠጉ፤ ህመሞች እንዲድኑ፤ ችግሮች እንዲፈቱ፤ ፈተናዎች እንዲታለፉ፤ ያለፈውን ጉዟችንን መመልከቻና የቀጣይ ጉዟችን ጠቋሚ፤ አዲስ የእሳቤ ማዕቀፍ ነው። የመደመር ጽንሰ ሐሳብ ባለፍኩባቸው የሕይወት አጋጣሚዎችና ሂደቶች፤ ባጋጠሙኝ መልካም ዕድሎችና ፈተናዎች፤ በተዋወቅኳቸው ሐሳቦች፤ ሀገራችን ባጋጠማት ፈተናን የ‹‹ምን መፍትሔ እንስጥ›› ጭንቀት ውስጥ የተቀመመ ነው።

የተለያዩ ሀገራትን በጎበኘሁባቸው ጊዜያት በተገነዘብኳቸው እውነቶችና በቀሰምኳቸው ልምዶች፤ ባነበብኳቸው ጽሁፎች፤ ባካበትኳቸው መረጃዎችና ዕውቀቶች ተቀርጾ የዛሬውን መልክ ይዟል። ያሳለፍኩት ሕይወት ራሱ መደመርን የወለደ የመደመር መንገድ ነበር ማለት እችላለሁ።

የመደመር መንገድ ያለፍኩበት የሕይወት መሥመር ውጤት ነው። መደመር በሕይወቴ መሥመር የተወለደ እሳቤና የሕይወት ጉዞዬ ልምድ ውጤት ቢሆንም፤ ሐሰቡ የሚያጠነጥነው ግን ስለሀገር ዛሬና ነገ ነው። ባሳለፍኳቸው ውጣ ውረዶች ውስጥ ያጋጠሙኝ ፈተናዎችና ችግሮች ባሳደሩት ተፅዕኖ የአስተሳሰብ ፓራዳይም ፈጥሮ የተወለደ ቢሆንም፤ ትኩረቱ በዛሬ ውስጥ የተገኘን ዕድል ተጠቅሞ በነገ ውስጥ የተቀየሰን ተስፋ ስለመገንባት ነው። ትውልድን በመሥራት ሀገር ስለመገንባት!

የመደመር ነገ - ትውልድ ነው። እርግጠኛው ሀገር የመገንቢያ መንገድም ትውልድን በማነጽ ውስጥ ያለው ምስጢር ነው። የዛሬ መልም ውጤቶችና እሴቶች ቀያጥነት የሚረጋገጠው በትውልድ ውስጥ ሲሠርፁ ነው። የመደመር ግብ ሀገር የሚያጠነክር እሴትን ባህል መገንባት ስለሆነ፤ ራሱን ትውልድ የሚግባባበትና የሚነጋገርበት ቋንቋ ለማድረግ ይተልማል። በፍቅር፤ በወንድማማችነትና በኅብር የሚግባባ ትውልድን ለማነጽ።

መደመር የዛሬን ትውልድ ዐቅም በማሰባሰብ፤ ካለፈው ትውልድ የወረሻቸውን ጥንካሬዎች በማሳደግ፤ እንዲሁም ክፍተቶችን በማረም፤ የቀጣዩን (የመደመር) ትውልድ የምንመከትበት የሃሳብ መነጽርና የመግባቢያ ሰነዳችን ነው። ይህ የትውልድ ግንበታ እውን እንዲሆን፤ በተገዳዳሪ አፍራሽ እይታዎች (ፓራዳይሞች) ውስጥ የመደመር ዕይታንና እሴትን ያለማሰለስ በትጋት ማሥረጽና ማጠናከርን ይጠይቃል።

‹‹የመደመር መንገድ›› የተሰኘው መጽሐፌ ተከታይ የሆነው ይሕ ‹‹የመደመር ትውልድ›› በሚል የተቀመረ መድብል፤ ትውልድን ከትውልድ ለመደመር የተቀየሰ መንገድ ነው። ካለፈው ትውልድ የተማረ የዛሬው ትውልድ፤ ነገ ሀገርን ተረክቦ ለሚመራው አዲስ ትውልድ የሚያሰማው ታላቅ የአደራ ደወል ነው። ከትውልድ ለትውልድ ስለ ትውልድ የቀረበ ሀገራዊ ጥሪ።

### ዐብይ አሕመድ

አዲስ አበባ፤ 2015 ዓ.ም

# ክፍል አንድ

# የትውልድ አረዳድና ገመድ

‹‹ትውልድ ይሄዳል፤ ትውልድ ይመጣል፤
ምድር ግን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች››
መክ. 1፡4

# ምዕራፍ አንድ

## የትውልድ ብያኔ ….. ከትውልድ ክያኔ

### የአባት ዕዳ ለልጅ…

ልጅ ከአባት የተነጠለ ኑሮ የለውም፡፡ የአባት ወረት ለልጅ ይቆያል፡፡ የአባት ዕዳም ለልጅ ይቀመጣል፡፡ አባት ብኩንና ስንፍና የተጫነው ከሆነ ልጅ መከራውን ተሸካሚ ይሆናል፡፡ አባት ብርቱ፣ መልካምና ለቤተሰቦቹ ፍቅር የሚሰጥ ከሆነ ደግሞ በረከቱን ለልጁ ያቋድሳል፡፡ ልጅን ጠንክሮ ያሳደገ አባት ፍሬውን መልሶ ይበላል፡፡ ቤተሰብ የተሰራው ወላጅ ለልጅ፡ ልጅም ለወላጅ በሚሰጠው የትውልድ ሰንሰለት ውስጥ ነው፡፡

ትውልድ በአንድ ቤተሰብ ደረጃ ሲታይ፤ ወደላይና ወደታች የሚፈስ ወንዝ ነው፡፡ አባትና እናት፣ አያት፣ ቅድመ አያት እያለ ወደላይ፤ ልጅ፣ የልጅ ልጅ በማለትም ወደታች የሚተረተር የቤተሰብ ሰንሰለት ነው፡፡ ልጅ የነበረው አባት፤ አባት የነበረው አያት፤ ቅድመ አያት ….እየሆነ የሚፈጥረው ቅጥልጣይ ገመድ ነው፡፡ የቤተሰቡ

ጥንካሬና መልካም ስም በእያንዳንዱ አስተዋጽዖና መልካም ሥራ ላይ ይመሰረታል። ስለዚህም የቀደመው ትውልድ ቀጣዩ ትውልድ በመልካም እሴቶች የታነጸ እንዲሆን አበክሮ ይሰራል።

ሀገር የምትሰራውም እንደ ቤተሰብ በትውልድ ቅጥልጣይ ውስጥ ነው። በሀገር ደረጃ ትውልድ ሲባል በተቀራራቢ ዕድሜ ደረጃ የሚገኙ፣ በተመሳሳይ የታሪክ አጋጣሚዎች ውስጥ ያለፉ፣ በዘመኑ የእሳቤ ማዕቀፍ ውስጥ የተቀረጹና፣ ተመሳሳይ ጠባይን የሚያንጸባርቁ የየዘመኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ናቸው። ማብቂያ የሌለው የሀገር ግንባታ ሂደት የሚከወነው፤ የየዘመኑ ትውልድ በሚሰራው መልካም ሥራና በሚቀጥለው ትውልድ ላይ በሚፈጥረው መልካም ተፅዕኖ ላይ ተመስርቶ ነው።

ትውልዶች በየዘመኑ በሚፈጠሩ ታሪካዊ ፈተናዎችና ዕድሎች ውስጥ ስለሚያልፉ፤ ፈተናዎቹን ለማለፍ እና ዕድሎቹን ለመጠቀም በሚያደርጉት ጉዞ ውስጥ ባህሪያቸውና ማንነታቸው መልክ ይይዛል። ለብቻው የሚፈጠር ትውልድ የለም። የቀደመው ትውልድ ውሳኔ የማይነካው፤ በምርጫውም የቀጣይ ትውልድን ዕጣ ፈንታ የማይወስን፤ ትውልድ ሊኖር አይችልም። ትውልድ ሁሉ ባገኘውና ባጣው የህይወት ልምምድ፤ የራሱን ዘመን ዕድልና ትግል በተወጣበት ልክ መልኩንና ትሩፋቱን ይወስናል።

‹‹የኢኮኖሚ ቀውስ የቤተሰቦቹን ንግድ ሲያከስር፣ ግብርናቸውን ዋጋ ሲያሳጣ፣ ተስፋቸውን ሲያመነምን ተመልክቷል። በአስከፊ ሁኔታ ውስጥ ‹‹አንድ ቀን›› እያሉ የመጪውን ዘመን በጎነት በምኞት ሲጠባበቁ አይቷል። የተከሰተው የኢኮኖሚ ቀውስ አባርቶም የኢኮኖሚው ማገገም አዲስ ተስፋን ሲፈጥር፤ ነገር ግን ይኽ ተስፋ ብዙ ሳይቆይ ጦርነት በሚባል ነገር ሲቆረቁዝ ከማየት በዘለለ፣ በለጋ ዕድሜው የትምህርት ቤት መለዮውን ቀይሮ ወታደራዊ መለዮ በመልበስ በአስከፊው ጦርነት ውስጥ ሀገሩን ለመጠበቅ ቆሟል።››

ይኽ ታሪክ አንድ ሰውን ወይም ጥቂት ሰዎችን ለመግለጽ የተከተበ ሳይሆን፤ ቶም በሮካው ‹‹ታላቁ ትውልድ››[1] በሚለው መጽሐፍ ውስጥ አንድን ትውልድ ለመግለጽ ያስቀመጠው ነው።

ቶም አንድን ትውልድ ሁለት ትላልቅ ክስተቶች ተፅዕኖ እንዳደረጉበት በሚያሳይ መልኩ፤ ትውልዱ ያሳለፈውን ሁኔታ እና የተቀረጸበትን መንገድ ይገልጻል። ይኽ ትውልድ በለጋነቱ፡ ‹‹ታላቁ የኢኮኖሚ ድባቴ›› በቤተሰቦቹ ላይ ካሳደረው ተፅዕኖ አገግሞ ሳይጨርስ፤ በወጣትነት ዕድሜው፡ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተሳተፈ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፤ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ተፅዕኖዎች ጠባዩን በመቅረጽ ረገድ ትልቅ አስተዋጽዖ አላቸው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የተቀረጸው ይኽ ትውልድ፡ ስነ ስርዓት፡ ቁርጠኝነትንና ለጋራ መቆም መገለጫዎቹ ተደርገው ይወሳሉ። በምዕራባውያን ዘንድ ‹‹ታላቁ ትውልድ›› ተብሎ የሚጠራው ይኽ ትውልድ፤ የታላቁ የኢኮኖሚ ድባቴና የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ትውልድ ነው።

የታላቁ ትውልድ አባላት መከባበር የሚስተዋልባቸው፣ አንዳቸው ለአንዳቸው መኖር አስፈላጊ እንዲሆኑ

የሚረዱ፣ በትዳር ውስጥም ይሁን በሌላ የህይወት ክፍላቸው ውስጥ ከፍተኛ ቁርጠኝነት ያላቸው፣ በአመዛኙ ከመጀመሪያ የትዳር አጋራቸው ጋር እስከ ህይወታቸው ፍጻሜ የቆዩ ናቸው። በወታደራዊ ህይወት ውስጥ ያለፉባቸው ስነ ስርዓቶችና የውጊያ ስነ ምግባራቸው፤ ለትውልዱ ውብ ጠባይ አስተዋጽዖዋቸው የላቀ ነበር። የታላቁ ትውልድ አባላት ከአሁኑ ትውልድ ይልቅ ከፍተኛ አይበገሬነትና ቁርጠኝነት ነበራቸው።

ከአሁኑ ትውልድ በተለየ የቀደመው፤ ከቀደመውም በተለየ የአሁኑ "ይኸ እሴት አለው"፣ "ይኸ ጥንካሬ አለው"፣ "ይኸ ድክመት አለበት" የሚባሉ ለየትውልዱ የሚሰጡ መገለጫዎችና ባህሪያት አሉ። በጊዜ ቅደም ተከተል አንዱ ትውልድ ከአንዱ ትውልድ ሙሉ ለሙሉ የተነጠለ ባይሆንም፤ በባህርይና በሚያንጸባርቁት የጋራ ማንነት ጠባይ የመለያየት አዝማሚያ ይኖራቸዋል። ለምሳሌ ***"እልፋ ትውልድ"*** ተብሎ የሚጠራው የምዕራባውያን የዛሬ ትውልድ፤ ከቀደሙት ትውልዶች በተለየ የቤተሰብ ባህሉ የመነመነና የግለኝነት ጠባይ የሚጎላበት ትውልድ ነው።

በዋና ዋና ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ውስጥ ተገልጦ እንደሚታየው፤ ትውልድ ከትውልድ ይለያያል። ትውልዶች የተለያየ የስነ ምግባርና የግብር ጠባይ አላቸው። በግብራቸውና በሚያንጸባርቁት ጠባይም አንዳንዶቹ ለበረከት ሲታጩ ሌሎቹ ለመረገምና ለመቅሰፍት እንደበቁ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ተጽፏል። በኦሪት ውስጥ ከግብጽ ባርነት የወጣው ትውልድ ፈጣሪውን ባለማመንና ባለመታዘዝ አስቆጥቶ ነበር። ያ ትውልድ በሞት እስኪያልፍ ወደ ተስፋይቱ ምድር እስራኤል እንደማይገባ ተወሰነበት።

በእስልምና ኃይማኖት አስተምህሮ ውስጥም ስለትውልድ ምልከታ በሰፊው ተጠቅሶ ይገኛል። አንድ ቀን ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተክዘው ቁጭ ይላሉ። ይኸን የተመለከቱ ሰሐቦች ይደናገጡና ነቢዩን ምን እንደሆኑ ይጠይቋቸዋል። ነቢዩም ‹‹ወንድሞቼ ይናፍቁኛል›› በማለት ይመልሱላቸዋል። ይኸን የሰሙት ካጠገባቸው ያሉት ሰሐቦች ‹‹እኛ ወንድሞችዎ አይደለንም እንዴ?›› በማለት ይጠይቃሉ። እሳቸውም ነገሩን እንዲህ በማለት ያስረዷቸዋል። ‹‹እናንተማ ጓደኞቼ ናችሁ። እኔን ሳያዩ እኔ ባደረስኩት መልዕክት የሚያምኑት፡ የሚመጡት ትውልድ ይናፍቁኛል›› ብለው ያስረዳሉ። አንድ ትውልድ ከሌላው ያየውና የሰማው በመለያየቱ ሊገጥመው የሚችለው ነገር እንዲሁ በእስልምና አስተምህሮ ውስጥ ተገልጧል።

የሰዎች ጠባይ እና እሳቤ እንደየቦታው እንደሚለያዩ ሁሉ፣ በጊዜም የተለያዩ ነው። የኢትዮጵያዊ ባህሪና ጠባይ ከአውሮፓውያን፣ ከጀርመናውያንና ከኬንያውያን በተወሰነ መጠን ይለያል። በአንድ ሀገር ውስጥ በየዘመኑ በኖሩ ትውልዶች፤ በትናንት፣ በዛሬውና በሚመጣው ትውልድ መካከል ልዩነቶች አሉ። ምክንያቱም እያንዳንዱ ትውልድ የሚያልፍበት የታሪክ ክስተት፣ የቴክኖሎጂ ለውጥና፣ የህይወት ፓራዳይም የተለያየ ነውና።

በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖር ህዝብ በኑሮ ደረጃና በጾታ፣ በተሰማራበት የሙያ ዘርፍ፣ በሚናገራቸው ቋንቋዎችና በባህል ማንነት፣ ወዘተ... ይለያያል። ከእነዚህ በተለያዩ መገለጫዎች ከሚገለጡ ማንነቶች

በተጨማሪ፤ በዕድሜ የሚለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በአንድ ዘመን የአንድ ሀገር ህዝብ ሆነው ይኖራሉ።

ሀገር የተለያዩ ጾታዎች፣ ብሔሮች፣ የሙያ ባለቤቶች ድምር ውጤት እንደመሆኗ ሁሉ፣ የተለያዩ በዕድሜ ስብጥር የተከፋፈሉ፣ አሁን ላይ ያሉና በቀጣይ የሚመጡ ትውልዶች መኖሪያና መገለጫ ናት። ሀገር ያለፈው ትውልድ መልካም ውጤቶች (ወረት) እና ውዝፍ ስራ፤ የዛሬው ትውልድ ጥንካሬና ድክመት፤ እንዲሁም የነገው ትውልድ ተስፋና ስጋት መስተዋት ናት።

በየዘመኑ የሚፈጠሩ ክስተቶችና ለውጦች በዘመናት መካከል በሰዎች ምልከታዎችና እሳቤዎች ላይ ለውጥ ይፈጥራሉ። አንድ ዘመን የሚጋሩ በተመሳሳይ ክስተቶች ውስጥ ያለፉ የህብረተሰብ ክፍሎች ትውልድ ይባላሉ። ትውልድ ማለት በትናንት፣ በዛሬ እና በነገ ጊዜ ቀመር ውስጥ ተፈጥረው ባለፉ፣ አሁን በሚኖሩና ገና በሚፈጠሩ ሰዎች መካከል ያለ ልዩነትን ለመግለጽ የምንጠቀምበት ብያኔ ነው።

በአጠቃላይ እያንዳንዱ ትውልድ ራሱን የቻለ ማንነቱ የሚገለጽበት እሴቶችና ልማዶች እንዲሁም ሌሎች የጋራ ጠባዮች አሉት። እነዚህም የጋራ ጠባዮች ከዕድሜ ማዕቀፉና ካለፈበት ታሪካዊ ኹነቶች ጋር ተዳምረው፤ ከሌላው ትውልድ የተለየ እንዲሆን ያደርገዋል። እያንዳንዱ የትውልድ አባል አንድ ዘመንን፣ ተመሳሳይ የህይወት ልምድና ታሪካዊ ኹነቶችን ተጋርቶ የሚያልፍ ስለሆነ ተቀራራቢነት ያለው ጠባይ የሚያንጸባርቅ ነው። በመሆኑም አንድን ትውልድ ለመረዳትና ከሌላው ትውልድ የሚለይበትን ቁም ነገሮች ለመገንዘብ፤ አራት ጉዳዮችን መመልከት ያስፈልጋል። እነዚህም የዕድሜ ክልል ወይም የትውልድ ዘመን፣ የጋራ ኹነቶችና ለውጦች፣ በዘመኑ ተቀባይነት ያለው የጋራ ዕይታ (ፓራዳይም) እና ተመሳሳይ ጠባይ ናቸው።

## *ትውልድ በምን ይገለጻል?*

ትውልድ የተቀራራቢ ዕድሜ ስብስብ ነው። ዕድሜ አንድ ሰው የኖረበት ወይም አንድ ክስተት የቆየበት የጊዜ ርዝማኔ ነው። በዚህ የቆይታ ርዝማኔ ውስጥ የሰው ልጅ በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ወይም የለውጥ ሂደት ውስጥ ያልፋል። በትውልድ ፍሰት ውስጥ እያንዳንዱ ሰው የመጪው፣ የዛሬው ወይንም ያለፈው ትውልድ አባል ተብሎ ሊቆጠር ይችላል። ትውልድ ህዝብን በዕድሜና በዘመን ከፋፍሎ የመመልከቻ መነጽር ነው። ግለሰብን የትውልድ አባል ከሚያደርጉት የትውልድ መገለጫዎች መካከል ዕድሜ አንዱ ነው። የአንድ ትውልድ አባላት የተቀራራቢ ዕድሜ ባለቤቶች ናቸው። ከሞላ ጎደል ልጅነታቸው፣ ወጣትነታቸው፣ ጉልምስናና እርጅናቸው በተቀራራቢ ወቅት የተፈጸመ ነው።

አንድ ትውልድ የተቀራራቢ ዘመን ተጋሪ ነው። ትውልድን ያለዘመን መግለጽ አይቻልም። ዘመን አንድ ትውልድ ተወልዶ፤ ዕድሜውን ኖሮ፤ ለቀጣዩ ትውልድ ዐሻራ ጥሎ፤ የሚያልፍበት የጊዜ ቁራጭ ነው። አንድ ትውልድ ለአንድ ወቅት እንጂ ለዘላለም አይኖርም። ወቅት ሲባል ካለፈው ትውልድ የተወረሰው መልካም ጉዳዮችና

ችግሮች ያሉበት፤ ለቀጣይ ትውልድ ዐሻራችንን የምናሳርፍበት፤ ተወልደን ኖረን የምንሞትበት የዘመን ሰሌዳ ነው። እንደ ዕድሜያችን ተማሪ፣ መሪ፣ መካሪ ወዘተ የምንሆንበት ወቅት የተለያየ ነው።

በምዕራቡ ዓለም አሁን ላይ በህይወት ያሉ የተለያዩ ትውልዶች አሉ። ሙሉ ለሙሉ ያለፈው ትውልድ (The Lost Generation, 1883-1900 እ.ኤ.አ.) የመጀመሪያው ትውልድ ሲሆን፤ የተቀሩት ሰባቱ ግን ቁጥራቸው የተለያየ ቢሆንም እነሱን የሚወክሉ ሰዎች ዛሬም በህይወት አሉ። እነዚህም፡-

- ታላቁ ትውልድ (The Great Generation: 1901-27 እ.ኤ.አ.)
- ዝምተኛው ትውልድ (The Silent Generation: 1928-45 እ.ኤ.አ.)
- ፍንዳታው ትውልድ (Baby Boomers)
- ኤክስ ትውልድ (Generation X)
- ሚሊኒየማዊው ትውልድ (Millinials / Gen-Y)
- ዜድ ትውልድ (Generation Z)
- አልፋ ትውልድ (Generation Alpha) እየተባሉ የሚጠሩት ናቸው።

ዕድሜ በአንድ በኩል ስነ ፍጥረታዊ የአካል ዕድገትና ለውጥ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የማህበራዊ ንብብሮሽ ዕድገትና ለውጥ ነው። ዕድሜ በማህበረሰብ ውስጥ የሚኖረንን ቦታ ይወስናል። በዕድሜያችን ምክንያት በተለያዩ ማህበረሰባዊ ሚና ባላቸው የዕድሜ ደረጃዎች ውስጥ እናልፋለን።

አንድ ሰው ከዕድሜው አንጻር መፃኢ፣ አዳጊ፣ ሰሪ፣ መሪ፣ ተጧሪ እና ተዘካሪ የሚሆንበት የተለያዩ ማህበረሰባዊ የዕድሜ ወቅቶችን ያሳልፋል። በዚህም የአንዱ ወይንም ሌላው ትውልድ አባል ሆኖ ያልፋል። ሰብሰብ አድርገን ካየነው ደግሞ ዕድሜ ወይም የአንድ ሰው የጊዜ ቆይታ በደምሳሳው ልጅነትና አዳጊነት፣ ወጣትነትና ጎልማሳነት እንዲሁም እርጅናና ስንብት ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ።

ይኸ ዕድሜን በወቅቶች የመከፋፈል ሂደት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የተለያየ መልክ አለው። በእስያ አካባቢ ዕድሜን በሃያ አምስት ዓመታት ወቅቶች ይከፍሉታል። የመጀመሪያው ሃያ አምስት ዓመት የመማሪያ፣ የማወቂያ እና የማደጊያ ዕድሜ ነው። ሰው በመጀመሪያው ሃያ አምስት ዓመታት ተምሮና ዐውቆ፤ በሁለተኛው ሃያ አምስት ዓመታት የተማረውና ያወቀውን በመተግበር፤ ታዋቂና ስኬታማ የሚሆንበት ይሆናል።

በእነዚህ ሁለት ሃያ አምስት ዓመታት ከማህበረሰብ ባገኘው የዳበረ ልምድና አቅም፤ በሦስተኛው ሃያ አምስት ዓመታት ማህበረሰብን የሚያገለግልበት፤ ከማህበረሰቡ ያገኘውን መልሶ ለማህበረሰቡ የሚሰጥበት ወቅት ነው። ዕድሜ ፈቅዶለት ወደ አራተኛው ሃያ አምስት ዓመታት የገባ ሰው፤ በቀደሙት ሶስት ወቅቶች የተማረውን፤ ያወቀውን፣ የሰራውን፣ ያበረከተውን መልሶ የሚያንጸባርቅበት ወቅት ነው። በአራተኛው ወቅት ሰዎች የህይወት

ልምዳቸውን በንግግር፣ በማስተማር፣ በመጽሐፍ እና በሌሎች አማራጮች ለትውልድ የሚያስተላልፉበት የህይወት ክፍል ነው።

በሀገራችንም የዕድሜ ወቅቶች በማህበረሰብ ውስጥ የስራ ድርሻ ክፍፍልን ይወስናሉ። ሰው በልጅነቱ ተማሪ፤ በዐዋቂነቱ መሪ፣ በስተእርጅናው ደግሞ መካሪ የመሆን ማህበረሰባዊ ኃላፊነቶች ይኖሩታል። ለዚህ ለዘመናት የኖረው የገዳ ስርዓት ትልቅ ማሳያ ነው።

በገዳ ስርዓት ዕድሜ ትልቅ ሚናን ይጫወታል። በየዕድሜ ዘመኑ የስርዓቱ አባል የሚኖረው የስራ ድርሻ እና አስተዋጽኦ የተለያየ ነው። በየስምንት ዓመቱ እያንዳንዱን የዕድሜ ደረጃ እያለፈ፤ የተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሚናዎች ይኖሩታል። ዕድሜ ከአንዱ የማህበረሰብ ኃላፊነት ወደ ሌላ የማኅበረሰብ ኃላፊነት ለመሸጋገር ትልቁ ጉዳይ ነው።

ሀገር በቀል የሆነው የገዳ ስርዓት የማህበረሰቡ አባላት ሁሉ በየርከኖቹ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኃላፊነቶችን የሚቀበሉበት አስተዳደራዊ ስርዓት ነው። የገዳ እርከን ደረጃዎች ብዛት እንደ አካባቢው የተለያየ ቢሆንም ሁሉም ወንዶች በዕድሜ በተከፈሉ የገዳ እርከኖች ውስጥ ያልፋሉ። በሁሉም የገዳ እርከኖች ውስጥ ለማለፍ ሰማንያ ስምንት ዓመታት ይወስዳል።

በገዳ ስርዓት ውስጥ የትውልድ መተካካት ቁልፍና ወሳኝ ጉዳይ ነው። በየስምንት ዓመቱ የትውልድ መተካካት፤ ከነበሩት ኃላፊነት፤ ወደ ሌላ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ኃላፊነትን ይሸጋገራሉ።

ዕድሜ ወቅቶችን ይሰጠናል። ትልቁ ቁም ነገር ዕድሜ በሚሰጠን ወቅት ዕድሜያችን የሚጠይቀንን ነገር የማድረግ ችሎታ ነው። መማር በሚገባ ዕድሜ ካልተማሩ፤ መስራት በሚገባ ጊዜ ካልሰሩ፤ መስከንና መምከር በሚገባ ጊዜ መምከር ካልቻሉ፤ የሰው ልጆች የተዛባ የህይወት ሁኔታ ውስጥ ያልፋሉ። ሀገርም ዜጎች በሚኖራቸው የዕድሜ ክፍልፋይ ወይም ወቅቶች ውስጥ ልጆቿን የማታስተምር፤ ወጣቶቿን የማታሰራ፤ እንዲሁም ሽማግሌዎቿን የማትጦር፤ ከሆነ ቀውስ ውስጥ ትገባለች።

ሽማግሌዎች የሚመክሩና ልምዳቸውን የሚያካፍሉ፡ ለበታቾቻቸው ቦታ የሚሰጡ፡ መንገድ የሚያሳዩ፤ ወጣቶች የሚያደምጡና የሚጥሩ፡ የዕድሜ የበላዮቻቸውንና የበታቾቻቸውን የሚደግፉ፤ ልጆች የሚታነጹና የሚማሩ ከሆነ ሀገር የተሻለ መሠረት ላይ ትቆማለች። ሀገር ጥንካሬ በዚህ የትውልድ ትስስርና ቅብብሎሽ ላይ የተወሰነ ነው። የተነጠለ የሚባል ትውልድ፤ የተነጠለ የሚባል ዘመን፤ እንዲሁም የተነጠለ የሚባል ዕድሜ የለም። አንዱ የአንዱ ቅጣይ ነው።

ዕድሜ የሰዎችን ባህሪና አመለካከት ከሚቀርጹ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው። ልጆች የሚያልፉበትን ሁኔታና

የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ተመልክቶ፤ መጪውን መገመት ይቻላል። ዕድሜ የመጪው ትውልድ አባል ሌላውን የሚቀርጽበት፤ የዛሬው ትውልድ ከቀደመው ተምሮ ለዛሬውና ለነገው የሚሰራበት፤ የነገውም ከዛሬው ተቀብሎ የሚተካበት ትውልዳዊ ዐሻራ ነው።

የዛሬው ትውልድ ለሚያንጸባርቃቸው እሴቶች፣ አመለካከቶችና ባህሪያት፤ የቀደመው ትውልድ አካል በነበረበት ወቅት ያለፈባቸው ክስተቶች፣ ሂደቶች፣ ሁኔታዎችና ለውጦች እጅግ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። ትውልድ ሁሉ የለውጥ ስሪት ነውና።

በትውልድ ጥናት ውስጥ፤ ትውልድን በዕድሜ ከፋፍለው ከሚመለከቱት በተቃራኒ፤ አንድን ትውልድ ከሌላው ትውልድ መለየት የሚችለው በዕድሜ ሳይሆን በኹነቶች ለውጥ እንደሆነ የሚገልጹ የትውልድ አጥኚዎችም አሉ። ጊዜ በራሱ የተመሳሳይ ነገሮች ድግግሞሽ እንደሆነ በመግለጽ፤ አንድ ትውልድ እንዲፈጠር ማህበራዊ ለውጦች የግድ እንደሆኑ ይገልጻሉ። ነገር ግን ትውልድን ከትውልድ ለመክፈልና ለይቶ ለማየት የዕድሜና የታሪካዊ ኹነቶች ሚዛናዊ አስተዋጽዖ አስፈላጊ ናቸው።

የሰው ልጅ ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ዕድገት በዕድሜ ደረጃ ውስጥ የሚያልፍ ቢሆንም፣ በዋናነት በታሪካዊ ለውጦች ተፅዕኖ የሚደረግበት ነው። ታሪካዊ ክስተቶችና ሂደቶች ሰዎች እንዴት እንደሚያስቡና እንደሚንቀሳቀሱ በመወሰን፤ አስተሳሰባቸውንና የጋራ ጠባያቸውን ይቀርጻሉ።

በጦርነት ውስጥ ያለፈ ትውልድ ወታደራዊ ጠባይንና ሁኔታን ተምሮ ያልፋል። በኢኮኖሚ ድቀት ውስጥ ያለፉ ሰዎች ቁጠባንና ሌሎች የኢኮኖሚ ባህሎችን ያዳብራሉ። በመሆኑም ትውልድ እንደወቅቱና እንደየዘመኑ የኖረባቸው የለውጥ ሁኔታዎች፤ ዓይነቶችና መልኮች፤ አንዱ ትውልድ ከሌሎች ትውልዶች የተለየ አመለካከት እንዲኖረው ያደርጋሉ።

ክረምትና በጋ ብለን የአየር ሁኔታው የሚለያይባቸውን ጊዜያት እንደምንከፍለው ሁሉ፤ የአንድ ትውልድ ወቅት፡ ክስተቶች የሚከሰቱባቸውን ጊዜያት የሚገልጽ ነው። የሰዎች የክረምትና የበጋ የአኗኗር ዘዬና ቅርጽ የተለያየ ነው። ለክረምት ዣንጥላ በመያዝ፣ ጃኬት በመደረብ እና የሚያሞቃቸውን ልብስና ምግብ በመጠቀም ብርዱን ያሳልፋሉ።

ቀለል ያሉ ልብሶችና የሚያቀዝቅዙ አማራጮች ደግሞ ለበጋው ሙቀት ምላሽ የሚሰጡበት መንገድ ሆኖ ያገለግላል። ከትውልድ ትውልድ እንደተወለዱበትና እንዳደጉበት የተለያዩ ወቅቶች፤ የሚያጋጥማቸው ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ክስተታዊና ሂደታዊ ለውጥም፡ እንዲሁ የተለያየ አመለካከት፣ ባህሪና ልማድ እንዲኖራቸው ያደርጋል።

ትውልድን የሚቀርጹ ለውጦች ድንገቴ ክስተቶች፤ ወይንም በሂደት እየተለወጡ የመጡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኹነቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከቀደመው ወቅትና ትውልድ በተለየ የተፈጠሩ ለውጦች፤ የተለየ አመለካከትና እሴት ያለው ትውልድ ይፈጥራሉ፡፡ ድንገቴ ለውጦች እጅግ ትልቅ ተፅዕኖ ያላቸው ያልታሰቡ ክስተቶች ሲሆኑ፤ የአንድን ትውልድ የአኗኗር ዘይቤ፣ ምልከታ፣ ባህሪና ፍላጎት በማስገደድ ሊለውጡ ይችላሉ፡፡ ድንገቴና የማናውቃቸው ጉዳዮች ወይም ናሲም ኒኮላስ ታሌብ ‹‹የጥቁር ዳክዬ ክስተቶች›› የሚላቸው ጉዳዮች፣ የዓለምን የአተያይ አቅጣጫና የምልከታ አድማስ ቀያሪ ናቸው፡፡

በኒኮላስ አገላለጽ በመካከለኛው ዘመን አውሮፓውያን ያደረጉት ከነበረው አዳዲስ የዓለማችንን ክፍሎች አሰሳ በፊት፤ ለሁለት ሺ ዓመታት በአውሮፓ ውስጥ እና በዙሪያው ባሉ የውሃ አካላት ስለምትገኘው ስዋን ስለምትባለው ዳክዬ ተመሳሳይ ግንዛቤ ነበር፡፡ በሁሉም ሀገራት የላባዋ ቀለም ነጭ መሆኑንና ዳክዬዋ ከነጭ ውጭ ምንም ዓይነት ሌላ ቀለም ያለው ዝርያ እንደሌላት በመላው አውሮፓ የሚታመን ሀቅ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ይኸ ሆኖ ሳለ በ1635 በንግስት ኤልሳቤጥ አዝማችነት የተለያዩ ቡድኖች ወደ ተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች በመበተን አሰሳ ሲያደርጉ ነበረ፡፡ ወደ አውስትራልያ የሄደው ቡድን ለበርካታ ዘመናት በመላው አውሮፓ ስለ ስዋን ዳክዬ የላባ ቀለም የታመነውን ነባር እውነትና ዕውቀት የሚቀይር አዲስ ነገር፤ በቀለሟ ጥቁር የሆነች ተመሳሳይ የዳክዬ ዝርያ ይመለከታል፡፡ የአሳሾቹ ቡድንም ዕይታ ለሁለት ሺህ ዓመታት ስለዳክዬዋ የላባ ቀለም ተይዞ የነበረውን ነባር ዕውቀት ሙሉ ለሙሉ ሊቀይረው ችሏል፡፡

የሰው ልጆች ዓለምን የሚያዩበትና ዕውቀት ነው ብለው የሚወስዱት እውነታ የሚፈጠረው በተደጋጋሚ ካጋጠማቸው ነገር ነው፡፡ የሚያዩትንና ለረጅም ጊዜ የኖሩትን ህይወት ሁሌም በተመሳሳይ ያለምንም መቆራረጥ በተረጋጋ ሁኔታ ይቀጥላል የሚል እምነት ይይዛሉ፡፡ አውሮፓውያን በተደጋጋሚ ለዘመናት ነጭ የስዋን ዳክዬ በማየት ስዋኖች ሁሌም ቢሆን ነጭ ብቻ ናቸው የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰው ነበር፡፡ ”ሌላ እስኪገኝ ይሄ ብቸኛ እውነት ይሆናል” ይባላል፡፡ ጥቁር ስዋን እስኪያገኙ ነጭ ብቻ ያለ ይመስላቸው ነበር፡፡

እንደ ኒኮላስ አባባል ዓለማችንን በዋነኝነት የሚዘውሯት የሚታወቁና የሚገመቱ የዕለት ተዕለት ለውጦች ሳይሆኑ፤ በሰው ልጆች ነባር ዕውቀት ላይ ተመስርቶ ሊደረስባቸውና ሊተነበዩ የማይችሉ፤ ከሰው ልጆች የማወቅ ዐቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ዓለማችንን በዋናነት የሚዘውሩ አዳዲስ ነገሮች የመከሰት ዕድላቸው እጅግ አነስተኛ ቢሆንም፤ ከተከሰቱ ግን ከፍተኛ ለውጥን የሚያስከትሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ከሲ.አይ.ኤ. ከፍተኛ ተንታኞች አንስቶ እስከ ዎል ስትሪት ያሉ ከፍተኛ የንግድ ባለሙያዎች የመስከረም አንዱን (9/11) የሽብር ጥቃት መተንበይ አልቻሉም፡፡ ይኸም የሚያመለክተው አደጋዎቹ የሚከሰቱበት መንገድና፤ በየጊዜው የሚታዩ አዳዲስ ፈጠራዎች፤ የጥቋቁር ስዋኖች መገለጫዎች ወይም ተምሳሌቶች ናቸው፡፡

ከኮምፒውተር መምጣት በፊት ኮምፒውተር የሰው ልጅ ህይወትን በሙሉ የሚለውጥ ቴክኖሎጂ ነው ብሎ

መገመት አይቻልም ነበር። ከናፖሊዮን መሞት በኋላ በነበረው አንድ መቶ ዓመታት ከፍተኛ ጥፋትን ያስከተለው የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ይከሰታል ተብሎ አይገመትም ነበር። እንዲያውም በአንዳንድ ምሁራን ዘንድ ጦርነት ጠፍቷል የሚል እሳቤ ላይ ተደርሶ ነበር። ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት መንስኤ የሆነውን የሂትለርን ወደ ስልጣን መምጣት መገመት ፈጽሞ አይቻልም ነበር።

አሁን የምንኖርበትን ዓለም የፈጠሩት፤ በወቅታቸው የመከሰት ዕድላቸው እጅግ አነስተኛ የነበረ፤ ነገር ግን ከተከሰቱ በኋላ ዓለምን እስከ ወዲያኛው የቀየሩ ሁኔታዎች ናቸው። እንደ ኒኮላስ ዕይታ ዓለማችን እጅግ ውስብስብና በጥቁር ስዋኖች (የማናውቃቸው፤ የማይገመቱና ከፍተኛ ለውጥ የሚያስከትሉ ጉዳዮች) መከሰት እየተለወጠች የምትሄድ ናት። ዓለማችን ለመገመት አዳጋች የሆነች በመሆኗ የሰው ልጆች አነስተኛ ለውጦች ላይ ተመስርተው በሚያደርጉት ትንበያ ላይ በመንተራስ እንዲህ ናት ብሎ ለመገመት የማትቻል ናት። ድንገተኛ ክስተቶች ትልቅ ተፅዕኖ ያላቸው በመሆኑ በዘመኑ የነበረውን ትውልድ ከቀደመው በተለየ ይለውጡታል።

በሂደት ለውጥ የሚያሳዩ ክንዋኔዎችም በጊዜያት ውስጥ በማህበረሰብ ላይ ለውጥን ያመጣሉ። በዝግመታዊ ለውጦች ለሚፈጠሩ መቀያየሮች ትውልዶች ምላሽ የሚሰጡባቸው መንገዶች የተለያየ ይሆናል። የኅብረተሰብ የአኗኗር ለውጥ፣ ኢኮኖሚያዊ ለውጦች፣ የህዝብ ፍልሰት እና መሰል ጉዳዮች ትውልድን የሚፈጥሩና የሚለውጡ ሂደታዊ ለውጦች ናቸው። በአጠቃላይ ትውልድ፤ በድንገተኛ ክስተትም ሆነ፤ በዝግመታዊ ሂደት መጥተው በሚሄዱ ተፅዕኖ ፈጣሪ ኹነቶች ምክንያት በሚመጣ የፓራዳይም ለውጥ፤ የሚፈጠር የማህበረሰብ የዘመን ክፍል ነው።

## *የፓራዳይም ለውጥና የትውልድ አፈጣጠር*

‹‹ምድር የፀሐይ ስርዓት ማዕከል ናት›› የሚለው ነባር አመለካከት፤ ኒኮላስ ኮፐርኒከስ እስኪሽረው ድረስ፤ በየዘመኑ የነበሩ ብዙ ጥናቶችን የቀረጸ የእሳቤ መሠረት ነበር። የኮፐርኒከስ ለውጥ እስኪመጣ ድረስ በዘርፉ የሚያጠኑ ተመራማሪዎች ‹‹ምድር የፀሐይ ስርዓት ማዕከል ናት›› የሚለውን ፓራዳይም መሠረት አድርገው ጥናታቸውን ይከውኑ ነበር።

በየዘመኑ የነበሩ ፓራዳይሞችና አተያዮች፤ በዘመኑ የነበሩ ትውልዶችን ያንጻሉ። መነሻው ከጥቂቶችም ይሁን ከብዙሃን፤ ጊዜው የደረሰ ሐሳብ ትውልድን ይቀርጻል። ለዚህም ነው ‹‹ጊዜ እንደሰጠው ሀሳብ ጉልበተኛ ሃይል የለም›› የሚባለው። ለምሳሌ ማርክሲዝም ከእነዚህ ተፅዕኖ ፈጣሪ እሳቤዎች መካከል አንዱ ነው። ካርል ማርክስ በጀርመን የተወለደ በፈረንሳይና በቤልጅየም የህይወቱን የተወሰኑ ዕድሜዎች ያሳለፈ ግለሰብ ነበር። ነገር ግን ማርክስ በተሰደደበት ፈረንሳይ ካገኘው ጓደኛው ጋር የጻፈው ‹‹ዘ ኮሙኒስት ማኒፌስቶ›› ጽሁፍና ፍልስፍናው ብዙ ትውልዶችን የቀረጸ፤ አብዮቶችን ያቀጣጠለ ነው። በአንዲት ትንሽ ክፍል ውስጥ የከተባቸው ጽሑፎች ሀገርን ተሻግረው ውቅያኖሶችን አቋርጠው በአውሮፓ፣ በአፍሪካ (ሀገራችንን ጨምሮ)፣ በአሜሪካ፣

በእስያና በሌሎች አካባቢዎች ትውልዶች ያነገቧቸው ዓላማዎች፣ የተግባቡባቸው ቋንቋዎችና የተጓዙባቸው መንገዶች ለመሆን በቅተዋል።

ታሪካዊ ኹነቶች ፓራዳይምን ይፈጥራሉ። በተቃራኒውም ፓራዳይም ታሪካዊ ኹነቶችን ይፈጥራል። አንዳንድ ጊዜ ታሪካዊ ክስተቶች ነባር የእሳቤ ማዕቀፍን ለመለወጥ ያስገድዳል። አዳዲስ ክስተቶችን በነባሩ የእሳቤና የአካሄድ ማዕቀፍ ለመመለስ ሳይቻል ሲቀር፤ የፓራዳይም ለውጥን ይገፋል። ለአዳዲሶቹ ኹነቶች አዲስ ምላሽን የምንሰጥበት መንገድ የእሳቤና የምልከታ ማዕቀፍ ይፈልጋል።

ፓራዳይም ዓለምን የመመልከቻ መንገድ ወይም መነጽር ነው። ዓለም የሆነችው ወይም መሆን ያለባት ይኸ ነው ብሎ የሚያስቀምጥ፤ ችግሮችን የምንረዳበት እንዲሁም ምላሽ የምንሰጥበት የእሳቤ ማዕቀፍ ነው። የእሳቤ ማዕቀፉ ለችግሮች ምላሽ ለመስጠት ሳይችል ሲቀር፤ የፓራዳይም ለውጥን ይገፋል። የፓራዳይም ለውጥ ደግሞ ትውልድ የሚመለከትበት መነጽርን እንዲሁም ሀገራዊ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ስሪቱን ጭምር ይለውጣል። በሀገራችን ‹‹ሶሻሊዝም መዳኛችን፤ ብቸኛው መንገድ ነው›› የሚለው የፓራዳይም ለውጥ ንጉሳዊ ስርዓትን ያፈረሰ፣ የመሬት ስሪትን የቀየረ፣ የአኗኗር ዘይቤን የለወጠ፣ የፖለቲካ አካሄዳችንንና ሌሎች ጉዳዮችን ጭምር ያናወጠ ነው።

የፓራዳይም ለውጥ ዓለም የሚሰራበትን እንዲሁም ትውልድ የሚያስብበት መንገድን ይለውጣል። ካፒታሊዝም የፈጠረውን ስርዓት ለመለወጥ በሚተልም መልኩ የማርክሲዝም ፓራዳይም ብቅ ብሏል። የማርክሲዝም እሳቤ መልሶ ደግሞ ብዙ ታሪካዊ ኹነቶችና ለውጦች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል። በዓለም ላይ የተቀጣጠሉ ብዙ አብዮቶችና ለውጦች የዚሁ እሳቤ ጥንስስ ናቸው። ማርክሲዝም በዚህ ዓይነት ሁኔታ ብዙ ትውልዶችን በየሀገሩ የቀረጸና አብዮታዊ ያደረገ ነው።

ፖለቲካዊ ስርዓቶች የሀሳብ ውጤቶች ናቸው። የፖለቲካ ፓራዳይም፡ የፖለቲካ ቡድኖችና ግለሰቦች ‹‹የተሻለው የፖለቲካ ስርዓት እንዴት ሊፈጠር ይችላል?›› የሚለውን ጥያቄ የሚመልሱበት አጠቃላይ የዕይታ ማዕቀፍ ነው። ይኸ ማዕቀፍ የተሻለ ስርዓትን ለመፍጠር ፖለቲካ እንዴት ይመራል? በፖለቲካ ውስጥ እንዴት መንቀሳቀስ አለብን? ችግሮችን እንዴት እናልፋቸዋለን? የሚሉ ጉዳዮችን የሚወስን አጠቃላይ ማዕቀፍ ነው። በዚህ ማዕቀፍ ስርዓቶች ይፈጠራሉ ወይም ይከሰማሉ፤ ይጠነክራሉ ወይም ይሰበራሉ።

እነዚህ ስርዓቶችም በሁለት ዓይነት የለውጥ ሂደቶች የተወጠሩ ናቸው። የመጀመሪያው ‹‹የፖለቲካ መደርጀት›› ነው። የፖለቲካ መደርጀት በፖለቲካ ስርዓት ውስጥ የሚከሰት አዎንታዊ ለውጥ ነው። ሁለተኛው ‹‹የፖለቲካ መፋለስ›› ሲሆን መነሻው ከውስጥም ይሁን ከከባቢው፤ ስርዓቱ ድጋፍን መገንባት ሲያቅተው፤ የራሱን ሂደት መቆጣጠር ሳይችልና፤ አንድነቱን ማስጠበቅ ሲሳነው፤ የሚፈጠር ነው። ስርዓቱ የቆመበትና የሚመራበት የሀሳብ ማዕቀፍ ውስጣዊ እና ውጫዊ ለውጦችን ተቋቁሞ፤ ድጋፍን ማመንጨት ሲያቅተው፤ በስርዓቱ ውስጥ

መፋለስን ይፈጥራል።

የፖለቲካ ፓራዳይም ጥንካሬውና ዘላቂነቱ የሚወሰ ነው፤ ፈተናዎችን ተቋቁሞ የፖለቲካ ስርዓትን ወደ መደርጀት በመውሰዱ ነው። አንድ የፖለቲካ ፓራዳይም ለስርዓቱ ጥንካሬን ለማምጣት፤ በስርዓቱ ላይ ለሚፈጠሩ ተፅዕኖዎች በቂ ምላሽ መስጠትና መቋቋም የሚችል መሆን አለበት። ‹‹መቋቋም›› ለሚመጣ ተፅዕኖ ምላሽ መስጠትን አመልካች ነው። እነዚህ ተፅዕኖዎች ውስጣዊም ውጫዊም መነሻ ሊኖራቸው ይችላል። ከስርዓቱ ውስጥም ይነሱ፤ ከስርዓቱ ውጭ፤ ከባቢ የፖለቲካ ስርዓቱ መደርጀት ወይም መፋለስ የሚመሰረተው፤ አሉታዊ ለውጦችን ለመቋቋም ባለው ዐቅም ላይ ነው።

ይኸ ማዕቀፍ ለችግሮች የመፍትሄ አቅጣጫ መጠቀም ሳይችል ሲቀር፤ እንዲሁም ወደ ተሻለ ስርዓት ማደግ ሲያቅተው፤ ለፓራዳይም ለውጥ ወይም ለአዲስ ፓራዳይም መምጣት በር ይከፍታል። ከውስጥና ከውጭ ለሚነሱ ለውጦች እና ፈተናዎች ምላሽ መስጠት ወይም መቋቋም ያልቻለ የፖለቲካ ስርዓት ይሻግታል። የፓራዳይም ለውጥ ማምጣት ካልተቻለ፤ ወይንም በነባሩ ፓራዳይም መቀጠል ካልቻለ፤ የስርዓት መናወጥ ይመጣል። ስርዓት ወደ ሻጋታ እንዳይሄድ ለተፈጠሩ ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎች ምለሽ የሚሰጥ የፓራዳይም ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል።

የፓራዳይም ለውጥ መነሻዎች ወይም ገፊ ምክንያቶች ውስጣዊና ውጫዊ ለውጦች ወይም ፈተናዎች ናቸው። እነዚህ ሀገራዊ ፈተናዎችና ለውጦች፤ እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ፈተናዎችና ለውጦች፤ በነባሩ ፓራዳይም የእሳቤ ክፍተቶች ምክንያት መቋቋም ሳይቻል ሲቀር፤ የፓራዳይም ለውጥ ማምጣት የግድ ይላል። ምክንያቱም በነባሩ ፓራዳይም ሀገር መምራት የማይቻልበት ደረጃ ሲደረስ፤ የአዲስ ፓራዳይም አስፈላጊነት ጎልቶ ይወጣል። በዚህም አዲስ ፓራዳይም ይወለዳል፤ ይጠናከራል። ማህበረሰብ አዲስ እሴትና የጋራ ጠባይ ወደ መቅረጽ ደረጃ ይደርሳል። ትውልድ የተቀራራቢ እሴት ተጋሪዎች ስብስብ ነው።

በጃፓን ‹‹New Breed Generation›› ተብሎ የሚጠራ የድህረ ፈተና ትውልድ አሉ። በ1960ዎቹ የተወለደው ይኸ ትውልድ በጃፓን ጠንካራ የኢኮኖሚ ጊዜ የተወለዱ ናቸው። ጦርነትን እና ከጦርነት በኋላ የነበሩ መንገራገጮችን አላዩም። ዩኒቨርሲቲን የተቀላቀሉትም የሀገሪቱ የተማሪዎች እንቅስቃሴ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ንጦ ከረጋ በኋላ ነው። ይኸንንም ተከትሎ የዚህ ትውልድ አባላት በአብዛኛው ለፖለቲካ ፍላጎት የሌላቸው፣ ተሳትፏቸው የቀነሰ፣ የህይወት ውጣ ውረድን መቋቋም የማይችሉና በቶሎ ተስፋ የሚቆርጡ ናቸው።

ፍንዳታው ትውልድ (Baby Boomers)፡ የሚባሉት ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ፡ የፈተናው ዘመን ትውልድ ናቸው። ምንም እንኳ ‹‹ፍንዳታው ትውልድ›› የሚለው ሀሳብ ምንጩ ከምዕራብ ቢሆንም፤ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት የተነሳውን፡ ልጆች የመውለድ ማዕበል ተከትሎ ጥቅም ላይ የዋለ ሀረግ እንደመሆኑ፤ በዓለም ላይ

ብዙ ሀገራት ይኸንን ትውልድ ለመጥራት ይጠቀሙበታል። የጃፓን ፍንዳታ ትውልድ አባላት የተወለዱት ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንዳበቃ ከ1947-49 እ.ኤ.አ. በነበረው የኢኮኖሚ እጥረት ውስጥ ሲሆን፣ ያደጉት የጃፓን ኢኮኖሚ እየተጠናከረ በመጣበት ጊዜ ነው። ዩኒቨርሲቲ የገቡት የተማሪዎች እንቅስቃሴ ውጥረት ከፍተኛ ደረጃ በደረሰ ጊዜ ነው። የዚህ ትውልድ ፖለቲካዊ ተሳትፎና በፖለቲካ ውስጥ ያለው እንቅስቃሴ ጠንከር ያለ ነው።

በየዘመኑ የነበሩ ክስተቶችና ለውጦች፤ እንዲሁም ተፅዕኖ ፈጣሪ ፓራዳይሞች፤ ትውልዶችን የተለያየ የጠባይና የእሴት ቅርጽ ይሰጧቸዋል። ትውልድ ከሚያልፍባቸው ተመሳሳይ ለውጦች እና ከዘመኑ ፓራዳይም የተነሳ፤ የአንድ ትውልድ አባላት ከሌላው ትውልድ አባላት የተለየ ተቀራራቢ ጠባይ ያንጸባርቃሉ። ትውልድ በዘመኑ በሚፈጠሩ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች የሚያልፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፤ ለእነዚህ ሁኔታዎች በሚሰጠው ምላሽ ተመሳሳይ ጠባይና እሴት ያዳብራል።

በጃፓን የኢኮኖሚ ለውጡና ፈጣኑ የቴክኖሎጂ ዕድገት፤ ቀድሞ የነበረውን የቤተሰባዊነት እሴት እያላሸቀ መጥቶ፤ የግለኝነት ጠባይ የአዲሱ ትውልድ ነጸብራቅ እንዲሆን አድርጓል። በአሜሪካም ውስጥ የሊበራል ርዕዮተ ዓለም፤ እንዲሁም ፈጣን የቴክኖሎጂ ለውጦች፤ ማህበረሰቡ ከትውልድ ትውልድ ይበልጥ ግለኝነትን የሚያንጸባርቅ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል።

እነዚህ ተመሳሳይነት ያላቸው ጠባያት፤ ሀገር ለመገንባትና ለማጠናከር ትልቅ ዐቅም አላቸው። የየዘመኑ ትውልድ የእሴቶች ድምር ውጤት ነውና። የትውልዱ እሴት ‹‹አብሮነትን የሚያንጸባርቅ ወይስ በመራራቅ ላይ የተመሰረተ?›› የሚሉት ጥያቄዎች በሀገር ላይ የራሳቸው ተፅዕኖ አላቸው። ጠንካራ የስራ ባህል ወይም ስራን መናቅ፤ እርስ በእርስ መከባበር ወይንም መናናቅ፤ የዓላማ ቁርጠኝነት ወይም በቀላሉ ተስፋ መቁረጥ፤ በሀገር ላይ ልዩነት የሚያመጡ ትውልዳዊ እሴቶች ናቸው።

ዜጎች የሚኖራቸው እሴት እንደ ሀገር ለሚኖር ስኬት ቁልፍ ነው። እሴቶች ከፓራዳይም የሚመነጩና፤ በድርጊቶች ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ፤ በህይወት ውስጥ ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው። ድርጊቶች ደግሞ እንደ ግለሰብም ይሁን እንደ ሀገር ስኬታማነትን ይወስናሉ። በመሆኑም ሀገራት ራሳቸውን ለማጠናከር በማሰብ የትውልድ እሴት ግንባታ ላይ ትኩረት አድርገው ይሰራሉ። የትምህርት ስርዓት፣ ሚዲያ፣ ቤተሰብ፣ ብሔራዊ አገልግሎትና የኪነ ጥበብ ኢንዱስትሪው ትውልድን የጠንካራ ወይም የደካማ እሴት ባለቤት ለማድረግ ዋነኛ ከመባሉ አማራጭ መንገዶች የሚጠቀሱ ናቸው። በደቡብ ኮሪያ ብሔራዊ አገልግሎትና ጠንካራ የትምህርት ስርዓት ከፍተኛ የመከባበር እሴት በትውልዶች ውስጥ እንዲዳብር አድርጓል።

## *የትውልድ ቅብብሎሽ ገመድና የትውልድ ትስስር ክፍተት*

ቻይና የአሁኑ ጥንካሬዋ የማዖ ትውልድ ውጤት ብቻ አይደለም፤ የነ ዴንግ ትውልድ ለውጥ፤ የነ ዢ ትውልድ ተዐምር ጭምር ነው። የቻይና የዛሬ ጥንካሬ ምንጮች እነዚህ ናቸው። ይኸ የአሁኑ የቻይና ስኬት ደግሞ የቀጣይ ቻይና የስኬት ጉዞ ማረጋገጫ አይደለም። ጥንካሬው እንዲቀጥል ቀጣይ ትውልድ በተጣለለት መሠረት ላይ፤ የተለያዩ ፈተናዎችን በመቋቋም፤ ተጨማሪ ውጤቶችን የሚያመጣ፤ መሆን አለበት። ይኸ ካልሆነ ግን፤ ከታላላቅ ስልጣኔዎቻቸው በኋላ የወደቁ ሀገራትን ታሪክ መድገም አይቀሬ ነው።

የቻይና ሀገራዊ ጥንካሬ የተመሰረተው በትውልዳዊ መወራረስ እና ቅብብሎሽ ላይ ነው። የማዖ ቻይና በመንግስት መር እና በህብረተሰባዊነት ፖለቲካ ኢኮኖሚ ሀገር ለማሳደግና ለማጠናከር የሞከረ ነው። የዴንግ ሪፎርም ደግሞ መንግስት መርነትና ህብረተሰባዊነት ላይ የተመሰረተው ፓራዳይም እዚህ ጋር ያበቃል ብሎ፤ የቀደሙ አካሄዶችን ሁሉ አፍርሶ፤ በአዲስ አካሄድ የተካ አይደለም። ይልቁንም ድክመቱን አርሞ አዳዲስ ማጠናከሪያዎችን ያመጣ ነው። በነበረው አካሄድ ተጨማሪ ጥንካሬዎችን በሚፈጥር መልኩ፤ ኢኮኖሚውን ወደ ውጪና ወደ ውስጥ ከፈት አደረገ። አሁን ላይ ያለው የዥ እሳቤም ቢሆን የቀደሙትን ሰብሮ የጀመረ ሳይሆን፤ አዳዲስ ጥንካሬዎችን ፈጥሮ፤ ቻይናን ወደ ሌላ ከፍታ ለማሸጋገር አልሞ፤ የተነሳ ነው።

የሀገር ግንባታ የዘመናትና የማያልቅ የትውልድ ቅብብሎሽ ውጤት ነው። ሀገር የትውልዶች ትስስር ውጤት ናት። የትውልድ ቅብብሎሽ ሲባል፤ በትውልዶች መካከል በሚኖር ጠንካራ ተግባቦት የሚፈጠር፤ የጠንካራ እሴት መወራረስ ነው። በዚህ ዓይነት መንገድ መልካም ያልሆኑ እሴቶች እየታረሙ፤ ጠንካራ ሀገራዊ እሴቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገሩ፤ ዘመኑን እየዋጁ ሲሄዱ፤ ሀገር እየተጠናከረ ይመጣል።

ትውልዶች የሚያልፉበት ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ የተለያየ ከመሆኑ የተነሳ፤ በትውልዶች መካከል የሚኖር ልዩነት አይቀሬ ነው። አልፎ አልፎም ልዩነቱ ወደ ተቃርኖና የለየለት ጠላትነት ሊለወጥ ይችላል። በትውልዶች መካከል ያለውን ልዩነት ተረድቶ ለማስማማትና ለማቻቻል አለመምከር በትውልዶች መካከል የትስስር ክፍተት ይፈጥራል። ይኸ የትውልድ ትስስር ክፍተት እየሰፋ ሲሄድ በሀገር ጥንካሬ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል። በቀደመውና በተተኪው ትውልድ መካከል ያለው እሴትና የባህሪ ልዩነት እጅግ የሰፋ ሲሆን፤ በማህበረሰብ መካከል የጥቅም ግጭት በመፍጠር አፍራሽ ሀገራዊ ሁኔታን ይፈጥራል። አንዱ የአንዱን ሁኔታ የሚገነዘብ ሳይሆን፤ ተተኪው የቀደመውን አምርሮ የሚጠላ፤ የቀደመው ተተኪውን የሚያብጠለጥል በመሆኑ፤ ባለው ላይ የመገንባት ሳይሆን የማፍረስ ባህል እንዲፈጠር ያደርጋል።

በሀገራችን የንጉስና የመኳንንቱ ትውልድ የተማሪዎቹን ትውልድ ጥያቄና ፍላጎት በሚገባ እንዳላደመጠው በብዙዎች ዘንድ ይታመናል። ከዚህም ባሻገር የጥያቄያቸውን ጥንካሬ የመገንዘብ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን የመረዳት ደረጃው አናሳ እንደነበር ይገልጻል። በተመሳሳይ የተማሪዎቹም ትውልድ የንጉሱንና የመኳንንቱን ትውልድ አካሄድና ውጤቶች አልተመለከቱም እየተባሉ ወቀሳ ይሰነዘርባቸዋል። ከመልሱ ይልቅ ለጥያቄው ከፍ ያለ ቦታ ተሰጥቶት ነበር። ከውጤቱ ይልቅ ርዕዮተ ዓለም ቦታ ይዞ ነበር። በዚህ የተነሳ የዚያ ዘመን ትውልድ

የፈጠረው አብዮት ሀገር የተሻለ ጥንካሬ እንዲኖራት ሳይሆን፤ የከፋ የህልውና ጥያቄ ጉዞ ውስጥ እንድትዳክር ስለማድረጉ ብዙዎች የመከራከሪያ ነጥብ ያነሳሉ። የመከራከሪያ ነጥቦቹ ትክክለኝነት ምንም ይሁን ምን ከሁለቱ ትውልዶች ያልተግባባ ፍትጊያ የምንረዳው አንድ ሀቅ ቢኖር፣ በትውልድ መካከል የሚኖር ተግባቦት፣ መደማመጥና መቻቻል ከአፍራሽ ሂደት ለመውጣትና ጠንካራ ሀገር ለመገንባት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ነው።

ከአንድ ትውልድ ተሸጋሪ ሆነው የሚቀጥሉ ጠባዮችና ልማዶች ሀገራዊ እሴቶች ይሆናሉ። ሀገራዊ እሴቶች በትውልዶች ውስጥ የማይቀያየሩ የትናንትም የዛሬም ትውልድ መገለጫና ማንነት ናቸው። ሀገራዊ እሴቶችና ባህሎች የሚፈጠሩት በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ ነው። በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ የጠባይና የባህል መወራረድ አለ።

ለምሳሌ ሀገርን ከጠላት የመከላከል በየዘመናቱ የነበሩ ኢይትዮጵያውያን የጋራ መገለጫ እሴት ነው። በየትውልዱ ሀገራችን ኢትዮጵያ የጠላት ወረራና የህልውና አደጋ ይገጥማታል። ነገር ግን ሁሉም ትውልድ ጠላትን መክቶ ሀገር ሳትደፈር ለቀጣይ ትውልድ አስተላልፏታል። ይኸም ሀገራችን በዓለማችን ተደፍረው እና በጦር ግንባር ተሸንፈው ከማያውቁ ጥቂት ሀገራት ተርታ እንድትሰለፍ አድርጓታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ተቻችሎ የመኖርና እንግዳ ተቀባይነት በሀገራችን የብዙ ትውልድ ዘመን ያስቆጠረ እሴት ቢሆንም፤ አሁን ባለንበት ዘመን ግን የውጭ እንግዳን ይቅርና የገዛ ወገናችንን እንኳን ለመቀበል እየተሳነን መጥተናል።

የዘር የኃይማኖትና፣ የፖለቲካ አተያይና የግል ፍላጎታችንን አሸንፈን አዲስ ትውልዳዊ መፍትሔን ካላበጀን፤ ያጋጠመንን የህልውና ፈተና ለማለፍ ብዙ ተግዳሮቶች ይጠብቁናል። ትውልድ አብሮ የተገመደና የተቋጠረ ብቻ ሳይሆን፤ እንደ ወንዝ ሳያቋርጥ የሚፈስስ የዘመናት የክስተት ውጤት ነው። ሊሸከሙትና ሊያሻግሩት የማይቻሉትን የምልከታ መነጽሮቹን አውልቆና የአተያይ አድማሱን አስፍቶ፤ የራሱን ፈተና በማሸነፍ ለሚቀጥለው ትውልድ የተሻለ ሀገርን ማስረከብ፤ የዚህ ትውልስ ጊዜ የማይሰጥ የቤት ስራ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## የዘመናዊት ኢትዮጵያ ትውልዶች ፍጥረትና ስንኝት

### እውን "እሳት አመድን ወለደ?"

"እሳት አመድን ወለደ" የሚለው ሀገረኛ ብሂል፤ ነባሩ ትውልድ አዲሱን ትውልድ ለመውቀስ የሚጠቀምበት የተለመደ አገላለጽ ነው፡፡ በትውልድ መካከል ካለው ልዩነት የተነሳ፤ ነባሩ ትውልድ የአዲሱን ትውልድ ባህርይና ዐሻራ ለመቀበል የሚቸገርበት ሁኔታ ውስጥ ሲገባ፤ ወይም ከአዲሱ ትውልድ ጋር በቀላሉ መላመድ ሲቸገር፤ አዲሱን ትውልድ መተቸቱ የሚጠበቅ ነው፡፡ በአዲሱም ትውልድ ዘንድ በአንድ በኩል የቀደመውን ትውልድ

ስራዎችና ዐሻራዎች የማናናቅና ኋላ ቀር አድርጎ የመውሰድ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የቀደመውን ትውልድ ስራዎች አግንኖና የማይለወጡ አድርጎ የማየት ወይም ያልኖረውን ያለፈ ህይወት የመናፈቅ፤ ዝንባሌዎች ይስተዋላሉ።

የትውልድ ዐሻራዎችን፣ ጥንካሬዎችንና ድክመቶችን በልካቸው ተመልክቶ፤ ከእያንዳንዱ ትውልድ ተገቢውን ትምህርት መቅሰም፤ አስፈላጊና ጥንቃቄ የሚፈልግ ጉዳይ ነው። ይኽንን ለማድረግ ዋናው ፈታኝ ጉዳይ ደግሞ፤ ነገረ ትውልድ ከታሪክ አጠናንና አረዳድ ጋር የተቆራኘ መሆኑ ነው። የታሪክ ጥራት የሚወሰነው ደግሞ ከሰሪው ማንነት ይልቅ፤ በተራኪው ሙያዊ ብቃትና የተረክ አመክንዮ ላይ ነው።

ታሪክ ሰው ከትናንት ስኬቱና ስህተቱ የሚማርበትና፤ ወደ ነገ፡ ወደ ፊት ለመስፈንጠር የሚጠቀምበት የጥናት ዘርፍ መሆኑ ቀርቶ፤ የርዕዮተ ዓለም ክርክሮች ማስረጃና ማጣፈጫ ቅመም ተደርጎ ሲወሰድ፤ ብዙ ችግሮች ይፈጥራል። በመሠረቱ ርዕዮተ ዓለም ነገን ለመቅረጽ የሚደረግ የሐሳብ ሙግት ቢመስልም፤ በብዙ ጉዳዮች ላይ ወደ ኋላ የማጠንጠንና፤ በሂደትም ዋናውን ጉዳይ ትቶ የታሪክ ጥናትነት መልክ እየያዘ መምጣቱን ማስተዋል ይቻላል። ከማርክሲዝም ርዕዮተ ዓለም መምጣት ጋር ተያይዞ፤ የቀደመ የሰው ልጆችን ህይወት፤ ከዛሬውና ከነገው ጋር አያይዞ ለመተንተን የሚሞክሩ ፈላስፋዎች፣ ፖለቲከኞች እና ማህበራዊ ሳይንቲስቶች፤ ወደ ታሪክ ጥናት ተስበው መግባታቸውም፤ ይኽንን ሀቅ በሚገባ ያሳያል። የዚህ ዓይነቱ አካሄድ፤ የታሪክ ባለሙያዎች የዘነጓቸውን የታሪክ ጉዳዮች በማስታወስ በኩል የራሱ ሚና ቢኖረውም፤ የታሪክ ጥናት ዘርፍ ከሚፈልገው የጥናትና ምርምር የጥራት ደረጃ በተቃረነ መልኩ፤ በዘፈቀደና በፍላጎት ብቻ የሚመራና የሚተነተን ጉዳይ እንዲሆን አድርጎታል።

ስለትውልድ ስንነጋገርም፤ የታሪክ ጥናት ዘርፍን ድንበር ባለመጋፋትና በተቻለ መጠን በቂ ስምምነት ባለባቸው ታሪካዊ ኹነቶች ላይ ተመስርተን፤ መሆን ይኖርበታል። ይኽ ትውልድ እንዲህ ነው፤ ያኛው ደግሞ እንዲያ ነው፤ ብለን ስንነጋገር የታሪክ ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀርም። ዋናው ጉዳይ በጥቅል እውነታ ላይ ተመስርተን፤ በቂ ስምምነትና ማስረጃ ያላቸው የታሪክ ኹነቶችን መነሻ አድርገን፤ ሊያስተምረን በሚችል መልኩ፤ የተከታታይ ትውልዶችን ጠባይና ሁኔታ መመርመር ነው። ስለዚህ በታሪካዊ ኹነቶች ዝርዝር ጉዳይ ላይ ከማተኮርና እነሱን ከመመርመር ይልቅ፤ ጉልህ ታሪካዊ ክስተቶችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የትውልድን የጋራ ጠባይ መመርመር የተሻለ ነው።

የትውልድን ጠባይ ለመመርመር በምናደርገው ሙከራ የሚገጥመን ሌላኛው ተግዳሮት፤ አብዛኞቹ የምንመረምራቸው ትውልዶች አሁንም በኢትዮጲያ ፖለቲካ ውስጥ ሚናቸው ገና ያላለቀ መሆኑ ነው። በታሪክ ጥናት ዘርፍ ውስጥ ሂደታቸው ያላለቀ የታሪክ ኹነቶችን ማጥናት አስቸጋሪ ነው። ግለሰቦች የሚጠናው ታሪክ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎና ዝምድና አስቸጋሪ ነው። ግለሰቦች የሚጠናው ታሪክ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎና ዝምድና ስላላቸው፤ በታሪክ ጥናቱ ሀቀኝነት ላይ የራሳቸውን ተፅዕኖ ማሳረፋቸው አይቀርም። ስለሆነም ከዝርዝር የታሪክ ጥናት ዘርፍ ጋር የተያያዙ ማስረጃዎችና ታሪካዊ እውነቶች ላይ ከማተኮር ይልቅ፤ ትውልድን

ለመረዳት በሚጠቅሙ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ በማተኮር፤ ዋናውን ቁም ነገር እንዳንስት መጠንቀቅ ይኖርብናል።

ይኸን ስናደርግ፤ ትውልድን በስሜት ከማድነቅም ከመኮነንም ወጥተን፤ ‹‹እሳት አመድን ወለደ››፤ አመድም እሳትን አዳፈነ ሳንል፤ ለቀጣይ ትውልድ ግንባታችን ትምህርት በሚሰጥ መልኩ መሆን ይኖርበታል። ይኸ ትውልድን የመረዳትና የመመርመር ሙከራ ለክርክርና ለሌላ ዓይነት አረዳዶች ክፍት ነው። ዋናው ጉዳይ የትውልድን ጠባይና አመጣጥ ለመረዳት በምናደርገው ጥረት ውስጥ፤ መሠረታዊ የሆኑ የትውልድ ስኬቶችንና ስህተቶችን ፈትሸን፤ ተገቢውን ትምህርት መውሰዳችን ነው።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ትውልዶች የነበራቸውን ሚናና ድርሻ ታሪክ የሚመሰክረው፤ እኛም የምንዘክረው መሆኑ ሳይዘነጋ፤ በዘመናዊት ኢትዮጵያ ትውልዶች ላይ የተለየ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይኸም፡ አንድም ለትዝታችን ቅርብ፤ ለጥናትም ምቹ በመሆናቸው ሲሆን፤ ሌላም የዛሬይቱና የነገይቱ ኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ላይ ያላቸውን ጉልህ ሚና ለመረዳትና ለማዛመድ ምቹ በመሆኑ ነው።

# *“ቀለም እና ደም”*
# *የኢትዮጵያ ትውልድ አመጣጥ*

የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት በዋናነት በመሪዎች ዙሪያ የሚያጠነጥንና ትልቁን ትኩረቱን በፖለቲካ ታሪክ ላይ ያደረገ ነው። ለዚህ የተለያዩ ምክንያቶችን ማስቀመጥ ቢቻልም፤ አንዱ ምክንያት ለታሪክ ዘጋቢዎች ቅርብና ተደራሽ የነበሩትና፤ ትኩረትን የሚስቡት የፖለቲካ መሪዎች በመሆናቸው ነው። ስለዚህ የዘመናዊት ኢትዮጵያን ትውልዶች አመጣጥ ለመመርመርና ጠባያቸውን ለመረዳት፤ የተሻሉ የታሪክ ሰነዶችና ማስታወሻዎች ያሉበትን የዘመናዊት ኢትዮጵያን ታሪክ መመርመር ተመራጭ መንገድ ነው።

የዘመናዊት ኢትዮጵያ ትውልዶች በተሉያዩ እንግዳ ክስተቶችና የአኗኗር ለውጦች ተፅዕኖ ስር እንዲወድቁና፤ በሚከሰቱ አዳዲስ ክስተቶች ምክንያት በየጊዜው ጉልህ የጠባይ ለውጥ እንዲኖራቸው ያደረገው፤ የዘመናዊነት መምጣት ነው። ዘመናዊነት ስንል በአጭርና በቀላል አገላለጽ ይኸን ዘመን ማጠናቀቂያ አንስቶ እስከ 20ኛው መክዘ (መቶ ክፍለ ዘመን) ያለው ዘመን ‹‹ዘመናዊ የዓለም ታሪክ›› ተብሎ ይጠራል። ዘመናዊነት የሚለው ብያኔ ግን ይበልጥ ከ19ኛው መክዘ ማገባደጃ እስከ 20ኛው መክዘ መጀመሪያ የተፈጠረውን ኪነ ጥበባዊ ንቅናቄ ለመግለጽ ይውላል። ይኸ ኪነ ጥበባዊ ንቅናቄ መላውን ዓለም የናጠ የለውጥ ማዕበል ነበር። ትውፊታዊ የሆነውን የጥበብና የባህል ዕይታ በማናወጥ፤ አዳዲስ ፓራዳይሞች የፈጠረ ነው።

አሁን በዓለማችን ላይ ያለው ዓይነት የሰው ልጆች የአኗኗር ዘይቤ በ18ኛው መክዘ የተጀመረ ነው። የካፒታሊዝም መምጣትና የኢንዱስትሪዎች መስፋፋት፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አብዮቶች መበራከት፣ የከተማና የከተሜነት መስፋፋት፣ የዘመናዊ ትምህርት መጀመር፣ የዘመናዊ ሀገረ መንግስታት መመስረት፣ ወዘተ… የሰው

ልጆች አሁን ያላቸውን ዓይነት የራሱ ቀለም ያለው የአኗኗር ዘይቤ እንዲያዳብሩ አድርጓቸዋል። ዘመናዊነት ከዘመናት የሰው ልጅ ስልጣኔዎች መካከል፤ የአንዱ ዘመን ስልጣኔ መጠሪያ ነው ማለት እንችላለን።

የዚህ ስልጣኔ አንዱ ጉልህ መለያው፤ የሰው ልጆች የፍጆታ ባህል ያዳበሩበትና በአያሌ ቁሳቁሶች የሚገለገሉበት ጊዜ መሆኑ ነው። የኢንዱስትሪ መስፋፋትን ተከትሎ ትውልዱ በየቀኑ የሚገለገልባቸውና የሚጠቀማቸው ቁሳቁሶች ብዛት የትየለሌ ነው። የምግቡና የመጠጡ ዓይነትና ብዛት፤ የልብሱና የመዋቢያ ዕቃዎች መበራከት፤ የመዝናኛዎቹ ቁጥርና ዓይነት መትረፍረፍ፤ የመጓጓዣ ዘዴዎች አማራጭ ዓይነት፤ ወዘተ… ዘመናዊ የሰው ልጅ ከጠዋት እስከ ማታ የተለያዩ ቁሶችን ሲጠቀም የሚውል፤ ስልጣኔና ስኬትንም በሚጠቀማቸው ቁሳቁሶች ብዛት የሚለካ፤ ትልቅ የፍጆታ ማሽን እንዲመስል አድርጎታል።

በምርትና ምርታማነት ሂደትም አዳዲስ የግብርና ግብአቶችንና የእርሻ መሳሪያዎችን መጠቀም፣ አዳዲስ የኢንዱስትሪ ማሽኖችን መትከል፣ አዳዲስ የመጓጓዣ ዘዴዎችን መገልገል ወዘተ… የዘመናዊ የሰው ልጆች አኗኗር መለያዎች ናቸው። ከዚህ ቁሳዊ ጠባዩ ባሻገር፤ የሰው ል በአጠቃላይ ፖለቲካዊ እሴቱና ባህርይውም ትልቅ ለውጥ ያደረገበት ጊዜ ነው - ዘመናዊነት።

የሰው ልች የእኩልነትና የነጻነት ጥያቄዎች የተነሱበትና የተለያዩ አብዮቶች የተካሄዱበት፤ የኢኮኖሚና የባህል ልዩነቶች ሳይገድቧቸው የሰው ልጆች መብቶች ሊከበሩ እንደሚገባ የተቀነቀነበት ጊዜ ነው - ዘመናዊነት። የሰው ልጆች ለቡድናቸው የኃይል የበላይነት ከመታገል ባሻገር፤ ሁሉም የሰው ልጆች እኩል መብት አላቸው የሚለውን ሀሳብ በሰፊው መገንዘብና የጀመሩበት የታሪክ ምዕራፍ ነው - ዘመናዊነት።

በዚህም ምክንያት መሬት በጥቂቶች ብቻ የሚያዝበት የፊውዳሊዝም ስርዓት፤ በሰው ልጆች ትግል ከታሪክ ጠፍቷል። ሀገራት በድንበር የታጠሩ ሉዓላዊና ቁም ግዛቶች እንጂ በየጊዜው ከሰራዊት ብዛትና ዐቅም ጋር የሚሰፋና የሚጠቡ ግዛት ዐፄዎች መሆናቸው ቀርቷል። የሰው ልጆች ፍላጎትና መብት በህግ አግባብ በታጠረ፣ በመርህ በተከለለ ማህበራዊ ውል እንዲንቀሳቀስ ተደርጓል።

ይኸ የዘመናዊነት አመጣጥ በተለያዩ ሀገራት በተለያየ ጊዜና በተለያየ መልኩ የተካሄደ ቢሆንም፤ ቀድመው አዲሱን ስልጣኔ ከራሳቸው ባህል፣ ታሪክ፣ አኗኗር፣ ነባራዊ ሁኔታ እና የማህበረሰብ ጠባይ ጋር አስማምተውና አስታርቀው፤ የራሱ ቀለም ያለው ዘመናዊነት የገነቡ ሀገራት እንዳሉ ሁሉ፤ በቀደሙት ጀማሪዎች በተለይም በምዕራብ አውሮፓ ዘይቤዎች ተማርከው ብዙ ጣጣ ውስጥ የገቡ ሀገራትም በታሪክ ውስጥ ታይተዋል።

የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያጠኑ ልሂቃን ‹‹ዘመናዊት ኢትዮጵያ›› የሚሏት ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመን በኋላ የመጣችውን ነች። ኢትዮጵያ ዘመናዊነትን የተቀበለችበት መንገድና፤ በየጊዜው የነበሩ ትውልዶች በኢትዮጵያ አዲሱን ስልጣኔ ለማንበር ያደረጉት ጥረት፤ የትውልድን ጠባይ እንዲሁም የአሁኗን ኢትዮጵያ ፖለቲካዊና

ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን የቀረጸ ሂደት ነው። ለዚህ ሂደት ደግሞ ዘመናዊ ትምህርትን፤ ማለትም ከባህላዊና ኃይማኖታዊ ትምህርቶች የዘለለውንና ብዙኃኑ የሚሳተፉበትን ትምህርት፤ የጀመረችበት ሂደት ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ይኸም በኢትዮጵያ የዘመናዊነት ጅማሮ፤ ምሁራዊ ባህልንና የትውልድ ጠባይን እጅግ የተሳሰሩ ጉዳዮች አድርጓቸዋል።

ዘመናዊነት ከዘመናዊ ትምህርት ጋር የተያያዘ በመሆኑ፤ ዘመናዊዎቹን ትውልዶች ከቀረጹ የታሪክ ሂደቶችና ክስተቶች ጀርባ፤ ትውልዶቹ በጋራ ያለፉበት የትምህርት ሂደትና ምሁራዊ ጠባይ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። በሌላ አነጋገር ዘመናዊነት ወደ ሀገራችን የገባውና ወደ መላው ህዝብ እየሰረጸ የመጣው በተማሪዎችና በምሁራን በኩል ስለነበር፤ የኢትዮጵያን የትምህርት ሁኔታና የምሁራኑን ጠባይ መመርመር፤ የኢትዮጵያን ዘመናዊ ትውልድ ጠባይ ለመረዳትና የሀገራችንን አሁናዊ ሁኔታ በአግባቡ ለመገንዘብ ያስችለናል። ስለሆነም በየጊዜው ካለፍንባቸው የታሪክ ክስተቶችና ሂደቶች ጋር የትምህርትን ጉዳይ አስተሳስረን መመልከቱ፤ ዘመናዊነትን የተረዳንበትንና የሀገራችንን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የቀረጽንበትን መንገድ ለመመርመር ይጠቅመናል።

ሌላው የኢትዮጵያን ትውልድ ስንመረምር ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ ጉዳይ፤ ኢትዮጵያ ህልውናዋን ለማስጠበቅ ያደረገቻቸው የተለያዩ ጦርነቶች ናቸው። ቅኝ ገዥዎች አፍሪካን ለመቀራመት ያደረጓቸውን ዘመቻዎች በመመከትና፤ የቅኝ ገዥዎች እርሾ በፈጠሯቸው አካባቢያዊ ጦርነቶችም ብርቱ የህልውና ትግል በማድረግ፤ ያለፈችባቸው ሂደቶች ትውልድን በመቅረጽ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ዘመናዊነትን በመገንባት ኢትዮጵያን በኋላ ቀርነት ለማላቀቅና፤ ህልውናዋን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማረጋገጥ የተደረጉ ጥረቶች በየትውልዱ ባህርይ ላይ የራሳቸውን ዐሻራ አሳርፈዋል።

በጥቅሉ ስንመለከተው የዘመናዊ ትውልዶቻችን አመጣጥ ከምሁራዊና ከጀግንነት ታሪካችን ይቀዳል። ከቀለምና ከደም ታሪካችን ጋር ይተሳሰራል። የኢትዮጵያን መፅሐፍና ጠመንጃ፤ ሀገር በቀሎቹን ሊቃውንትና ሰራዊትን መረዳት፤ የየትውልዱን ጠባይና ዐሻራ ለመገንዘብና የኢትዮጵያን የህልውና ትግል ለመፈተሽ በእጅጉ ያግዛል። የህልውና ትግሉ የሚካሄደው፤ በዕውቀት ኃይል አለያም በመሳሪያ ኃይል በመሆኑ፤ ሀለቱን ጉዳዮች በአግባቡ መመርመር የየትውልዱን ስኬትና ስህተት አንጥሮ ለመለየት ይጠቅማል።

እንግዲህ ዋናው ጥያቄ የጀግንነት ታሪካችን ላይ ያሳየናቸው የአይበገሬነት ተጋድሎዎች፤ በምሁራዊ ታሪካችን ላይ ያልተደገሙት ለምንድነው? የሚለው ነው። አድዋ ላይ ያሸንፍነው የምዕራባውያን የበላይነት መንፈስ፤ በሶሻሊስት ርዕዮት በኩል እንዴት ሾልኮ ሊገባ ቻለ? በጠመንጃ ያሳየነው በራስ መተማመን፤ እንዴት ራስንና ታሪክን በሚያስንቁ ርዕዮተ ዓለሞች ተተካ? ይኸ ቀላል ጥያቄ አይደለም። አንድ በኩራት መንፈስ ራሱንና ነጻነቱን የሚያስከብር፤ በጀግንነት ለህልውናው የሚታገል፤ መሸነፍን ፈጽሞ የማያውቅና የማይወድ ኩሩና ጀግና ህዝብ፤ ራሱንና ወጉን በሚጠላና በሚያጥላላ፤ የፈረንጅን ሁሉ ነገር በሚያደንቅ፤ ስለፈረንጅ ስልጣኔ ብቻ በሚያወራ፤ የዘመን መንፈስ እንዴት ተወሰደ? በጠመንጃው አሸንፈን ለምን በመጽሐፉ እየተሸነፍን

መጣን? በደማችን የጻፍነውን ገድል ለምን በቀለማችን አደበዘዝነው?

## *የዘመናዊት ኢትዮጵያ ትውልድ*

## *1. ወግ አጥባቂው ትውልድ*

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ትምህርት ጅማሮ ቀዳሚዎቹ ሙከራዎች የዳግማዊ ምኒልክና የራስ መኮንን ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ በእነዚህ ትምህርት ቤቶችም ሆነ በተለያዩ የውጭ ሀገራት የመማር ዕድል ያገኙ ኢትዮጵያውያን፤ በዘመናዊ ታሪካችን ውስጥ ኢትዮጵያን ለመገንባት የመጀመሪያዎቹን ጥረቶች አድርገዋል፡፡ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ከነባሩና ከባህላዊው ስርዓትና አኗኗራችን የበቀሉ፤ ባህላዊና ኃይማኖታዊ ትምህርቶችን የተማሩ፤ በተጨማሪ ደግሞ በተለያየ የግል አጋጣሚ የውጭ ሀገር ትምህርት የቀመሱ ዜጎች ናቸው፡፡

ይኸ ትውልድ በዘመናዊ ኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዎቹን የዘመናዊነት ጣዕሞች የቀመሰ ትውልድ ነው፡፡ የአስኳላ ትምህርት፣ ሆቴል፣ መኪና፣ ሲኒማ፣ አውሮፕላን፣ ጋዜጣ፣ ወዘተ. ለመጀመሪያ ጊዜ የተመለከተም የተገለገለም ነው፡፡ ይኸ ትውልድ በአንድ በኩል የአድዋ ድል ኩራትና አይበገሬነትን ሲሰማና ሲያወጋ ያደገ፤ በሌላ በኩል በሁለተኛው የጣልያን ጦርነት ጊዜ ያየው ፈተና ቁጭት የፈጠረበት ነው፡፡ በአንድ ጎኑ እንደ ዐለት የጠጠረው ኢትዮጵያዊ መንፈስ በልቡ ውስጥ ጸንቶ ቆሟል፤ በሌላ ጎኑ በውጭ ሀገራት የተመለከተው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እልህ ፈጥሮበታል፡፡ በውጭ ሀገር የተመለከተውን ዕድገትና የዘመናዊነት ተሞክሮ፤ ወደ ሀገሩ ለማምጣትና ኢትዮጵያን ካደጉት ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ ህልም የሰነቀ፤ በአድዋ አሸናፊነት የጸናው ኢትዮጵያዊ መንፈሱ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ዕድገቱም እንዲጸና መሻት ያደረበት፤ ከውስጡ የሚተናነቀው ኢትዮጵያዊ አይበገሬነት በዘመናዊት ኢትዮጵያ ግንባት እንዲደገም ምኞት የነበረው ትውልድ ነበር፡፡ ይኸ ትውልድ ሀገርን ለመለወጥ በመተጋገዝና በኢትዮጵያዊነት መንፈስ በጋራ መቆም ያስፈልጋል፤ የሚል አቋም ነበረው፡፡ በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያን ዕድገትና የዘመናዊነት ግንባታ ለማሳካት፤ ዘግይታ ወደ ዘመናዊነት የገባችውን የጃፓንን ተሞክሮ መቅሰም አስፈላጊ ነው፤ የሚል እምነት አዳበረ፡፡ በጊዜው የነበሩና የጃፓንን ተሞክሮ የሚያቀነቅኑ ሊቃውንት፤ ጃፓን እንደ ኢትዮጵያ በመሳፍንት አገዛዝ ስትታመስ ቆይታ ወደ አንድነቷ መመለሷን፣ እንደ ኢትዮጵያ ጥንታዊት ሀገር መሆኗን፣ የውጭ ወረራን ተቋቁማ ነጻነቷን ማስከበሯን፣ ወዘተ. በመጥቀስ እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ካፒታሊዝምን የገነባች ሀገር መሆኗን በማስታወስ፤ ኢትዮጵያ የጃፓንን ተሞክሮ ብትቀስም ያዋጣታል፤ የሚል ሀሳብ ያቀርቡ ጀመር፡፡

ጃፓን ዘመናዊነትን የተቀበለችው ከራሷ ቀለምና ባህል ጋር አጣጥማ፣ የነበረውን ንጉሳዊ የአስተዳደር ስርዓት ተከትላ፣ እንዲሁም ከውጭ የሚነሱ ግፊቶችን በአይበገሬ ኩራት በመመከት በመሆኑ፤ ለእነዚህ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ትኩረት የምትስብ ሀገር ነበረች፡፡ አንዳንድ የዐፄ ኃይለ ስላሴ እርምጃዎች፤ በተለይም ህገ መንግስታዊ የንጉስ ስርዓት ለመመስረት የመጀመሪያውን ህገ መንግስት ማስተዋወቃቸው፤ የዚህ ከጃፓን ተሞክሮ የመቅሰም ፍላጎት አካል ይመስላል፡፡ ምንም እንኳን ጃፓን በጊዜው የነበረችበት ሁኔታ በአንጻራዊነት የዘመናዊነት ምልክቶች ትንሽ ቀደም ብለው የታዩበት ቢሆንም፤ ሁለቱ ሀገራት በነበሩበት ተቀራራቢ የታሪክ፣

የፖለቲካና የኢኮኖሚ ነባራዊ ሁኔታ እንጻር ከጃፓን ተሞክሮ ለመቅሰም ማሰባቸው የሚገርም አይደለም።

ኢትዮጵያ በአድዋ ጊዜ ቅኝ ገዥዎችን አንገት አስደፍታለች። ጃፓኖችም ሳይቀሩ በኢትዮጵያ የነጻነት ትግል ትኩረታቸው ተስቦ ነበር። ቢሆንም በአይበገሬነትና በኩሩነታችን ላይ መገንባት የነበረበት የዘመናዊነት ጅማሮ ከመዘግየቱ ባሻገር፤ አቅጣጫውን ስቶ በፈቃዳችን በወጉ ያልተላመጠ የተውሶ ሀሳብ ተሸካሚ እንድንሆን በማድረጉ ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል። ለዘመናዊነት ግንባታ በመዘግየታችን ምክንያት ጣልያን መልሶ ተደራጅቶ ሊወጋን ሲመጣ፤ በቂ ዝግጅት አድርገን አለመጠበቃችን ቁጭት የሚፈጥር ጉዳይ ነበር።

በዚህም ምክንያት ይኸ የዘመናዊት ኢትዮጵያ የመጀመሪያው ትውልድ በአድዋ ድል ኩራትና፤ በሁለተኛው የጣልያን ጦርነት ቁጭት ውስጥ የተፈጠረ እንደመሆኑ፤ በዚህ የታሪክ ሂደት ያገኘውን የዘመናዊ ትምህርት ዕድል፤ ኢትዮጵያን ከነኩራቷና ከነዕድሏ ለማስቀጠን ጥረት እንዲያደርግ የሚያነሳሳው ነበር።

በሁለቱም ጦርነቶች የታየው የኢትዮጵያውያን ጀግንነትና አይበገሬነት፤ ትውልዱን ኩሩነትንና ራስን የማክበር ስነ ልቦና ያላበሰው ከፍ ያለ የታሪክ ሂደት ነበር። ከፋሽስት ጣልያን ጋር የነበረው እልህና፤ ፋሽስት ይዞት የተነሳውን የእብሪት መንገድ ለማስተንፈስ፤ ኢትዮጵያን አዘምኖ በማንም ኃይል የማትበገር ሀገር ለማድረግ፤ የነበረው የቁርጠኝነት መንፈስ ጠንካራ ነበር።

ይኸ ከፍተኛ የጀግንነት፣ የአይበገሬነት፣ የዐርበኝነትና የኩሩ ህዝብነት መንፈስ፤ የዘመናዊነት እሳቤን ከኢትዮጵያ ወግና እሴት ጋር አጣጥሞ ለመሄድ የሚገፋፋ ነበር። በዚህም ምክንያት ይኸ ትውልድ የኢትዮጵያን ዘመናዊነት ሊቀምር የፈለገው፤ የኢትዮጵያን ህዝብ ወግና ስርዓት፣ አኗኗርና ታሪክ፣ የዐርበኝነትና የኩሩ ህዝብነት መንፈስ፤ እንደያዘ ነበር። የዘመናዊነት ፍላጎቱ መነሻም ይኸንኑ የአይበገሬነት መንፈስ ለማጽናትና፤ ኢትዮጵያን በዓለም አደባባይ እስከነክብሯ ለማቆየት ነበር።

ይኸ ትውልድ ነባሩንና ባህላዊውን ስርዓት መጠየቅ፤ እንዲሁም የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ መፈተሽና ማሻሻል የጀመረ፤ የለውጥ መንፈስን ያነገበ ትውልድ ነበር። ከቀደመው የሸዋ መኳንንት ወግ አጥባቂ ዝንባሌ ጋር ሲተያይ፤ የለውጥ መንፈስ ያነገበና ከእነርሱ ጋርም የታገለ ነው። ከኋለኞቹ ትውልዶች አንጻር ሲታይም ነባሩን ከዘመናዊው አጣጥሞ ለመጓዝ የተነሳ ትውልድ ነበር። በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትውልድ አንጻራዊ ዕይታ ስንመለከተው ግን፤ የለውጥ እሳቤዎቹ ወግን በመጠበቅ ዘመናዊነትን ሊያሳልጥ የተነሳ እንደመሆኑ፤ “ወግ አጥባቂው ትውልድ” ተስማሚ ስያሜው ነው።

ይኸ የትውልድ ብያኔ የሚወክለው በሀገሪቱ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስርዓቶች ላይ ትንታኔ የማድረግና ሀሳብ የመሰንዘር እድሉ ያለውን የልሂቃን ቡድን የሚገልጽ እንጂ ሰፊውን ህዝብ የሚመለከት አይደለም። በዚያን ዘመን የነበረው ህዝብ የኑሮ ሁኔታው ሁለት ዓይነት ነበር። በአንድ በኩል ቁጥራቸው ጥቂት የሆኑ የመሬት

ከበርቴዎች አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ሰፊው ህዝብ ጭሰኛ ሆኖ ያረሰና ያመረተውን ለመሬት ከበርቴው በገፍ እየሰጠ የበይ ተመልካች ሆኖ ኑሮውን ይገፋል። እንደ ከበርቴዎቹ ሁሉ ቤተ አምልኮዎችም በጭሰኛው የሚያሳርሱት ሰፊ የሆነ የመሬት ይዞታ አላቸው። የተቀረውም ዜጋ በንግድ፣ በልዩ ልዩ የእጅ ሙያዎች እና በቤተ አምልኮዎች አገልጋይነት የተሰማራ ነበር።

ሀገሪቱ ዓመታዊ ምርት ላይ ከዘጠና በላይ የሚሆነው የሚሸፈነው በግብርናው ዘርፍ እንደመሆኑ መጠን ከመሬት ከበርቴው በተጨማሪ ሌላውም ህዝብ በአንድም በሌላም መንገድ የጭሰኛ ገበሬውና የአርብቶ አደሩ ሸክም መሆናቸው አይቀሬ ነው። የጦር መሳሪያ ታጥቆ ወታደር የሚሆነው እንዲሁም ሸፍቶ በመሳሪያው እየዘረፈ የሚያድረውም ከጭሰኛ ገበሬውና አርብቶ አደሩ ላብ ተቋዳሽ ነው። ይኸ የተዛባ የምርት ግንኙነት በግብርና ላይ የተሰማራውን የህብረተሰብ ክፍል እያማረረው አልፎ አልፎ ለህዝባዊ አመጽ እንዲነሳሳ ይዳረግ ነበር። በሰሜን ቀዳማዊ ወያኔ፣ በደቡብ ምስራቅ የባሌ ገበሬዎች እንዲሁም በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ጎጃም ገበሬዎች ያቀጣጠሏቸው ህዝባዊ አመጾች በልሂቃኑ ያልተመሩና ቀጥታ ህዝቡ የምርት ግንኙነቱ የፈጠረበትን ከልክ ያለፈ ተጽዕኖ በመቃወም ብሶቱን የገለጸባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ። እነዚህና ሌሎች ሰፊው ህዝብ የሚከተላቸው የኑሮ ዘይቤዎችን ተከትለው የሚፈጠሩ ተቃርኖዎች በአንድም በሌላ መንገድ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አቅጣጫ የመተለም አቅም የነበራቸው ናቸው። ዳሩ ግን ተጽዕኖአቸው የተንጸባረቀው ከዘመኑ ልሂቃን ይልቅ ቆይቶ በተፈጠሩት ትውልዶች ላይ ሆኖ እናገኘዋለን። በዚያን ዘመን ከነበረው ህዝብ ይልቅ ልሂቃኑን በተለየ ‹‹ወግ አጥባቂ ትውልድ›› የሚል ስያሜ ሊያሰጥ የቻለበት ሌላኛው ምክንያት ልሂቃኑ ወደ ኢትዮጵያ ዝመናን ለማምጣት በሚያደርጉት ትግል ውስጥ ይኼንን የሰፊው ህዝብን አንገብጋቢ ጥያቄ የለውጥ እንቅስቃሴያቸው አካል ለማድረግ ፍላጎታቸው አናሳ በመሆኑ ጭምር ነው።

## *2. ህልመኛው ትውልድ*

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ ከወግ አጥባቂው ትውልድ ቀጥሎ የሚመጣው፤ ብዙ ጸሐፍት ‹‹ያ ትውልድ›› ሲሉ የሚገልጹት፤ በትውልዱ መሠረታዊ ባህርይ ምክንያት "ህልመኛው ትውልድ" ብለን ልንጠራው የምንችለው ትውልድ ነው። ይኸም በ20ኛው መክዘ አጋማሽ ላይ የተፈጠረውና የ1960ዎቹ ትውልድ በመባል የሚታወቀው ነው። ይኸ ትውልድ በዐፄ ኃይለ ስላሴ ዘመን የተፈጠረው፤ ከዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት፣ ከመገናኛ ዘዴዎች መምጣትና የውጭ ሀገር ልምድ መጨመር የተነሳ ነው።

ይኸ ትውልድ በ1953 ዓ.ም. በንጉሱ ላይ የተሞከረውን፤ ‹‹የታህሳሱ ግርግር›› በመባል የሚታወቀውን የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተከትሎ በመጣው የለውጥ ንፋስ ውስጥ ያለፈ ትውልድ ነው። በተማሪዎች ንቅናቄ ሂደት ውስጥ የጎረምሰ፤ በምስጢራዊ የጥናት ክበቦችና በሀገራዊ ዘመቻዎች ውስጥ ራሱን ስለ ሶሻሊዝም ያስተማረና በምስጢር ያደራጀ፤ በነጭ ሽብርና በቀይ ሽብር መከራዎች ውስጥ ያለፈ፤ በገፍ ሀገሩን ጥሎ የተሰደደ መከረኛ ትውልድ ነው። አንዳንዶች ይኼንን ትውልድ መከራ የቀመሰ አድርገው

ሲያስቀምጡት፣ ሌሎች ደም ለዛሬው ትውልድ መከራን ያወረሰ አድርገው ይቆጥሩታል። ያም ሆነ ይኸ፣ ህልመኛው ትውልድ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እጅግ መሠረታዊ የሚባል የታሪክ እጥፋት ውስጥ ያለፈና፤ ኢትዮጵያ አሁን ላለችበት ነባራዊ ሁኔታም የራሱን ጉልህ አሉታዊ ሚና የተጫወተ ስለመሆኑ ብዙዎቻችንን ያስማማል።

"ህልመኛው ትውልድ" በልሂቃኑ ዘንድ "ያ ትውልድ" ተብሎ መጠቀሱ የራሱ መነሻ ሊኖረው ቢችልም፤ በመሠረቱ ቃሉን በቀጥታ ስንመለከተው ተምሳሌታዊ ትርጉም የሚሰጥ ሆኖ እናገኘዋለን። ከማህበሩ በመነጠል ፈንጠር ብሎ እንደቆመ ሰው ‹‹ያ›› ተብሎ ጣት የሚጠቆምበት ህልመኛው ትውልድ፣ በእርግጥም ልቡ የሚማልልላቸውን ከባህር ማዶ የተገኙ አስተሳሰቦችና ማንነቶች ከሀገሩ እሴትና ወጎች ጋር እንዲስማማ አድርጎ ማስኬድ ስላዳገተው ከሀገሩና ከህዝብ ልብ የራቀ፣ ከእውን ይልቅ በህልም መመላለስን የመረጠ ተደርጎ ይታሰባል። የኢትዮጵያ ታሪክ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከኩሩና አይበገሬ ትውልድ ወጥቶ፤ ራሱን አጥብቆ የሚንቅና ፈረንጅን በተለየ ሁኔታ የሚያከብር፤ የራሱ የሆነን ነገር ሁሉ እንደ ኋላ ቀር የሚመለከት፤ የራሱን ሀገር ለመፈተሽና ለማዘመን በአድዋ ተራሮች ድል የነሳቸው ቅኝ ገዥዎችን ቡራኬ የሚፈልግ ትውልድ ወደ መፍጠር የተሸጋገረ ነው የሚል ወቀሳ ይሰነዘርበታል።

በሌላ በኩል ደሞ ህልመኛው ትውልድ በኢትዮጵያ ውስጥ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት የለውጥ ችቦን ያቀጣጠለ ተደርጎ ሲወደስ ይደመጣል። በዚያን ዘመን በኢትዮጵያ የነበረውን ነባራዊ ሁኔታ የሚለውጡ ሶስት መሠረታዊ ጥያቄዎች የተደመጠበት ወቅት ነበር። ከእነዚህም መካከል የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ በጉልህ የሚጠቀስና ያ ትውልድ በኩራት የሚናገረው ታላቅ ገድል ተደርጎ በብዙዎች ይቀመጣል።

"የመሬት ለአራሽ" እንቅስቃሴ ተቀጣጥሎ በመጨረሻ በአዋጅ ምላሽ እስኪሰጠው ድረስ በኢትዮጵያ የነበረው የእርሻ መሬት ይዞታው በጥቂት ባላባቶች እጅ እንደነበረ ታሪክ ይነግረናል። በወቅቱ የነበረው የገባሪ - አስገባሪ ስርዓት ባላባቱ መሬት ያቀርባል፤ ጭሰኞች ዓመት እስከ ዓመት ቤተሰቦቻቸውን ይዘው ያርሳሉ፣ ይዘራሉ፣ ያጭዳሉ። ምርቱ ሲደርስ የወቅቱ የገባር ስርዓት እጅግ ከፍተኛ የሆነውን የግብርና ምርት ባላባቱ እንዲወስድ የሚፈቅድ ሲሆን፤ አራሹ ገበሬ የሚያገኘው ጥቅም ከልፋቱ አኳያ እዚህ ግባ የማይባልና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ እንዲገፋ እንኳን የማያስችል ነበር። ይኸ የምርት ግንኙነት እንዲቀየር የዚያ ትውልድ አባላት ከአስር ዓመታት ለበለጠ ጊዜ ያደረጉት ትግል የመሬት ስሪቱን በመቀየር፤ በሀገራችን አዲስ ዓይነት የኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ስርዓት መፍጠር ችሏል። የገጠርን መሬት ለአራሽ ያደረገው አዋጅ መጽደቁን ተከትሎ የዘመኑ ወጣቶች አደባባይ በመውጣት እንዲህ ሲሉ ስለማዜማቸው ይነገራል።

*"ዋይ ዋይ ባላባት፣*
*ከእንግዲህ ቀረ ተኝቶ መብላት።*
*ኃይለኛ እየሄደ ያስገብራል የትም፣*
*መሬት የሁሉም ናት ባለቤት የላትም።"*

ከመሬት ለአራሹ በማስከተል ያ ትውልድ በጉልህ የሚጠቀስለት የለውጥ ጥያቄ የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር በኢትዮጵያ እንዲሰፍን የነበረው ምኞት ነው። ምንም እንኳን ምኞቱ የኋላ ኋላ ቅዠት በመሆን ቢጠናቀቅም፣ ንጉሳዊ የአስተዳደር ስርዓትን አፍርሶ ህዝባዊ መንግስት እንዲመሰረት ያደረገው ትግል ከፍተኛ ነበር። በተሳካ ሁኔታ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ስላሴን ከመንበራቸው መፈንቀል ቢችልም ስርዓቱን ወደ ታለመለት ዴሞክራሲያዊ የህዝብ አስተዳደር ስርዓት መገንባት አልቻለም። አንድ ንጉስ ተሸኝቶ መቶ ሃያ ወታደሮች ነገሱ። ‹‹ያለ ምንም ደም›› በሚል መፈክር የተጀመረው ሽግግር የእብደት ዘመንን ወለደ፤ የአንድ ሀገር ልጆች እርስ በእርስ የሚባሉበት ሁኔታ ተፈጠረ። በትውልዱ መካከል እያቆጠቆጠ የቆየው የርዕዮተ ዓለም ክርክር ወንድምን ከወንድም ያጨካክን ጀመረ፤ ሚሊዮኖች በደም ጎርፍ ታጠቡ፤ ዜጎች ሀገርና ቀያቸውን ጥለው በየአቅጣጫው መሳደድ ያዙ።

ስለ ኢትዮጵያ በመቆጨት ረገድ በወግ አጥባቂውና በህልመኛው ትውልድ መካከል ተመሳሳይነት አለ። ልዩነቱ የተፈጠረው በተከተሉት የመፍትሄ መንገድ ላይ ነው። ወግ አጥባቂው ትውልድ ምንም እንኳን የጥንቱን ወግ ለመንካት ፍርሃት የሸበበው ቢሆንም እየተሸኮረመመ ቢሆን ነባሩን እሴት ከዘመናዊነት ጋር አጣምሮ ለመያዝ ሙከራዎችን አድርጓል። ህልመኛው ትውልድ ደግሞ ነባሩ እሴት ላይ አንዳች ጠቃሚ ነገር የሌለ እስኪመስል ምንም ዓይነት የማሻሻል ፍላጎት ሳያድርበት በምትኩ ሶሻሊስታዊ እሴት በሞላው አዲስ ባህል ሀገር ለመመስረት ታግሏል።

በዚህ ምክንያት “ያ ትውልድ” ኢትዮጵያ የነበረችበት ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ ቁጭት የፈጠረበት፤ ነገር ግን ቁጭት የራስን ማንነትና ኩራት ወደ መተውና የፈረንጅን ነገር ሁሉ እንደ ወረደ የመተግበር አባዜ የተጠናወተው ትውልድ ተደርጎ እንዲታይ አድርጎታል። ለዚህም በወቅቱ በዓለም ዘንድ ከፍተኛ ተፅዕኖ የፈጠረው የማርክሲስት ርዕዮተ ዓለም፣ በተለያዩ ዓለማት የተከሰቱ ከፍተኛ የተማሪዎች እንቅስቃሴዎችና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች መነሳሳት፣ በሀገር ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ጅማሮ የነበረበት ጊዜ መሆኑን ይኸም የትምህርት ሂደት በምዕራባውያኑ አስተምህሮ የተቃኘ መሆኑ ወዘተ. በሰበብነት ሊጠቀስ ይችላል።

የህልመኛው ትውልድ አባላት ምንም እንኳን የኢትዮጵያን ነባራዊ ችግር ለመተንተንና ተገቢውን መፍትሄ ለማፍለቅ፤ ኢትዮጵያዊ ወጎችና እሴቶችን ትተውና ከራሳቸው ማንነት ርቀው የነበረ ቢሆንም፤ በኢትዮጵያ የነበሩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ፈጽሞ አልተረዷቸውም ማለት ግን አይደለም። በአውሮፓውያን ልማድና አስተሳሰብ የተቃኘ ምልከታ ቢኖራቸውም፤ የተማሩት ዘመናዊ ትምህርት የህብረተሰባቸውን ችግር እንዲያስተውሉና ለወገናቸው መብትና ጥቅም እንዲጨነቁ አድርጓቸዋል።

የዚህ ትውልድ ልሂቃን ዋናው ችግር ከመሬትም ሆነ ከብሄር፤ ከኢኮኖሚያዊም ሆነ ፖለቲካዊ ችግሮች ጋር የተያያዙትን ጉዳዮች በራሳችን ዐውድና ሁኔታ መረዳት፤ እንዲሁም በራሳችን ወግና እሴት መሠረት መፍታት

የምንችልበት የካበተ ልምድ ያለን ሀገር መሆናችንን መዘንጋታቸው ነው። ለዘመናት ፖለቲካዊ ችግሮቻችንን በፈረንጆች ሀሳብና እርዳታ ሳይሆን በራሳችን መላና ዘዴ ስንፈታ የኖርን ህዝቦች ነበርን። ነገር ግን በአንዴ ከባህር ማዶ በተቀዳ ሀሳብ ሁሉንም ነገራችንን ካልተነተንን አልን። የሁሉም ነገር መፍትሄ ከሶስት ሰዎች ጭንቅላት ይቀዳል ተብሎ በትውልዱ ጉምቱ ልሂቃን ዘንድ ታመነ። የማያውቁን ሰዎች ለራሳቸው የሰፉትን ልብስ ለሁላችንም ይበቃል ብለን ወሰንን። የራሳችን ሀገራዊ መላዎች የነበሩባቸውን የሀሳብና የአተገባበር ድክመቶች እያረመንና በአዳዲስ ሀሳቦች እያጎለበትን መሄድ ሲገባን፤ ጥቃቅን ድክመቶችን ሳይቀር በመጥቀስ አሽቀንጥሮ ለመጣልና ኋላ ቀር አድርጎ ለመሳል የነበረን ዝንባሌ ከእውነተኛ ማንነታችን እንድንነጠል አደረገን።

ይልቁንም በጦርነት ታሪካችን ያበላሸናቸውን ነገሮችና፤ ችግሮችን በኃይል የመፍታት ልማዶቻችንን ለማረም፤ ሀገራዊ መላዎቻችንን ማጠናከርና በአዳዲስ ሀሳቦች እያደረጁ መሄድ፤ ተመራጩ መንገድ መሆን ነበረበት። ነገር ግን በወቅቱ በዘመናዊ ትምህርት ጅማሮ የተቀበልነው የፈረንጅን ነገር ከተገቢው በላይ የማዳነቅ ሁኔታ በመጠኑ ከመንገዳችን አስቶናል። ይኸ በቀጥታ የተቀበልነው ፖለቲካዊ ልማድና ባህል ደግሞ ቀስ በቀስ በአክራሪነትና በማፍረስ ላይ እተገነባ ሰመጣ ሳናስበው የትውልድ ቅብብሎሹን እየናድነው፤ ከነባራዊ አውነታና ማንነታችን ፍጹም የራቀ ሀሳባዊ ዓለም ለመፍጠር ትግል ውስጥ ገባን።

ሃይማታዊ በሆነ ሀገር ላይ ፈጽሞ ኢአማኒነት የሚቀነቀንበት አስተሳሰብ መጣ። ቤተ እምነቶችና መድረሳዎች፣ ካህናትና ሼኮች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና በዘመናት የዳበረ ሀገራዊ እሴታችንን ጠንቅቀው የሚያውቁ ጉምቱ አባቶች በሀገር ጉዳይ ላይ ድምጽ ተነፈጋቸው። በውይይትና በምክክር ችግሮችን በሚፈታ ህዝብ ላይ አንዱ አንዱን ካላጠፋ ስርዓት ሊገነባ አይችልም የሚል አብዮት ተፈጠረ። በመከባበርና በሆደ ሰፊነት ለመራመድ በሚሞክር ህብረተሰብ ውስጥ፤ በሴራና በመጠላለፍ የሚመራ ፖለቲካ ተተከለ።

"ያ ትውልድ" አንድ ህልም የሚያስፈልገውን ሀሳብ ጥራትና እውን የመሆን ዐቅም ከግንዛቤ ሳያስገባ የወሰዳቸው እርምጃዎች ከፍተኛ የጀብደኝነት ባልን ፈጥረዋል። ጀብደኝነት ዐቅምን ያላገናዘበ አጉል ድፍረት ነው፤ ዓላማ ስኬት ይልቅ በመንገዱ ላይ ለሚደረገው መስዋዕትነትና አላስፈላጊ ዋጋ የበለጠ ትርጉም ይሰጣል። ጀብደኝነት ከጀግንነት የሚለየው ጀግና ዓላማውንና ዐቅሙን በሚገባ ለይቶ የሚያውቅ ጠቢብ ሲሆን፤ ጀብደኛ ግን በግልጽ ለማያውቀው ዓላማ፤ ባልተረዳው ዐቅሙ፤ አላስፈላጊና ውጤት የማያመጣ ዋጋ የሚከፍል መሆኑ ነው። እሳት ለማጥፋት የዛፍ ቅርንጫፍ የሚዘነጥፍ፣ ውሃ የሚቀዳ፣ ወደ እሳቱ ተጠግቶ ርብርብ የሚያረግ ጀግና ነው። እሳት ለማጥፋት በሚል ሰበብ ዘሎ እሳት ውስጥ የሚገባ ሰው ግን ጀብደኛ እንጂ ጀግና አይደለም።

በሌላ በኩል ስንመለከተው ግን ሕልመኛው ትውልድ ለዓላማው የነበረው ጽናትና፤ ለሀገሩ የነበረው ተቆርቋሪነት እጅግ የሚያስደንቅ ነው። የግዛት አንድነቷ የተጠበቀች ኢትዮጵያን ለትውልድ ለማሻገር ይበጃል

ባለው መንገድ ተንቀሳቅሷል፡፡ ምንም እንኳን ሁሉን ለውጥ ዛሬውኑ በሚል ግትር አቋምና ይኼንን ለማሳካት በብዛት የሚመርጣቸው የለውጥ መንገዶች አብዮታዊና ደም አፋሳሽ መሆናቸው እንደ ሀገር ብዙ ዋጋ ቢያስከፍልም ትውልዱ ለሀገሩ ያለው ፍቅር እምብዛም ጥያቄ ውስጥ አይገባም፡፡ ለግንባሩ ሳይሳሳ የሲያድ ባሬን ወረራ የመከተውም ይኼ ትውልድ ነው፡፡ የህዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የወሰዳቸው አብዛኞቹ እርምጃዎች ትክክለኛነት እና ውጤታማነታቸው ላይ ክርክር ቢነሳም ትውልዱ በህዝብ ጉዳይ የነበረው አቋም እጅግ ጠንካራ እንደነበረ አያጠያይቅም፡፡ ከላይ እንደጠቀስነው የሀገራችንን የመሬት ስሪት ከገባር ስርዓት እንዲወጣ ማድረጉና ሌሎች የእኩል ተጠቃሚነት እንዲረጋገጡ ያደረጋቸው ትግሎች ትውልድ ለህዝብ ተጠቃሚነት ያለውን የጸና አቋም ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ፡፡ በችሎታና በእውቀቱ ህዝብን ለማገልገል ገጠር ድረስ መውረዱ፤ የገበሬውን ጥማትና ርሃብ እየተጋራ መሠረታዊ ትምህርቶችን ማስተማሩ ለሀገሩና ለህዝቡ ስላለው ቀናኢ ፍቅር ምስክር መሆን ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከቁሳዊ ሽሚያ ባሻገር ለዓላማ መኖር ምን ማለት እንደሆነ እስከ ጥግ ድረስ ያሳየ ትውልድ በመሆኑ፤ ቀጣዮቹ የኢትዮጵያ ትውልዶች ትልቅ ትምህርት ሊወስዱበት የሚገባ ነው፡፡

## *3. ውል አልባው ትውልድ*

ሶስተኛው የኢትዮጵያ ትውልድ ‹‹ውል አልባው ትውልድ›› ነው፡፡ በ20ኛው መክዘ የመጨረሻዎቹ ሶስት ዐስር ዓመታት፤ ማለትም በደርግ መንግስት ማብቂያና በኢህአዴግ መንግስት መጀመሪያ አካባቢ፤ ለዐቅመ ፖለቲካ የደረሰው ትውልድ ነው፡፡

ይህ ትውልድ የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለምን ይዞ የመጣው  የ‹‹ያ ትውልድ›› ተፅዕኖ ያረፈበት ነው፡፡ ከ‹‹ያ ትውልድ›› ስልጣኑን የነጠቀው ወታደራዊ መንግስት ሲናጥና ሲወድቅ አይቷል፡፡ የ‹‹ያ ትውልድ›› የብሔር ፖለቲካ ክንፍ በድንገት ስልጣን ሲይዝ ተመልክቷል፡፡ የሶሻሊዝም ገባናነት ሲንኮታኮት ታዝቧል፡፡ የተራዘመ ጦርነትና ብሔራዊ ውትድርና አሳሩን አሳይቶታል፡፡

የ‹‹ያ ትውልድ›› ብሔርተኛው ክንፍ ጫካ ውስጥ በሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም ሲታገል ቆይቶ፤ በለስ ቀንቶት ወደ ቤተ መንግስት ሲገባ፤ ሲታገልለት የቆየው ርዕዮተ ዓለም በዓለም ላይ ዓይንህ ላፈር የተባለበት ጊዜ ስለነበር አንቅሮ ተፍቶታል፡፡ ለሶሻሊዝም ወጣትነታቸውን የገበሩ ታጋዮች፤ በድንገት ከአዲሱ የዓለም ነባራዊ ሁኔታ ጋ ለመላመድ ተቸገሩ፤ ምክንያቱም የታገሉለት ርዕዮትና ለስልጣን የበቁበት ወቅት አልተጣጣሙም፡፡ በዚህም የተነሳ ውሉ የጠፋበትና ግልጽነት የጎደለው የፖለቲካ ስርዓት መገንባት ጀመሩ፡፡

ይህ በሶሻሊዝም ርዕዮት ካፒታሊዝምን ለመገንባት የተደረገ ውል አልባ ሙከራ፤ ውል አልባውን ትውልድ ፈጠረው፡፡ ‹‹ውል አልባው›› የምንለው ትውልድ የ‹‹ያ ትውልድ›› የብሔር ክንፍ ፖለቲከኞች ወደ ስልጣን

መምጣትና፤ በወቅቱ የነበረው ግራ መጋባት የፈጠረው ስም የታገለው ኢህአዴግ፤ በወቅቱ በሀገራችን ላይ ሊፈጥረው የፈለገው ፖለቲካ ግራ የገባው ነበር። በዚያ ዘመን ለዐቅመ ፖለቲካ የደረሰውን ትውልድም ግራ መጋባት ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል። በአንድ በኩል የመደብ ፖለቲካን በሌላ በኩል የብሄር ፖለቲካን፤ በአንድ በኩል ሶሻሊዝምን በሌላ በኩል የካፒታሊስት የገበያ ስርዓትን ማቀንቀኑ የተደበላለቀና እርስ በእርስ የሚፃረር የፖለቲካ አውድ ፈጥሯል። ይህ በግራ መጋባት ውስጥ የነበረ የፖለቲካ ተዋስዖ፤ ግራ የተጋባና ውል የሌለው ትውልድ ፈጠረ

የዚህ ትውልድ ፖለቲካ የረጋና በግልጽ ለመናገር የሚያስችል እሳቤና ይዘት አልነበረውም። በመሠረቱ በመላ ሀገራችን የቀይ ሽብርና የነጭ ሽብር ፖለቲካ የፈጠረው ሰቆቃና ከፖለቲካ የመራቅ አዝማሚያ፤ ትውልዱ ንቁ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዳይኖረው ያደረገ ነበር ማለት ይቻላል። በአንጻራዊነት ከፍ ያለ ፖለቲካዊ መነቃቃት ያሳየው በምርጫ 97 ጊዜ ነበር። ወትሮውንም በፖለቲካፍራቻ እንደ ዔሊ ራሱን ቀብሮና ደብቆ የነበረው ትውልድ ለጥቂት ጊዜ ቢነቃቃም ምርጫ 97 የፈጠረው አለመረጋጋትና ውጥረት ተመልሶ ወደ ዋሻው እንዲገባ አድርጎታል። ይህ ትውልድ በኢህአዴግ በተዘረጋው የልዩነት የፖለቲካ ትርክት ውስጥ ያለፈ በመሆኑ፤ የብሄርና ሃይማኖት ግጭቶች የተስተዋሉበትና ሀገራዊ የደበዘዙበት ነበር ማለት ይቻላል።

## *4. ባይተዋሩ ትውልድ*

አራተኛውን ከሚሊኒዬሙ ማግስት የተፈጠረው ትውልድ በልዩነት ፖለቲካ ተኮትኩቶ ያደገው ‹‹ባይተዋሩ ትውልድ›› ነው። እርስ በእስ ባይተዋር፤ ለሀገሩ ባይተዋር፤ ለታሪኩ ባይተዋር፤ በአጠቃላይ ለሚኖርበት ህረተሰብ ባይተዋር በመሆን፤ በመክፋትና በምሬት ውስጥ የተዋጠ ትውልድ ነው። ባይተዋርነቱ ከሁለት ዋና ዋና ምንጮች ይቀዳል፤ አንደኛ፡ የልዩነት ፖለቲካና ትርክት ተቋማዊ ቅርጽ ይዞ የተቀነቀነበት ዘመን በመሆኑ፤ ትውልዱ ለገዛ ሀገሩና ለወገኖቹ ባይተዋር ሆኖ አድጓል። ሁለተኛ፡ እየተስፋፋ በመጣው ሉአላዊነትና የዓለም ነባራዊ ሁኔታ የተነሳ፤ እንዲሁም የሚዲያዎችና የማህበራዊ ሚዲያዎች መስፋፋት በፈጠረው ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ምክንያት ወደ ውጭ በመሳቡ፤ ለገዛ ሀገሩ ባይተዋር ሆኗል። ስለዚህም ሀገሩ የሌላትን የሚጠይቅ፤ አልሰጠችኝም ብሎ ትቷት የሚሰደድ፤ መብቱን እንጂ ግዴታውን በውል ጠንቅቆ ያልተረዳ ትውልድ ሆኗል።

እነዚህ የጠቀስናቸው ሁለት ተቃራኒ ጉዳዮች፤ ማለትም በአድማስ ጠባብ የማንነት ፖለቲካ ማደጉ እና በአድማስ ሰፊ የሉአላዊነት ዘመን ላይ መኖሩ፤ የሚፈልገውን በቅጡ እንዳያውቅና የባይተዋርነት ስሜት እንዲፈጠርበት አድርጎታል። ባይተዋርነት በመብሰክሰክ፣ በተበዳይነትና፣ በተስፋ መቁረጥ የተዋጠ ስሜት ነው። በመሆኑም ግጭት፣ እርስ በእርስ መካሰስ፣ ጠያቂነትና ጠባቂነት በትውልዱ ውስጥ በሰፊው ይንጸባረቃሉ። ማህበራዊ ሚዲያው የፈጠረው የመረጃ ምንጮች መበራከት፤ መረጃን አጣርቶ ለመጠቀም ፈተና የጋረጠበትና፤ በዚህም ምክንያት ከተለያዩ አቅጣጫዎች በሚነሱ ነፍሶች የሚወዛወዝ ትውልድ አድርጎታል።

ይኸ ትውልድ ከህልመኛው ትውልድ ጀምሮ ሲቀነቀን የነበረው የአክራሪነት ፖለቲካ ጫፍ የደረሰበትና ፍሬ ያፈራበት ትውልድ ነው፡፡ በተለይም በድህረ 1983 በመዋቅር ደረጃ ልዩነትንና በደልን ብቻ ሲሰበክ በማደጉ፤ ሉአላዊነት በፈጠረው ዓለም አቀፋዊነት ድባብ ያለፈ ቢሆንም እንኳን፤ ከቡድንና ከማንነት አስተሳሰብና ፖለቲካ ጋር በእጅግ የተቆራኘ ነው፡፡

ዓለም አቀፋዊ ሁኔታውና ኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሂደት ዴሞክራሲን አጥብቆ እንዲያቀነቅን ቢያደርገውም፤ ዴሞክራሲ እንዲሰጠው እንጂ ዴሞክራሲን ለመገንባት የሚያስፈልገውን ዲሲፕሊንና ኃላፊነት በሚገባ አልተረዳም፡፡ ዘውትር የመብት ጥያቄዎቹን ቢያቀነቅንም፤ ግዴታዎቹን በማክበርና ኃላፊነቱን መወጣት ግን ፈተና የሆነበት ትውልድ ነው፡፡

ከላይ ተዘረዘሩት አራት ትውልዶች “ወግ አጥባቂው”፣ “ህልመኛው”፣ “ውል አልባው” እና “ባይተዋሩ” ትውልድ የሚለያዩበትም የሚመሳሰሉበትም ባህርያት አሏቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የትውልድን ቁጥርም ሆነ ስያሜና ባህርይ ከዚህ በተለየ መንገድ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ምናልባትም ‹‹ባይተዋሩ›› ብለን ከሰየምነው የመጨረሻው ትውልድ በኋላም ሌላ ትውልድ ተፈጥሮ እየተመመ ሊሆን ይችላል፡፡ ትልቁ ቁም ነገር ሀገርንና ለውጥን ስናስብ፤ የትውልድን ታሪካዊ ፋይዳና ተግባራዊ አንድምታ መረዳቱ ላይ ነው፡፡ ሀገርን በቦታ፣ በክልልና በዞን ከፋፍለን እንደምናስተዳድር፤ ዘመንንም በትውልድ ከፋፍሎ ማየትና መረዳት ያለው ጠቀሜታ ቀላል አይደለም፡፡ በተለይም ካለፉት ትውልዶች ተምሮ፤ መጪውን ትውልድ በተገቢ መንገድ ለመቅረጽና የስልጣኔን መሠረት ለመጣል እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## ትውልድ ፈጣሪ ኃይላትን መረዳትና መምራት

## ፈተናችንን መለየት፤ መፍትሔ ለማበጀት

የዘመናዊት ኢትዮጵያ ትውልዶች የፖለቲካ ልሂቃን የተለያዩ ፓራዳይሞች አቀንቃኞች የነበሩ እንደመሆኑ፤ በየዘመናቸው የፈጠሯቸው፤ አሁንም ድረስ ሲንከባለሉ የኖሩ አዎንታዊም፤ አሉታዊም ተፅዕኖዎች አሉ። ከሁሉም በላቀ ሁኔታ የሶሻሊዝም ፓራዳይም ጫና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የጎላ ነው። የኢትዮጵያ ትውልዶች እና ፖለቲካ በአብዛኛው የሶሻሊዝም ፓራዳይም ተፅእኖ ይንጸባረቅባቸዋል። ሶሻሊዝም የህልመኛውን ትውልድ ካጥለቀለቀው ጊዜ ጀምሮ፤ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዋነኛ መገለጫ ሆኖ ቆይቷል።

ከንጉሱ መውደቅ በኋላ የመንግስትን ስልጣን በተቆጣጠሩት ዘንድም ይሁን በተፎካካሪው ጎራ የተሰለፉት ሶሻሊዝም የተጫናቸው ነበሩ። ከህልመኛው ትውልድ በሶሻሊስታዊ ቅኝት ኢትዮጵያን የማዘመን ትልም ጀምሮ፤ ሶሻሊዝም የፖለቲካ ባህላችን ላይ ጉልህ የተፅዕኖ ድርሻ ነበረው።

አንዳንዶች እንዲሉት "ኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ" የትውልዱ ኢትዮጵያን የማዘመን ፍላጎት ዋነኛ መገለጫ ነበር። ትውልዱ የሶሻሊዝም እሳቤዎችን እንደ ፍጹማዊ ቃል የሚመለከት፤ ፓራዳይሙም ኢትዮጵያ ውስጥ እውን እንዲሆን በከፍተኛ ደረጃ የተንቀሳቀሰ ነበር። የሀሳቡ ወራሽ የመጀመሪያው ትውልድ ከአለባበስ ጀምሮ ዓለም አቀፍ የእሳቤው ተምሳሌቶችን የተከተለ ነበር። ከህልመኛው ትውልድ በኋላም ቢሆን የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከፓራዳይሙ ተፅዕኖ ጫና አልተላቀቀም። ስርዓቱ ከወደቀ ሶስት ዐስርት ዓመታት ቢያልፍም፤ እነዚህ ኮሙኒስታዊ እሴቶች በሀገራችን የፖለቲካ ባህል ውስጥ ተደባልቀው፤ አሁንም ፖለቲካውንና ኢኮኖሚውን የሚዘውሩ የጨዋታው ደንብና ህግጋት ሆነው ያገለግላሉ። የግራ ዘመም እሳቤ በጥቂት ውስጥ አብዮታዊና የገዘፈ የፖለቲካ ለውጥን የፈጠረ እንደመሆኑ፤ በፖለቲካችን ውስጥ ያሳረፈው ዐሻራ አሁን ድረስ ገዥ ፓራዳይም ሆኖ እንደ ቀጠለ ነው። ፓራዳይሙ በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ እንዲህ ዓይነት የገዘፈ ሚና እንዲኖረው ያደረጉት ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው። የመጀመሪያው፡ እሳቤው ከተቃዋሚነት ጎራ አልፎ መንግስታዊ ስልጣንን የተቆጣጣረ ኃይል፤ ሀገር የሚመራበት ማዕቀፍ የነበረ እሳቤ ከመሆኑ ጋር የተገናኘ ነው። በደርግ ብቻ ሳይሆን በኢህአዴግ/ሕወሃት አገዛዝ ዘመንም እሳቤው መንግስታዊ ስልጣንን የተቆጣጠረ ነበር። በዚህም እሳቤው መዋቅራዊ ቅርጽ ይዞ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለመሸጋገር ዕድሉን አግኝቷል።

ሁለተኛው ምክንያት፡ እሳቤው መዋቅራዊ ቅርጽ ከማግኘቱ በተጨማሪ በሶሻሊዝም የተቃኘው የህልመኛው ትውልድ የፖለቲካ ተፅዕኖ በዘመኑ ብቻ የተገደበ አለመሆኑ ነው። የትውልዱ አባላት አሁን ድረስ የፖለቲካ ተሳትፏቸው አለማባራቱ፤ ሶሻሊዝም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የፈጠረው ተፅዕኖና የፖለቲካ ባህል የገዘፈ እንዲሆን አድርጎታል። የሶሻሊዝም ዐሻራ የፈጠረው የፖለቲካ ባህል አሁን ድረስ የፖለቲካችን መገለጫ ሆኖ፤ ዛሬም የስልጣን መወጣጫ ዓይነተኛ መንገድ ሆኖ ይታያል።

በሶስተኛነት፡ በሀገራችን ሶሻሊዝም አበቃለት ከተባለም በኋላ፤ የተጠናከረ አማራጭ ፓራዳይም ብቅ ማለት

አለመቻሉ ነው። እዚህም እዚያም የተለያየ እሳቤዎች በተለያየ ደረጃና ጊዜ ብቅ ጥልቅ ቢሉም፤ ወጥ ሆነውና ተጠናክረው በመውጣት ለትውልዱ አማራጭ ገዥ ፖለቲካዊ ተረክና መሪ ፓራዳይም ለመሆን አልቻለም። በመሆኑም የፖለቲካ ጨዋታው ህግጋት በቀደመው የእሳቤ ማዕቀፍ ላይ የተመሰረተና የተቸነከረ ሆኖ እንዲቆይ አድርጎታል። በእነዚህ ምክንያቶችም በሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለማዊ መነጽር፤ ትውልድን የመፍጠርና የመቅረጽ አንድ ኃይል ሆኖ፤ ላለፈው ግማሽ ምዕተ ዓመት እንደቀጠለ ነው።

ሆኖም ሶሻሊዝምና ከዚያ ቀደም ብሎ የነበሩ ፓራዳይሞች የፈጠሩት ፖለቲካ ተፅዕኖ መታረም በሚገባቸው ጊዜ ባለመታረማቸው፤ ከዚህ በላይ መጓዝና ማስጓዝ ወደማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ፓራዳይሞቹ የሞረዱት የፖለቲካ ባህል ሀገርን ለከፍተኛ ውጥንቅጥ ዳርጓል። በዚህ ከቀጠለም ከፍተኛ አደጋን ወደሚያስከትልበት ደረጃ ላይ መድረሱ እሙን ነው። የርዕዮተ ዓለሙ ውሃ ፈስሶ ፈስሶ ወደ ፊት መጓዝ ከማይችልበት የአስተሳሰብ ተራራ ጋር በመላተሙ፤ አቅጣጫውን መቀየር የግድ ሆኗል። ነባሩ የፖለቲካ ማዕቀፍ የተናጋና ቀውስ የተፈጠበት በመሆኑ፤ ነባራዊ ሁኔታን በሚያገናዝብ አዲስ ፓራዳይም ሊተካ ያስፈልጋል።

የተለያዩ የፖለቲካ ማዕቀፎች በየዘመኑ የፈጠሩት መልካም ውጤት አለ። ይሁንና አሁን ሀገራችን እየተፈተነች ባለው ፈተናዎችና ችግሮች ተገፍታ በደረሰችበት ደረጃ፤ በአረጀ ፓራዳይም መመራት አትችልም። የፓራዳይም ለውጥ የግድ ሆኗል። የቀደሙት ትውልድ ያለፉበት የፖለቲካ ፓራዳይም፤ ዴሞክራሲንና ጠንካራ ሀገር ግንባታን ለመሸከም ያስቻለ ባለመሆኑ፤ ከቀደሙት ፓራዳይሞች አሉታዊ ተፅዕኖዎች የተላቀቀ፤ አዳዲስ የፖለቲካ እሴቶችን የተላበሰ፤ ተተኪ ትውልድን የሚገነባ አዲስ ፓራዳይም ስፈላጊነቱ ጎልቶ ወጥቷል።

ይህ የፓራዳይም ለውጥ አስፈላጊነት የሚመነጨው ከተለያዩ መሠረታዊ ጉዳዮች ነው። በዋናነት ግን የነባሩ ፓራዳይም መሠረታዊ ክፍተቶች ከቀረጸው ትውልድ ቀውስ፤ ፓራዳይሙ ከፈጠረው ሀገራዊ ሁኔታና፤ በፍጥነት እየተለወጠ ካለው ዓለም አቀፋዊ እውነታ ጋር የሚያያዝ ነው።

## *የሰማዩን ጥግ ፍለጋ*

አክራነት የሰማይን ዳርቻ ፍለጋ የሚደረግ ከንቱ ግስጋሴ ነው። ሰማይን ስንመለከተው ከተራራው ወይም ከሩቅ ከሚታየው አንድ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ነገር ጀርባ የተሸሸገ ጥግ ያለው ይመስለናል። ነገር ግን ከአድማስ ጥጉ ለመድረስ እስከ ተራራው ጫፍ ብንጓዝም፤ ከሩቅ የሚታይ ሌላ የሰማዩ ዳር የሚመስል አዲስ አድማስ እናገኛለን። ከቀጣዩ አድማስ ጥግ ደርሰን ብንመለከትም ሰማይ ከምድር የተሰፋበት የሚመስል ሌላ ነገር ከሩቅ ይጠብቀናል።

በዘመናዊቱ ኢትዮጵያ ሀገራዊ ጉዞ ውስጥ፤ አክራሪነት ዓይነተኛ ኃይል ሆኖ ትውልዶችን የመፍጠርና የመቅረጽ ከፍተኛ ሚናው ቀጥሏል። አክራሪነት የአንድ ሀሳብ የመጨረሻ ጥግን መፈለግ ነው። አንዱ ዳር ሲደርሱ

ሀሳብን እየለጠጡ ሌላ ጫፍ የመፈለግ። የማያባራ የአንድ ጽንፍ ፍለጋ ጉዞ። ይህም አንድን ጥግ የመፈለግ ወይም ውል የሌለው ልዩነትን የመለጠጥ የማያባራ ጉዞ፤ በትብብርና በፉክክር ሚዛን የመሳት ውጤት ነው።

በአንድ በኩል ከእኔ ጋር ብቻ ተስፋ የሚል አላስፈላጊ ልሙጥ የሆነ ትብብር ፍለጋ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ እኔ ወይ አንተ ብቻ ትክክል ነን፤ የሚል የተወጠረ ፉክክር መልክ አለው። አክራሪነት ‹‹እኔን ምሰል›› የሚል ጠቅላይነት እና ‹‹አትመስለኝም›› የሚል አግላይነት ያቀፉት፤ ከራሱ የተጣለ የአስተሳሰብ ዝንባሌ ነው።

አክራነት ‹‹የእኔ ብቻ›› ሀሳብና ድርጊት የሚል ቢሆንም፤ የራሱን ከመውደድ ይልቅ የሌላውን በመጥላት የሚገለጽ ባህላዊ መሠረት ያለው የሀሳብና የድርጊት ውቅር ነው። ሀይማኖትንና ብሄርን መሰረት ያደረገ ደካማ የውይይትና ያለመቻቻል ባህል ለአክራሪነት መሠረት ነው። አክራሪነት በባህል ደረጃ በብዙኃኑ የህብረተሰብ ክፍል የሚታይ ነው። በሀሳብ ደረጃ የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል የሚገልጽ ሲሆን፤ ልዩነትን ለማስተናገድ ፍቃደኛ ያልሆነ፤ ተቃዋሚ የመቀነስ ዝንባሌ ነው። ነገሩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስነ ልቦናዊ መነሻ ያለው ሲሆን፤ ሰዎች በንግግራቸውና በጽሁፋቸው ውስጥ ዕለት ተዕለት ይኖሩታል።

ጽንፈኝነትና ዋልታ ረገጥነት ዋነኞቹ በሀሳብ ደረጃ የሚታዩ አክራሪነቶች ናቸው። ጽንፈኝነት ርዕዮት ዓለማዊ፤ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ሀይማኖታዊ መነሻ ያላቸው እንደ ናዚዝም ያሉ ጫፍ የረገጡ ሀሳቦችን ፈጥሯል።

ዋልታ ረገጥነት ደግሞ ምንም እንኳን ይህ ነው የሚባል ርዕዮተ ዓለማዊ ልዩነት ባይኖራቸውም፤ ሰዎች በቡድናዊ ስሜት ልዩነትን አለአግባብ የመለጠጥ አባዜ ሲጠናወታቸው የሚያሳዩት፤ አስተሳሰባዊና ግብራዊ መገለጫ ነው። ለምሳሌ በሀገራችን ዘመናዊ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ፤ ኢህአፓንና መኢሶንን የመሳሰሉ በርዕዮተ ዓለማዊ ጉዳይ ልዩነት ሳይኖራቸው፤ በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ በነበረ የገመድ ጉተታ ጦስ ለዋልታ ረገጥነት ተጋልጠው የተጠፋፉ ፓርቲዎችን መጥቀስ ይቻላ።

በሀገራችን ያአለመቻቻል ባህል በነባር ፓራዳይሞች ርዕዮተ ዓለማዊ ጽንፈኝነት ውስጥ ይበልጥ ቅርጽና መልክ ይዞ፤ ለሀገር አሳሳቢ የሆነበት ደረጃ ላይ ደርሷል። በብዙሃኑ ዘንድ የሚታየው የአለመቻቻል ባህልና ፖለቲካ ልሂቁ ዘንድ ያለው ጽንፈኝነትና ዋልታ ረገጥነት በጊዜ ካታረመ፤ ሀገር አፍራሽ በሆነ የከፋ ድርጊት መገለጡ አይቀርም። ድርጊቱ ማንነትን ወይም ልዩነትን መሠረት ያደረገ ጥቃት ሲሆን፤ ብዙሃኑን ሳይሆን ጥቂት የህብረተሰቡን ክፍልን የሚገልጽ ነው። የአክራሪነት ጥቃት ጥቂት የህብረተሰብ ክፍልን የሚገልጽ ቢሆንም፤ ተፅዕኖው ወደ ብዙሃኑ ተዛምቶ አከራሪነት እንዲባባስና ከቁጥጥር ውጪ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ጦሱ እጅግ ከፍ ያለ መሆኑ አይቀርም።

አክራሪነት አለመተማመን እንዲሰፍን እና ማህበራዊ መስተጋብር እንዲላላ ያደርጋል። በባህርይ ደረጃ አክራሪነት ማህበራዊ አልያም ፖለቲካዊ መልክ ሊኖረው ይችላል። ማህበራዊ አክራሪነት በማህበረሰብ ደረጃ፤

በግልጽ በሚታይ ወይም በስውር በማይታይ መንገድ፤ ልዩነቶችን መሰረት አድርጎ የሚኖር ጫፍ የረገጠ እሳቤና ድርጊት ነው። አንዳንድ ጊዜ ማህበራዊ አክራሪነት በማህበረሰብ ውስጥ የተጣበቀና በባህል ውስጥ የተሰፋ ስለሚሆን፤ ማህበረሰቡ ችግሩን ሳይገነዘብ አብሮት ሊዘልቅ ይችላል። በዕለት ተዕለትም ሴቶችንና ህፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችንና የተለየ ተፈጥሮ ያላቸውን፣ አዛውንቶችንና እንግዶችን በማግለል ዓይነት፤ በማህበረሰብ ውስጥ ሊታይ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ዘረኝነት፣ አውራጃዊነትና ሃይማኖታዊ ጽንፈኝነት ከማህበራዊ አክራሪነት ተርታ የሚመደቡ ናቸው።

ማህበራዊ አክራሪነት መልክና ቅርጽ ይዞ ፖለቲካዊ ግብን ሲያነግን፤ ወደ ፖለቲካዊ አክራሪነት ደረጃ ይሸጋገራል። ፖለቲካዊ አክራሪነት በአብዛኛው በፖለቲካ ልሂቃን የሚዘወር ሲሆን፤ ልሂቃን ህብረተሰቡን በማንቀሳቀስ የፖለቲካ ግባቸውን ለማሳካት የሚጥሩበት አደገኛ መንገድ ነው። በእሳቤ ደረጃ ፖለቲካዊ አክራሪነት በተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ተወለደ ባይባልም፤ ከ1960ዎቹ ጀምሮ በነበረው ሶሻሊዝም በተጫነው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ጠንክሮ እንደወጣ አያጠያይቅም።

አክራሪነት የፖለቲካ ባህላችን ዋነኛ መገለጫ እየሆነ ስለመጣ፤ የአክራሪነት ድርጊቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ፤ አክራሪነት የፖለቲካ ጨዋታው ገዥ ህግ፤ መጠፋፋት ደግሞ ቀዳሚው መንገድ ሆኖ፤ ህልውናችንን በከፋ የአደጋ አፋፍ ላይ አድርሰውታል። ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተወራረሰ መጥቶም የጠንካራ ሀገር ግንባታ ዋነኛው ደንቃራ ሆኗል።

በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ የአክራሪነት መጠናከር ለለውጥና ለሀገር ግንባታ ፈታኝ የሆነ ሶስት ተግዳሮቶችን ፈጥሯል። እነዚህም ስር ነቀልነት፣ ደካማ ዴሞክራሲያዊ ባህል እና ደም አፋሳሽነት ወይም ያልዘመነ የትግል ስልት ናቸው። ስር ነቀልነት አንዱ የሰራውን እያረሙ በእርሱም ላይ የተሻለ ነገር እየጨመሩ ከመሄድ ይልቅ፤ አፍርሶ እንደገና የመጀመር ደካማ የፖለቲካ ባህል ነው። ሀገራችንን ሰርክ አዲስ ጎጆ ወጪ እንድትመስል የሚያደርጋት ይህ አፍርሶ የመጀመር አባዜ ነው።

ዴሞክራሲያዊ ባህል በሐሳብ የበላይነት የማመን፤ እንዲሁም ዜጎች በሚመለከታቸው መንግስታዊና ህዝባዊ ጉዳይ ላይ፤ በተናጠልና በቡድን የመሳተፍ ፍላጎትና ዐቅም ነው። ይህ ፍላጎትና ዐቅም የስልጡን ፖለቲካ ምልክት ሲሆን፤ ሁለት ጉዳዮችን አጥብቆ ይሻል። በአንድ በኩል የዜጎችን ተሳትፎ የሚፈቅድና የሚያደምጥ መንግስት፤ በሌላ በኩል በሰለጠነ መንገድና የሌላውን መብት በማይጥስ አካሄድ የሚሳተፍ ግለሰብና ቡድን ይፈልጋል።

በሀገራችን የዜጎችን ተሳትፎ የሚፈቅድ መንግስት ባለመኖሩ ምክንያት፤ ዋነኛው የትግል ስልት ኃይልን የቀላቀለ ኢ-ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ሆኖ ቆይቷል። ይህ ለዘመናት ሲደጋገም በመቆየቱም ደካማ የዴሞክራሲ ባህል እንዲኖር አድርጓል። ደካማ የዴሞክራሲ ባህል በከፍተኛ ደረጃ የሰረጸ በመሆኑ፤ የትውልድ እሴት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖና ጫና እያደረሰ ነው። ከዚህም የተነሳ በለውጡ የፖለቲካ ምህዳርን የማስፋት እና ዴሞክራሲን

የመትከል ሙከራዎች ቢታዩም፤ ፖለቲካዊ ትግል የሚደረግበት አካሄድ ገና አልተለወጠም። ይልቁንም የዴሞክራሲ ጅማሬው የሚሰጠውን ነጻነት በመጠቀም፤ በኃይልና በኢ-ዴሞክራሲያዊ መንገድ መንግስትን ለመለወጥ የሚደረግ ጥረትና፤ የፖለቲካ ግብን ለማሳካት ልዩነትን በደም አፋሳሽ መንገድ ለማስተናገድ፤ የሚከውኑ ስልቶች ተስፋፍተዋል። ማህበራዊ ሚዲያ የፈጠረውን ዕድል በመጠቀም፤ የሃይማኖት ተቋማትንና የትምህርት ማዕከላትን ሳይቀር ለእኩይ ዓላማቸው በማሰለፍ፤ ስልጣን ለመቆጣጠር የሚደረጉ ሙከራዎች ቀላል አይደሉም።

አሁን ያለው ትውልድ በአክራሪነት ጦስ ከተፈጠሩት ተግዳሮቶች በላይ በማሰብና በመኖር አሸንፎ እንዲወጣ ካላደረግን በስተቀር፤ የቀደመውን ትውልድ ቀውስ ውስጥ የከተቱት አዙሪቶች፤ የዚህም ትውልድ ዕጣ ፈንታ መሆናቸው አይቀርም። ሥር ነቀልነትን በተሀድሷዊ ለውጥ መቀየር ይገባል። ደካማ ዴሞክራሲያዊ ባህል፤ በሀሳብ የበላይነት በሚያምን፤ ፈቃድና ዐቅም ባለው፤ አሳታፊና ሰፊ፤ ፖለቲካዊ ምህዳር መተካት ይኖርብናል። እንዲሁም ደም አፋሳሽ የሆነ ደካማ የትግል ስልታችንን፤ በሀሳብና በግብር ብልጫ በሚደረግ ትብብር ያልጎደለው ሰላማዊ ውድድር፤ የመለወጥ ስራ ልንሰራ ይገባል። ቀጣዩን ትውልድ በተሻለ መሠረት ላይ ልንገነባ የምንችለው፤ የአክራሪነትን ኃይል በዚህ መልኩ መግታትና፤ አዳዲሶቹን አመለካከቶች በአዲሱ ትውልድ ላይ ማስረጽ ስንችል ብቻ ነው።

## *የሳሳ የሀገረ መንግስት ቅቡልነት*

የሰው ልጅ ፖለቲካዊ ስርዓት ካልተፈጠረበት ኢተገማችና ውጥንቅጡ ከወጣ ሁኔታ፤ የፖለቲካ ስርዓቶችን ወደ መፍጠር የተሸጋገረው፤ የተሻለ የደህንነት ሁኔታ ለማግኘት እንደሆነ፤ በፖለቲካ ስርዓት አፈጣጠር ዙሪያ የሚያጠኑ ምሁራን ይገልጻሉ። የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፤ ስርዓት ካልነበረበት ሁኔታ ወደ ሰከነ እና ወደ ደረጀ ስርዓት የተሸጋገረው፤ ፍላጎቱ በተሻለ ደረጃ ይጠበቅልኛል ብሎ በማመን ነው። ይህ ምርምር ሀገራት የተፈጠሩበትን ሁኔታ ሙሉ በሙሉ የሚገልጽ ነው ለማለት ባያስደፍርም፤ የፖለቲካ ስርዓት እየተጠናከረና እየደረጀ የሚሄደውንና ቀጣይነቱ ሊረጋገጥ የሚችለው የስርዓቱ አባላት ፍላጎታችንን ያስጠብቅልናል ብለው በሚያምኑት ልክ መሆኑ እሙን ነው። የስርዓቱ አባላት ስርዓቱ የእነርሱ እንደሆነ በሚተማመኑበት መጠን፤ ስርዓቱ ይበልጥ ለመጠናከር ዕድል ያገኛል። ቅቡልነት በአንድ የፖለቲካ ስርዓት ስር የሚኖሩ አባላት፤ ስርዓቱ የፍላጎታቸው አስጠባቂ እንደሆነ ያላቸው መተማመን ነው። የሀገር መንግስት ቅቡልነት ማለት ህዝብና ልሂቃን ሀገር መንግስቱን የፍላጎታቸው አስፈጻሚ ወኪል አድርገው የሚቆጥሩበት መጠን ነው። አንድ ማህበረሰብ በጎንዮሽ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያለው መተማመን፤ እንዲሁም ሽቅብ ከስርዓቱ መሪዎች ጋር የሚኖረው እምነት፤ ለአንድ ስርዓት ዕድገትና ጽናት መሠረት ነው። የሀገረ መንግስቱ ቅቡልነት ሲኖር ዜጎች ኃይልን የመጠቀም ብቸኛ ስልጣን ያለው ሀገረ መንግስት ብቻ እንደሆነ ይቀበላሉ። የሀገረ መንግስት ጥንካሬም ከተቋማቱ ብርታትና የማስፈጸም ዐቅም ባሻገር፤ በዚህ የሀገረ መንግስት ቅቡልነት ላይ የሚመሰረት ነው።

ቅቡልነት ጠንካራ ትርክት ይፈልጋል። ትርክት ማለት ዜጎች እንደ አንድ ማህበረሰብ ስላለፈው የጋራ

ታሪካቸው፣ ዛሬ ላይ ስላላቸው ሁኔታና፣ በቀጣይ ለመድረስ ስለሚያልሙት መዳረሻ፤ የሚኖራቸው የጋራ ተቀባይነት ያለው ሀሳብ ነው። ትርክቶች በፓራዳይም ውስጥ ይወለዳሉ። ፓራዳይም ያለፉ ድሎቻችንንና ችግሮቻችንን የምንመለከትበት፤ ዛሬ ላይ ያሉ ክፍተቶችን የምንደፍንበትና ዕድሎችን የምንጠቀምበት፤ ወደ ነገም የምንዘረጋበትና የምንደርስበት፤ የእሳቤ ማዕቀፍ እና የመረዳት ምልክታችን ነው። ይህ የእሳቤ ማዕቀፋችን እና ምልክታችን፤ ካለፈው የታሪክ ሂደታችን ተነስቶ፤ በዛሬና በነገ ዙሪያ ትውልዶች የሚኖራቸውን የጋራ ህልምና አመለካከት በመቅረጽ፤ ቅቡልነትን ያጠናክራል። ይህ የቅቡልነት ተረክና የተረኩ አጠቃላይ ፓራዳይም፤ ትውልድን ከመፍጠርና ከመቅረጽ አንጻር የሚኖራቸው ተፅዕኖና ሚና ከፍ ያለ ነው።

ሀገራችን በዘመናዊ ታሪኳ የተለያዩ መሪዎችን እና የመንግስት መዋቅሮችን አስተናግዳለች። ነገር ግን ጠንካራ የሀገረ መንግስት ቅቡልነት ማምጣት ፈተና ሆኖባታል። መሪዎች በተቀያየሩ ቁጥር ለኢትዮጵያ ይበጃታል ያሉትን የየራሳቸውን ፓራዳይም ቢያመጡም፤ የቅቡልነት ክፍተቱን ግን መሙላት ተስኗቸዋል። ይልቁኑም በተናጠላዊና አቅላይ ምልከታ የኢትዮጵያን ችግር እያሳነሱ የሄዱበት መንገድ፤ የሀገረ መንግስቱን ጥንካሬ የሚንጥና ቅቡልነቱን የሚያሳጣው ሆኖ ቆይቷል።

ነባር ፓራዳይሞች የኢትዮጵያን እግሮች የተመለከቱበትና መፍትሔውን የቃኙበት ፓራዳይም፤ አቅላይነትና አክራሪነት የተጫነው ነው። ይህ ፓራዳይምና ትርክት በትውልድ ውስጥ ሰርፆ የሀገረ መንግስት ቅቡልነት ማጣትን አባብሶታል። አቅላይነት ሰፊ ችግሮችን በአነሰ ምልከታ በመገንዘብ፤ ሁለንተናዊ መፍትሔን ከማቅረብ ይልቅ፤ ተናጠላዊና ቀላል መፍትሔዎች ላይ መጠመድ ነው። በሌላ በኩል አክራሪነት በአንድ ላይ ለሚያቀራርብ የጋራ እሳቤ ለመቆም ይልቅ፤ ለተናጠላዊ አጀንዳዎች የጠነከረ ትኩረት በመስጠት፤ የሀገረ መንግስት ቅቡልነትን የሚሸረሽር ነው። በመሆኑም ይህ ዓይነት በአቅላይ ምልከታና በአክራሪነት አካሄድ የታጠረው ታሪካችን፤ የሀገረ መንግስት ቅቡልነት ማጣትን ይበልጥ አባብሶታል።

የመጀመሪያውና የቀደመው ፓራዳይም ጠንካራ አንድነት እና ቅቡልነት ሊመጣ የሚችለው ኢትዮጵያ አንድ ዓይነት ስትሆን እንደሆነ ታሳቢ በማድረግ፤ ሀገራችንን አንድ ዓይነት ለማድረግ የተካሄደበት መንገድ ነው። ማዕቀፉ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ልዩነቶችን የዘነጋና፤ ኢትዮጵያን በወጥነት ብቻ የተመለከተ በመሆኑ፤ ለችግሮች መፍትሄ ከማምጣት ይልቅ አዳዲስ ችግሮችን ፈጥሯል።

ስርዓቱ የኢትዮጵያን ብዙሃነት ያላከበረ መሆኑን ተከትሎም፤ ልዩነት በሚገባ አልተከበረው፤ አልተስተናገደምም የሚሉ ኃይሎች ሌላ ፓራዳይም አንግበው ከአደባባይ እስከ ትጥቅ የደረሰ ትግል በማድረግ፤ የሀገረ መንግስቱን ጥንካሬና ቅቡልነት እንዲናጥ አድርገዋል። በመጨረሻም ይህ ልዩነትን መሠረት ያደረገ አዲስ ትኩረት፤ ከብዙ ትግል በኋላ፤ የቀደመውን ስርዓት ገርስሶ ስልጣንን ተቆጣጠረ።

እነዚህ ልዩነትን መሠረት ያደረገ ትኩረትን አንግበው የተነሱ ኃይሎች ወደ ስልጣን ሲወጡ፤ ስር ነቀል

ተናጠላዊ መፍትሄን ለኢትዮጵያ ችግሮች መፍቻ አድርገው አቅርበዋል፡፡ ከዚያም ቀድሞ የተገነባውን በማፍረስ፤ መንግስት የሚመራበት መሪ ማዕቀፍ‹‹ልዩነትን ማቀንቀን›› እንዲሆን አደረጉ፡፡ ልዩነት የፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችና የአስተዳደራዊ መዋቅሮች መሠረት ሆነ፡፡ ይሁንና ይህ ፓራዳይምም የኢትዮጵያውያንን ዘርፈ ብዙ መጋመድና ጥልቅ አንድነት በመዘንጋት፤ ልዩነትን ብቻ የትኩረት ማዕከሉ በማድረጉ፤ መፍትሄ ከማምጣት ይልቅ እንደ ቀደመው ፓራዳይም ክፍተትንና ቀውስን የፈጠረ ሆነ፡፡

ሁለቱ ጫፍና ጫፍ ያሉ ፓራዳይሞች በየተራ መንግስታዊ መዋቅርን የቀረጹና ትውልድን የፈጠሩ ናቸው፡፡ የፈጠሩት ተቃራኒ ትውልድ እንደመሆኑ፤ በፈጠሩት ትውልድ መካከል የሚደረገው ሽኩቻ የስርዓት መናጋት እያመጣ፤ የሀገረ መንግስቱን ቅቡልነት አሳሳው፡፡ የኢትዮጵያን ሀገረ መንግስት የማጠናከር ጉዳይ፤ ዋልታ የረገጡ የትውልድ እሳቤዎችን በሚያስታርቅ አቀራራቢ ትርክት መተካትን፤ በትርክቱም ትውልድ ማነጽን ይጠይቃል፡፡ ሀገራችንን ወደ አለምንላት የሰላምና የብልጽግና ምዕራፍ ሊያሻግራት የሚችለው፤ በቅቡል ሀገረ መንግስት አውድ የሚታነጽና የሚፈጠር ትውልድ ብቻ ነው፡፡

## *ዓለም አቀፍ ሽኩታ፣ የቴክኖሎጂ ለውጥ እና ግራጫ ጦርነት*

ትውልድን በክስተታዊና ሂደታዊ መንገድ ከሚቀርጹና ከሚፈጥሩ ኃይላት መካከል፤ የቴክኖሎጂ ለውጥ፣ ዓለም አቀፍ ግጭቶችና የኃይል አሰላለፎች፣ የተፈጥሮ አደጋዎችና ወረርሽኞች ይገኙበታል፡፡ ለምሳሌ ያህል የኢንተርኔትና እርሱን ተከትለው የመጡ የመረጃና የግንኙነት ፍሰት ለውጦች፤ ዓለምን በእጅጉ እየቀየሯት ይገኛሉ፡፡ ይህም ትውልዱን የመረጃ ጎርፍ ተጠቃሚም፤ ተጠቂም፤ የአዲሱ ሚዲያ ተዋናይም አድርጎታል፡፡ ከዚያም አልፎ በፖለቲካውና በኢኮኖሚው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ፤ ድንበር ዘለል ማበራዊ ተፅዕኖን የፈጠረና፤ እያንዳንዱን ግለሰብ በነፍስ ወከፍ የነካ ክስተት ሆኗል፡፡ ዘመኑ የሰው ሰራሽ አስተውሎትና (Artificial Intelligence) የዲጂታይዜሽን ዘመን እንደመሆኑ፤ የትውልዱን አስተሳሰብ፣ ስብዕናና ኑሮ በፍጥነትና በጥልቀት ከዚህ እውነት ጋር እንዲስማማ አድርጎ እየቀረጸ ይገኛል፡፡

ዓለም በሉላዊነትና በአክራሪ ብሄርተኝነት መካከል ተወጥራ፤ በየክፍለ ዓለሙ የፈነዱና የተወጠሩ ግጭቶችን በማስተናገድ ላይ ትገኛለች፡፡ የኮቪድ ወረርሽኝና የዩክሬይን ጦርነት የፈጠረው ኢኮኖሚያዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ውጥረት እንደቀጠለ ነው፡፡ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ይህንን ዓይነት ዓለም አቀፍ ስፋት ያለው ግጭትና ከዚያ ጋር ተያይዞ የሚመጣው የውገና ግዴታ ታይቶ አይታወቅም፡፡ የዓለም የአገዛዝ ስርዓት ምናልባትም ምዕራብ መር ብቻ ከመሆን፤ በብዙ ዋልታ የተከፋፈለ የኃይል ሚዛን ወዳለው አዲስ ስርዓት እያመራ ይሆን? የሚለው ጥያቄ ተገቢነቱ እየጎላ መጥቷል፡፡ በሀገራችንም ከተከሰተው ለውጥ በኋላ የመጡ ዐበይት ክንዋኔዎችና ክስተቶች፤ ነባሩን ትውልድ በመቅረጽና አዲስ ትውልድን በመፍጠር ረገድ ያላቸው ሚና ቸል የሚባል አይደለም፡፡

ግጭት በተለያዩ ምክንያቶች የሚነሳ ቢሆንም፤ ከእነዚህ መካከል የኃይል ሚዛን ለውጥ (የኃይል ሚዛን

ከፍታና ዝቅታ) ተጠቃሽ ነው። በቀደምት ጊዜያት ከፍ ያለው ኃይል፤ ኃይሉ እየቀነሰ መምጣቱና፤ ከታች የነበረው ኃይል ደግሞ ከፍ እያለ መሄዱ፤ ግጭትን አይቀሬ ያደርገዋል። የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት፤ የምስራቁን ጎራ እንኮታኩቶ፤ ምዕራባውያንን ብቸኛ የዓለም ዋልታ አድርጓቸው ቆይቷል። የሊበራል ዓለም አቀፍ ስርዓት ብቸኛው የእውነት መንገድ ተደርጎ ያለተቀናቃኝ ዓለምን ሲመራ ቆይቷል።

ከቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ የተፈጠረው ባለ አንድ ዋልታ ዓለም አቀፍ የኃይል ሚዛን፤ የተጋፈጣቸው ፈተናዎች ውስጥ፤ ሀገራቱ በውስጥ እያጋጠማቸው ያለው ችግር እና የተለያዩ ኃይላት ብቅ ማለታቸው ሊጠቀሱ ይችላል። በአሜሪካ እና በምዕራቡ ዓለም የውስጣዊ ችግሮች ማሳያ የሆነው የህዝበኝነት ፖለቲካ እየጨመረ መጥቷል። እንግሊዝ ከአውሮፓ ህብረት ከመውጣቷ በተጨማሪ፤ የአውሮፓውያን ህብረት ፈተና ገጥሞታል። የአትላንቲክ አቋራጭ ግንኙነት ላልቷል። ከእነዚህም ጋር የኢኮኖሚ ቀውሶችና ሌሎች የውስጥ ሁኔታዎች ታክለው፤ የምዕራቡ ዓለም ተፅዕኖ በሌሎች ሀገራት የሚፈተን እንዲሆን አድርጎታል።

በሌላ በኩል ምዕራባውያን የነበራቸው የበላይነት፣ ዐቅማቸው እየፈረጠመ በመጡ የምስራቅ ሀገራት እየተፈተነ ነው። ቻይና ከፍተኛ የኢኮኖሚ ተዐምር በመፍጠር፤ በዓለም ፖለቲካ ተወዳዳሪና ጠንካራ ሀገር ሆና ብቅ ብላለች። ሩሲያ ከቀዘቀዘችበት እየተነሳች ነው። እንደ ህንድ፣ ቱርክ፣ ኢራን እና ሌሎች የሊብራሉን ዓለም አቀፍ ስርዓት የመረበሽ ዐቅም ያላቸው ኃይላት ተፈጥረዋል። ይህም ባለ አንድ ዋልታው ዓለም ከባድ ፈተና እንዲገጥመው አድርጓል።

ዓለም ከአንድ ዋልታነት በየአካባቢው ብቅ ብቅ እያሉ ወደሚመጡ ብዙ ዋልታዎች እየተለወጠች ነው። ሉላዊ ከሆነ የዓለም አቀፍ ሁኔታ ወደ ጂኦፖለቲካና አካባቢያዊ ኃይሎች መነቃቃት ሽግግር እያደረገ ነው። ዓለም አቀፍ ለውጡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ እየተፈጠረ ቢሆንም፤ ትልቁ ስጋት በለውጥ ሂደት እና በለውጡ እየተፈጠሩ ያሉ ተፅዕኖዎች ናቸው።

ሽግግሮች እና ለውጦች እየመጡ ያሉት በከፍተኛ ዓለም አቀፍ ውድድር ውስጥ ነው። ይህ ዓይነቱ ትላልቅ ግጭቶችን አይቀሬ እያደረገ የመጣ ዓለም አቀፍ የውድድር ሁኔታ ተፅዕኖው ከፍ ያለ ነው። ውድድሩ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ እና በሌሎች ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው። ውድድሩ በኃያላኑ መካከል የሚደረግ ቢሆንም፤ የሚደረግበት ቦታና ሁኔታ ተወሰነ ሳይሆን፤ ሽኩቻውና ግጭቱ ወደ ተለያዩ ቦታዎች የሚዛመት፤ ተፅዕኖውም ዓለም አቀፋዊ ነው።

በዚህም ዓለም አቀፍ ሁኔታ ውስጥ አሸንፎ ለመውጣት፤ ምዕራቡ የእነዚህ ተገዳዳሪ ኃይላትን መስፋፋትና ዓለም አቀፍ ተፅዕኖ ለመግታት የሚያስችል ስትራቴጂዎችን ይነድፋል። ከስትራቴጂዎቹ አንዱ ተገዳዳሪ ሀገራት ጥቅምና መልካም ግንኙነት በፈጠሩባቸው ሌሎች ሀገራት ላይ ተፅዕኖ ማድረግን የሚጨምር ነው። በተመሳሳይም በምስራቅ ያሉ ትልቅ ዐቅም የፈጠሩ ሀገራትም ዋነኛ ትኩረታቸው፤ የምዕራቡን መስፋፋት

መግታት ነው።

በዚህ ሁኔታ ቴክኖሎጂ በራሱ አዳዲስ ዕድሎች እና አዳዲስ ፈተናዎችን ይዞ ብቅ ብሏል። የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ኢኮቴ) ዕድገት፤ የሰው ሰራሽ አስተውሎትና የዲጂታይዜሽን በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋት፤ ለውጡን በመላው ዓለም እንዲፋጠንና የራሱን መልክ እንዲይዝ አድርጎታል። በቴክኖሎጂ ዕድገቶች ምክንያት ዓለም ይበልጥ የተሳሰረች ሆናለች። ቴክኖሎጂዎች በዓለም አቀፍ ሁኔታና ፖለቲካ ላይ ካላቸው ተጽዕኖ የተነሳም፤ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎቹ በአለም አቀፍ ፖለቲካ ውስጥ እንደ ጠንካራ ተዋናይ ሆነዋል። ለምሳሌ ማህበራዊ ሚዲያዎች ከምርጫ ጀምሮ፤ በተለያዩ ሀገራትና አካባቢዎች ግጭትን በማባባስ እና የፖለቲካ አለመረጋጋትን በመፍጠር፤ በሀገራት ፖለቲካ ውስጥ ቁልፍ ተዋናይ ሆነዋል።

ሀገራት ህልውናቸውን ለማስጠበቅ እና ጠንክረው ለመውጣት ቴክኖሎጂ ያመጣላቸውን ዕድሎች በአግባቡ መጠቀም፤ ፈተናዎቹን ደግሞ በሚገባ መቋቋም አለባቸው። ማህበራዊ ሚዲያና ኢኮቴ ፖለቲካ የሚመራበትን እንዲሁም ፖለቲከኞች የሚንቀሳቀሱባቸውን መንገዶች እንዲለውጡ አስገዳጅ ሁኔታን ፈጥረዋል። ማህበረሰቡ በፖለቲካ ውስጥ ያለው ተሳትፎ የተለየ ሆኗል። ሀገርን ለማጥቃትና አንድነትን ለመናድ የሚቻልበትን አማራጮች አስፍቷል። በአጠቃላይ ፖለቲካና ፖለቲካው የሚከወንበት ሁኔታ ላይ መልካም ዕድል ይዞም የመጣ ቢሆንም፤ የፈጠረውም ተፅኖ ቀላል አይደለም።

በሀገራችን ከአሁን ቀደም ቴክኖሎጂ ሳይስፋፋ የነበረውን የ1983 ዓ.ም. ሽግግርና፤ በብዙ ቴክኖሎጂ መስፋፋት ውስጥ የተከሰተውን የአሁኑን ለውጥ ስንመለከት፤ በርካታ ልዩነቶችን እናስተውላለን። ማህበራዊ ሚዲያ ከቀደመው ለውጥ በተለየ በዋናነት የመንግስትን የሚዲያ እና የትርክት የበላይነት በመሸርሸር፤ አፍራሽ ትርክቶች ከየትኛውም ጫፍ ተነስተው በፖለቲካው ላይ ተፅዕኖ እንዲኖራቸውና አለመረጋጋት እንዲፈጠር አስችሏል። በተጨማሪም የውጭ ኃይላት በቴክኖሎጂ አማካኝነት በቀላሉ በሀገራችን ፖለቲካ ላይ ተጽዕኗቸውን በከፍተኛ ደረጃ ማሳረፍ ችለዋል።

የዓለም አቀፍ ውድድር መጠናከር ከቴክኖሎጂ ለውጦች ጋር ተጣምሮ፤ ሀገርን የማጥቂያ መንገዶችና ጦርነቶች መልካቸውንና ባህሪያቸውን እንዲቀይሩ አስገድዷል። ሀገራት ላይ ጥቃት የመክፈቻ አዳዲስ መንገዶች መበራከታቸው፤ በሰላም እና በጦርነትመካከል ያለው ልዩነት የደበዘዘ እንዲሆን አድርጎታል። ወታደራዊ ስትራቴጂስቶች ተለምዷዊ የጦርነት ባህሪን በሶስት ይገልጹታል። የመጀመሪያው ዐመፃ ወይም ግጭት ሲሆን፤ ሁለተኛው ኢተገማችነቱ፤ እንዲሁም ሶስተኛው ፖለቲካዊ ቁጥጥሩ ነው።

በተሳሰረና ውድድር በበዛበት ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ላይ፤ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ያለመቋረጥ መፈጠርና ጥቅም ላይ መዋል ተዳምረው፤ ዐመፅ ወይም ግጭት የተባለውን የመጀመሪያው የጦርነት ባህሪ ግራ የሚያጋባ እንዲሆን አድርገውታል። በተለመደው የጦርነት አካሄድ በየብስ ታንኮችና ወታደሮች፤ በአየር ላይ

ጀቶችና ተምዘግዛጊ መሣሪያዎች፤ በውሃ ደግሞ ባህር ሰርጓጆችና መርከቦች ወዘተ… የሚሳተፉበት፤ በተገዳዳሪዎች መካከል የሚደረግ ማጥቃትና መከላከል ነበር። ነገር ግን ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ሳይፈጠርና በተለምዶ ጦርነት የምንለው ሁኔታ ሳይከሰት የሚደረጉ ጥቃቶች፤ ብዙ ውድመት የሚያደርሱ ሆነው ብቅ ብለዋል። ከዐመፅ መለስ ያሉ፤ ሙሉ ለሙሉ ግጭት ተብለው ሊጠቀሱ የማይችሉ፤ ነገር ግን ሀገር ላይ ከፍተኛ ጫናንና ውድመትን የሚፈጥሩ ጉዳዮች ብቅ ብለዋል። ነጭም (ሰላም) ያልሆኑ፤ ጥቁርም (ግጭት) ያልሆኑ፤ ግራጫ ጦርነቶች በነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ስትራቴጂያዊ ፍላጎትን ማስፈጸሚያ ዋነኛ ስልቶች ሆነዋል።

ግራጫ ጦርነት ከተለምዶ ጦርነት ደረጃ ያነሰ፤ ከተለምዶው ሰላማዊ ውድድር ደግሞ ከፍ ያለ የግጭትና የውድድር ዓይነት ነው። ይህ ዓይነቱ ጦርነት ብሄራዊ ዐቅምን (ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ወታደራዊና ሌሎች ዐቅሞችን) በማሰባጠር፤ የተገዳዳሪን ዐቅም በማሳነስ፤ መደበኛ ጦርነት ለማስቀረት የሚደረግ ነው። ጦርነት ኢኮኖሚ፣ የህዝብ ስነ ልቦና፣ ሀገራዊ ውሳኔ ሰጪነት እና ሌሎች ጉዳዮችን ይፈልጋል። ግራጫ ጦርነት እነዚህን ጉዳዮች በማጥቃት፤ የተገዳዳሪን የማድረግ ዐቅም አሳንሶ፤ ወደ ጦርነት እንዳይገባ የማድረግ ስትራቴጂ ነው። ተገዳዳሪ በተወነሰ አካባቢዎች ላይ ያለውን ቁጥጥር፣ ሀገራዊ መረጋጋት እና የውሳኔ አሰጣጥ በማሳነስ ስትራቴጂካዊ ግብን እውን ለማድረግ ያስችላል።

የሥነ ልቦና ጦርነት የግራጫ ጦርነት ዋነኛው ስልት ነው። በሰው አእምሮ ላይ መረጃዎችን ለመጫን የሚደረግ ጥረት፤ የስነ ልቦና ጦርነት በመባል ይታወቃል። ለሥነ ልቦና ጦርነት ቴክኖሎጂ፣ ሬድዮ እና ኢንተርኔት ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። የኢራቅና አፍጋኒስታን መሪዎች ምን ያህል ‹‹አሰቃቂና ክፉ›› እንደሆኑ ያለማቋረጥ በሚዲያዎች ባይራገብ፤ የአሜሪካ ህዝብ በኢራቅ እና በአፍጋኒስታን ላይ የተከፈተውን ጦርነት ላይደግፈው ይችል ነበር።

“ማየት ማመን ነው” እንዲል የሀገራችን ብሂል፤ ሲ.ኤን.ኤን.፣ ቢ.ቢ.ሲ እና መሰል ሚዲያዎች፤ ለምዕራቡ ህዝብ አሳማኝ የሚመስሉ መረጃዎችን ያቀርባል። እነዚሁ ሚዲያዎች ከጥቅምት 24ቱ የህወሃት ክህደት ማግስት የሽብር ቡድኑን በመደገፍ በሀገራችን ላይ የከፈቱት የስነ ልቦና ጦርነት ይታወሳል። የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ የተደፈሩ ሴቶች፣ የተራቡ ህፃናትና የመሰረተ ልማት ዕቀባ በሚሉ ክሶች፤ የፌደራል መንግስቱን ቀን ተሌት ሲከሱ ነበር። በጎን ደግሞ ህወሃትን በመደገፍ፤ ደሴ ላይ ሲደርስ በሳምንት አዲስ አበባን ይቆጣጠራል፤ የሚል የስነ ልቦና ጦርነት ተከፍቶብን፤ ብዙዎችን ሽብር ውስጥ መክተታቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በበርካታ ሀገራት በስነ ልቦና ጦርነት አማካኝነት መንግስታት ተቀይረዋል፤ ሀገራት ፈርሰዋል። በስነ ልቦና ጦርነት ዛሬ ነጭ የሆነው ነገ ትቁር ይሆናል። ዋነኛ ዓላማው በአንድ ወገን ያለውን ፍላጎትና ጥቅም የማስከበር እንጂ እውነትን ማሳወቅ አይደለም። በስነ ልቦና ጦርነት አሸናፊ የሚያደርግህ የያዝከው እውነት ሳይሆን፤ ያሰራጨኸው የመረጃ መጠንና የማሸበር ዐቅም ነው።

በተጨማሪም የመረጃ ኦሬሽኖች፣ ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖና ለዐማፅያን የሚደረግ ሁለገብ ድጋፍ እና አጋዥ ግራ

አጋቢ ኃይላት (መንግስታዊ ይሁኑ አይሁኑ የማይለዩ ኃይላት) ዋና ዋና የግራጫ ጦርነት አካላት ናቸው። በመረጃ ኦፕሬሽኖች የጠላትን የመረጃ አካባቢ በመረበሽና በማውደም፤ የጠላት የውሳኔ አሰጣጥ ላይ በቴክኒክም በስነ ልቦናም ተፅዕኖ ይደረጋል። ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖን በማሳደር ተገዳዳሪን ከማዳከም እርምጃዎች በተጨማሪ፤ በተገዳዳሪ ሀገር የሚንቀሳቀሱ ዐማጽያንን በመደገፍና ግራ አጋቢ ኃይላትን በመጠቀም የተወሰኑ ኢላማዎችን ማጥቃት፤ ሀገሩ እንዳይረጋጋ ማድረግ፤ እንዲሁም መንግስት በአንዳንድ አካባቢዎች የሚኖረውን ቁጥጥር ማሳነስ፤ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራባቸው ያሉ አዳዲስ የጦርነት መስኮች ናቸው።

በአጠቃላይም በጦርነትና በሰላም መካከል፤ በተዋጊና ተዋጊ ባልሆነው (በወታደሩና በሲቪሉ) መካከል ያለውን ልዩነት አሻሚ ያደረገ፤ አዲስ የጦርነት ባህሪ ተፈጥሯል። ጦርነት የሚጀምረው የተገዳዳሪን ባህሪ ከመቀየር ነው። ይህ በውድድር ደረጃ ቀጥተኛ ያልሆኑ የውጊያ መንገዶችን በመጠቀም፤ ዋናው ጦርነት ሳይጀመር በማሸነፍ፤ በሰላም ጊዜም ጦርነት (ከተለምዷዊ ጦርነት ያነሱ ግጭቶች) ስለሚኖሩ፤ ሀገራት ሁሌም በስጋት ውስጥ ወይም በተራዘመ ጦርነት አዝማሚያ ውስጥ እንዲሆኑ ያደርጋል። በመሆኑም ሀገራት ለጦርነት ዝግጅት በማድረግ ተጠምደው ይቆያሉ። ፍጹማዊ ሰላምን ማምጣት አዳጋች መሆኑን ተገንዝቦ፤ ሀገራዊ አቅምን በማሰባጠር፤ በግራጫ ሁኔታ ውስጥ ሀገርን ለማጠናከር፤ ትውልድን በአዲስ የጀግንነት እሳቤ መቅረፅ ያስፈልጋል።

ሰላም እንደ የሁኔታው አሻሚ በሚሆንበት ነባራዊ የዓለም ሁኔታ፤ በቀደሙ ፓራዳይሞች ሀገርን መምራት አይቻልም። ምክንያቱም የተለወጠው ባለብዙ ዋልታ ዓለም፤ በነበረው ፓራዳይም መቀጠልን አዳጋች ያደርገዋል። ዓለም አቀፋዊ ለውጡ የደቀናቸው አደጋዎች፤ ጥንቃቄና አዳዲስ እሳቤዎችን ይፈልጋሉ። በተለወጠ ዓለም አቀፍ ሁኔታ ውስጥ ሀገራዊ ለውጥን ማምጣት፤ ዓለም አቀፍ ሁኔታውን የሚረዳ የዕይታ ማዕቀፍን ይፈልጋል።

የዓለም ሁኔታን የሚገነዘብ የፓራዳይም ለውጥ ማምጣት፤ እንዲሁም ቀጣዩ ትውልድን በዓለም ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲወጣ በሚያስችል መልኩ፤ በተለወጠ ፓራዳይም ለተለወጠ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ዝግጁ ማድረግ ብቸኛ አማራጭ ነው። በመሆኑም ይብዛም ይነስ የተረጋጋ ባለአንድ ዋልታ ሊበራል ዓለም አቀፍ ስርዓት ከነበረበት ዘመን ወጥቶ፤ ውድድር ወደ በዛበት ባለብዙ ዋልታ ዓለም የሚደረገው ሽግግር የሚፈጥረውን ተፅዕኖ ተቋቁሞ፤ ሀገርን ለመምራትና ለማጠናከር አዲስ አቅጣጫን መቀየስ ይፈልጋል።

ዓለም አቀፋዊ የግጭትና የኃይል አሰላለፍ ለውጡን፤ ከቴክኖሎጂያዊ ለውጡ ነጥሎ ማየት አይቻልም። አዲስ ስርዓት ደግሞ አዲስ ትውልድና ሀገራዊ ፓራዳይምን ይጠይቃል። ስለዚህም አዲስ የሚፈጠረው ትውልድን በትጋትና በብልሃት፤ ለአዲሱ ክፍለ ዘመንና ዓለም አቀፋዊ ውድድር፤ ብቁና ንቁ አድርገን መቅረጽና ማበጀት ይጠበቅብናል። ይህንንም ለማድረግ ትውልዱን የመረጃና የሚዲያ፤ የትምህርትና የክህሎት፤

የአስተሳሰብና የሰብእና ግንባታን፤ ዓለም አቀፋዊ ከሆነ ቁመናና ብቃት ጋር ማስታጠቅ ያስፈልጋል፡፡

## *መታደስ በአፍሪካዊ ህብረት*

አፍሪካ ቀዳሚ የስልጣኔ ባለቤትና በዓለም አቀፍ መድረክ በንግድ፤ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ህይወት ዋነኛ ተዋናይ የነበረችበት ጊዜ የተካደ ታሪክ ሆኗል፡፡ ይህም የምዕራባውያን የባሪያ ንግድና ተከትሎ የመጣው የቅኝ አገዛዝ ዘመን የፈጠረው ተረክ ውጤት ነው፡፡ አፍሪካን ድኻ፣ ጨለማና ኋላ ቀር አድርጎ መሳልና አሳንሶ ማሳየት ዛሬም በሰፊው የቀጠለ ድፍረት ነው፡፡

በድህረ ቅኝ ግዛት ዘመን ላለፉት 60 ዓመታት አካባቢ መልኩን የቀየረ እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝና አፍሪካን የመበዝበዝ አባዜ፤ በምዕራባውያኑ የሚዘወተር ዓይን ያፈጠጠ ነውር ነው፡፡ ለዚህም አፍሪካውያን የተረጋጋ መንግስት እንዳይኖራቸው፤ በሙስና የተዘፈቁ አምባገነን መሪዎችን በመሪነት ኮርቻ ላይ አስቀምጦ መዘወርን እንደ ብልሃት የመውሰድ እንቅስቃሴዎች በስፋት ይስተዋላሉ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቻይናና የሌሎች ምስራቃውያን ሀገሮች ወደ አፍሪካ መትመምና ከምዕራባውያን ተወዳዳሪ ሆነው መቅረብ፤ አዲስ የኃይል አሰላለፍን እየፈጠረ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአፍሪካውያን ንቃትና ለተሀድሶ መነሳሳት የፈጠረው ድባብም አለ፡፡ አፍሪካ፤ ለአፍሪካውያን፤ በአፍሪካውያን፤ የሚለው እሳቤ ከመፈክርነት አልፎ ወደ እውነት ሊመጣ የሚችልበት ጊዜው አሁን ነው፤ የሚል አንድምታ በየስፍራው መሰማት ጀምሯል፡፡ ይህም የአፍሪካን ተሀድሶ አጨንግፎ፤ ለሁለተኛው የቅኝ ግዛት ቅርምት መረባረቡ፤ ለኃያላን ሀገራቱ ሁሉ ቅዠት ከሆነ ሰንበትበት ብሏል፡፡

ታዲያ በዚህ ጊዜ በመሪነትና በሰሪነት ላይ ያለው ትውልድ፤ ተማሪና ተተኪ የሆነውን ትውልድ እንዴት ይቀርፀዋል? እንዴትስ ይመራዋል? የሚሉትን ቁልፍ ጥያቄዎች ለመመለስ፤ የአፍሪካ ዕጣ ፈንታና የአፍሪካውያን ጊዜ የማይሰጥ ምላሽ፤ ዋነኛ ትውልድ ፈጣሪ ኃይል መሆኑ አይቀርም፡፡ አሁን እየተፈጠረ ያለው ትውልዳችን ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን አፍሪካዊ ለመሆኑም የነቃ መሆን አለበት፤ አዲስ አበባ ብቻ የሚከናወነው ብቻ ሳይሆን፤ ዳሬ ሰላምና ካዛ ብላንካ፤ ኬፕታውንና ካይሮ፣ ሌጎስና ሀራሬም የሚሆነው ጉዳይ፤ የራሱ እንደሆነ ማሰብ አለበት፡፡ በዓባይ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በቀይ ባህርም ጉዳይ ባለቤትነቱን ተረድቶ፤ ድምፁን ማሰማት ይኖርበታል፡፡ በምግብና በኢነርጂ ራሱን ከመቻል አልፎ፤ የጎረቤት ሀገራትንና የዓለም ገበያ ተቋዳሽ ለመሆን መስራት ይጠበቅበታል፡፡

የተለወጠው ዓለም አቀፍ ሁኔታ አፍሪካ በአጠቃላይ፤ እንዲሁም ቀጣናችንን በተናጠል፤ ወደ ምን አቅጣጫ እየወሰደ እንዳለ መረዳት የትውልዱ ኃላፊነት ነው፡፡ ሁኔታው አህጉራችንን በተለይም ቀጣናችንን ከፍተኛ የሽኩቻ ሜዳ አድርጎታል፡፡ የተለወጠው ዓለም አቀፍ ሁኔታና ቴክኖሎጂ የፈጠረውን የጦርነትና የውድድር

ለውጥ፤ አፍሪካ ባላሰበችበት፣ ባልተዘጋጀችበት እና በሌለችበት ጦርነት ውስጥ፤ ዋነኛ የውድድር ሜዳ እንድትሆን አድርጓታል። አፍሪካ በኃያላኑ ሀገራት ላይ ጥገኛ በመሆኗ፤ ተገድዳም ቢሆን የዓለም አቀፍ ሽኩቻ ተሳታፊ እንድትሆን ተደርጋለች።

ዓለም አቀፉ ሽኩቻ በአፍሪካ የሚገለፀው በዋነኛነት በሶስት መንገዶች ነው። አንደኛው መፈንቅለ መንግስቶች ወይም የስርዓት ለውጦችን ማድረግ ነው። ኃያላኑ ሀገራት ጥቅሜን አያስከብርም ወይም ከተገዳዳሪዬ ጋር ቆሟል ያሉትን መንግስት፤ ከስልጣን ለማውረድና የስርዓት ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። በወታደር ውስጥ፣ በሲቪል ውስጥ ወይም በፓርቲዎች ውስጥ፣ ወዘተ. አንጃ በመፍጠር፤ አንዱ አንዱን ገፍቶ ከስልጣን እንዲያወርድ በማድረግ፤ ጥቅማችንን ያስከብርልናል ያሉትን ኃይል ወደ ስልጣን እንዲመጣ ያደርጋሉ።

ሁለተኛው በህዝባዊ ግፊት በውስጣዊ ሁኔታ የመጡ ለውጦች እንዳይረጋጉ ማድረግ ነው። ለውጦች ከተከሰቱ በኋላ ለጥቅማችን ስጋት የሚሆን ነገር ተፈጥሯል ብለው ካሰቡ፤ ለውጡ ረግቶ ጠንካራ መንግስት እንዳይፈጠርና እንዳይረጋጋ ጫናዎችን ማድረግ ነው ከእነዚህ ጫናዎች መካከል መንግስትን የሚገዳደሩ የተለያዩ ቡድኖች እንዲጠናከሩና እንዲወጡ ማድረግ፤ ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎችን መፍጠር፤ የሚዲያ ዘመቻዎች እና ዲፕሎማሲያዊ ጫናዎችን ማድረግ ይገኝበታል።

ሶስተኛው ደግሞ በሀገራት ወይም በጎረቤቶች መካከል ሽኩቻዎችን መፍጠር ነው። አንዱን ጠላት አንዱን ወዳጅ በማድረግ በጎረቤቶች መካከል መተማመን እንዳይኖርና ግጭት እንዲፈጠር ያደርጋሉ። የተገዳዳሪ ሀገር አጋር ያሉትን ጠላት በማድረግ፤ ሌላኛውን ጎረቤት ወዳጅ በማድረግ፤ በጎረቤቶች መካከል መተባበርና አጋርነት ሳይሆን፤ አለመተማመን እና ግጭት እንዲፈጠር ይሰራሉ። ሱዳን ኢትዮጵያን እንድታጠቃ የማድረግ ተደጋጋሚ ሙከራዎች ለዚህ ትልቅ ማሳያ ሲሆን፤ በሌሎች አፍሪካውያን ሀገራት መካከል ህብረት እንዳይፈጠር የሚደረጉ ጥረቶችም በርካቶች ናቸው።

አህጉራዊ ሁኔታው ከፍተኛ ጫናን የሚፈጥር ሲሆን፤ ሀገርን ለመለወጥና ለማጠናከር በሚደረገው ጥረት ላይ አደጋን የሚፈጥር ነው። አፍሪካ ከቀድሞ ቅኝ ግዛት ብትላቀቅም በዳግም ስውር ቅኝ ግዛት ውስጥ እየዳከረች ትገኛለች።

ቀጣናችንን ስንመለከተው ኢትዮጵያ የምትገኝበት የአፍሪካ ቀንድ የቀይ ባህር አዋሳኝ መሆኑና፤ የቀጣናው የብዙ ዓለም አቀፍ ኃይሎች መሻኮቻ መሆን፤ ቀይ ባህርን ከኢትዮጵያ ህልውናና ጥቅም ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ስፍራ አድርጎታል። ቀይ ባህር የዓለም ወሳኝ የንግድ ማሳለጫ መስመር ነው። ከዚያም ባሻገር ውቅያኖሶችን አቋርጦ ለሚደረግ ማናቸውም ዓይነት የባህር ኃይል እንቅስቃሴዎች እጅግ አስፈላጊ ስፍራ ነው። በሀገራት መካከል የሚደረጉ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ወታደራዊ ግብግቦች፤ በቀይ ባህርና በቀጣናው በሚኖረው የኃይል

ሚዛን ላይ የተመሰረተ ነው።

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በባህሩ ዳር የተፈጠረች፤ ዕጣ ፈንታዋም ከባህሩ ጋር የተቆራኘ ሀገር ናት። በቀይ ባህር ላይ የነበራት ይዞታ፤ ኢትዮጵያን ጠንካራና በጂኦፖለቲካው ውስጥ ተፈላጊ ሀገር ያደርጋት ነበር። ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ላይ የነበራት ይዞታ እየሟሸሸ ሲመጣና፤ በመጨረሻም ሸቀጧን የምታራግፍበት ኩርማን ወደብ እንኳን ማግኘት ያልቻለችበት የታሪክ ሁኔታ ሲፈጠር ኢትዮጵያ በጂኦፖለቲካው ላይ የነበራት ሚና ኮሰመነ። ኢትዮጵያ በየትኛውም ዓይነት ሁኔታ ከቀይ ባህር ስትርቅ የምትሟሸሽ፤ ለቀይ ባህር ስትቀርብ ደግሞ ገናና የምትሆን ሀገር መሆኗን ታሳቢ ያደረጉ አሻጥሮች የዛሬውን እውነታ ሊፈጥሩ ችለዋል።

የአፍሪካ ቀንድ ምንም እንኳን ወሳኝ የጂኦፖለቲካ ስፍራ ላይ የሚገኝ ቀጣና ቢሆንም፤ በቀጣናው ላይ ያሉት ሀገራት በግጭትና የእርስ በእርስ ጦርነት የሚታመሱ፤ ፖለቲካዊ መረጋጋት የሌለባቸው በመሆኑ፤ ደካማና ዘላቂ ጥቅማቸውን ማስከበር የማይችሉ ሆነዋል። በአንጻሩ ከባህሩ በሌላው ጎን የሚገኙት የገልፍ ሀገራት፤ በኢኮኖሚ የፈረጠሙ በመሆናቸው፤ ለቀንዱ ሀገራት ጊዜያዊ ጥቅም በመስጠት ብቻ፤ ዘላቂ የሆነና የበላይነታቸውን የሚያረጋግጥ ጥቅም ከቀንዱ እንዲያገኙ አድርጓቸዋል።

የአፍሪካ ቀንድ በኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ውስጥ በቅኝ ገዥዎችና በሌሎች የውጭ ኃይሎች ሴራ ተሸራርፎ ከኢትዮጵያ ግዛት የወጣ ቀጣና ሆኗል። ሆኖም ኢትዮጵያና የቀንዱ ሀገራት በአጠቃላይ ባላቸው የጂኦፖለቲካ ስፍራ፣ ባላቸው ለም መሬትና፣ በህዝብ ብዛታቸው ብቻ ሰፊ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉበት ዕድል ከበፊትም የነበረና አሁንም ክፍት ሆኖ የሚኖር ነው።

ቀጠናው ለብዙ ኃያላን ሀገራት መናኸሪያ በመሆኑ፤ በቀጠናው ሀገራት ውስጣዊ ፖለቲካ እጁን ሰድዶ የሚፈተፍተውና፤ ሀገራቱ ጠንክረው እንዳይወጡ የሚያሴረው ኃይል ብዛቱ የትየለሌ ነው። ይህን ሴራና የጂኦፖለቲካ ግብግብ መቋቋምና ብሄራዊ ጥቅምን ማስከበር የሚቻለው፤ ውስጣዊ አንድነታችንን አጠንክረን፤ ከጎረቤቶቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት በማሳለጥ ሰላምን ማረጋገጥ ስንችል ነው። የቀጣናው ሸኩቻ ውስብስብ፣ ብዙ ኃይሎች ያሉበት፣ ተለዋዋጭና በስጋት የተከበበ በመሆኑ፤ ይህን ውስብስብ ሁኔታ አልፎ በብቃት ዘላቂ ጥቅምን ለማስከበር እንዲቻል፤ ውስጣዊ የፖለቲካ መረጋጋትና ጠንካራ አንድነት ያስፈልገዋል።

ሌላው ቀርቶ ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ማስተንፈሻ ድጋፎችን ከባህር ሰላጤው ሀገራት ለማግኘት እንኳን በቀጠናው ያለን ይዞታ መጠንከርና በቀይ ባህር ላይ የሚኖረን ሚና መጨመር አለበት። ይህም አንዱ ትውልዳዊ የፓራዳይም ለውጥና አዲስ የትውልድ ቀረፃ ስራ የሚያስፈልገው ትልቅ ጉዳይ ነው።

# ክፍል ሁለት

## የትውልድ አካሄድን መንገድ

‹‹እያንዳንዱ ትውልድ ከእርሱ ከቀደመው
ትውልድ ይልቅ ብል እንደሆነ፤ ተከትሎት
ከሚመጣው ትውልድም ይልቅ በእጅጉ
የተሻለ ጠቢብ እንደሆነ ያስባል፡፡››

~

ጆርጅ ኦርዌል

# ምዕራፍ አራት

## የትውልድ ስብዕና - ማንነትና ባለቤትነት

ትውልድ በአንድ ዘመን የኖሩ ባህልን ፣ ልምድንና ማንነትን የተጋሩ ግለሰቦች አንድነትና ውህደት ሲሆን በማንነትና በባለቤትነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ነው። ግለሰቦች የተፈጠሩበትን ትውልድ እንደሚመስሉ ሁሉ፤ትውልዱም በውስጡ የያዛቸውን ሰዎች ይመስላል። ስለዚህም ትውልድን ለመረዳትና ትውልዱም ተፅዕኖ ለመፍጠር እያንዳንዱ ትውልድ ከማንነትና ከባለቤትነት አንፃር መገንዘብ ተገቢ ይሆናል።

# ዞሮ ዞሮ ከቤት፤ ኖሮ ኖሮ ከመሬት

አለ በውስጣችን

እውነት ፍፁም ሆና የምታበራበት

ደግሞም ማወቅ ማለት

ከውጪ ያለውን ሄዶ ከመፈለግ

ከውስጥ የበራውን እንዲወጣ ማድረግ

~

**ገብረ ክርስቶስ ደስታ**

የኢትዮጲያ ትውልድ የሀገር ፍቅርና የአርበኝነት ታሪክ በአጭሩ ሲገለፅ፤ኢትዮጲያውያን ከውጭው ዓለም ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አንጥሮ ያሳያል።

በመጀመሪያ ኢትዮጲያ በሯ ክፍት ነበረ። በአክሱምና በዛግዌ ዘመነ መንግስታት ኢትዮጲያ በንግድ እና በቴክኖሎጂ ከሌሎች ሀገራት ጋር የነበራት ግንኙነት ጠንካራ ነበር። በመካከለኛውም ዘመን ኢትዮጲያን በምስራቅ እስከቻይና፣በምዕራብ እስከ ስፔን ፖርቹጋል ይሄዱ ነበር።ሰሜን አፍሪካና መካከለኛ ምስረቅ መንቀሳቀሻቸው ነበር። ለአያሌ የውጪ ሰዎችም በኢትዮጵያ መኖር የተለመደ ነበረ። ከ17ኛው መከዘ በኋላ ግን ቀስ በቀስ በሯን እያጠበበችና እየመለሰች፤ ከውጪ የሚመጣባትን ጫና ለመቋቋም በሚል ግንኝነቷን እያቀዘቀዘች መጣች። በመጨረሻም በሯን ጠርቅማ ዘጋች።ግኑኝነቷንና ግዛቷን አሳነሰች፤ ማንነቷንም እንደገና አጥብባ ሠራች።

በ16ኛውና በ17ኛው መክዘ የተከሰተው የእርስ በእርስ ጦርነት፤ ከውጭ ሲመለከቱት የሃይማኖት ይመስል እንጂ ውስጡግን የወቅቱ የዓለም ኃያላን የተልዕኮ ጦርነት ውጤት ነበር። አትዮጵያውያን የውጪ ጣልቃ ገብነት የሚያመጣባቸው ጦስ ከራሳቸው ታሪክ ስለተማሩ፤ የውጩ ነገር ይቅርብን ብለው በራቸውን እንዲዘጉ ሰበብ ሆኗችዋል።

በዓፄ ፋሲል ከዘነመንግስት (ከ17ኛው መክዘ) ቢያንስ ለሁለት ከፍለ ዘመናት ያህል በራችንን ቆልፈን ማንም እንዳይደርስብን ብለን እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ። ይኸ በርን በመዝጋት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ፖሊሲ፤ ከዓለም ጋር ያለንን የንግድ፣የቴክኖሎጂና የዕውቀት ትሥሥር ስለጎዳውና ኢትዮጲያን በብቸኝት ጉድለት ውስጥ ስለጣላት በዕድገት ጉዞዋ ላይ አሉታዊ ሚና ተጫውቷል። የብቸኝነት ጉድለት ከሌሎች ጋር

የሚኖረን ግንኙነት ስለሚያቋርጥ፤ ግንኙነቱ ከተቋረጠ ደግሞ ለለውጡ የሚሆን ትምህርት መሰተጋብረ ስለማይኖር፤ ወደ ብልፅግናና ክሱትነት ሳይሆን ወደ መክሰምና መዝቀጥ እንድናመራ አድርጎናል፡፡

አዳዲስ ነገሮችን የምናገኘውና እኛም ለሌሎች ምናጋራው፤ በሁኔታችን የምንቆጨውና የምንኮራው፤ ለተግብርና ለዓላማ የምንነሣሣው፤ ከሌሎች ጋር በምናደርገው መስተጋብርና ከከባቢያችን ጋር በሚኖረን ትብብርና ፉክክር ውስጥ ነው፡፡ በመሆኑም ግኑኝነት ከሌለ የዕድገት ለውጥ የለም፡፡በአንፃሩ ባሉበት መቆምም ሰለማይቻል የቁልቁለት ጉዞ አይቀሬ ይሆናል፡፡

ውሎ አድሮ ግን ኢትዮጵያ በሯን ገርበብ አድርጋ ከፈተች፡፡ኢትዮጵያ በሮቿን ዘግታ ምዕራባዊያን እንዳይደርሱባት ካደረገች ከዘመናት በኋላ በሯን ገርበብ አድረጋ የከፈተችው በዘመናዊት ኢትዮጲያ ጅማሬዎች አካባቢ ማለትም በ19ኛው መክዘ መጫረሻዎቹ ግድም ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ሌሎችን ስለተወቻቸው አይውአትም፡፡ባትሄድም ይመጣሉ፡፡ ከ17ኛው መክዘ ጀምሮ በአሰሳ ላይ የነበሩት ምዕራባዊያን አፍሪካንና የቀይባሕር አካባቢን ማማተር ቀጥሎም ማንኳኳት፤ በመጨረሻም እየሰበሩ መግባት ጀመሩ፡፡ ኢትዮጵያዊያም በዙሪያዋ ያንዣበቡትን ኃይሎች ለማወቅም ሆነ ለመገዳደር ወዳጅ ፍለጋ በሯን ከፍታ ወደ ውጪ ለማማተር ተገዳለች፡፡

በዚህ በሯን ገርበብ አድርጋ በከፈተችበት ዘመን፤ ለለውጥ የሚሆናትን ግንኙነት ከአንዳንድ ምዕራባዊያን ኃይሎች ጋር በማድረግ ሥልጣኔዎችን ፍለጋ አማትራለች፡፡ ኢትዮጲያዊያን ወደ አውሮፓና መካከለኛው ምስረቅ ለትምህርትና ለመንግሥታዊ ጉብኝት መጓዝ ጀመሩ፡፡ አውሮፓዊያን፤ እሲያውያንና የመካከለኛ ምሥራቅ ሰዎችም በኢትዮጲያ ውስጥ በንግድ፣ በዲፕሎማሲ፣በሞያ ሥራ በሃይማኖት ትምህርት ገቡ፡፡ ይህም ኢትዮጵያውያን ራሳቸውን ከሌሎች ጋር እንዲያነፃፅሩ ዕድል ሰጣቸው፡፡

በዚህም ኢትዮጲያን ካደጉት ሀገራት ተርታ የማሳለፍ ቁጭትና የለውጥ ፍላጎት በትውልድ ዘንድ አንሰራራ፡፡ ኢትዮጵያ ሌላውን ዓለም የፈለገችው በወዳጅነትና በስልጣኔ አጋርነት ነበር፡፡ ብዙዎቹ የምዕራቡ ዓለም ኃይሎች ግን ኢትዮጲያን የፈለጓት ቅኝ ለመግዛት ነበር፡፡ ይኽም ፍላጎት መለያየትን አስከተለ፡፡ በዙሪያችን አፍሪካን ለመቀራመት አሰፍስፈው የነበሩ ኃሎችም ገርበብ ተደርጎ በተከፈተው በር ስተት ብለው በመግባት የቅኝ ግዛት ቀንበራቸውን ለመጫን ሲሞክሩ በኢትዮጵያ ልጆች የአርበኝት ስሜት በአድዋ ተራሮች ሥር ተቀበሩ፡፡

የጣሊያን ተመልሶ መምጣት በዚያን ዘመን በኢትዮጲያ ትውልድ ላይ ሁለት ዓይነት ተጽዕኖዎችን አሳድሯል፡፡ የሁለቱም ተጽዕኖ ምንጩ የጣሊያን ወረራ ከቀድመው ጋር ሲነፃፀር ከፍ በማለቱና የቴክኖሎጂ ብልጫ በማሳየቱ የሚነሳ ነው፡፡ እናም ትውልዱ በአንድ በኩል ሀገሩ የደረሰባትን የቴክኖሎጂና የሥልጣኔ ብልጫ በመሙላት ኢትዮጵያን በፍጥነት እንዳደጉት ሀገራት የማሳደግ ቀና ምኞት ያደረበት ነው፡፡ከዚህኛው ወገን የሚመደቡት የትውልድ አባላት በሀገራቸው ታሪክና እሴት በመኩራት፤ የውጪውን ስልጣኔ፤ በማድነቅ ሁለቱንም ያጣጣመ የመዘመን መንገድ ለመከተል ሞክረው ነበር፡፡ በሌላ በኩል ሌላኛው ትውልድ የቴክኖሎጂ ብልጫው በስራና በትጋት የማይተካ እስኪመስል ድረስ ‹‹የራስን ጥሎ የውጪውን

የማንጠልጠል ›› አባዜ ውስጥ የገባ ነበር፡፡ሀገሩን የሚወቅስ፤የራሱ የሆነውን ሁሉ ኋላ ቀርነትና የድንቁርና ምክንያት አድርጎ የሚቆጥር፤የውጭውን የሚናፍቅ ብቻ ሳይሆን የሚያመልክ ትውልድ እየተፈጠረ መጣ፡፡ በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ በሮች ሁሉ ለውጭውም ዓለም ብርግድግድ ብለው መከፈታቸው ሳይበቃ፤ ከውጭ ለሚገፉትም አካላት ከውስጥ የሚተባበር ኃይል እየተፈጠረ መጣ፡፡

በተከፈተው በር ቅኝ ገዢዎችን ደብቆ ለማስገባት ከቅኝ ገዢዎች ጋር ያደሩ፤ ክብርና ኩራታቸውን መርሳት የጀመሩ፤ ባንዳ ወንድሞቻችን ያኔም እንደ ዘንድሮው ነበሩ፡፡ባንዳ ማለት በገንዘብ፣በትርክት፣በዕውቀት ወይም በሌላ ጉዳይ ተታሎ፤ሀገሩንና ማንነቱን በክህድት አሳልፎ ለጠላት የሚሰጥ ማለት ነው፡፡ ባንዳነት ለራስ ክብር ያለመስጠት በሽታ ነው፡፡ አንድ ግለሰብ ለራሱ ክብር ካልሰጠ፤ በራስ መተማመን የለውም ማለት ነው፡፡ በራስ መተማመን ከሌለው ደግሞ ሌሎችን ለመምሰል ይጥራል እንጂ ራሱን አይለውጥም ራሱን አያሳድግም፡፡ ባንዳነት የትውልድ ነቀርሳ በመሆኑ፤ ውሎ አድሮ የታሪክ ጠባሳን በሀገርና በወገን ላይ ሳይጥል አያልፍም፡፡

ማንኛውም ሰው በልጅነቱ ጊዜ ያለው ዕውቀት፤ ገንዘብና ችሎታ በጣም አናሳ ነው፡፡ ሲያድግ መሆን የሚፈልገውን እያለመ፤ አርአያዎቼ ናቸው ከሚላቸው እየተማረ፤ በራሱ መተማመኑን ይዞ ያድግና፤ ከዓመታት በኋላ ታላቅ ሰው ይሆናል፡፡ በራስ መተማመን የሌለው ሰው ግን፤ የራሱን ነገር እየደበቀ፤ ያልሆነውን ለመምሰልና የሎሎችን ለማስመሰል ስለሚሞክር፤ ራሱን ለመገንባት ላይ አያተኩሩም፡፡ የውስጥ እርግጠኝነት የጎደለው ሰለሚሆን ፤ሁሌም የሰው ድግስ አድማቂ ሆኖ ይቀራል፡፡

በሀገር ደረጃም ዜጎች በራሳቸውና በሀገራቸው የማይኮሩና መተማመን የሌላቸው ከሆነ፡፡ ምን መሆን እንደሚፈልጉና ምን አይነት ሀገር እንደሚገነቡ የራሳቸውን ህልም ካሌላቸው፤ስልጣኔን መገንባትና ከሌሎች ሀገራት ጋር የሚስተካከል ቁመናን ማዳበር አይችሉም፡፡ የባንዳነት አባዜ የፈጠረብንን ጣጣ፤ የኢትዮጵያውያንን በራስ የመተማመን ሀገራዊ ኩራት ሸራርፎ በመናድ፤ ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ነገር ሁሉ የሚንቁና የሌላውን የሚያደንቁ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

ለዘመናት በራቸውን ዘግተው የቆዩት ኢትጵያውያን፤ በዘመናዊት ኢትዮጵያ ጅማሮ በራቸውን ገርበብ አድርገው ሲከፈቱ፤ ጎን ለጎን ቅኝ ገዥእንዳይገባባቸው የሀገራችን ጀግኖች በኩራት ተፍልመው ነበር፡፡ ዳሩ ግን በጥቂቶች ተጀምሮ እያቆጠቆጠ የነበረው የባንዳነት እንቅስቃሴ በጊዜ ሂደት ክስተት ብቻ ሳይሆን ባህልም ሆነ፡፡ መጀመሪያ ፈረንጅን አሾልከው ያስገቡት ኢትዮጵውያን፤ከጊዜ በኋላ በድንገት በራቸወን ከፍተው ወደ ፈረንጅ ሀገር ሄዱ፡፡ ረሳቸውን ንቀው ከአዕምሮ ተሰደዱ፡፡ እምቢ ለሀገሬ የሚለው እየቀረ እምቢ ከሀገሬ ሆነ፡፡ ዓላማችን ‹‹መዘመን መሆኑ ቀረና መፈረጅ» ሆነ፡፡

የምዕራባውያኑን ዱካ እያሰስን ከእግራቸው ስር ተቀምጠን ስንማር ቆየንና፤ በቅኝ ግዛት ያባረርናቸውን አውሮፓውያን በማርክሲዝም ሌኒኒዝም በኩል ተከተልናቸው፡፡ሕልማችን አድራሻውን ሰቶ፤ መልኩን ቀይሮ፤ፈረንጅን በኮሚኒስት እሸግ ጠቅልሎ ተቀበለው፡፡ በኮሚኒስት እሽግ ውስጥ የመጣው ፈረንጅ የመምሰልና የመኮረጅ ልምድ፤ ጭራሹን እንደ ስልጣኔ ተቆጠረ፡፡

በመጨረሻም ኢትዮጵያ በሯን ሰብራ ጣለች፡፡ በሩ የተሰበረበት ቤት የቤትነት ባሕርይና ክለላ የለውም፡፡

ክፍትነት እንደተተወ ሌማት፤ ማንም እየመጣ ከማዕዱ ያሻውን እየቆረሰ እንደሚሄደው የእኛም ነገር እንዲያ እየሆነ መጣ። ሌማቱ ባለቤት ያጣ መሰለ። ኢትዮጵያ በሯን ሰብራ ስትጥል ልጆቿም ትተዋት ሄዱ።ምድራቸውን ትተው ተሰደዱ ለማያውቋቸው ማርክስና ሌኒን ሲሉ ተጋደሉ። መለኪያቸው ማርክስና ሌኒንን በማወቅ፣ በመውደድና በማቀንቀን ሆነ።

አስቀድሞ በተማሪዎች ንቅናቄ ጊዜ አእምሯቸው የተሰደደው ኢትዮጵያውያን በመጨረሻም በአካል ተሰደዱ። ሀገራቸውን መቅኖ ቢስ በማኻይማን መጫወቻ አደረጓት። በእነሱ የተጠነሰሰው ቀስ በቀስ እየበረታ ሄደ፤ ጉልበት እንደ ዕውቀት፤ ክፋትም እንደ ብርታት ተቆጠረ። ሙስና ብልጠት፤ ስንፍናም ብልሀት መስሎ ታየ። ሀገራዊ እሴቶች ፈራርሶ፤ ተቋማትም ተናዱ።

እንዲህ እንዲህ እያለ ከኢትዮጵያ የመራቅና የመነጠል ዝንባሌ፤ የራሱን ማንነትና የራሱን ቤት የማጠልሸት ልማድ ቀስ በቀስ እየጎለበተ መጣ። በመጀመሪያ እዚሁ ተሁኖ ፈረንጅ እንዲገዛን ማደግደግ ተጀመረ።ቀጥሎ ፈረንጅ ፍለጋ በሐሳብ መፍለስ ወይም በአዕምሮ መሰደድ ቀጠለ። በመጨረሻም ከነአካቴው ሀገርን ትቶ የፈረንጅ ሀገር ለማገልገል በአካል መገስገስ ተጀመረ። የራሴን ቤት መጥታችሁ አስተዳድሩልኝ ከሚል የራስ ንቀት ጀመሮ፤ ልምጣና ራሴን አስተዳድሩኝ ወደ ሚል አደገኛ አባዜ አደገ። አርበኝነትና ኩሩነት እየሸረሸሩ ሄደው፤ በደም የመከትናቸውን በገዛ አግራችን ሄደን ደጅ ጠናናቸው።

ሀገራችንን ለመጠበቅ በየተራራዎቻችን የሞትን ኢትዮጵያውያን፤የሰው ሀገር ለማገልገል በየባህሩ ሰጥመን መሞት ጀመርን። ውጭ መሄድ ነውር ከነበረበት የኩራትና በራስ መተማማን መንፈስ ወጥትን፤ እኔ ሀገሬን መለወጥ እችላለው ከሚል ጠንካራና አይበገሬ ስሜት ርቀን፤ እንደ ቤት አልባ ጥገኝነት ጠየቅን ፤የባዕዳን እስር ቤቶችን አጣበብን።

ይኼ እንዴት ሊሆን ቻለ? ኃይለኛው እንዴት ወደቀ? ኩሩውስ ሕዝብ እራሱን እንዴት አዋረደ? ቀስ በቀስ ከራሳችን እየነጠለ የወሰደውን ነፍስ፤ ቀስ በቀስ በራስ መተማመናችንን እየቦረቦረ የወሰደ ጎርፍ፤ በመጨረሻም የፈረጅን እጅ ተመልካች ሲያደርገን መመልከት፤ ዓይን ውስጥ እንደገባ ጉድፍ፤እንደ ጣት ላይ ቁስል እየጠዘጠዘ ዕረፍት የሚነሳ ሆነብን።

ስለዚህም መጪው የመደመር ትውልድ እንደ ከርታታው ይሁዲ ከሀገር ሀገር መዞሩን ትቶ፤ ወደ ቤቱ እንዲመለስ መስራት ያስፈልጋል። ከርታታው ይሁዲ በተለያዩ ጊዜያት፤በተለያዩ የስነ ፅሁፍና የሥነ ጥበብ ሥራዎች ላይ አሻራውን ያሳረፈ፤ የመካከለኛው ዘመን አፈ ታሪክ ነው። አፈ ታሪኩ ስለ አንድ ለዘላለም ሲንከራተት እንዲኖር ስለተፈረደበት አይሁዳዊ የሚተርክ ነው። ከሀገር ሀገር እየዞረ ይኖራል። አይሞትም። ከአንዱ ቦታ አለማርጀቱን እየተወ ሲሳለቁበት ሀገር ቀይሮ ደግሞ ሌላ ቦታ ኑሮውን ይቀጥላል። እንዲህ ከሀገር ሀገር እየተንከራተተ ኑሮውን የሚገፋ በዚህ ከርታታ ይሁዲ ታሪክ የኢትዮጵያንን አሁናዊ ፈተና ለማብሰልሰል የሚመች ነው።

መጪውን ትውልድ ከማንነቱና ከኩራቱ አፍልሶ፤ ከቤቱና ከቀየው ስቦ፤ከሀገሩና ከመንደሩ ገፍትሮ፤ሌላ ሀገር ደጅ እንዲጠና ያደረገውን ሕመም እንዴት እናክመው? ብዙ ችግር የፈጠረብን፤ የትውልድ የተሳሳተና ገሐድ

የማይሆን ሕልም በመሆኑ ሕልሙን ማቅናት ያስፈልጋል። የትኛውም ወላጅ ልጁ ‹‹የሰው ቤት ሄጄ፤ የሰው ቤት አገልግዬ፤ የሰው እንጀራ በልቼ›› የሚል ሕልም እንዲያልም አያፈልግም። ይልቁን በራሱ እንዲተማመን፤ ትልቅ ሕልም እንዲኖረው፤ ትልቅ ደረጃ ላይ እንዲደርስልት ይመኛል። ከራሱ ቤት ይልቅ የሰውን ቤት የሚሻ፤ የራሱን ማንነት ነቆ ሰው ነገር የሚያስመስል፤ የራሱ ሕልምና ፍላጎት የሌለውና በሰው ህልምና ፍላጎት ብቻ የሚመራ ልጅ እንዲኖረው የሚፈልግ ወላጅ የለም።

የራሱን ህልም በማለም የራሱን ዜዴ ፈጥሮ ከሌሎች ትምህርት በመቅሰም የራሱን ፍልስፍና ቀምሮ ታላቅ ሳይንቲስት፣ ፈላስፋ፤ ወይንም መሪ ሆኖ ‹‹እከሌ» ተብሎ የሚጠራ ሰው እንዲሆንለት ያሰፈልጋል። እንደ ጥላሁን ገሠሠ ወይንም እንደ አፈወርቅ ተክሌ፤ እንደ አክሊሉ ለማ ወይንም እንደ ፀጋዬ ገብረ መድኅን፤ ስማቸው ጎልቶ የተፃፈ ልጆች እንዲኖሩት የማይመኝ ወላጅ የለም።የጥላሁን ድምጽ የሚመስል ወይም የአፈወርቅ ተክሌን ሥዕል አስመስሎ የሚስል ሰው ከጓደኞቹ በዘለለ በሰው ልጆች ስሙ የሚነሳ ፈርጥ እንዲሆን ከፈለገ የራሱን ቀለምና ፍልስፍና መከተል ይገባዋል። ራስን ፈልጎ ማግኘት እንጂ ዘለቄታው እያስመሰሉ መኖር የሌላ ሰው ካርቦን ቅጅ መሆን ነው። ኢትዩጵያውያንም ይኽን ራስን ፈልጎ የማግኛት ጎዞ እንዲጀምሩና መጪው ትውልድ ራሱን ፍልጎ በማግኘት ከኢትዮጵያዊ ማንነቱ ጋር የታረቀ እንዲሆን ሰፊ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል።

የመጪው ትውልድ ሕልም ራሱን ፈልጎ ማግኘት ራሱን መገንባት እንጂ ሌሎችን እያስመሰሉ መኖር እንዳይሆን ማገዝ ይኖርብናል። ‹‹የሰው ወርቅ አያደምቅ›› እንዲሉ የራሱን ወርቅ ፈልጎ ማውጣት አለበት። በጊዜ ሂደት ሁለንተናውን ትቶ የተሰደደው ኢትዮጵያዊ፤ ዞሮ ዞሮ ወደ ሀገሬ በማለት ወደ ቤቱ እንዲመለስ፤ ሕልሙን በሀገሩ ላይ እንዲያደረግ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል። ሕልሙን ሀገሩ ላይ ከተከለ፤የሚመኘውን ነገር በምድሩ ላይ መፍጠር እንደሚችል ከተገነዘበ፤ አውሮፓና አሜሪካ ሳይሄድ እዚሁ የስልጣኔ በረከት መቋደስ እንደሚቻል ከተረዳ፤ ኑሮውን እዚሁ መገንባት እንደሚችል ካመነ፤ ኢትዮጵያን አሳምሮ ማበጀት አያቅተውም።

በሐሳብም በአካልም ሀገርን ትቶ መሰደድ ለፖለቲካውም ለኢኮኖሚውም የፈረንጅን ዳረጎት መሻት፤ ከአሸናፊዎች ሀገራት ሥር ጥገኛ ለመሆን ባሕር መግባት፤ ከኩሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባሕርይ ጋር አይሄድምና ላይመለስ መፋቅ አለበት። መጪው ትውልድ በራሱና በኢትዮጵያ አቅም የሚያምንና ህልሙን በሀገሩ ላይ ያደረገ፤ለሌሎች የተፈቀደ ለእኛ ያልተፈቀደ ምንም ነገር የለምና ፤ ኢትዮጵያ እንደተራራዎቿ ከፍ ትላለች ብሎ ያመነ መሆን ይኖርበታል። ይኽን ለማድረግ ግን ኩሩነትና በራስ መተማመንን የሚገነባ ነገሮችን ሳንዘነጋና ችላ ሳንል መፈፀም ይኖርብናል።

አንጋጦ ወደ ውጭ ከመመልከት ይልቅ ከውስጡ ያለውን ብርሃንና በረከት የሚመለከት ሀሳብንም ሸቀጥንም ከውጭ ልሸምት ከሚል ይለቅ እዚሁ ልፍጠራቸው ብሎ የሚነሣ፤ በሌሎች ላይ አይቶ የሚጎመዠውን ራሴ መፍጠር እችላሁ የሚል፤ ለሀገሬ እኔ ራሴ በቂ ነኝ የሚል እምነት ያለው ትውልድ ሊነሳ ይገባል። ፈረንጅ እስኪያፀድቅለትና እስኪፈርምት ከሚጠብቅ ይልቅ፤የራሱን ጀግኖችና የራሱን ሀብት ማድነቅ የሚቸል ከሩና

ሀገር ወዳድ የባለቤትነትና የማንነት ኩራት የተጎናፀፈ ትውልድ ልንፈጥር ይገባል፡፡

በዚህ ውስጥ ትውልድ ወደ ራሱ ሀገርና ቤት እንዲመለስ እናደርጋለን፡፡ ሥራና ምግባሩን ከጓሮውና ከአካባቢው እንዲጀምር እናደርጋልን፡፡ ውበትና አድናቆቱን ከዙሪያ ገባው ኮረብታና ወንዝ እንዲጀምር መንገዱን እናሳየዋለን፡፡ ሩቅ የሚመስልውን አቅርበን በማሳየት እንደምንችል እናስተምረዋልን፡፡ ለመኮረጅ ሳይሆን ለማወቅ ጉጉት እንዲኖረው፤ ለመቀበል ሳይሆን ለመስጠት የሚነሳሳ እንዲሆን፤የሙላትና በራሱ የመተማመን መንፈሱን ለማጎልበት የምንችለውን ሁሉ እንደረጋለን፡፡

ሕልሙን ከሰጠነው ገሐዱን በአካል ይጨብጠዋል፡፡ ትውልድ የሚንከራተተው የማንነቱን የባለቤትነቱን ካርታ ስቶ እንጂ፤ ኢትዮጵያን መለወጥና መገንባት ከባድ ሆኖ አይደለም፡፡ ሕልሙን ካሳጨበጥነው፤ካርታውን ካፋለግነው፤ የማንነት ሕንጻውን መገንባት፤ የባለቤትነት መብቱን መጎናፀፍ ቀላል ነው፡፡ የተሳሳተው ሕልማችንን ያኖርንበት አድራሻ ነው፡፡ ገጣሚው እንዳለው፡-

**"ከውጪ ያለውን ሄዶ ከመፈለግ**

**ከውስጥ የበራውን እንዲወጣ ማድረግ"**

ይኸ ነው-በትውልድ ውስጥ የምንገነባው የማንነትና የባለቤትነት ትውልዳዊ ግንባታ ቁም ነገር፡፡ ሕልሙን በሀገሩ እንዲያደርግ ካስቻልን በኋላ ሌላኛው በትውልድ ልብ ውስጥ የምናኖረው ቁም ነገር፤ ሕልሙን መልካም እንዲያደርግ ማስቻል ነው፡፡ ለራሱና ለኢትዮጵያ ብሎም ለሰው ልጆች ሁሉ የሚጠቅምና አስተዋጽዖ የሚያበረክት፤ ስልጣኔን በማዋጣትና በመስጠት አስተሳሰብ የተቃኘ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በእያንዳንዱ እንቅስቃሴያችንና ድርጊቶቻችን ውስጥ ትውልድ "እኔ ብቻ" ከሚል ስግብግብ ስብዕና ወጥቶ እኛነትን እንዲላበስ እና "አምጡ" ከማለት ይልቅ "እንኩ" ማለትን እንዲለምዱ የሚያስችሉ ተግባራትን መፈፀም አለብን፡፡ ንግግርና ተግባሮቻችን ትውልዱ ከሀገራዊነቱ፣ ከሕልሙና ከጎሊናው ጋር ታርቆ መኖርን እንዲያውቅ የምንስችልበት መሆን ይገባዋል፡፡ መሪዎች አርአያ በመሆን ትውልዱ እንዲላበስ የምንሻቸውን ጠባዮች ተላብሰን እየኖርን ልናሳየው ካልቻልን ነገሩ "ላም አለኝ በሰማይ" ይሆናል፡፡

መጭው ትውልድ የሚመራበት የሕይወት ፍልስፍና ግላዊ ስኬትንና ሀገራዊ ጥቅምን አጣጥሞ የሚሄድ ምልዓታዊ ፍልስፍና ነው፡፡ ግንባታችን ይኸ ምልዓታዊ የሕይወት ፍልስፍና በትውልድ ላይ እንዲሠርፅ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት የምናደርግበት ይሆናል፡፡ ግለ ስኬትንና ማህበራዊ ዓላማን አጣጥመው፤ ኅሊናቸውን ከተግባራቸወ አስታርቀው፤ ለራሳቸው ታምነው የሚሰሩ ግለሰቦችን መፍጠር ከተቻለ፤ ሀገራችንን ከምናስበው ርዕይ እናደርሳታለን፡፡ ከራስ ጋር መታረቅ፤ የዕርቆች ሁሉ መጀመሪያ ነው፡፡ ለራስ መታመን፤ የመታመንና የመተማን ሁሉ መነሻ ነው፡፡ ስለዚህም ባለፉት ዓመታት በማህበራዊና በመንግስታዊ ሥርዓቱ ላይ ትልቅ ተፅዕኖ ከፈጠረው የግለዊ ስኬት ፍልስፍና በመውጣት፤ ሐቀኝትን የሚያጎለበት የሕይወት ፍልስፍና በትውልድ ውስጥ መትከል ያስፈላጋል፡፡ ትውልዱ የግል መብቱንና የጋራ ደህንነቱን፤ የራሱን ስኬትና

የማህረሰቡን ተጠቃሚነት ሳያዛባ ማራመድ ከቻለ፤ የማንነት ልዕልናንና የባለቤትነት ከፍታን ረገጠ ብለን ልንኮራ እንችላን።

# ከሞፈር እስከ መሶብ

*"የእኔ አባት እስከ ሦስት መቶ ከብት ነበራቸው፤ አንዲት ጥጃ*

*ተረፈቻቸው አሉ። ስሟን "ሳለሁ ድረሽ" አሏት። ረሃቡን ያስነሳው*

*የከብቱ ማለቅ ነው አሉ። በምን ይታረስ ? መሬት ሳይታረስ እንዲያው*

*እንዳለ ቀረ። ረሃቡም ያን ጊዜውን ከብቱ እንዳለቀ ተከተለ፤ እስከ*

*ሦስት ዓመት ደረስ ሰነበተ።*

ይኸ የተጠቀሰው ቃል የባለቅኔ የመንግስቱ ለማ አባት አለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ፤ስለ ከባዱ ረሃብ "ክፉ ቀን" የተናገሩት ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ "ክፍ ቀን" የሚባለው ረሃብ በአፄ ሚኒሊክ ዘመን መንግሠት የተከሰተና፤ አንድ ሦስተኛ የሚሆነውን ሕዝብ ፈጅቷል የሚባለው ነው። ረሃቡ የተከሰተው ከውጪ በመጣ የደስታ በሽታ ከብቶች ስላለቁና በዚህም ምክንያት እርሻ ማረስ ስላልተቻለ ነበር። የከብቶቹ በሽታ ጣልያኖቹ ወደ ምፅዋ ካመጧቸው በቅሎዎችና ፈረሶች ተነሥቶ፤ከሰሜን ጫፍ እስከ እስከ ደቡብ ጫፍ በጥቂት ዓመታት ውስጥ የተሰራጨ ነበር። በሽታው ወደ 90 በመቶ የሚሆኑትን የኢትዮጵያ ከብቶች ጨርሷል።

በአለቃ ለማ ቃል ውስጥ እስከ ሦስት መቶ ከብት የነበራቸው አባታቸው አንዲት ጥጃ እስከቀር ድረስ ሁሉም በሞት ሲያልቁባቸው፤ በአንዷ ጥጃ ላይ ተስፋቸውን ጥለው "ሳለሁ ድረሽ ብለው" ሰየሟት። "ሳለሁ ድረሽ" ሲሉ እኔ ሳልሞት ጊደር ሆነሽ እንዳይሽ ያብቃኝ ማለታቸው ነው። ሦስት መቶ ከብት የነበራቸው ሰው አንዲት ጥጃ ቀርታቸው፤ በእርሷ ተስፋ አድርገው ተስፋቸውን በስሟ ቀርፀው አስቀመጡት ይህ የተስፋ ጥግ የኢትዮጵያውያንን የብርቱነት ልክ የሚያሳይ ይመስለኛል። በእያንዳንዳችን ታሪክ ውስጥ ያለና የሚኖር የአይበገሬነታችን ማሳያ ሕያው ታሪክ ልንለው እንችላን።

በኢትዮጲያ ታሪክ ውስጥ በብርቱ ልንማርባቸው ከሚገቡ ጉዳዮች አንዱ ከረሃብ ጋር የተያያዘውን ታሪካችንን ነው። በአድዋ ተራሮች ላይ በአባቶቻችን ደም ደምቆ የተፃፈውን ስማችንን በጥላሸት፤ እየሰረዘ እየደለዘ አንገታችንን ሊያዳፍን የሚሞክረው የረሃብ ታሪካችን ነው። ከተመዘገበው ታሪካችን ብንነሳ እንኳን ከዘጠናኛው መክዘ ጀምሮ እየደጋገመ ረሃብ መትቶናል። ያለ ረሃብ የተሻገርነው አንድ ክፍለ ዘመን ነበር ማለት አይቻልም።

ከትላንት እስከ ዛሬ የሚከተለንን ይሕን ክፉ ችጋር ነቅልን ካልጣልን ፤በእውነት እኛ ማነን እንላለን? ቀና ያለውን አንገታችንን በግድ ጨምድዶ እንድናቀረቅር ሊያደርገን የሚሞከረውን፤ በአስተሳሰባችንና በባህላችን ውስጥ ገብቶ ሰቀቀንና እጦትን እንድናሰብ ያደረግንን፤ የጠላቶቻችን መዘባበቻና የምፅዋት ተመልካች ያደረገንን፤ይኸንን እሾህ በቶሎ ነቅለን ካልጣልን፤ ማነን እንላለን? ከዓመታት በፊት በተፃፈ የኢትዮጵያ

ረሃብንና የምዕራብ ጋዜጦችን አስተያየት በሚመረምር አንድ ጥንታዊ ጽሑፍ ላይ ጸሐፊው በአንክሮ እንዲህ ይላሉ፡-

*"ማንም ሰብአዊ ፍጡር ሊገምተው እንደሚችለው ሆዱን ሞልቶ*

*የማያድር ሕዝብ ብሔራዊ ኩራት ሊኖረው ከቶ አይችልም"*

ኢትዮጵያውያን ብሔራዊ ክራታችንን ከሚፈታተኑ ነገሮች አንዱና ዋነኛው ረሀብ መሆኑን መካድ አንችልም። በእርግጥ ረሃብ ከኢትዮጵያውያን ጋር ተሳስሮ የሚነገርበት ዋነኛው ምክንያት፤ ከሌሎች ሀገራት የባሰ የረሃብ ታሪክ ስላለን አይደለም። በመዝገበ ቃላት ሳይቀየር ሀገራችንን የረሃብ ምሳሌ አድርጎ ለማስቀመጥ የተሞከረው ሙከራ ምክንያቱ ምን እንደሆነ በነጻ ልቦና መመርመር አስፈላጊ ቢሆንም ስማችንን ለማጠልሸት እንዲጠቀሙበት በር የከፈትነው ራሳችን መሆናችንን ልብ ልንል ይገባል።

"በራቸውን ከፍተው እየሔዱ ሰውን ሌባ ይላሉ" የተባለው አይነት ነው። ኢትዮጵያ ከአውሮፓም ሆነ ከእሲያ የባሰ የረሃብ ታሪክ የላትም። ለምሳሌ በ20ኛው መክዘ በዓለም ላይ 70 ሚልዮን የሚጠጉ ሰዎች በረሃብ ሞተዋል። ከዚህም ውስጥ ኢትዮጵያ በረሃብ ያጣቻቸው ልጆቿ፤ ከፍ ባሉት የቁጥር ግምቶች ብንወስድ እንኳን፤ እስከ 2 ሚልዮን የሚሆኑ ናቸው። በአንፃሩ ቻይና 40 ሚሊዮን፣ሶቪየት ኅብረት 11 ሚልዮን ፣ዩኮሬን (በሶቪየት ግዛት ሥራ እያለች) 8 ሚልዮን ሰሜን ኮሪያ 4 ሚልዮን፣ ሕንድ 3 ሚልዮን፣ ወዘተ. አልቀውባቸዋል። ይኽንን ግርድፍ የቁጥር ስሌቶች ወስደን ብናይ እንኳን፤ እነዚህ ሀገራት በረሃብ ያለቀበቸው ሕዝብ ቁጥር ከኢትዮጵያ በእጅጉ የባሰ መሆኑን እናመለክታለን።

በእያንዳንዱ የረሃብ ከስትት ያለውን ቁጥር ከተመለከትን ደግሞ ኢዮትዮጵያ ከፍተኛ ሕዝብ ያለቀባት በ1976 ዓ.ም በተከሰተው ረሃብ ሲሆን ፤ ከፍ ባለው የቁጥር ግምት እስከ 1 ሚልዮን የሚጠጋ ሕዝብ በሞት አጥታለች። ቻይና በአንድ ጊዜ ከ30 ሚልዮን በላይ ሕዝብ በረሃብ አጥታ ታውቃለች። ሕንድ 3ሚልዮን፤ ካምቦዲያ 2 ሚልዮን ናይጄሪያ 1 ሚልዮን ሕዝብ አጥታለች። ታዲያ ኢትዮጵያን የረሀብ ተምሳሌት አድርጎ ለማቅረብ እና ስሟን ለማጠልሸት የተደረገው ሙከራ ከምን የመነጨ ነው?

እንደ አህጉርም ስንመለከተው፤ በ20ኛው መክዘ አፍሪካ 4 ሚልዮን የሚጠጋ ሕዝብ ሲሞትባት፤ቀሪው ከ60 ሚልዮን በላይ ሕዝብ በረሃብ የሞተው ግን በአውሮፓና በእሲያ ነው። ታዲያ አህጉራችንን የረሓብ መነሻና መድረሻ፤ ሀገራችንን የረሃብ ምልክት አድርጎ ለመሳል የተደረገው ጥረት ከሰብአዊነት የመጨ እውነት ነው? ወይስ ከዘረኝት የመነጨ ሽፍጥ?

ወደ ኋላ ሄደን ታሪክን ብንመለከት ደግሞ በ9ኛወ መከዘ በኢትዮጵያ ከፉ ቀን ሕዝባችንን በረሃብ ሲፈጅብን፤ አየርላንድ ከ1.5 ሚልዮን በላይ ሕዝብ በረሃብ ሞቶባታል። ከ1 ሚልዮን በላይ ደግሞ ተሰዶባታል። ወደ መካከለኛው ዘመን ተጉዘን ምሳሌ ብንጠቅስም በኢትዮጵያ በግርድፉ ወደ 20 ገደማ ረሃቦች ተከሥተዋል።በአንፃሩ በፈረንሳይ ብቻ ከ70 በላይ ረሃቦች ተከስተዋል። በ14ኛው መክዘ በተከሰተ ረሃብ ብቻ እስከ ሦስት አራተኛ የሚሆነው የአውሮፓ ሕዝብ በረሃብ አልቋል።

እንግዲህ በረሃብ ታሪክ ውስጥ ብዙ ሕዝብ በሞት የረገፈባቸው አውሮፓና እስያ እያሉ፤ አፍሪካን ብሎም ኢትዮጵያን የረሃብ ተምሳሌት ለማድረግ የተሄደበት መንገድ ከምን የመነጨ ነው? ነገሩን በወጉ ስናጤነው ‹‹ጅብ የማያውቁት ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ›› እንደሚባለው ዓይነት ነው፡፡ እነርሱ ያገኙትን ቀድሞ የመተረክ ዕድል ተጠቅመው፤ በየሚዲያውና በየመጽሐፉ ስማችንን ስላጠፉት እንጂ፤ የረሃብ ታሪክስ ካለበት ሀገር ነበር፡፡

እነርሱ በረሃብ ደጅ ያላለፉ፤ እኛ ግን በረሃብ ጎጆ ውስጥ የተቆለፈብን ሕዝቦች አስመስሎ ለመሳል የተደረገው ጥረት፤ በሚዲያዎችና በተለያዩ ድርጅቶች ሲነዛ ቆይቷል፡፡ ሆኖም የእኛ ዋና ጉዳይ በውሸትና በዘረኝነት ላይ የተመሰረተውን ስም የማጠልሸት ዘመቻ የምናከሽፈው፤ አስቀድመን ክፍተታችንን በመድፈን መሆኑን መገንዘባችን ላይ ነው፡፡ ‹‹አውቆ የተኛ››ን ስለ እውነቱ ለማስረዳት ጊዜ ከማባከናችን በፊት፤ የረሃብን ደና ከኢትዮጵያ ምድር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማጥፋት ይኖርብናል፡፡ የረሃብ መርዛማ ጣቶች ዳግም የወገባችንን ጀርባ እንዲቧጥጡ ዕድል መስጠት የለብንም፡፡ ይኸን ለማድረግ ደግሞ ከራሳችን ጋር ግብግብ መግጠምና ራሳችንን ማሸነፍ ይኖርብናል፡፡

ከውጭ ወራሪዎች ጋር ታግለንናል፡፡ እርስ በርሳችን በፖለቲካ ታግለናል፡፡ አሁን ከችግራችንና ችግሩን ከፈጠረው አስተሳሰባችን ጋር የምንታገልበት ጊዜ ነው፡፡ ወደ ሌላ ሰው ጣትን ከመጠቆም በፊት፤ በሰፊ መሬትና በበርካታ ወንዞች መሐል እየኖርን፤ እንዴት ለራሳችን የሚሆን እህል ማምረት ተሳነን፤ ብለን ከእውነታው ጋር መፋጠጥ አለብን፡፡ ይሄ ሁሉ ምሁር፤ መሪና ባለሙያ ያላት ሀገር፤ እንዴት በቂ እህል ማምረት ተቸገረች? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ ረሃብ ከኢትዮጵያዊ ኩራታችን ጋር ፈጽሞ የማይሄድ የጎን እሾህ ነው፡፡

መጪው ትውልድ የረሃብ ታሪካችንን ለሌሎች በሚደርስ መትረፍረፍ ገልብጦ፤ ኢትዮጵያን የጥጋብና የመትረፍ ምሳሌ የሚያደርግ ትውልድ ሊሆን ይገባል፡፡ ኢትዮጵያውያን እህል ከውጭ የሚሰፈርላቸው ሕዝቦች መሆናቸው ቀርቶ፤ ለሌሎች በማካፈል የሚታወቁ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል፡፡ ከእጦት ኑሮና ታሪክ የሚመነጭ የስስትና የሰቀቀን አስተሳሰብ ተቀርፎ፤ የጥጋብና የመትረፍረፍ ማንነት የሚፈጥረውን የለጋሽነት ሥነ ልቦና ልናዳብር ይገባል፡፡ ከምግብ እጥረት ወጥቶ ለምግብ ጥራት የሚሰራ፤ ጎተራው ሞልቶ የተትረፈረፈ አምራችና ሰጪ ትውልድ፤ መጪዋን ኢትዮጵያ ሊረከብ ይገባል፡፡

ይኸን ሕልም ለማሳካት፤ ከሁሉም በፊት ስማችንን ያጠለሸውን የረሃብ ታሪክ በሙሉነት ታሪክ ለመተካት፤ ‹‹የእኔ ሚና ምንድነው?›› የሚል ከራስ ጋር የሚደረግ ጥልቅ ውስጣዊ ትግል ያስፈልገናል፡፡ ከውጭ ኃይሎችም ሆነ እርስ በርሳችን የምናደርገው ግጭትና ጣት መጠቋቆም ከዚህ መሠረታዊ ቀውስ የሚያስጥለን አይሆንም፡፡ በመሸሸና ራስን በመሸንገል መደባበቅ አያስፈልግም፡፡ ስለ ኢትዮጵያና ስለ ኢትዮጵያውያን የምንቆረቆር ከሆነ፤ ስለ ሕዝባችን ያገባናል የምንል ከሆነ፤ ከሁሉም በፊት የተትረፈረፈ ምርት ባለቤት መሆን ይኖርብናል፡፡ ስለርሃብና ስለችግሩ የምናወራበትን ጊዜና ጉልበት ቀንሰን፤ ለመፍትሔው እጅጌያችንን የምንሰበስብበት ጊዜ አሁን ነው፡፡ የችግራችንም የመፍትሔውም ባለቤት ራሳችን መሆናችንን ስንረዳ፤ ማንነታችንን የምንረዳበትና የምንገልጥበት መንገድ ይቀየራል፡፡

# ሞልቶ የተፈረው ትውልድ

ከረሃብ ጋር የተያያዙ ሃልዮታዊ ትንታኔዎች፤ በአንድ በኩል ረሃብና ጥጋብን በግልጽ መሥመር እንደሚለያዩ ሁለት ተቃራኒ ኹነቶች የሚመለከቱ ዕይታዎች ናቸው፡፡ ቀደም ሲል ምዕራባዊያን ከዚያም የእስያ ሀገራት ከረሃብ የወጡባቸውን ጊዜያት ‹‹ታላቁ ማምለጥ›› ሲሉ የሚጠሩት ምሁራን፤ በእነዚህ ሃገራት ከረሃብ ወደ ጥጋብ ሽግግር መደረጉን ያትታሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የምግብ ችግር ደረጃው ይለያያል እንጂ፤ ረሃብና ጥጋብ በሚል ሁለት ተቃራኒ ምድቦች ሃገራትን ማስቀመጥ አስቸጋሪ እንደሆነ የሚከራከሩም አሉ፡፡ በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ፤ በአጠቃላይ ከምግብ ጋር የተያያዙትን ችግሮች በሁለት ተቃራኒ ምድቦች ከፍሎ ከማየት ይልቅ፤ በልኬትና በዓይነት ለይቶ የማየት ዝንባሌዎች እየበረከቱ መጥተዋል፡፡

ሆኖም ረሃብን ከሌሎች ምግብና አመጋገብ ችግሮች ለይቶማየት ችግሩን በአግባቡ ለመረዳት ይጠቅመናል፡፡ ረሃብ የሂደት ውጤት ነው የሚሉ ቢኖሩም በጥቅሉ ስንመለከተው ግን ረሃብ ክስተት ነው ማለት እንችላለን፡፡ በሳይንሳዊ ትርጓሜው ረሃብ ማለት በደፈናው የምግብ እጥረት ወይም ደግሞ ሆዳችን ባዶ ሲሆን የሚሰማን ስሜት አይደለም፡፡እሱ በማናቸውም ጊዜ በማንኛውም ሰው ላይ ሊከሰት የሚችል ተለምዷዊ ሁኔታ ነው፡፡ ይልቁንስ ረሃብ የምንለው ሰውነታችን በምግብ እጥረት ምክንያት በውስጡ ያለውን መጠባበቂያ ጨርሶ፤ ራሱን መመገብ ሲጀምርና በመጨረሻም ለሞት ሲዳርግ ነው፡፡ ምናልባትም ጠኔ የሚለው ቃል የተሻለ ሳይገልጸው አይቀርም፡፡ ሰውነታችን የገዛ ራሱን እየበላ ለመቆየት የሚታገልበት ይኽ አይነቱ አሰቃቂ ሁኔታ በተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት ሊከሰት ይችላል፡፡

በሀገራችን በተደጋጋሚ የሚስተዋሉ ዋነኛ የረሃብ ምክንያቶች ድርቅና ጦርነት ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ በአየር ንብረት መለዋወጥ ምክንያት በተለያዩ ጊዜያት ለዝናብ እጥረትና ወቅቱን ላልጠበቀ ዝናብ ትዳረጋለች፡፡ በሀገራችን ድርቅ ተደጋግሞ ከመከሰቱ የተነሳ ድርቅና ረሃብን አንድ አድርጎ የመቁጠር ዝንባሌዎች አሉ፡፡ ድርቅ በማንኛውም ሀገር ላይ በማንኛውም ጊዜ ሊከሰት የሚችል የተፈጥሮ አደጋ ወይም የአየር ንብረት ለውጥ ሲሆን ረሃብ ግን ይኽንን ለውጥ ተከትሎ አዝርዕት ባለመብቀላቸው ምንክያት የሰው ልጆች የሚመገቡት ሲያጡ የሚከሰት ችግር ነው፡፡

የአንበጣ መንጋ ከድርቅ ሊያገግም የሚሞክረውን ሰብል የሚያወድም ሌላኛው አደጋ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በተለይም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተደጋጋሚ በአንበጣ መንጋ ትጠቃለች፡፡ ከድርቅ በኋላ የሚመጣው

ዝናብ የሚፈጥረው እርጥበት ለአንበጣ ምቹ መፈልፈያ እንደሆነ ይገለጻል። በሰሜን ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ዘመን ጀምሮ በርካታ የአንበጣ መንጋ አደጋዎች እንደተከሰቱ የታሪክ መፃህፍት ይጠቅሳሉ። በክፉ ቀን ረሃብ ጊዜም የአንበጣ መንጋ ከፍተኛ ሰብል እንዳወደመ ይጠቀሳል። በቅርብ ጊዜ ታሪካችን በ1950ዎቹ መጀመሪያ ላይ በትግራይ ለተከሰተው ረሃብ አንዱ ዋና ምክንያት የአንበጣ መንጋ ነበር።

በሌሎችም ረሃቦች ጊዜ ድርቅንና ጦርነትን ተከትሎ የአንበጣ መንጋ እየመጣ ከፍተኛ ውድመት ማድረሱ የተለመደ ነው። አሁን በቅርቡ እንኳን ከኮረና ጋር ተዳብሎ የመጣብን የአንበጣ መንጋ በሀገራችን ምን ያህል ሰብል እንዳወደመ የምናውቀው ነው። ከአንበጣ በተጨማሪ በሽታዎችም በተለይም ወረርሽኞች ለረሃብ ትልቅ ምክንያት ናቸው። ይሁንና በሀገራችን ለተከሰቱ ረሃቦችና ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ ቀዳሚውንና በጣም ትልቁን ድርሻ የሚይዙት ድርቅና ጦርነት ናቸው። ድርቅና ጦርነቶችም ብዙውን ጊዜ ተዳብለው የሚከሰቱበት ሁኔታ ረሃብን ለመከላከል አቅም ሲያሳጣን ቆይቷል።

ድርቅ ከረሃብ ባመለጡ ሀገራትም የሚከሰት፤ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚመጣ የተፈጥሮ አደጋ እንደመሆኑ፤ በዘላቂነት የሚቀረፈው የአየር ንብረት ለውጥን በመከላከል የዝናብ እጥረትንና የዝናብ ወቅትን በማስተካከል ነው። ድርቅ አዝርዕትን በእንጭጩ ያሰቀራል ወይም ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብ ምክንያት ያለጊዜያቸው ፍሬያቸውን ያራግፋል። ዕጽዋትን ቀርጥፎ ከበላ በኋላ የሾለ ጥርሱን ወደ እንሰሳትና ወደ ሰው ያዞራል። ይሁንና ድርቆች ሁሉ ረሃብን አያስከትሉም።

ረሃብ ድርቅን ለመቋቋም የሚችል የእህል ክምችትና የስርጭት አቅም ባለመኖሩ የሚከሰት ነው። በቂ የእህል ክምችት ወይም መሸመቻ ገንዘብና የስርጭት አቅም ካለ ድርቅ ቢከሰትም እንኳን ረሃብ ሊኖር አይችልም። በቅርብ ጊዜ ታሪካችን በ1950 ዓ.ም፤ በ1964 ዓም እና በ1976 ዓ.ም ለተከሰቱ ከባድ ረሃቦች አንዱና ዋናው ምክንያት ድርቅ ነው። ከዚያም በኋላ እስከ አሁንም ድረስ ድርቅ እየተፈራረቀ በተለያየ መጠን መምጣቱን ባያቆምም ረሃብ ግን በሀገራችን አልተከሰተም። ሆኖም ከብቶችን በመግደል እንዲሁም ሳርና አዝርዕትን በማድረቅ ከፍተኛ የረሃብ አደጋ እንዲደቀንና የምግብ ተረጂዎች ቁጥር እንዲበረክት አድርጓል።

በሀገራችን የአርሶ አደሩም ሆነ የአርብቶ አደሩ ሕይወት በከብቶች ላይ ተመሰረተ ነው። የሚታረሰው በከብት ነው፤ ከብት ሲሞት እርሻም ይቆማል። ከብቶች በረሃብ ከሞቱ ሕዝቡም ለረሃብ የመጋለጥ እድሉ ከፍተኛ ነው። በከፋ ቀን ረሃብ ጊዜ በሽታ ከብቶችን ሲጨርስባቸው፤ አጼ ምኒሊክ ሕዝቡ በዶማ እየቆፈረ እንዲዘራ አዝዘው ነበር። አንዱ ቁጭት የሚቀሰቅሰው ጉዳይ ይኸ ከሆነ ከብዙ ዓመታት በኋላ እንኳን ተመሳሳይ ችግር ቢገጥመን የምናልፍበት በቂ መላ ሳናዘጋጅ መቆየታችን ነው። ያንን ችግር ያየን ሕዝቦች ምን ተማርን? አሁንስ ከብቶቻችን በአንዳች ተፈጥሯዊ ምክንያት ቢሞቱብን፤ ምን ልናደርግ ነው? ተምረን ተመራምረን ይኸንን እንኳን መለወጥ ካልቻልን፤ እኛ ማነን? ይኸን ጥያቄ ለራሳችን በማቅረብ ከራሳችን ጋር ብርቱ ትግል ማድረግ የሚገባን ጊዜ ላይ እንገኛለን።ከአድዋ ማግስት ፋሽስት እንደገና ተዘጋጅቶ ሲመጣ፤ እኛ ተዘናግተን ጠበቅነው፤ ከክፉ ቀን ማግስት ደግሞ ረሃብ በድጋሚ በአጼ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ሲመጣ እንዲሁም በመዘናጋት ጠበቅነው። የቀደመውን ሥርዓትና መንግስት ለማጣጣል እንደ አንድ እንከን የምናነሳው ረሃብ ዞሮ ተዟዙሮ

በእኛም ዘመን ሲያጋጥም አይተን ከማለፍ በዘለለ በሌላ ዙር እንዳይመጣ ወገባችንን አስረን እስከ ወዲያኛው ልንመከተው አልተነሳንም። ይኸ ከፈተና ያለመማርና አምርሮ ለነገ ዝግጅት ያለማድረግ ልማድ ጊዜያዊ ሕልውናን ብቻ የማስጠበቅ የዕለታዊነት አስተሳሰብ ውጤት ነው።

ጊዜያዊ ሕልውና ላይ የማተኮር ዝንባሌያችን ‹‹ሙሽራ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ›› እንደሚባለው ዓይነት ነው። ይኸ ልማዳችንም ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል። ፖሊቲካችን ሁሉ በታሪክ እሰጥ አገባ ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ ከታሪክ በቂ ትምህርት ለመማር አልቻልንም። ታሪክን የምናጣቅሰው እንዲሁ ለመበሻሸቅ ግፋም ሲል ለተራ ፖሊቲካዊ ትርፍ መሆኑን ይኸ እውነት ያሳብቅ ይሆን?

መጪው ትውልድ በጊዜያዊ ጉዳዮች ላይ ሙሉ ትኩረቱን ከማድረግ ይልቅ ስለነገ የሚያስብና ዘላቂ ሕልውና ላይ የሚያተኩር እንዲሆን መስራት ያስፈልጋል። አደጋዎችን አስቀድሞ የሚያጠና፤ ለዚያውም ተገቢውን ዝግጅት የሚያደርግ፤ ከታሪክ ተገቢውን ትምህርት የሚወስድና ስለነገ እያሰበ የሚራመድ እንዲሆን ይጠበቃል። የታሪኩ ባለቤት የሆነ ትውልድ የማንነቱም ባለቤት ነው። ረሃብንም ሆነ ጥጋቡን ሊሰጠን የሚችል ኃይል በምድር ላይ የለም። ‹‹ረሃብተኞች›› ወይንም ‹‹የተትረፈረፋቸው›› የሚለውን ስም የሚያጎናጽፈንም በቀዳሚነት የራሳችን ተግባርና ውሳኔ ነው። ስለዚህም የምንፈጥረውና የምንቀርጸው ትውልድ ረሃብተኝነትን ሳይሆን መትረፍረፍን ችግረኝነትን ሳይሆን በችግር ደራሽነትን የተጎናጸፈ እንዲሆን ዛሬ ጠንክረን ልንሰራ ይገባል።

የሰው ልጆች በተለያየ ዘመን በርካታ ያልተጠበቁ አደጋዎችና ፈተናዎች ገጥመዋቸዋል። ወረርሽኝ፣ድርቅ፣ጦርነት፣ የጎርፍ አደጋ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ እና መሰል በርካታ ችግሮች የሰው ልጆችን ሲፈትኑ ኖረዋል። እነዚህን ያልታሰቡ አደጋዎች በቀላሉ የሚሻገሩት የታወቁ ፈተናዎቻቸውን በቶሎ ቋጭተው ላልታወቁ ፈተናዎች ዝግጅት የሚያደርጉ ትውልዶች ናቸው። ድርቅ ለእኛ የሚታወቅ ያልደበዘዘ ጥቁር ታሪክ የጻፈ በየጊዜውም የምንጋፈጠው አደጋ ነው። ለዚህ የሚታወቅ አደጋ በቶሎ መላ አበጅተን ለመጪው የማይታወቅ አደጋ ዝግጅት ማድረግ ሲገባን በምናውቀው አደጋ በተደጋጋሚ እየተጎዳን ነው። ጦርነት ለኛ የሚታወቅ አደጋ ነው ። ለዚህ የሚታወቅ አደጋ ዘላቂ መፍትሔ አበጅተን ለማይታወቀው አደጋ ካልተዘጋጀን በቀላሉ ለጠላቶቻችን ጥቃት መጋለጣችን የማይቀር ነው።

የኮረና ወረርሽኝ በዘመናችን የተከሰተ ፈጽሞ ያልተጠበቀ አደጋ ነው። ለአፍሪካና መሰል አካባቢዎች እድል ፊቷን አዙራልን ወረርሽኙ የተፈራውን ያህል ጉዳት ባያደርስም ለአደጋ ካለን ዝግጅት አንጻር ስንመለከተው ችግሩ ቢከፋብን ኖሮ እንዴት እንወጣው ነበር? ብሎ ማሰብ ተገቢ ይመስለኛል። ወረርሽኝን ለመቋቋም የሚችል በቂ ዝግጅት ይኖራቸዋል ተብሎ በሚታሰቡት ሀገራት እንኳን የሰው ልጅ በየቀኑ እንደቅጠል ሲረግፍ በሰቀቀን ተመልክተናል። አስቀድመው ዝግጅት ያደረጉና ለዘላቂ ሕልውና ራሳቸውን ያዘጋጁ ጥቂት ሀገራት ግን ይኸንን ፈጽሞ ያልተጠበቀ ክስተት በቀላሉ ተቆጣጥረውታል።

በዓለም ላይ ቀጣይ የሀገራት ሕልውና የሚመሰረተው፤ ያልታወቁና ያልተገመቱ አደጋዎችን ለመቆጣጠርና በአደጋው ውስጥ አሸንፎ ለመውጣት ባላቸው ዝግጁነት ልክ ነው። ያለንበት ዘመን ነገሮች አይገመቴ

የሆኑበትና በቶሎ የሚለዋወጡበት የሰው ልጆች የሚሰሯቸው ስራዎችና ቴክኖሎጂዎች ወዴት እንደሚያመሩ በግልጽ የማይታወቅበት ነው። አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግና ከዓለም ሁኔታ ጋር በፍጥነት እየተላመዱ መሄድ የግድ እንደሆነ መገንዘብ እንችላለን።

ስለሆነም የነገዋ ኢትዮጵያ ከአሁን በፊት የገጠሙንንም ሆነ እስካሁን ያልገጠሙንን አደጋዎች አስቀድመው ለመከላከል ዝግጁ የሆኑ ልጆች ይኖሯታል። ስለነገ አስቀድመው የሚተልሙና ስለዘላቂ ሕልውና መላ የሚያበጁ፣ ሙሽራው ከመምጣቱ በፊት በርበሬ አዘጋጅተው የሚጨርሱ፣ ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት እንዲከስሙ መፍትሔ የሚያዘጋጁ፣ የፊት የፊቱን ብቻ ሳይሆን የሩቁን እያሰቡ የሚራመዱ፣ ከትናንት እና ከዛሬ የተማሩ ልጆች ይደርሱላታል። ድርቅ በድጋሚ እንዳይጎበኘን የሚያደርጉና ተፈጥሮን ለማደስ የሚረዱ ስራዎች የነገው ትውልድ ባህል ይሆናሉ።

ኢትዮጵያ ለምለም ትሆናለች ከርሰ ምድሯና ገጸ አፈሯ ለም ነውና። ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ ምድሯን ያረሰርሳል።ተፈጥሮ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ትታደላለች።በዛፍ መጨፍጨፍ የተራቆተው መልክአ ምድሯ ደን ይለብሳል።በአፈር መሸርሸር የደረቀው ሰውነቷ ሕይወት ይዘራል። በነገዋ ኢትዮጵያ ድርቅና ነፋስ እንደ ፈለገ አያፏጭም። ቢያፏጭም ድምጽ አያስተጋባም። የነገዋ ኢትዮጵያ ርጥብ፣ ለም እና በዛፎች ጥላ ስር የሚታረፍባት ትሆናለች። መትከል እንጂ መንቀል ባህል መሆኑ ይቀራል። ማሳደግ እንጂ የመቁረጥ ልማድነቱ ያበቃል። ሀገርም እንደ ሰው ካልተከባከቧት እንደምትገረጣና ልጆቿን የምታጠባበት ጡቷ እንደሚነጥፍ የተገነዘበ ትውልድ ይመጣል።

ሌላው ለረሃብ የሚዳርገን ብርቱ ጉዳይ፤ ከውጭ ኃይሎች ጋር እና እርስ በርሳችን የምናደርጋቸው ጦርነቶች ናቸው። ኢትዮጵያ ከሩቅም ከቅርብም በሚነሱ ጠላቶቿ፤ እንዲሁም እርስ በርስ በሚፈጠር አለመግባባት ምክንያት፤ በርካታ ጦርነቶችን አሳልፋለች። እነዚህን ጦርነቶች ሕዝቡ የእርሻ ወቅትን በጦርነት እንዲያሳልፍ በማድረጋቸው፤ የሀገር ሐብት ለጦርነት የሚውልበት ሁኔታ ስለሚፈጠርና፤ ሕዝብ ያለውን አሟጦ ለተዋጊው ስንቅ እንዲያቀርብ በማድረጋቸው፤ ረሃብ እንዲከሰት ትልቅ ምክንያት ሆነዋል።

በጦርነት ጊዜ አምራች ሕዝብ ልጆቹን ይገብራል። የሚያመርትበት ከብት ያልቃል።ዕጽዋትና አዝርዕት በእሳትና በዘረፋ ይወድማሉ። በጦርነት ጊዜ እህል ከቦታ ወደ ቦታ ማንቀሳቀስ አስቸጋሪ ነው። ጦርነት ለእርሻ የሚውለውን ጊዜ ለውጊያ ስለሚያውለው፤ ሕዝብ የሚበላውን እንዳያመርት ያደርጋል። በተለይ ደግሞ የተፈጥሮ ፈተናዎች ከጦርነት ጋር አብረው ሲከሰቱ የሚፈጥሩት የረሃብ አደጋ እጅግ አሰቃቂ ይሆናል።

የእርስ በርስ ጦርነት በኢትዮጵያ ከባድ የረሃብ ምክንያት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ከሁሉም ወገን ሕዝብ በጦርነት ይጠመዳል። የእርሻ ጊዜ ያልፋል። ውድመትና እልቂት ይከተላል። በተለይም ቀደም ባለው ጊዜ ዘመናዊ ሰራዊት ስላልነበረ፤ ሰራዊቱ የዕለት ቀለቡን የሚያገኘው ከሕዝቡ ነበር። አንዱ ወገን አሸንፎ አካባቢውን ሲቆጣጠርም፤ ዝርፊያና ውድመት የሚጠበቁ ክስተቶች ነበሩ። በጦርነቱም አምራች የሆነው የኅብረተሰብ ክፍል ያልቃል። ኀዘንና ሰቆቃ የሕጻናትን፤ የእናቶችንና የአዛውንቶችን ቅስም ይሰብራል።

ተከትሎም ሰው ሰራሽ የሆነ ወረርሽኝ ሲከሰት፤ ያልበላ አንጀት ሊቋቋመው ስለማይችል ብዙ ሕይወት እንደቅጠል ይረግፋል።

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ አጼ ዮሐንስ በጎጃም የደረጉትን ዘመቻ ተከትሎ ትልቅ ረሃብ ተከስቶ እንደ ነበር ታሪክ ይጠቅሳል። በጣም ብዙ ሰው ያለቀበት የ1976ቱ ረሃብም አንዱ ምክንያት፤ በትግራይ ሲካሄድ የነበረው ጦርነት ነበር። የኢትዮጵያን የመካከለኛው ዘመን ታሪክን ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመረምርም፤ ጦርነትን ተከትለው የተከሰቱ ረሃቦች ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም።

የእርስ በርስ ጦርነት ከድርቅ ጋር እየተመሳቀለ፤ ሕዝብን ለረሃብ የሚዳርግበት የታሪክ አዙሪት መበጠስ ይኖርበታል። በሀገራችን እርስ በርስ ጦርነቶች በዋናነት ብሔርተንነትን፤ አውራጃዊነትን እና ሃይማኖትን መሠረት አድርገው ሲከሰቱ ኖረዋል። በተለይም በቅርብ ጊዜ የሀገራችን ታሪክ ውስጥ የብሔር አክራሪነት እያየለ በመምጣቱ፤ በቂ መነሻ የሌላቸውና ከዘመናዊ የሰው ልጆች  አኗኗር ጋር የሚጣረሱ፤ የእርስ በርስ ጦርነቶች ውድመቶቸና እልቂቶች ተከስተዋል።

የውጭ ወራሪዎችን አሳልፎ በመመለስ የሚታወቀው ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በጀግንነቱ ያገኘውን ሀገራዊ ኩራት በእርስ በርስ ጦርነት እያጣው ነው። ጠላቶቹን በብርቱ ክንዱ በአንበረከከ ማግስት እርስ በርስ በሚፈጠረው ግጭት ምክንያት አምርቶ መብላት የማይችልበት ሀገራዊ ኀፍረት ገጥሞታል። በጀግንነቱ ያገኘው ሀገራዊ ኩራት፤ በረሃብ ምክንያት በደረሰበት ሀገራዊ ኀፍረት እየተጋረደበት ነው። በዓለም ፊት በኩራት የምንቆም የአድዋ ልጆች፤ ክፍ ቀንን መሻገር እየተሳነን አንገታችንን አቀርቅረናል። ብሔራዊ ኩራታችንን ሀገራዊ ኀፍረታችን ፈትኖታል።

ክብራችንን ማስመለስና ምሉዕ ሀገራዊ ኩራትን መላበስ የመጪው ትውልድ መለያ ሊሆን ይገባል። ሰራዊታችን የሀገራችንን ክብርና ጥቅም ለማስከበር በየሸንተረሩ በጀግንነት ሲፋለምና ሲዋደቅ፤ ሌሎቻችን ተመካክረንና ተስማምተን በመሬታችን ላይ የልማት ተአምር ካልሰራንበት፤ ሀገራችንን ወደ ከፍታ መውሰድ አስቸጋሪ ይሆናል። ሰራዊታችን በጀግንነት ሀገሩን ሲያስከብር፤ ሌሎቻችን በአጉል ጀብደኝነት ለሕዝባችን ስቃይና መከራ የምናመጣ ከሆንን፤ ጉዟችን ‹‹በባሕር ዝንጀሮ፤ በገደል ላይ ዓሳ ይሆናል። መጪው ትውልድ ከወንድሞቹና ከተፈጥሮ ጋር በመታረቅ፤ በጥጋብና በመትረፍረፍ የምትታወቅ ኢትዮጵያን ለመፍጠር፤ ታጥቆ ሊነሳ ይገባል።

ጀብደኝነትን በወንድማማችነት መተካት ሀገርን ለጠላት አሳልፎ ከሚሰጥና ለረሃብና ለችጋር ከሚያጋልጥ ቁርሾ ይታደገናል። መቁረጥና መንቀልን በመትከልና በማሳደግ ተክቶ ለምለሚቷን ኢትዮጵያ እንደ ስሟ ለምለም ማድረግ አይሳነንም። እነዚህን ሁለት የቤት ስራዎችን በማከናወን የረሃብ ታሪካችንን ለመቀየር ትልቁን ድርሻ ይወስዳል። ለረሃብ ተፈጥሯዊ መነሻ የሆነውን ድርቅ በተፈጥሮ ክብካቤና በደን ልማት፤ ሰው ሰራሽ የሆነው ጦርነትን ደግሞ በጥልቅ የውይይት ባህል መተካት ከቻልን ዋናው ችግር ተቃለለ ማለት ነው።

በየአካባቢው በጀብደኝነት እየተነሱ ምላጭ መሳብና የኢትዮጵያን ሕልውና መፈታተን፤ የገዛ ሕዝባችንን

ለማስራብ ካልሆነ ምን ይፈይዳል? በዘመናዊ ታሪካችን በሰሜን ኢትዮጵያ በተከታታይ በተደረጉ ጦርነቶችና ግጭቶች፤ ሕዝባችን ከረሃብና ከኀፍረት በስተቀር ምን አተረፈ? ድርቅና ጦርነት የ1976ቱ ረሃብ ፈጥሮ ሕዝብ ሲፈጅ የተመለከተ ትውልድ፤ ያንኑ ስህተት ለመድገም አለመሳቀቁ እጅግ አስገራሚና አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ለአካባቢዬና ለብሔሬ እታገላለሁ የሚሉት ልሂቃን ጥንትም ትናንትምዛሬም ሕዝቡን ከችግርና ከመከራ ሊታደጉት ቀርቶ ለትንሽ እፎይታ እንኳን አላበቁትም።

መጪው ትውልድ እርስ በርስ ከሚደረግ ባዶ የጀብደኝነት ፉክክር ወጥቶ፤ በጋራ እየመከረ ኢትዮጵያን ከረሃብ ያመለጠችና፤ የረሃብ ምስሏን ቁልቁል የገለጠች ሀገር ሊያደርጋት ይገባል። የረሃብ ምስልን ቁልቁል መገልበጥ ማለት ጥጋብን ማምለጥና በቂ ምርት ማምረት ብቻ አይደለም። ሁኔታውን ፈጽሞ የተገላቢጦሽ በማድረግ፤ ኢትዮጵያን በጥጋብና በምርት መትረፍረፍ የምትታወቅ ሀገር ማድረግ ማለት ነው። ይኸ ሲሆን የትውልዱ ሀገራዊ ክብር ማንም ስቦ ከማያወርድበት ማማ ላይ ይሰቀላል። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንም በብሔራዊ ኩራት መንበር ላይ እንዳይነቀነቁ ሆነው ይቀመጣሉ።

ጀብደኝነትና ድርቅን አጥፍተን በሙሉ አቅማችን ወደ ምርት ለመግባትና የዳቦ ቅርጫት የሆነች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የሚያስፈልገን አንዱ ዋና ጉዳይ ያለንን በአግባቡ የመጠቀም አስተሳሰብን ማዳበር ነው። የመሬት ሽሚያ የሚመነጨው ከጀብደኝነቱ በተጨማሪ ያለንን በአግባቡ ካለማወቅና ካለመጠቀም ችግራችን ነው። ኢትዮጵያን የምታክል ሰፊ ሀገር ይዘን እንደ ደም ስር በመላ ሰውነቷ በሚያረሰርሱ ወንዞች ተከብበን ደጃችንን ሳናለማና ሳናመርት ለመሬት ሽሚያ የምናደርገው ሽኩቻ ከፍተኛ የእጦትና የእጥረት እሳቤ ውጤት ነው። መቼ አምርተንበት ነው መሬት ያነሰንና ለመሬት የምንሻኮተው? ምርታችንን የቀነሰው በሽሚያና በልፊያ የምናሳልፈው ጊዜ እንጂ የመሬት እጥረት መች ሆነና።

መጪው ትውልድ ይኸን የእጥረትና የእጦት አስተሳሰብ ተሻግሮ፤ የማያለማውን መሬት ሲሻማ ዘመኑን ከሚገፋ ይልቅ የቆመበትን መሬት በአግባቡ የመጠቀም ልማድ አዳብሮ ከራሱ ተርፎ ለሌሎች ለማካፈል የሚተጋ የመስጠት ትውልድ እንዲሆን እንፈልጋለን። መጪው ትውልድ አካባቢውን በማልማትና በረከቱን በመቁጠር የሚታወቅ ከቤቱ ጀምሮ ያለውን ተጠቅሞ ሕይወቱን ለመቀየር በእጅጉ የሚተጋና ወደ ውስጡ ጠልቆ በመመልከት መፍትሔውን የሚፈልግ ትውልድ መሆን ይኖርበታል።

የዚህ ትውልድ ኢትዮጵያ ጾሙን የሚያድር መሬትና በከንቱ የሚፈስስ ወንዝ ሊኖራት አይገባም። መሬት ጾም ካላደረ፤ ወንዝ በከንቱ ካልፈሰሰ ደግሞ፤ የሰው ልጅ ጾሙን አያድርም። መሬት ጾሙን ሲያድር ወንዝ በከንቱ ሲንጀረጀር ነው እኛ ጾም የምናድረው።

መጪው ትውልድ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የመኖርን የሕይወት ዘይቤ በመልመድ ከተፈጥሮ ጋር የተሰናኘ ይሆናል። ገጠሮቻችን ከከተማ ሕይወት የራቁና ዘመናዊነትን በሩቁ የሚመለከቱ ሳይሆኑ ማንኛውም ሰው የሚኖርባቸው ምቹ ስፍራዎች ሊሆኑ ይገባል። ገጠርም ከተማም መኖር እንደየሁኔታው የሚመረጡ የሕይወት ዘይቤ አካል ናቸው። ገጠር መኖርና መስራትን እንደ መስዋዕትነት ሳይሆን እንደ ጸጋ የሚቆጥር ገጠርም

ከተማም እንደ ሁኔታው የሚኖር ገጠርንና ከተማን እያስታረቀ የሚሄድ ትውልድ ልንፈጥር ጊዜው አሁን ነው፡፡

ይኸ ሁኔታ ገጠሮችን ከተማ ከማድረግ የዘመናዊነት ተለምዷዊ ዝንባሌ ይልቅ ከተሞችም የገጠርን መልካም ጎኖች እንዲወርሱ መንገድ ይከፍታል፡፡ የገጠር አካባቢዎች የከተማን መልካም ጎኖች እንዲወርሱ ሆነው የገጠር ከተማነትን ተላብሰው በጊዜ ሂደት እየተሰናሰሉ የሚቀራረቡበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በዚህ ሂደትም ከራሱና ከምንጩ ከታሪኩና ከወገኑ ጋር የታረቀ ትውልድ ይገነባል፡፡ አምራችነትና ምርት የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ጉልህ መገለጫ ይሆናሉ፡፡ በደሙም በላቡም ጀግንነቱን የሚያስመሰክር ትውልድ ይኖራል፡፡ ይኸ ሲሆን የሚፈጠረው ትውልድ የማንነትና የባለቤትነት ቀውሱን የፈታ ከውስጡና ከዙሪያው ከሌሎችና ከአካባቢው የተስማማ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## የትውልድ ልዕልና - ምናባዊ

## ዕውቀትና ሥነ ምግባራዊ ሕይወት

# ከአክሊሉ እንዶድ ሥር

ለአንድ ሀገር ብልጽግና መሠረታዊ ከሚባሉት ጉዳዮች አንዱ በዕውቀት ላይ የሚኖር የበላይነት ነው። ዕውቀት እንደማንኛውም ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ሀብት ሁሉ በክንደ ብርቱዎች ቁጥጥር ስር የመዋሉ ነገር ለኃያላኑ የበለጠ ጉልበት ይሰጣቸዋል።ላላደጉትም በፍጥነት እንዳያድጉ መሰናክል ይሆንባቸዋል።

ፕሮፌሰር አክሊሉ ለማ ለብዙ አመታት በእንዶድ ዙሪያ ባደረጉት ምርምርና ውጤቱንም ለአለም ለማስተዋወቅ በተጓዙበት መንገድ የገጠማቸውን ሲያስቀምጡ ‹‹በአፍሪካ ለሚደረጉ ምርምሮች ዋና እንቅፋቶች ለምርምር አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችና የበጀት እጦት ብቻ ሳይሆኑ በኢንዱስትሪ በበለጸጉ ሀገራት የሚገኙ ግለሰቦችና ድርጅቶችም ጭምር መሆናቸውን በፈተናዎቻችን ተምረናል›› ብለዋል። የበለጸጉት ሀገራት በአንድ በኩል በማንኛውም ሁኔታ ላይ የሚኖርን መረጃ ከምንጩ ለመቆጣጠርና የሰው ልጆችን አመለካከት በሚፈልጉት መንገድ ለመቅረጽ ይጠቀሙበታል። በሌላ በኩል ደግሞ የቴክኖሎጂ የበላይነት እንዲኖራቸው በማድረግ በኢኮኖሚና በፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች መሪውን ድርሻ እንዲይዙ ያስችላቸዋል። ሀገራት በእውቀት ላይ የሚኖራቸው የበላይነት፤ በፖለቲካም በኢኮኖሚም የበላይነት እንዲኖራቸው ዕድል የሚከፍትላቸው ይሆናል።

በዘመናችን ጉግልን (Google) የመሳሰሉ የዕውቀት መፈለጊያ ማሽኖች ፌስቡክን የመሳሰሉ የማኀበራዊ ትሥሥር ገጾችና መሰል የዕውቀት ምንጮች በጥቂቶች ቁጥጥርሥር መዋላቸው ሰዎች ማወቅ ያለባቸውንና የሌለባቸውን እነዚሁ ጥቂቶች እንዲወስኑላቸው አድርጓል። በእነዚሁ ማሽኖች ላይ የምናገኘው ዕውቀት መጠኑም ሆነ ዓይነቱ የሚወሰነውም፤ ማሽኖቹን በሚቆጣጠሩትና ለማሽኖቹ ዕውቀት በሚመግቡት ተቋማት ባለቤቶች ላይ ነው። ምን ማወቅ እንዳለብንና እንደሌለብን የትኛው መረጃ እንደ እውቀት እንደሚቆጠር፤ የትኛው መረጃ በሰፊው መሰራጨት እንዳለበት የሚወስነው፤ አስቀድሞ በዕውቀቶቹ ምርትና ገበያ ላይ የበላይነት ያለው አካል ነው።

ለምሳሌ የአንድን ነገር ብያኔ ማወቅ ብንፈልግ፤ ልናነብና ልንሰማ የምንችለው በእነዚህ ማሽኖችና የዕውቀት ተቋማት የሚሰጠንን ብያኔ ነው። ከዚያ ውጭ የሚኖር ብያኔ የአቅርቦቱም የሥርጭቱም መጠን ዝቅተኛ ስለሚሆን፤ ለብዙኃኑ ተደራሽ አይሆንም። ይኸ ሁኔታ በተለይም በፖለቲካው ረገድ የሚኖር አመለካከትንና አስተሳሰብን ከአንድ ወገን እንዲቀረጽ የሚያደርግ ነው። በቴክኖሎጂው የበላይ የሆነ አካል የፖሊቲካ አስተሳሰቦችንና መረጃዎችን በበላይነት ማሥረጽ የሚችልበት ዕድል ከፍተኛ ነው።

በኢኮኖሚው በኩል ስንመለከትም፤ የበለጠ ዕውቀትን በበላይነት ለተቆጣጠሩ ወገኖች ያደላ ሆኖ እናገኘዋለን። በተለይም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚኖር የዕውቀት የበላይነት፤ በአጠቃላይ የኢኮኖሚ የበላይነትን እየረጋገጠ ስለሚመጣ፤ በዕውቀት ዘርፍ ተወዳዳሪ ያልሆነ ሀገር፤ ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ስኬት አይቀዳጅም።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በዕውቀት ዘርፉ ተወዳዳሪ ሆና እንድትወጣና፤ በውጤቱም ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ስኬት ለማስመዝገብ ትውልድ በዕውቀት ታንጾ እንዲያድግ ማድረግ ይኖርብናል። ከኢኮኖሚያዊና ከፖለቲካዊ

ጥገኝነት በጉልህ ደረጃ መላቀቅ የሚቻለው የዕውቀት ጥገኝነትን በማስወገድ ከዓለም ተወዳዳሪ የሚያደርግ የዕውቀት ጉልበት ማፈርጠም ስንችል ነው። ለዚህም በማንኛውም ሁኔታ ሐሳብ ማፍለቅ የሚችል፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂዎችን መፍጠር የሚችል፣ በምርምር ባህል ውስጥ ያደገና ያለድጋፍ ሕልሙን በራሱ እውን የሚያደርግ ትውልድ መፍጠር ያስፈልጋል።

በሀገራችን በመንግስትና በግሉ ዘርፍ የተከፈቱ ከመቶ ያላነሱ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች በእነዚህ ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተማሪዎች ይገኛሉ። ይኸውም ለረጅም አመታት በአንድ ዩኒቨርስቲና በጥቂት ኮሌጆች ታስራ ለኖረች ሀገራችን ትልቅ ሀብት ነው።

ሆኖም የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን ዲግሪ ማምረቻ ፋብሪካዎች ከመሆን ነጻ ወጥተው የወጣቶቻችንን ምናብ መቀስቀሻ፣ ችግር ፈቺነትን መማሪያ፣ ምክንያታዊነትንና ፈጠራን መለማመጃ ሊሆኑ ይገባል። ተቋሞቻችን የሌሎች አፍሪካ ሀገራት ተማሪዎችን ተቀብለው የሚያሰለጥኑ ብቻ ሳይሆኑ ተመራቂዎቻቸው በየሀገራቱ ተበትነው በተማሩበት መስክ በመሥራት አዲሱን ትውልድ የዕውቀት መሪና የምናብ ተስፈንጣሪ ሊያደርጉት ይገባል።

በዓለም ላይ የኢኮኖሚና የፖሊቲካ መነቃቃቶች ሁሉ በቅድሚያ በሐሳብና በዕውቀት መነቃቃት ውስጥ የተተለሙ ናቸው። ትውልድ በዕውቀት ያልተነቃቃ ከሆነ፤ ቴክኖሎጂውም ሆነ ሌላ ማንኛውም ሐሳብ የማይጸናና የሚዋልል የማየቆምና የሚናድ ይሆናል። ለበጎ የተባለው ሐሳብም በትውልድ ብሩህ አእምሮ ላይ ካልተተከለ በአግባቡ አለመጽናቱ ብቻ ሳይሆን ጭራሹንም ያልታሰበ መጥፎ ውጤትን ሊያስከትልም ይችላል። የዚህ ትውልድ መለያው፤ የምናባዊ ዕውቀት ባለቤትነቱና የሥነ ምግባራዊ ሕይወት ልዕልናው ሊሆን ይገባል።

አሁን ባለንበት ዘመን በተለይም በሳይንስና በቴክኖሎጂው ዘርፍ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመውጣት እንደ በፊቱ ረጅም አመታትን መጠበቅና ደረጃ በደረጃ የሚፈጠርን የቴክኖሎጂ ክምችት ማዳበር የግድ አይልም። ሳይንስና ቴክኖሎጂ ያለበቂ የዕውቀትና የቴክኒክ ክምችት እንዲሁም ያለበቂ የኢንዱስትሪና የምርምር ተቋማት ልምድና እሴት በአግባቡ አይዳብርም። በዘመናችን ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ ይኸን ልምድ ማካበት የሚቻልበት ልዩ ሁኔታ ተፈጥሯል። ለዚህም የኢንተርኔት መፈጠርን ተከትሎ የመጣውን የዕውቀት መፈታትና እንደ ልብ መገኘት አንዱ ነው። ሌላው ደግሞ ሰፊ ቦታን የሚጠይቁና ብዙ ገንዘብ የሚያስወጡ መጻሕፍትና ሌሎች የመረጃና የዕውቀት ምንጮች በነጻ በሚባል ደረጃ በተጠቃሚ እጅ መግባታቸው ነው።

ሌሎች ለመፍጠር በአስርት ዓመታት የፈጀባቸውን ግኝቶች በምስል ምህንድስናና በተለያዩ ሌሎች ብልሐቶች፤ በአጭር ጊዜ ባለቤት የሚኮንበት መንገድ ተፈጥሯል። በዚህ ረገድ ሳይንስና ቴክኖሎጂውን በኩረጃ ቶሎ የማስረጽና በሌላ በኩል ደግሞ በፈጠራ ላይ የማተኮር የፖሊሲ አዝማሚያዎች በምሁራን ዘንድ ሲቀርቡ ይስተዋላል። ለፈጣን ኢኮኖሚያዊ መነቃቃትና በቶሎ ከቴክኖሎጂ ጋር ለመላመድ፤ ቴክኖሎጂን አስመስሎ መሰራት ወይም መኮረጅ የራሱ አዎንታዊ ጎን ቢኖረውም ጥልቅ መሠረት ያለው ሕዝብና ሀገር ለመገንባትና ዘላቂ ሀገራዊ ጥቅምን ለማስከበር ግን በዕውቀት ራስን መቻል እጅግ አስፈላጊ ነው።

በምርምርና በጥናት፤ በውይይትና በሙግት የሚዳብርን የዕውቀትና የሥልጣኔ ስሪት ሊተካ የሚችል አቋራጭ አለመኖሩን መረዳት ተገቢ ነው። በፖለቲካም ይሁን በኢኮኖሚ፤ በማኅበራዊም ይሁን በመልክአ ምድራዊ፤ በእያንዳንዱ አስተሳሰብ ውስጥ የዕውቀት አድማሱን አስፍቶ ራሱን ያልቻለ ሀገር ሁሌም የሌሎች አድናቂ ተቀባይና ሉዓላዊነቱ በሥጋትና በጥርጣሬ የተከበበ መሆኑ አይቀርም። የፈለገውን ያህል ጠንክሮ ቢወጣ በራሱ የዕውቀት ባለቤትነት ላይ ካልተመሰረተ በዓለም ላይ ተወዳዳሪና የራሱን ፍላጎት የሚያስከብር ሀገር መሆን በእጅጉ ይከብደዋል።

ስለሆነም በሳይንስም ሆነ በፖሊቲካው በቴክኖሎጂም ሆነ በፍልስፍናው የራሱን ኀብረተሰብ በጥልቅ ዕውቀትና በሐሳብ ምንጭነት ኮትኩቶ በራሱ እንዲቆም ማድረግ አስፈላጊ ነው። ለዚህ ደግሞ ዕውቀትን የሚያከብርና የዕውቀትን ዋጋና ትርጉም የተረዳ ትውልድ መፍጠር የግድ ይላል። አካባቢውን የሚመረምር የማወቅ ጉጉት ያለው፤ የአዳዲስ ሐሳቦችና ቴክኖሎጂዎች አፍላቂ የሆነ ትውልድ መገንባት ያስፈልጋል።

ለዚህ አንደኛው ቁልፍ ምሥጢር የትውልዱን ምናባዊ ተሰጥኦ በዕውቀት ኮትኩቶና አርሞ ማሳደግ ነው። ዘላቂነት ያለው የዕውቀትና የክህሎት ሀብት ለማዳበር ደግሞ በሥነ ምግባርና በትጋት የታነጸ ትውልድ መፍጠር አማራጭ የለውም።

አዲሱ ትውልድ ይኸን የዕውቀት ሰሪነትና አመንጪነት ሚና ይዞ በሁለም ዘርፎች ተወዳደሪ የዕውቀት ባለቤት መሆን ይገባዋል። ኢትዮጵያም አዳዲስ ሐሳቦች የሚፈልቁባትና እንደ ሌሎቹ ዘርፎች ሁሉ በእውቀት ዘርፍ ተወዳዳሪና ሉዓላዊነቷን የምታስከብር ሀገር እንድትሆን ከፍ ያለ ራዕይ ተቀምጧል። በዕውቀት ዘርፍ በራሱ መቆም የማይችል ሕዝብ ሁሉን ነገር ከሌላው በተውሶና በልመና ሊያሳካ ስለማይችል የሉዓላዊነት የመጨረሻ ምሽጉ በዕውቀት ራስን መቻል ብቻ ነው።

በኢኮኖሚና በፖለቲካው በውትድርናውና በሳይንሱ፤ በመሠረተ ልማቱና በማኅበራዊ አገልግሎት ዘርፉ፤ ሁሉ የሚኖሩን ስኬቶች በዕውቀት ላይ በሚኖረን ድርሻ ይወሰናሉ። ይኸንን የስኬቶች የወሳኝነት ድርሻ በእጅ ለመያዝ፤ መጪው ትውልድና አዲሲቷ ኢትዮጵያ የሐሳብ መነሻዎችና የፈጠራ መፍለቂያዎች መሆናቸው አማራጭ የለውም።

ይኸ ራዕይ እውን ይሆን ዘንድ ትውልድ በምርምርና በንባብ ተኮትኩቶ የሚያድግበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል። ትውልድ በየአካባቢው በማንበብ፤ በመጻፍና በመመርመር እንዲያድግና ብዙ ጊዜውን በዕውቀት ቁፈራ ላይ እንዲያልፍ በርካታ የንባብና የምርምር ተቋማት በነገዋ ኢትዮጵያ ውስጥ የተለመዱ ሊሆኑ ይገባል። የሳይንስና የቴክኖሎጂ ፈጠራ ቤተ ሙከራዎች የፍልስፍና የሐሳብ መለዋወጫና የጥበብ መከወኛ አዳራሾች በየትምህርት ቤቱና በየማህበረሰቡ መኖሪያ አካባቢ የተለመዱ እንዲሆኑ ማዳረስ ያስፈልጋል። በተለያዩ የዕውቀት ዘርፎች፤ ስለዕውቀትና ስለ ሳይንስ ረሃብን የሚያጭሩ የሳይንስ ሙዚየሞችና ሁለንተናዊ ማዕከላት፤ ከሕጻናት እስከ ጎልማሶች ሁሉን አቀፍ ሆነው በብዛት መገንባት አለባቸው።

የመደመር ፓራዳይም ሁልጊዜም ለአካባቢያችን ክፍት መሆንና ከአካባቢያችን መማርን ተመራጭ ያደርጋል። አዲስ ነገር ለመማር ጉጉ በመሆን ከሌሎች ልምድ ለመቅሰም ዝግጁነት ከሌለ ለውጥ እውን ሊሆን ይችላል

ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው፡፡ በቆሞ ቀርነት ደጅን ዘግቶ መቀመጥ ራስን አይለውጥም፡፡ ሀገርንም ለሚለውጥ ዓላማ ዝግጁ አያደርግም፡፡ ስለሆነም ሁልጊዜም ለመማርና ለማወቅ ዝግጁ የሆነ ትውልድ መፍጠርና የማወቅ ጉጉት በኅብረተሰባችን ማኅበራዊና ባህላዊ ክዋኔ ውስጥ ትልቅ ድርሻ እንዲኖረው ማድረግ ይገባናል፡፡

አዲስ ሐሳብን ለማወቅና ለመረዳት ዝግ የሆነ ዕይታ ለለውጥና ለዕድገት ትልቅ መሰናክል መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ ብዙ ፖለቲካዊ እሳቤዎቻችንን በቶሎ እያሻሻልናቸው ያልሄድንበት አንዱ ምክንያት አዲስ ነገር ለማወቅና ራስን እየቀየሩ ለመሄድ ያለብን እምቢተኝነት ነው፡፡ በግለሰብ ደረጃ ለለውጥ፤ ለአዲስ አስተሳሰቦችና ልምምዶች ዝግጁ ከሆንን ተቋሞቻችንም ሆነ በአጠቃላይ ሀገራችን ወደ ሁለንተናዊ ለውጥና እመርታዊ ዕድገት ይራመዳሉ፡፡ አዳዲስ ሐሳቦችንና ዕቅዶችን ለመተግበር ፈተና የሚሆንብንን የዝግነትና የዝገት ባህል አስወግደን ለፍሬያማ ሐሳቦች ፍለጋና ሥርጸት ክፍትና ዝግጁ መሆን ይኖርብናል፡፡

ዕውቀትን የሚያከብር ባህል ለመገንባት በሐሳብ የበላይነት ማመንን ይጠይቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሰው ልጆች እድሜ ልካቸውን ተማሪዎች እንደሆኑ ከመገንዘብ የሚመነጭ ነው፡፡ ዕውቀት በትምህርት ቤቶች ብቻ የሚገበይ አለመሆኑን፤ የሰው ልጅ ከሚያውቀው ነገር የማያውቀው በእጅጉ የበዛ መሆኑን መገንዘብና እያንዳንዱ ሐሳብ ሁልጊዜም ሌላ ተፎካካሪ ሐሳብ እንዳለው መረዳት ይገባዋል፡፡ በአንድ ወቅት የሚሰራ ሐሳብ በሌላ ጊዜ ፋይዳ ቢስ ሊሆን እንደሚችል ተገንዝቦ፤ ያለማቋረጥ አዲስ ሐሳብን ለማድመጥና በምክንያታዊነት ለመቀበል ዝግጁ የሆነ ትውልድ መፍጠር አለብን፡፡

በጊዜ ሒደት የሚኖርን የሕዝብ ዕይታና የአኗኗር ለውጥ በቀላሉ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ለዓለም ሥርዓት አዝማሚያንና ለውጥን ጊዜ ሳያባክኑ መገንዘብና ከአዳዲስ እሳቤዎችና የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች ጋር በጊዜው መተዋወቅ የዕውቀት ደጅን ከፋች ነው፡፡ በዓለም ላይ የተከማቸና በአንድ የሕይወት ዘመን ተዝቆ የማያልቅ ዘርፈ ብዙ ጥቅል እውቀት አለ፡፡ በየጊዜው በሚፈጠረው አዳዲስ የዕውቀትና የመረጃ ጎርፍ የተነሣ፤ ያለውን ዕውቀት ሁሉ የራሱ ለማድረግና በካዝና ቆልፎ ለማስቀመጥ ከማይቻልበት ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡ ለዚህ ፍቱን መድኃኒቱ የተሳለ ምናብና የእውቀት ለውጥን መምራት የሚችል፤ ተለጣጭ ሥርዓትን የሚገነባ ትውልድን መፍጠር ነው፡፡ ምናባዊ ዕውቀቱን የገነባ ትውልድና ሥርዓት የ21ኛው መክዘ ተወዳዳሪና መሪ ሆኖ፤ በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ በኩራት መቆም ይችላል፡፡

እንደ ማንኛውም ሀብትና የተጽዕኖ ምንጭ፤ እውቀት ከፍተኛ ኃይል በውስጡ የታመቀ ጉልበት አለው፡፡ ኃይል በበዛ መጠን ደግሞ የሞራል ውድቀትና የሥነ ምግባር ንቅዘት አደጋ ከፍ ብሎ ይኖራል፡፡ ሀገራችን ከድህነት ወደ ብልጽግና፤ በኋላ ቀርነት ወደ ዕውቀት መሪነት መለወጧ አይቀሬ ነው፡፡ ይኸ እውን ከሆነ በኋላ የዕውቀት ልዕልናዋን አስከብራ መቀጠል እንድትችል በአስተሳሰቡና በግብሩ ልዕልና ያለው ሕይወት የተላበሰ ትውልድ ልንፈጥር ይገባል፡፡

የምዕራቡን ዓለም ሥልጣኔ መሪዎችና አዳጊ ሀገራትን እንዲሁም በፍጥነት ወደ ሉላዊ ልዕለ ኃይልነት እየተስፈነጠሩ ያሉትን ምሥራቃውያንን እያሠጋ ያለው ፤እየተፈረካከሰ ያለው የሞራል ልዕልናና የሥነ ምግባር

ልልነት ነው። በሀገራችንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በገሐድ እየታየ እንዳለው፤ ሌብነትና ዓይን ያፈጠጠ ዝርፊያ፤ ጭካኔና አውሬያዊ ባሕርይ፤ ስንፍናና የምናገባኝ ግዴለሽነት፤ ግለኝነትና የማይጠረቃ ስግብግብነት፤ ከቁጥጥር ውጪ እየሆነ ነው። ከፍተኛ የሆነ የህሊና ግሸበትና የሞራል ድቀት በወረርሽኝ ደረጃ እያጥለቀለቀን ነው። በዚህ ሞራላዊ ቁመና ብልጽግናና ሰላም፤ ሀገራዊ እመርታና ትውልዳዊ ተሐድሶ የማይታሰብ ነው። በአፋጣኝ የትውልዱን ህሊና ማደስና የሕዝባችንን ሞራላዊ ቁመና ወደ ስፍራው ልንመልስ ይገባል።

ለዚህም ከቤተሰብ እስከ ቤተ እምነት፤ ከትምህርት ቤቶች እስከ የጥበብ ቤቶች፤ ከሕግ ማስከበር ተቋማት እስከ ሚዲያ ተቋማት ድረስ፤ በተናጠልና በመናበብ የሀገራችንንና የትውልዱን የሞራል ደረጃ፤ ከወደቀበት በማንሳት፤ በፍጥነት እንዲያንሰራራ ሊያደርጉ ይገባል። ይኸውም በምሳሌነት፣ በማስተማር፤ በማደፋፈርና በተጠያቂነትም ሊፈጸም የሚገባው አጣዳፊና ምትክ ሌለው ስራ ነው።

ስንፍናን በትጋት፤ ግዴለሽነትን በባለቤትነት ስሜት፤ ሌብነትን ጠንክሮ በመሥራት፤ ስግብግብነትን ለሌሎች በማካፈል ልንለውጣቸው ይገባል። በሌብነት የበለጸጉ ሰዎች ስራቸው በአደባባይ አሳፋሪነቱ ተገልጦ አንገታቸውን ሊደፉ ይገባል። ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን የማይወጡ ስግብግቦች ያለ ማኅበረሰቡ ምንም መሆናቸውን ሊገነዘቡ ይገባል። ለሌሎች የሚኖሩ፤ በታማኝነት የሚሰሩና ሀገርን ለመለወጥ ቀን ከሌት የሚታትሩ ደግሞ ሊመሰገኑ፤ ሊሞገሱና በሕዝብ ታላቅ ዕውቅና ሊሰጣቸው ይገባል።

ተፈጥሮንና አካባቢን የሚንከባከቡ፤ ያለአድልዎና ያለወገንተኝነት ለአንድነትና ለኀብረ ብሔራዊ ማንነት የሚተጉ፤ ከሀገራቸው አልፈው አፍሪካዊነትን በተግባር የሚኖሩ ወጣት ኢትዮጵያዊያን ከተደበቁበት ወጥተው እንዲያበሩ ማደፋፈር ያስፈልጋል። ምናባዊ ዕውቀታቸውን በሥነ ምግባራዊ አኗኗራቸው ለማሳየት የቻሉ ኢትዮጵያዊያን፤ የነገዩቱ አፍሪካ መሪ ሆነው የሚወጡበት ጊዜው አሁን ነው። መጪው ትውልድ አፍሪካን በችሎታ ብቃትና በባህሪይ ጥራት እየመራን ሀገራችን በዓለም መድረክ ላይ ቀና ብላ እንድትራመድ የሚያደርግ ሊሆን ይገባዋል።

# ምዕራፍ ስድስት

## የትውልድ ትሩፋት - ዘመን

## ተሻጋሪነትና ድንበር የለሽነት

# ዘመን ተሻጋሪነት

# ‹‹ለምን ኢየሩሳሌም?››

የበዓለ ሲመት ንግግሬ ላይ ‹‹እኛ እድለኞች ነን፤ ውብ ሀገር አኩሪ ታሪክ አለን›› የሚል ሐሳብ አንስቼ ነበር። የሀገራችን ውበት ሐብት ነው። ልንጠብቀው ልንከባከበው የሚገባ፤እንደ ሌሎቹ በክረምት ሙቀትን ፍለጋ ድንበር ተሻግረን መሄድ የማይጠበቅብን፤ በበጋ ሙቀቱን አማርረን እንድንሸሽ የሚያደርግ የአየር ንብረት የሌለባት ሀገር ባለቤቶች ነን። በደጃፋችን አስደናቂ ታሪክ፤ ቀልብ ገዥ የሥልጣኔ ትሩፋቶችን ለመመልከት የታደልን ነን። ድንቅ ባህልን ከየጎረቤቶቻችን የምንታደም፤ ባለብዙ ኅብረ ቀለማት ሕዝቦች በመሆናችን ዕድለኞች ነን።

ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ተፈጥሯዊ፤ ባህላዊና ታሪካዊ መስሕቦችን የሰው ልጆች ሁሉ ሀብት ስለሆኑ ይመዘግባቸዋል ይጠብቃቸዋልም ። የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፤ የሳይንስና የባህል ድርጅት ዩኒስኮ፤ እንደ አላማ ይዞ ከሚንቀሳቀስባቸው ዐበይት ጉዳዮች መካከል፤ እነዚህን የዓለም ውበትና ትሩፋት መገለጫዎች የሆኑ ተፈጥሯዊ፤ ባህላዊና ታሪካዊ መስሕቦችን በመጠበቅና በማቆየት ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ ነው።

ዓለም ሁሉ ውበትን ለመጠብቅ ኅብረት ፈጥሮ በሚንቀሳቀስበት ዘመን፤ እኛ ውብ ሀገር እንደማይገባን ቆጥረን የምናነሳቸው ሙግቶች ገራሚና አሳፋሪ ናቸው። በአዲሱ የለውጥ ሂደት ውስጥ፤ዜጎች የሚያርፉባቸው፤ የሚዝናኑባቸውና የሚሰሩባቸው ውብ ሥፍራዎችና መሥሪያ ቤቶች ተገንብተዋል። በእነዚህና በመሳሰሉ ሥራዎች ላይ ከሚነሱ ጥያቄዎችና ከሚወረወሩ ነቀፋዎች መካከል፤ ‹‹ሌሎች ጉዳዮች ለምን አይቀድሙም? ሀገር ሰላም ሳይኖራት ከተማ ማስዋብ፤ ቢሮ ማሣመር ምን ያደርጋል?

ሰው በየቦታው እየተጫረሰ ችግኝ መትከልና ሀገርን አረንጓዴ ማድረግ ምን የሚሉት ልማት ነው?›› የሚሉና የመሳሰሉት ናቸው።

በአብዛኛው ይኸን የሚሉና የተባለውን በየዋሕነት ተቀብለው የሚያስተጋቡ ዜጎች፤ ቀና አመለካከትና የዋሕ ልቦና ያላቸው ናቸው። የአንዱን መኖር ለሌላው መንስኤ አድርገው የተረዱም አይጠፉም። ትልቁ ነገር የሀገራችን የግጭትና ድህነት፤ የጭካኔና የሌብነት ምንጩ፤ የደረቀ አስተሳሰብና የቆሸሸ ሕሊና ያስከተለው መሆኑን ካለመረዳት የሚመጣ ነው። አካባቢን ለመቀየር ውስጠ ማንነትን መቀየር አስፈላጊ እንደሆነው ሁሉ፤ ውስጠ ማንነት የሚለወጠው ደግሞ አካባቢን መሠረታዊ በሚባል ደረጃ በመለወጥ ሂደት ውስጥ ሲታለፍ ብቻ ነው። ‹‹ሰው ቦታን፤ ቦታም ሰውን ይቀድሰዋል›› የሚባለውም ለዚህ ነው።

አካባቢውን የሚያለመልም ሰው የውስጡን ድርቀት መጋፈጡ አይቀርም። በንጹሕና በቂ ብርሃን ባለው ቢሮ ውስጥ የሚሰራ ሰው ከተለመደው ለተራ ስርቆትና ስንፍና ራሱን አሳልፎ ከመስጠት ይልቅ፤ በታታሪነትና በፈጠራ ስራውን ለመስራት ይነሳሳል። የእጽዋትና የእንሰሳትን ሕይወት መንከባከብ የጀመረ ሰው እንደርሱ

ባለ ክቡር ሰው ላይ እጁን በክፋት ከመዘርጋት ይልቅ፤ በደግነት ያለውን ለማካፈል ልቡ እንደሚነሳሳ እሙን ነው፡፡

ብዙዎች በሕይወታቸው ውስጥ የውብና ጽዱ ነገርን አስተዋጽኦና፤ ለውብና ለጽዱ ነገር ሊኖራቸው የሚገባውን ቦታ ገና አላስተዋሉም፡፡ ማንም ጤነኛ የሆነ ሰው ካለው ላይ ቀንሶ በዐቅሙ የጸዳ መልበስና በአማረ ቤት መኖር የሚጠላ የለም፡፡ ከፍ ሲልም፤ ጽዱና ውብ በሆነ መሥሪያ ቤት መሥራትንና፤ በተዋበ ከተማ መኖርን እንደ ቅንጦትና እንደማይገባ ትርፍ ነገር መመልከቱ አስገራሚ ይሆናል፡፡ ጓሮው ለምና አረንጓዴ እንዲሆንለን የሚመኝ ሰው፤ ከተማውና ሀገሩ ስትለማ ሲያይ፤ እንዴት የቅንጦት ነገር ይመስለዋል? ሀገር በሚገባ የተጠበቀች፤ውብና ለኑሮ ተስማሚ እንድትሆን ፍላጎት ብቻ ሳይሆን፤ ከትውልድ የተቀበልነው የአደራ ግዴታም ጭምር በመሆኑ፤ ጠዋትና ማታ ተግተን መጠበቅና ማስፋፋት አለብን፡፡

ለምሳሌ በሀገራችን ቀደምት ትቅልድ ዘንድ ቀልብን ሳቢ የነበረችው ጃፓን፤ ለተፈጥሯዊ፤ ለታሪካዊና ለባህላዊ ሀብቶቿ ልዩ ቦታ ትሰጣለች፡፡ የራሷን ቀለምና የባህል ዐሻራ ሳትለቅ ዘመናዊነትን የተቀበለችው ጃፓን፤ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ ቀዳሚ በሚባለው ትውልድ ዘንድ፤ ትልቅ መነሳሻና ሞዴል ሆና ትታይ ነበር፡፡ እውነትም ጃፓንን ጎብኝቶ ላስተዋለ፤ አሁንም ቢሆን ብዙ ቅናት የሚያጭሩ፤ ዘመናዊነትን ከባህልና ከቀደምት ታሪክ ጋር ያጣጣሙ ውበቶች በየስፍራው ይታያሉ፡፡ የከተሞቹ ጽዳትና አረንጓዴነት፤ በሌላ አካባቢ የማይታይ የራሷ ለየት ያለ ጃፓናዊ ውበት ተጨምሮባቸው ድንቅ ውበትን ፈጥረዋል፡፡

ሀገሪቱ በቴክኖሎጂ ዕድገት፤ዘመናዊ በሆኑ ሕንጻዎች፤ በባቡር መሥመር ዝርጋታዎችና በሌሎች ጉዳዮች፤ ከዓለም ቀዳሚዎቹ ተርታ የምትሰለፍ ናት፡፡ ነገር ግን ይኸ ዘመናዊነት የጃፓን ተፈጥሯዊና ታሪካዊ ውበት ተክቶ የበቀለ ሳይሆን፤ ከባህሏ ጋር ተሰናኝቶ ድንቅ ኀብርን የወለደ ነው፡፡

ከተሞቿ እጅግ ጽዱና አረንጓዴ ከመሆናቸውም ባሻገር፤ የታሪክና የባህል ግጭት ወይም ጥንታዊውን ከዘመናዊው የሚያጋጭ ረብሻ የለባቸውም፡፡ የዚህ ውበት ምንጮች የመንግስት ፖሊሲ ትግበራና የመንግስት ልማት እንቅስቃሴ ብቻ አይደለም፡፡ በዋናነት የኀብረተሰቡ የኃላፊነት ስሜት ነው፡፡ ‹‹ይኸ የእገሌ ኃላፊነት ነው፤ ያ ሰው መጥቶ ይስራው›› ከሚል የተንሸዋረረ አካሄድ ይልቅ፤ ‹‹ይኸ የጋራ ሀብታችንና የጋራ ከተማችን ስለሆነ፤ በጋራ እንጠብቀዋለን›› የሚል ባህልን ጃፓኖች አዳብረዋል፡፡

ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ ተማሪዎች ጽዳትን የሚማሩበት ሰዓት አላቸው፡፡ ከምሳ በኋላ ሁሉም ተማሪ ትምህርት ቤቱን በጋራ ያጸዳል፡፡ ይኸም ተማሪዎች የጽዱ ትምህርት ቤትና የጽዳት ባህል ባለቤት ብቻ ሳይሆኑ፤ እንደ ትውልድም የአልጋይነትና ውብ የሥራ ባህል ተቀርጾባቸው እንዲያድጉ ያደርጋል፡፡ ይኸ የጃፓኖች ሥነ ሥርዓት በሕዝብ ዘንድ የኃላፊነትን ስሜት የሚፈጥር፤ እንዲሁም በጃፓን ጎዳናዎች ለሚታየው ውበትና ሰላማዊ እንቅስቃሴ መሠረት ነው፡፡

የጃፓን ሕዝብ ከራሱ ታሪክ አልፎ ለሌሎች ሀገራት ታሪክ የሚሰጠውን ቦታ ለመገንዘብ፤ ጀግናው አበበ ቢቂላ በጃፓናውያን ዘንድ ያለውን ቦታና የሚሰጠውን ክብር መመልከት በቂ ነው፡፡ ወደ ጃፓን የሚሄድ ኢትዮጵያዊ የሀገሩን ልጅ ታሪክ ከጃፓኖቹ አንደበት ያደምጣል፡፡ ይኸ ድንቅ ጉዳዮችን ለትውልድ ቀርጾ የማስተላለፍና

ጠብቆ የማቆየት ልማዳቸው፤ የጃፓንን ታሪክ ውበቱን ጠብቆ አሁን እንደተከወነ ያህል ልዩ ስሜት እንዲሰጥ አድርጎታል፡፡የታሪክ፤ የኪነ ጥበብና የሳይንስ ሙዚየሞችና አውደ ርዕዮቻቸው፤ ሕዝብን ከቀደመውና ከመጪው ጋር የሚያስተዋውቁ ሆነው፤ በየስፍራው በብዛት ይታያል፡፡

ውበት የሀገራት ልማትና ሀብት አካል ነው፡፡ የተባበሩት ዓረብ ኢምሬቶች ውበትን ወደ ሀብት ቀይረውታል፡፡ በበረሃው ላይ ብዙ ሀብት በማፍሰስ ሰዎች ለማየት የሚመኙትን ገነት የሚመስል ተናፋቂ ሥፍራ ፈጥረዋል፡፡ ሀገሪቱ ያላት የነዳጅ ሀብት ትልቅ ዐቅም የሚሰጣትና ዜጎቿም የተደላደለ ኑሮ እንዲኖራቸው የሚያደርግ ቢሆንም የመሪዎቻቸው የላቀ ምልከታ ግን ከነዳጅ ባሻገር ያለ ሀብትን ለመፍጠር አትግቷቸዋል፡፡ ኤምሬትስ ለዜጓቿ የተሻለ ውብ ሀገርን ፈጥራለች፡፡ ይኸም ለኢኮኖሚው ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ሆኖላታል፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ የተፈጠሩት ታላላቅ ሆቴሎችና የገበያ ማዕከላት፤ የመኖሪያና የሥራ ቦታ የሆኑ ቅንጡ ሕንጻዎች፤ የትራንስፖርት ቴክኖሎጂዎችና የመዝናኛ ሥፍራዎች ሁሉ፤ ሀገሪቱን የዓለም ሕዝቦች የሀብት መሰብሰቢያና የታላላቅ ተቋማት መናኸሪያ አድርጓታል፡፡

የምግብ ጥያቄን ብቻ መሰረት ያደረገና የኢኮኖሚን ዕድገት በጠባቡ የሚመለከት ኢኮኖሚያዊ ልኬት፤ ሀገራትን የሚያሳንስና ለዜጎችም ሙሉ እርካታን የማያጎናጽፍ ኋላ ቀር አመለካከት ነው፡፡ ምግብና ሕልውና ላይ ብቻ የተንጠለጠለ የሀገር ዕይታ ‹‹ዶሮ ብታልም ጥሬዋን›› ዓይነት ብቻ ሳይሆን፤ አንዱን ለመስራት አንዱን የመጣልና የማበላሸት፤ ‹‹የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ፤ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ›› ዓይነት ነገርም ነው፡፡ የዜጎችን ፍላጎትና ዐቅም የሚገድብና ከመሰረታዊ ፍላጎት ያልዘለለ፤ ደካማ፤ በድህነት ከታጠረ አስተሳሰብ የሚመነጭ ዕይታ ነው፡፡ የሰው ልጆች በውብ፤ ጤናማና ንጹህ ሥፍራ ውስጥ መኖርና መሥራት ይገባቸዋል፡፡

ውበት አልባ ሕይወት መኖር፤ ቀለም አልባ እይታ፤ወይንም ጣዕም አልባ ማጣጣም ዓይነት፤ የታመመ ሕይወት ነው፡፡ በየዓመቱ በመቶ ሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ውበትን ፍለጋ ገንዘባቸውን ከስክሰውና ውድ ጊዜያቸውን መሥዋዕት አድርገው፤ ከሀገር ሀገር ሲዞሩ ስናይ፤ ሰዎች ውበትን ምን ያህል እንደሚራቡ ይገልጽልናል፡፡

ደስተኝነት፤ ጤንነትና ረዥም ዕድሜ የመኖር ምስጢር፤ የሰዎች ሁሉ ጥያቄ ነው፡፡ ደስታን የሚፈጥሩ ዕይታዎችና፤ በንጽህና የተከሸነ ውበት፤ የጤንነት ምግብ ነው፡፡ በውብ ስፍራዎች መኖር፤ በጽዱ ከተሞች መንቀሳቀስና፤ በምቹና ዓይነግቡ ቢሮዎች ውስጥ መስራት፤ ለሕይወት ጥራትና ርዝመት አስተዋጽዖ እንደሚኖራቸው ግልጽ ነው፡፡ በአጠቃላይ ውብ ሀገር ውስጥ መኖር ለነዋሪው ትልቅ ሀሴትና እፎይታን እንዲሁም ዐቅምን ይሰጣል፡፡ የሀገራት ውበት ለሕዝብ ቀዳሚ የደስታ ምንጭ ነው፡፡ በዓለም ደረጃ ደስተኛ ሀገራት ተብለው የቀዳሚውን ተርታ የሚይዙት የስካንዲቪያን ሀገራት፤ በጽዳት ደረጃቸውም ከቀዳሚዎቹ ተርታ የሚሰለፉ ናቸው፡፡ የሀገራቱ ጽዳትና ውበት ለሕዝብ ደስተኝነትና እርካታ ሚያደርገው አስተዋጽዖ ቀላል አይደለም፡፡

ሰው ሰራሽ ነገሮች ዋነኛ አስፈላጊነታቸው፤ ተፈጥሮን አጉልቶና ጠብቆ ለትውልድ ለማቆየት ነው፡፡ እንጦጦ፤ጫካው እየተመናመነ ቢመጣም ለዘመናት ባለበት ነበር፡፡

ጥቂት ሰዎች የሚያዩትና የሚጎበኙት ቢሆንም ባለመልማቱ ምክንያት ብዙዎቹ የሚያዘወትሩት፤ ሕጻናት የሚቦርቁበት፤ ቤተሰብ ራሱን የሚያሳርፉበት ሳይሆን፤ እንደተገተረ ዘመናት አልፈዋል፡፡ እንጦጦ ላይ የተጨመረበት ሰው ሰራሽ ውበት፤ ብዙዎች የሚመርጡትና ቀጣዩ ትውልድ የሀገራቸውን ውበት እያደነቁና እየወደዱ የሚያድጉበት ስፍራ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ዛሬ ዛሬ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ሊይዋቸውና ጊዜያቸውን ሊያሳልፉባቸው ከሚፈልጓቸው ውብ ሥፍራዎች አንዱ እንጦጦ ፓርክ ሆኗል፡፡

እንደዚህ ዓይነት በተፈጥሯዊና በታሪካዊ ቅርሶች ላይ የሚሰሩ እሴት የመጨመር ሥራዎች፤ ተዛማጅ ውበትን ለማድነቅ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ ከመሆናቸውም ባሻገር፤ ለነባሩም ሆነ ለመጪው ትውልድ ደስታና እርካታን እየለገሱ፤ በሀገሩ እንዲኮራ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

እነዚህ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተሰሩ ሥራዎች፤ በቀጣዩ ትውልድ ዘንድ ‹‹እንጦጦን፤ አንድነት ፓርክን፤ ሸገር ፓርክን የምንጎበኘው መቼ ነው?›› የሚል ስሜት እንዲፈጠር አድርገዋል፡፡ ተመሳሳይ ሥራዎች እየተጠናከሩ ሲመጡ ደግሞ፤ የብዙዎች ባሕር ማዶን አማትሮ የማየት ዝንባሌ እየቀነሰና፤ የራሳቸውን ሀገር ለመጎብኘት ጉጉት እያደረባቸው ይመጣል፡፡ ኢትዮጵያዊያን ወደ ዓለም መሄድ ብቻ ሳይሆን፤ ዓለምን ወደ ኢትዮጵያ እንድትመጣ ያደርጋል፡፡

ይኸን ለማድረግ ግን እንደ ቅዱስ ላሊበላ ዓይነት ‹‹ለምን ኢየሩሳሌም?›› የሚል ጠያቂ ኀሊና ይፈልጋል፡፡ የቅዱስ ላሊበላ ጥያቄ፤ ኢየሩሳሌም መሄድ ብቻ ሳይሆን፤ ኢየሩሳሌምን ኢትዮጵያ ውስጥ መስራት ይቻላል የሚል የቁጭት ሐሳብ ነው፡፡ ሕዝቡን ከሚያማትርበት ባሕር ማዶ ሊመልስ የሚችል ዘመን ተሻጋሪ ድንቅ ስራን ለመስራት፤ ሀገራችን ብቁ እንደሆነች አምኖ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ለአሁኑና ለመጪው ትውልድ እንደ ላሊበላ ድንቅና ቅዱስ ስፍራን እዚሁ መፍጠር ይቻላል የሚያስብል፤ ትልቅ የፓራዳይም ለውጥ ማምጣት አስፈላጊ ነው፡፡

በሀገራችን እንዲህ ዓይነት ፓራዳይሞች ጠንክረው ባለመውጣታቸው፤ዘመናችንን ሙሉ ለትልቅ ሥራና ለውበት የማንበቃ እንደሆንን እየተሰማን እንድንኖር አድርጎናል፡፡ ሀገራችን አሁን ያላት ውበት ለአንድ ኢትዮጵያዊ ደስታን ብቻ ሳይሆን የቁጭት ስሜትን ሊፈጥር ይገባል፡፡ ኮይሻንና አካባቢውን ስመለከት ይኸን ዓይነት ቁጭት ያዘለ መነሳሳት ተሰምቶኛል፡፡ ይኸ ስሜት ሲሰማኝ ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም፡፡ በስራ አጋጣሚዎች እንዲሁም ለዕረፍት በተለያዩ ጊዜያት ሀገራችንን ተዘዋውሬ ስመለከት ተመሳሳይ ስሜት ተመላልሶብኝ ያውቃል፡፡ በየስፍራው ስንሄድ የምናየው ተፈጥሯዊ ውበትና አስደናቂ ታሪካዊ ስፍራዎች ከባህላዊ እሴቶቻችን ጋር ተዳምረው የደስታን ስሜት ቢያጭሩብኝም እነዚህ ድንቅ ጸጋዎች ምንም ልማት ስላልተካሄደባቸውና በልካቸው ታይተው ለጥቅም አለመዋላቸው፤ ጥልቅ ቁጭትን ፈጥሮብኛል፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ውበታቸው እየረገፈ መሆኑ ሲታሰብ ደግሞ፤ የደስታው ስሜት ብዙም ሳይቆይ ሥጋትና ጸጸት እንዲጫነው ያደርጋል፡፡

ከዐርባ ምንጭ ከተማ ባሻገር ያለውን ውብ ደንና በውስጡ ያሉትን ኩልል ያሉ ምንጮች ለመጎብኘት በቻልኩበት አንድ አጋጣሚ፤ የዛፎቹን አስደናቂ ውበትና የጫካውን ጥቅጥቅነት የፈጠረብኝን መደመም፤

በአስጎብኚነት እየመሩን ላሉት፤ በፓርክ ውስጥ ለብዙ አመት የሰሩ ትልቅ ሰው ስነግራቸው የመለሱልኝ መልስ ያልጠበቅሁት ነበር። ‹‹ለኔ የሚታየኝ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ሳይሆን፤ ምድረ በዳ ነው። የዛሬ ሰላሳ አመት ብትመጣ ኖሮ፤ ለመተላለፊያ እንኳን ስንዝር ቦታ የሌለው ደን ነበር›› ብለው ኀዘን በሞላው ፊት ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁና፤ በያዙት በትር ወደ ጫካው ግራና ቀኝ እየጠቆሙ ሲነግሩኝ፤ ያልጠበቅሁት ድንጋጤና ሐሳብ ውስጥ ከተቱኝ። ዛሬ ላይ እዚህ ደረጃ ላይ ደርሶ እንዲህ ውበትን የተጎናጸፈ ከሆነ፤ ቀድሞ ሊኖረው የሚችለውን ውበት በዓይነ ኀሊናዬ ለመሳል ሞከርኩ። በሚገባ ተጠብቆ ቢሆን ምን ይመስል ነበር? የሚል ሐሳብ በውስጤ ተመላለሰ።

መብላትን እንጂ መተካትን፤ መጠቀምን እንጂ መንከባከብን ባለማወቃችን፤የተሰጠንን ለትውልድ አስፍተንና አበርክተን ሳናቆይ፤ ብዙ ነገር አመንምነናል፤ አውድመናል። ከትውልድ ድርሻ ቀድመን በልተን፤ ስንት ዕዳ በላያችን ተጭኗል። የነበረው ላይ ከመጨመር ይልቅ፤ ካለው ላይ እየተሸረሸረ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈው ዐቅም ያደገ ሳይሆን የተሸራረፈ ሆኗል። ኢትዮጵያችን ውበቷ እያማረና እጎመራ ሳይሆን፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየወየበ እዚህ ደርሷል። ተጨማሪ ለመፍጠር የሚያስችል ውበት አድናቂነት በውስጣችን ባለመኖሩ እልፍ የሀገር ውበት ተመልካች አጥቶ ቀርቷል። ከራሱ ዘመን አሻግሮ የማያይ ትውልድ፤ ከሌላው ትውልድ የተሸጋገረለትን እየበላና እያወደመ፤ የቀጣይ ትውልድን ሀብት አጥፊ ሆኖ ያልፋል የሀገራችን ሙሉ ዐቅሟና በልጽግናዋ ሊረጋገጥ የሚችለው ዘመን ተሻጋሪ ውበትንና ሀብትን መፍጠር የሚችል ትውልድ ሲፈጠር ብቻ ነው። ይኽ ትውልድ የሚፈጠርበት ጊዜው አሁን ነው።

የኢትዮጵያ ውበት ተመልካች አጥቶ ገረጣ እንጂ አልሞተም፤ አቧራ ተጭኖት ደበዘዘ እንጂ ከነጭራሹ አልጠፋም። አላፈራም እንጂ ከነአካቴው አልረገፈም። ኢትዮጵያ አሁንም ሊወጡ የሚችሉ ብዙ አስደማሚ የውበት ጸጋዎችን ታድላለች። ሀገራችን ጥበበኞች በአድናቆት የሰላ ብዕራቸውን ቀለም የሚያንቆረቁሩባት፤ ተዐምራትን መፍጠር የሚያስችል ዕምቅ ውበት ባለቤት ናት። የዚህ እምቅ ውበት ምስጢር የተለያዩ ኀብረ ቀለማት በአንድ ላይ የተሰባጠሩባት ዐሻራ መሆኗ ነው። ከደብረ ብርሃን የጠባሴ ብርድ እስከ የአፋር ኤርታሌ ሙቀት የሚስተናገድባት፤ ከራስ ዳሸን ከፍታ እስከ ዳሎል ዝቅተኛ ቦታዎች፤ከታላቁ ዓባይ ወንዝ እስከ ዐርባ ምንጮች፤ ከሰላሌ ሜዳዎች እስከ ገርዓልታ ተራራዎች፤ ከከፋ ጥቅጥቅ ደኖች እስከ ኦጋዴን በረሃማ ሥፍራዎች ድረስ፤ ተፈጥሮ ልዩነቶችን በአንድ ላይ አስተሳስሮ ያስቀመጠባት የውበት መስፈሪያ ናት።

ብዙ ሀገራት በተፈጥሮ የታደሉ ከሆኑ፤ ለዓለም የሚያሳዩት እጅግም ሰፊ ታሪክ አይኖራቸውም። አንዳንድ የድንቅ ታሪክ ባለቤት የሆኑ ሀገራት ደግሞ፤ እዚህ ግባ የሚባል የተፈጥሮ ሀብትና ውበት ባለቤቶች ሆነው አይገኙም። ኢትዮጵያችን ግን በዓለማችን ድንቅ ታሪክን፤ ተፈጥሯዊ ውበትንና ባህላዊ ጸጋዎችን በገፍ ታድለው ከተጎናጸፉ ውሱን ሀገራት መካከል የምትመደብ ናት። የክርስቲያንና የሙስሊም ስልጣኔ ነጸብራቆች የሚታዩባት ሙዚየም ናት። በበርካታ ባህሎች ሀብታም የሆነች፤ ብዝኃነትና አንድነት በአንድ ላይ የገጠሙባት ስፍራ ናት።

የነገዩቱን ኢትዮጵያ የሸፈናት አቧራ ተራግፎ፤ እውነተኛ ውበቷ ጎልቶ መውጣት አለበት። አዲሱ ትውልድ፤

የተፈጥሮ ጸጋዎች ለምተውና ተጠብቀው፤ ለዓይን ከሚማርኩ ሰው ሰራሽ መሰረተ ልማቶች ጋር ተሳልጠው፤ ድንቅ ውበትን የሚያጎናጽፉ እንዲሆኑ ይሰራል። ሀገራችን ጥንታዊነትና ዘመናዊነት፤ እንዲሁም ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ውበቶች በአንድ ላይ የተዛመዱባት የማራኪ ገጽታ ባለቤት እንድትሆን፤ ዘመን ተሻጋሪ ስራዎችን መስራት ይኖርብናል። ያኔ ነባር ተፈጥሯዊ ታሪካዊ መስህቦቻችን ከዘመናዊ ኪነ ሕንጻዎችና ወቅታዊ ሥልጣኔዎች ጋር ተዋድደው ልዩ ውበትን ይፈጥራሉ።

የዚህ ውበትን የመግለጥ ስራ መነሻ ደግሞ፤ የሕዝብ መገልገያ ተቋማት መሆን አለባቸው። የመንግስት ባለ ሥልጣናት፤ የግል ድርጅት ባለቤቶችና ሌሎች ኢትዮጵያዊያን የሚኖሩበት ቤት እንዲያጌጥ እንደሚፈልጉት ሁሉ፤ ስለ ቢሮአቸው ቆሻሻ ሊጨነቁ ይገባል። አመራሩ መስሪያ ቤቱንና ቢሮውን መለወጥ ሲችል በዚያ የተጀመረው የፓራዳይም ለውጥ የራሱንና የሚያገለግለውን ሕዝብ አካባቢ ላይ የሚጋባ ይሆናል። የከተማ ከንቲባዎች ባማረ ቤት እየኖሩ፤ በቆሻሻ የታጨቀ ከተማ ሊያስተዳድሩ አይገባምና።

የጠቅላይ ሚኒስትርነት ኃላፊነትን ተረክቤ ወደ ቤተ መንግስት ስገባ ያጋጠመኝ ነገር ይኸንን ይመስል ነበር። የጠቅላይ ሚኒስትሩ መኖሪያ ያጌጠና ያማረ ነው። ነገር ግን ከጠቅላይ ሚኒስትሩ መኖሪያ በትንሽ ርቀት ላይ የሚገኘውን ግቢ በቆሻሻ ክምር የታጨቀ ነበር። ወደ ቢሮ ሲገባ የሚያጋጥመው ሁኔታ ፈጽሞ ሰዎች ሊሰሩበት የማይችሉበት አካባቢ ነበር። ይኸም በሀገራችን የብዙ ቢሮዎች ገጽታ ሆኖ ቆይቷል።

ከለውጥ በኋላ የጀመርነው ከቢሮ አንስተን ሀገርን የማጽዳት ሂደት ነባሩን በራሳችን የታጠረ የጽዳት ዝንባሌን በመቅረፉ፤ ሕዝብ በጸዱ ቢሮ መሥራት፤ በጽዱ ቢሮ መገልገል፤ እንዲሁም ዕረፍት በሚሰጥ ከተማ ውስጥ መኖር ይገባዋል፤የሚል ምልከታን የተከተለ ነበር። በሀገራችን ያልጸዱ ቢሮዎች ለደካማ የስራ ባህል አስተዋጽኦ የሚያደርጉና፤ ተነሳሽነትን የሚገድሉ ሆነው ኖረዋል። ጽዱና ውብ በሆኑ ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የተሻለ ጤና ያላቸው፤ በሕይወት የመቆየት መጠናቸውም የረዘመ እንደሆነ ጥናቶች ያረጋግጣሉ። ጽዱ ከተሞችን መገንባት፤ በተላላፊና በሌሎች በሽታዎች የመታወክ መጠንን በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሰዋል።

ተፈጥሯዊ ውበትና ባህላዊ እሴቶች ተጣጥመውና በረቀቀ መንገድ ውበትን፤ ንጽሕናንና ምርታማነትን ተከትለው በልህቀት ከተሰሩ፤ ዘመን የሚሻገር ሥራ ተሰራ ማለት ነው። ዘመን የተሻገረ ሥራ ደግሞ ከትውልድ ወደ ትውልድ ዋጋው የሚጨምርና የሚሸጋገር ታሪክ ይሆናል። የግብር ይውጣና የአቋራጭ ስራዎች ለሰራቸው ትውልድ ኀፍረት፤ ለመጪውም ዘመን ሸክም መሆናቸው አይቀርም። ያለፉ አባቶቻችንና እናቶቻችን በተለያዩ፤ አቅጣጫዎች ያቆዩልን ዘመን የተሻገሩ የጀግንነት፤ የጥበብ፤ የእምነትና የውበት ቅርሶቻችን ብዙ ናቸው።

ፈጣሪም በቸርነቱ የለገሰን ልዩ ተፈጥሯዊ ውበትና ሀብት ቁጥር ስፍር የለውም። በቅርብ ጊዜ የተበላሹና ያረጁ፤ ውበትና ዓላማቸውን ያጡ ቅርሶቻችንን በማደስና፤ አዳዲስ መስሕቦችን በመፍጠር፤ ይኸ ትውልድ ዘመን ተሻጋሪ ታሪክ ሰሪነቱን ለማሳየት፤ ከዚህ የተሻለ ዕድል ሊመጣለት አይችልም።

# ድንበር የለሽነት - ሁለንተናዊ አርነት

‹‹ተስፋ አልባዋ አፍሪካ›› ይላል በግንቦት 11/2000 ዓ.ም በዘ-ኢኮኖሚስት መጽሔት የወጣው ጽሑፍ።

ትንታኔው ሲጀምር ምዕራብ አፍሪካዊቷን የሴራሊዮን ዋና ከተማ ፍሪታውንን ያነሳል፤ በ19ኛው መክዘ መጀመሪያ ላይ ምን ያህል በተስፋ የተሞላች እንደነበረችና፤ ከሁለት ክፍለ ዘመናት በኋላ በ21ኛው መክዘ መባቻ ላይ፤ እንደ ፍሪታውን ያሉ ተስፋ የማይታይባቸው፤ ፍራቻ የሸበባቸው ከተሞች እንደሆኑ ያስረዳል። የሴራሊዮን ሁኔታ ከአፍሪካ በልዩነት የሚነሳ ሳይሆን የአህጉሪቱ ‹‹ተስፋ የለሽነት›› ዓይነተኛ ማሳያ እንደሆነም ያትታል።

አፍሪካ በእንደዚህ ዓይነት ጨለመተኛ ትኩረት ስትገለጥ የመጀመሪያም መጨረሻም አይደለም። አዎንታዊ ትርክቶች ስለአፍሪካ በሚሰሙበት በአሁኑ ወቅት እንኳን ተመሳሳይ አሉታዊ ትርክቶች ከቅርብና ከሩቅ ያስተጋባሉ። በዩክሬን ጦርነት የተለያዩ የሚዲያ ተንታኞች ‹‹ይሄ እንደ አፍሪካ የጦርነት ቦታ አይደለም፤ አውሮፓ የሰለጠነ የዓለም ክፍል ነው›› የሚል፤ ጦርነትን አልሰለጠኑም የሚሏቸው የአፍሪካዊያን መገለጫ እንደሆነ ዘረኝነት በተሞላበት መልኩ አቅርበዋል።

አፍሪካ እየተነሳች እንደሆነ የሚገልጹ ትርክቶች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተለመዱ ቢሆኑም፤ አሁንም ስለ አፍሪካ የሚወሩ አሉታዊ ወሬዎች ብዙ ናቸው። አሉታዊ ትርክቶች በአፍሪካ ውስጥ እየተፈጠረ ያለውን ክስተት በመግለጽ የተወሰነ እውነትነት ቢኖራቸውም፤ ክስተቶችን ተመልክቶ ሙሉ አህጉርን ተስፋ አልባ አድርጎ መጠቅለል ግን፤ የዐውቆ አጥፊነት ስራ ለመሆኑ ምስክር አያሻውም። ችግሮችና ክስተቶች በየትኛውም የዓለም አካባቢ ሊፈጠሩ ይችላሉ። ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ አንድን ታላቅ አህጉር ተስፋ ቢስ አድርጎ መሳል፤ የአካባቢን ዐቅም አለመገንዘብ ነው።

አፍሪካ ብዙ ዐቅም ቢኖራትም ሙሉ ጉልበቷን ተጠቅማ ባለመንቀሳቀሷ፤ በኋላ ቀርነት ተረኮች እንድትሳል ተደርጋለች። ከምንም በላይ ግን እነዚህ ተረኮች፤ በዓለም ላይ ለሰፈነው በእኩል ሚዛን ላይ ላልቆመ ግንኙነት መሠረት ናቸው። ለዚህ የተንሸዋረረ አካሄድ ቀዳሚው ማሳያ ቅኝ ግዛት ነው። አሁንም ድረስ አፍሪካ በተጫነባት ‹‹የተበዳይነት ዕዳ›› በዓለም አቀፍ ሁኔታ ውስጥ ተጽዕኖ መፍጠር የምትችል አልሆነችም። የአፍሪካ ጎዳናዎች ሁሉ እርስ በእርስ ሀገራትን የሚያያይዙ ሳይሆኑ፤ወደ ባሕር ወደቦቻቸው ብቻ የሚገሰግሱ የሆኑበት ምሥጢር የቅኝ ግዛት ቧንቧ በመሆናቸው እንደሆነ ከመቼውም ይልቅ በግልጽ ታውቋል።

በአፍሪካ ዙሪያ የተቀነበቡት ገዥ ትርክቶች ሁሉ የተዛቡ የዓለም አቀፍ ግንኙነት ሁኔታዎችን ፈጥረዋል። ከእነዚህም መካከል አንዱ፤ ‹‹በድንቁርና ወደ ተሞላው ጨለማው አህጉር ሄደን ማሰልጠን የእኛ የነጮች ዕዳ ነው›› በሚል የተፈጠረው የቅኝ ግዛት ማሳመኛ ተረክ ነው። ቅኝ ግዛት፤ አፍሪካዊ የሆነ የሀገር ግንባታ ሒደትን በማቋረጥ፤ አፍሪካውያን የራሳቸውን መልክና የዕድገት ሒደት በመተው፤ በውጪ ኃይላት የተጫነ የሀገር ምስረታ ማንነት እንዲኖራቸው ያደረገ ዘመን ተሻጋሪ ክፋት ነው። ይኸው በአፍሪካ ላይ ሊገመት የማይችል ማኅበራዊ፤ ታሪካዊና ሰብአዊ ቀውሶችን ፈጥሯል። የአፍሪካ ማህበረሰቦች ጥንታዊ አስተዳደር ፈርሷል። ማህበረሰቦች በተለያዩ ሀገሮች ድንበሮች እንዲሸነሸኑ አድርጓል። አፍሪካ ታሪክ እንደሌላት ሁሉ የቅኝ ግዛት ታሪክ የአፍሪካ ታሪክ መነሻ እንዲሆን ተደርጓል፤ አያሌ ታሪካዊ፤ መንፈሳዊና ባህላዊ ቅርሶቿም ተመዝብረዋል።

ትግል ረጅም ጊዜን የሚጠይቅና እጅግ አድካሚ በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ ተስፋ እስከ መቁረጥም ያደርሳል። በተለይም ለነጻነት የሚደረግ የእንቢተኝነት ትግል ከፍተኛ የኃይል ሚዛን አለመመጣጠን የሚታይበት እንደመሆኑ፤ እልህ አስጨራሽ፤ የተለየ ስልትና ወኔ የሚጠይቅ ነው። በአፍሪካና በዓለም ዙሪያ ያሉ ጥቁር ህዝቦች፤ ከተያዙበት የዘመናት የቅኝ ግዛት አስተዳደር ለመላቀቅ የሚያስችል፤ ይኸ ነው የሚባል የትግል እንቅስቃሴና ተስፋ ባልነበረበት በዚያ የባርነት ዘመን፤ በተለያዩ አካባቢዎቸ የተነሱ የነጻነት ትግሎችና ለውጦች፤ በተከታታይ በየአካባቢው ለሚነሱ ሌሎች ትግሎች በር ከፋችና ተስፋ ፈንጣቂ ነበሩ።

የአድዋ ድል እንደዚህ ዓይነት በር ከፋች ከሆኑ ታሪካዊ ክስተቶች መካከል የሚመደብ ነው። ዝናው በነጻነት ፈላጊ ሕዝቦች ዘንድ ሁሉ የናኘ፤ የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ትግል አብሪ ኮከብ ነበር። የተዛባ ዓለም አቀፍ ግንኙነት በሰፈነበት ጨለማ ዘመን ውስጥ ፋና ወጊ በመሆን የእኩልነት ትግልን ለማፋፋም አስችሏል። አድዋ የኢትዮጵያን ነጻነት ከማስጠበቅ ተነስቶ፤ የብዙ ጥቁር ወንድሞቻችንን ልብ በይቻላል መንፈስ ያሞቀ የዘመን ገሞራ ነው። በመቀጠልም ከግማሽ ምዕተ አመት በኋላ በሰፋ ምናብ የራሳችንን ነጻነት ከማስጠበቅ አልፈን፤ አፍሪካውያን ወንድሞቻችን ነጻነትን እንዲያገኙ ያደረግነው ጥረት፤ በቅኝ ግዛት የማብቃት ታሪክ ውስጥ ጉልህ ድርሻ አለው።

በቅኝ ግዛት መስፋፋት በተቋረጠው አፍሪካዊ የሀገር ግንባታ ሂደት ውስጥ ራሷን ከወረራ ተከላክላ፤ በተጽዕኖ ውስጥም ቢሆን፤ የራሷን ሀገረ መንግስት ግንባታ የከወነች ኢትዮጵያ ብቻ ናት። ሀገራችን ኢትዮጵያ ከቀዳሚዎቹ የአፍሪካ ብሎም የዓለም ስልጣኔዎች መካከል ከመሆኗ በተጨማሪ ለጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ትግል ባደረገችው አስተዋጽኦ የነጻነት አርማና አፍሪካዊ የጀግንነት ተምሳሌት ሆና ትኖራለች። አፍሪካዊነትና የጥቁር ሕዝቦች ወንድማማችነት እንዲጎለብት የነበራት ማዕከላዊ ሚና በአፍሪካ የነጻነት ትግልና ድል ውስጥ ጉልህ ስፍራ አለው።

ጥቁር ሕዝቦች በጭቆና ውስጥ በነበሩበት ዘመን ጥቁር ሕዝቦች ነጻነት እንደሚገባቸውና፤ ነጻነታቸውን ታግለው ማግኘት እንደሚችሉ ማሳያ የሆነችው ኢትዮጵያ ናት። ብዙዎች ኢትዮጵያን መሆን እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስከበረውን ነጻነት ማግኘት ተመኝተው፤ ትግላቸውን በኢትዮጵያ ስም ሰይመው ታግለዋል። ይኸ የኢትዮጵያ ተምሳሌትነት በጥቁር ሕዝብ ዘንድ ኩራት፤ በራስ መተማመንና ትብብርን የፈጠረ ነው። ሀገራችን ተምሳሌታዊነቱ የፈጠረውን መነቃቃትና ትብብር መነሻ በማድረግ፤ አፍሪካዊ ወንድማማችነት እንዲጎለብትና በመጨረሻም ቅኝ ግዛት እንዲያበቃ የተጫወተችው ሚና ቀላል አይደለም።

አፍሪካችን በተባበረ ጥረት ከቀጥታ ቅኝ አገዛዝ ነጻ በትወጣም፤ አሁንም በዓለም አቀፍ መድረክ ውስጥ ያላት ስፍራ ኢምንት ነው። ከግጭት፤ ከመፈንቅለ መንግስት፤ ከበሽታና ከረሃብ መውጣት አልቻለችም። በድኅረ ቅኝ ግዛት፤ አህጉራዊ የአንድነት ድርጅትን መስርቶ የተወሰኑ ውጤቶችን ማምጣት ቢቻልም፤ በሀገራት መካከል አለመተማመንን አጥፍቶ መቀራረብን በማጠናከር፤ አፍሪካዊ ብልጽግናን ማረጋገጥ እና ሰላምን ማስከበር ግን ዛሬም አልተቻለም። አፍሪካውያን የሚገጥማቸውን ችግር ለመፍታት ከሚያስፈልጋቸው ኅብረት ይልቅ መራራቅን በመምረጥ፤ ዛሬም ለውጭ ጠላቶች ጣልቃ ገብነት በራቸውን ወለል አድርገው ከፍተው

ይገኛሉ።

አፍሪካ የብዙ ሕዝቦች መኖሪያና የከፍተኛ ዐቅም ባለቤት አህጉር ብትሆንም በዓለም ፖሊቲካ ውስጥ ተገቢውን ቦታ ተነፍጋ፤ በየጊዜው የሚነሱ ኃይላት ጥቅማቸውን ለማስከበርና ፍላጎታቸውን ለመጫን የሚወዳደሩባት የጋራ ሜዳ ሆናለች። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የአህጉሩ ሀገራት ቀድሞ ከገቡበት ችግር ጨርሰው ለመውጣት አለመቻላቸው ነው። ከዚህም በተጨማሪ ከነጻነት በኋላ የተነሱ መሪዎችና ትውልዶች፤ በቅኝ ግዛት ድንበር የታጠሩ፤ በሰፈር ማንነት የሚመሩና በጊዜያዊ ጥቅም የታወሩ መሆናቸው አስተዋጽኦ አድርጓል።

በጸረ ቅኝ ግዛት ትግል ውስጥ ኢትዮጵያ የነጻነት ተምሳሌት በመሆን በአፍሪካውያን ነጻነት ውስጥ ፋና ወጊ የመሆኗን ያህል፤ ዛሬም አፍሪካ ካለችበት የማንነት ቀውስ ተላቅቃ፤ ትክክለኛ ሥፍራዋን እንድትይዝ ፈር ቀዳጅ መሆን ትችላለች። ኢትዮጵያ ከቀደመው ስምና ዝናዋ እንዲሁም በአህጉሪቱ ካላት ታላቅ ቦታ አንጻር፤ የአፍሪካውያንን የብልጽግና፤ የሰላምና የአንድነት ቀጣይ ጉዞ ለማነሳሳትና ለመምራት ትልቅ አቅምና እድል አላት። ለዚህ ኃላፊነት ብቁ ለመሆን ግን፤ የራሷን ሁለንተናዊ ነጻነትና ድንበር የለሽ ማንነት የሚያረጋግጥ ትውልድ ልትፈጥር ይገባታል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካዊ ኅብረትና የአፍሪካዊ ወንድማማችነት ማዕከልና የኩራት ምንጭ ናት። ሆኖም ይኽ ሁሉ ተዘንግቶ፤ ሚናዋና ተጽዕኖዋ ተቀዛቅዞ፤ በራሷ ችግር የተጠመደች ሀገር ሆናለች። የነጻነት ተምሳሌት ሆና ሳለ ከራሷ ችግር ነጻ መሆን አቅቷት የምትሰቃይ፤ ለአፍሪካ አንድነት መናገሻ ሆና ሳለ አንድነቷ የላላና በክፍተቶቿ ተጠቅመው ታሪካዊ ጠላቶቿ ወደ ባርነት የሚጠመዝዟት ሀገር ሆናለች። እኛን የነጻነትና የአንድነት ተምሳሌት አድርገው ለሚመለከቱት ሕዝቦች፤ ይኽ ምን አይነት መልዕክት ያስተላልፋል? የአፍሪካዊ አንድነት የስበት ማዕከል የሆነው የኢትዮጵያ አንድነትና ሰላም ነው። ይኽ የኢትዮጵያ አንድነትና ሰላም እየላላና እየተዳከመ ከመጣ፤ ይኽ ትውልድ ለአፍሪካ ኅብረትና አንድነት መላላት ከታሪካዊ ተጠያቂነት አያመልጥም።

በሀገራችን ፓን አፍሪካኒዝም ትልቅ ቦታ ቢኖረውም፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይኽ አፍሪካዊ ስሜት እየተቀዛቀዘ መጥቷል። ኢትዮጵያውያን አፍሪካንም ረስተው፤ ራሳቸውንም ዘንግተው፤ በእርስ በእርስ የእኔ ይበልጥ ፉክክር ውስጥ ተጠምደዋል። በክፍፍል ምጣድ ላይ ተጥደው ሲቃጠሉ ዓመታት ተቆጥረዋል። የጥቁር ሕዝቦች መካ እና ኢየሩሳሌም ልትሆን የምትችል ሀገር፤ የራሷንና የአፍሪካን ጥቅም ከማስከበር ይልቅ፤ በውስጧ በተፈጠረ የማንነት ቀውስ ስትታመስ ቆይታለች። ከትውልድ ወደ ትውልድ በሕዝብ ዘንድ የሚንጸባረቀው የፓን አፍሪካኒዝም ስሜት ተመናምኖ፤ ድንበር የለሽ አፍሪካዊነትና ሁለንተናዊ አርነት ሳይሆን፤ የሰፈር ሽኩቻና የብሔር ቁርቁዝ መለያዋ እንዳይሆን ያስፈራል።

ጦርነት ሀገር ገዳይና አቆርቋዥ እንደመሆኑ፤ ለሀገራችን መልካም ከመመኘት የተነሳ የሚፈጠሩ የአካሄድና የመርህ አለመግባባቶች ሁሉ፤ በሰላምና በፍቅር መፍታት ወሳኝ ነው። በሰሜን የተከፈተብንን ጦርነት ለመመከትና የተፈጠረውን የሕልውናና የሕግ ማስከበር ኃላፊነት ለመወጣት ብዙ ጥረቶችን አድርገናል። ጦርነት ለብልጽግና የሚመረጥ መንገድ ባለመሆኑ፤ ጦርነት እንዲቆም የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በቀና

እንመለከታቸዋለን። ሆኖም ግን ጦርነትን ከማስቆም በዘለለ፤ በፖሊስ ነጻነታችን ላይ የተሰነዘሩ የሉዓላዊነት ጥያቄን የሚያጭሩ፤ ይኸን ካላደረጋችሁ ይኸን አናደርግላችሁም የሚሉ ጉዳዮች ከግራና ከቀኝ ሲወነጨፉብን ቆይተዋል።

በብዙ መልኩ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ከመቶ አመት በፊት ‹‹እውነት እኛ አርነት አለን ወይ?›› ሲሉ የጠየቁትን ጥያቄ መልሼ በመጠየቅ፤ ነባሩን እውነታ እንደ አዲስ እንዳሰላስል አድርጎኛል። ይኸ ጥያቄ ደግሞ የእኛ የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካውያን ሁሉ መሆኑ ቀድሞ የሚታወቅ ቢሆንም፤ ከቀድሞ ይልቅ ደግሜ ደጋግሜ እንዳስበው ተገድጃለሁ።

መጪው ትውልድ ከእንደዚህ ዓይነት ተጽዕኖ የተላቀቀ መሆኑ፤ አማራጭ የሌለው ብቸኛ ምርጫችን ነው። የቀደመው ትውልድ ባስከበረው ነጻነት አርአያ ሆኖ፤ ጥቁሮች ነጻነታቸውን ማስከበር እንዲችሉ በር ተከፍቷል። የቀደሙ የሀገራችን ትውልዶች አፍሪካዊ የታሪክ ዐሻራ ይኸ ነበር። አዲሱ የመደመር ትውልድ የዚህ አፍሪካዊ ዐሻራ ወራሽ ብቻ ሳይሆን፤ የራሱን የነጻነትና የብልጽግና ዐሻራ በኢትዮጵያ ከማኖር አልፎ፤ አፍሪካዊ የሆነ ሁለንተናዊ አርነትንና ድንበር ተሻጋሪ ተጽዕኖን ሊፈጥር ይገባል።

አርነትን እና እኩልነትን ለማምጣት ትልማችን የሰፋ መሆን አለበት። ሁሌም ያነሰ ምልከታ ይበልጥ እያሳነሰን መምጣቱ አይቀርም። የሚሰፋ ምልከታም እንደዚሁ ይበልጥ እየሰፋ መሄዱ አይቀርም። ስለ ሰው ልጆች ሁሉ የሚቆረቆርና ዓለምን የተሻለ ስፍራ ለማድረግ፤ አፍሪካዊ ኅብረትን፤ የሚያጠናክር ሕልም ሊኖረን ይገባል። ተልዕኳችን የመንደር ተልዕኮ አይደለም፤ራዕያችን በወንዝ የሚታጠር አይደለም፤ተጽኖዋችንም እስከ ተራራው አይደም ። ዓለምን ለማን ትተን ነው መንደር ውስጥ የምንቀረው? አፍሪካን ለማን ትተን ነው በወንዝ የምንታጠረው? እንዲህ ስናስብ ከፍ ያለ እሴትንና ዘላቂ ጥንካሬን መፍጠር ይቻላል። ከዚህ በተቃራኒ የሚሄዱ አካሄዶች ሁሉ፤ ወደ ውስጥ በአነስተኛ ግብ ላይ ተወጥረው፤ ፉክክርን በማጉላት ድቀትን የሚፈጥሩ ናቸው።

ለምሳሌ እኩልነት ተገቢና አስፈላጊ ቢሆንም፤ በእኩልነት ትግል ስም ፉክክርና አላስፈላጊ መካረር፤ በነጻነት ስም የሌላውን መብት መጋፋትና ደም አፍሳሽ ዐመጾች እኩልነትን አይፈጥሩም። ይልቁንም ለሁሉም የማይበጅ የተዳከመ ሀገራዊና ቀጣናዊ ብሎም አህጉራዊ ሁኔታን ይፈጥራሉ። ትውልድ ከዚህ አይነት ጠባብ ምናብ ወጥቶ፤ ለሰው ልጆች ሁሉ የተሻለ ሁኔታን ለመፍጠር የሚተልም አመክንዮአዊ አካሄድን ሲከተል፤ የራሱም የሌሎችም ጥቅም የሚከበርበትን ሁኔታ ይፈጥራል።

በዓለም ላይ በየዘመኑ ስልጣኔዎችና የተለያዩ ለውጦች ይነሳሉ፤ ይወድቃሉ። በዚህም ሒደት ስልጣኔዎቹ በተነሱበት አካባቢና በሰፊው ዓለም ላይ የሚታይ ከፍተኛ አዎንታዊና አሉታዊ ዐሻራ ይኖራቸዋል። በፈረንሳይና በጥቂት የአውሮፓ አካባቢዎች የተነሳው የአብርሆት እንቅስቃሴ፤ በመላው አውሮፓና በአሜሪካ ከፈጠረው ተጽዕኖና ለውጥ በተጨማሪ፤ የዘመናዊው ዓለም እሴቶች መነሻ በመሆን፤ በብዙ ሀገራት ላይ ዐሻራውን አኑሯል። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቃት በኋላ የአሜሪካ ጠንክሮ መውጣት፤ በጦርነት በፈራረሰችውና በተዳከመችው አውሮፓ ላይ ያመጣው ለውጥ ቀላል አይደለም። ከቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ማብቃት በኋላ

የተፈጠረው የምዕራቡ ዓለም የበላይነት፤ የምዕራቡ ዓለም እሴቶችን በመላው ዓለም እንዲስፋፋ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

አዲሱ ትውልድ ወደ ውስጥ ብቻ በመመልከት ከሚፈጠር ውስጣዊ ልዩነትን የሚያጎላ ፖለቲካ ወጥቶ፤ አፍሪካዊ ኅብረትና ትብብርን ወደሚያጠነክር ፓራዳይም ሊሸጋገር ይገባል፡፡ ሀገራችን ራሷን በማጠናከር አፍሪካ ውስጥ ያላትን ቦታ ማጉላት፤ እንዲሁም ፓን አፍሪካዊ ድምጾች የአፍሪካውያን ገዥ መርሕ ሆነው እንዲወጡ ማድረግ አለባት፡፡ አፍሪካ ተጠናክራ እንድትወጣ ከፈለግን፤ ኢትዮጵያ በአዲስ ፖሊቲካ፤ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ተጠናክራ መገኘት አለባት፡፡

የኢትዮጵያ መጠናከር ለአፍሪካ መነሳት ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ የፓን አፍሪካ እሴቶች በአዲሱ የአፍሪካ ትውልድ ላይ እያበበ እንዲወጣ የማድረግ አቅምም አለው፡፡ ኢትዮጵያን ለማንበርከክና ለመስበር የሚደረጉ ተደጋጋሚ ሙከራዎችም፤ አፍሪካዊ ኅብረት እንዳይነሳሳና እንዳያብብ ለማድረግና፤ አፍሪካን ያለ ተምሳሌት ለማስቀረት የሚደረግ የተቀነባበረ ጥረት አካል ነው፡፡ ኢትዮጵያ እነዚህን ተግዳሮቶች በአይበገሬነት ካለፈች፤ ወደ ልዕልና ከፍታዋም ከተጠጋች፤ ለአፍሪካ መነሳትና ሁለንተናዊ አርነት የጥንካሬ መሠረት ትሆናለች፡፡

የድሮው ዘመን አፍሪካዊ ተምሳሌትነት በቅኝ አገዛዝ ነጻነት ትግል ውስጥ የተቃኘ ነው፡፡ አዲሱ ዘመን የአፍሪካ ተሐድሶ ጠበቃነት ደግሞ የአፍሪካን መልከ ብዙ ችግሮች መቅረፍን የሚተልምና፤ ሁለንተናዊ አርነትን ከድንበር ተሻጋሪ ማንነት ጋር ያቆራኘ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ይኸን አፍሪካዊ ሚናዋን አዲሷ አፍሪካዊት የስህበት ማዕከል በመሆን፤ እንደ አዲስ መቅረጽ አለባት፡፡ አዲሱ የስህበት ማዕከልነት እንደ ቀደመው የጸረ ቅኝ ግዛት ታጋዮችን በማስታጠቅ እና በመደገፍ የሚገለጽ አይደለም፡፡ ዘርፈ ብዙ የማንነት የባለቤትነትና ዓለም አቀፋዊ ወሳኝ ድምጽ በመሆን እንጂ በተለያዩ የአለም ክፍሎች የነበሩ ስልጣኔዎች እንደነበራቸው አበርክቶ ሁሉ፤ የአዲሱ ትውልድ የኢትዮጵያ ስልጣኔ አበርክቶው የመደመርና የፓን አፍሪካን እሴት ማጽናት ነው፡፡ የኢትዮጵያ መነሳትና ጠንክሮ መውጣት፤ ኢትዮጵያዊ ተጽእኖን ብቻ የሚያጎላ ሳይሆን አፍሪካዊ ጥንካሬም የሚኖረው ነው፡፡ ከአፍሪካ ጋር የተሳሰረ ጥንካሬና ለውጥ፤የኢትዮጵያ ብልጽግና መሠረትም መዳረሻም ነው፡፡ መዳረሻችን የኢትዮጵያን ከፍታ በማረጋገጥ ብቻ የሚያበቃ አይደለም፤ የአፍሪካንም ጭምር እንጂ፡፡ የመደመር ትውልድ አፍሪካ የተባበረችና ጠንካራ አህጉር እንድትሆን የሚተጋ ነው፡፡ በውስጣዊ ልዩነቶች ‹‹እኔ እበልጥ፡ እኔ እበልጥ›› ከሚል ፉክክር ተሻግሮ፤ ከፍ ወዳለ ሰብዓዊ ትልም የሚያመራ፤ አፍሪካውያንን በተገቢው ክብርና እኩልነት ቦታ ላይ ለማስቀመጥ የሚሰራ ነው፡፡

በመደመር ፓራዳይም የተቃኘው የኢትዮጵያ ብልጽግና፤ ቀዳሚ የዓለም ስልጣኔ የሆነው የአፍሪካ ስልጣኔ እንደገና እንዲያንሰራራ ቀስቃሽ ኃይል ነው፡፡ ይኸ ተምሳሌተ አፍሪካ ስልጣኔ ነባራዊ ሁኔታዎችን የተገነዘበና አፍሪካዊ እሴቶችን አንግቦ አፍሪካዊ ለውጥን ለማምጣት የሚተልም ነው፡፡ በዚህ የፓራዳይም ለውጥ የተቃኘው ትውልድንም ፓን አፍሪካኒዝም እሴቶችን የሚላበስ የቀደመውን ዘመን የአፍሪካን የነጻነት ትግል ከመሩ ንቁ ወጣቶች ጋር የሚመሳሰል ትውልድ ነው፡፡ የአፍሪካን የአዲስ ዘመን ብልጽግና የሚመራውም እርሱ ነው፡፡

የነገዩቱ ኢትዮጵያ የመደመር ትውልድ ለሰብዓዊ ልዕልና የቆመ፤ አፍሪካን ወደ ከፍታዋ የሚመራና የሚያግዝ መሆን አለበት። አዲሱን አፍሪካዊ ክብርና ልዕልናን በሚያረጋግጥ መንገድ አፍሪካን ከተጫናትና ለሌሎች ጫናዎችም ከሚያጋልጣት ኢኮኖሚያዊ ዝቅጠት በማላቀቅ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው። ኢትዮጵያ መከላከያ ኃይሏን ለአፍሪካ ኩራት በሚሆን መልኩ በማጠናከር ዓለም አቀፍ ፖለቲካዊ ተደማጭነቷን ከፍ በማድረግ ኢኮኖሚያዊ ትብብሮችንና ትስስሮችን በማሳለጥ እንዲሁም ከአፍሪካ ሀገሮችና ሕዝቦች ጋር የባህልና ትምህርት ልውውጥ በማድረግ፤ አፍሪካዊ ጥንካሬን ለመፍጠር እንዲቻል፤ አዲሱን የመደመር ትውልድ በመቅረጽ ላይ ትገኛለች።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ የዲፕሎማሲ፤ የኢኮኖሚና የባህል ስህበት ማዕከል በመሆን፤ አፍሪካን የተሻለ የሰው ልጆች መኖሪያ የማድረግ ጥረትን ከፊት መምራት አለባት። ይኸውም አዲስ አፍሪካዊ መንገድ ኢኮኖሚያዊ የመሰረተ ልማት መሳለጥና ግንኙነት ንግድ ልውውጥ የኢነርጂ ትስስርን ሁሉ ያቀፈ ነው። ንግድንና የሕዝብ እንቅስቃሴን የሚያሳልጡ የመንገድ፤ የባቡር፤የወደብና የኮሙኒኬሽን መሰረት ልማቶች መጠናከር ለአፍሪካውያን ኢኮኖሚያዊ ለውጥና እድገት እጅግ ቁልፍ ሚና ይኖራቸዋል። መሰረተ ልማቶቹ የንግድ ልውውጥ እንዲስፋፋና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት እንዲጠናከር በማድረግ ሰፊ የስራ እድል እንዲፈጠር ያደርጋሉ። ኢኮኖሚያዊ እድገቶች እንዲኖሩና የተሻለ የኑሮ ደረጃ እንዲፈጠር ከማስቻል ባለፈ፤ ኅብረትና አንድነትን ያቀላጥፋሉ። በተጨማሪ ኢትዮጵያ ያላትን የታዳሽ ኢነርጂ ዐቅም ተደራሽነት በማስፋፋት ሀገራት በኢነርጂ የተሳሰሩና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ ዘላቂነት ያለው ልማት እንዲፈጥሩ ያስችላቸዋል።

አፍሪካውያን በቅኝ ግዛት ከተያዙበት ዘመን አንስቶ ኢትዮጵያ የሰው ልጆች እኩልነት እንዲረጋገጥ ለመላው ጥቁር ሕዝብ ድምጽ ሆና ነበር። ከዚያም በተጨማሪ ሀገራችን የአፍሪካውያንን አጀንዳ ቀዳሚ ጉዳይዋ በማድረግ በዓለም መድረክ ተንቀሳቅሳለች። የነገዩቱ ኢትዮጵያም አፍሪካዊ ድምጽነቷንና የአፍሪካ ኅብረት ማዕከልነቷን አጠናክራ በመቀጠል፤ አፍሪካውያን ተሰሚነታቸውና ተቀባይነታቸው ከፍ እንዲል ታደርጋለች። በመጪው ዘመን፤ አፍሪካ የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ መቀመጫ እንዲኖራት ማረጋገጥ የመደመር ትውልድ ሀገራዊና አህጉራዊ ተቀዳሚ ግብ ነው።

የባህልና የትምህርት ልውውጥ በራሱ አህጉራዊና ቀጣናዊ ኅብረትና ትስስርን ለመፍጠር ቁልፍ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ አፍሪካውያንን ተቀብላ የምታስተምር የአፍሪካውያን የባህልና ትምህርት ማዕከል ስትሆን የአፍሪካውያን ሁሉ መሰብሰቢያ መድረክነቷ ይጨምራል። በመሆኑም ታላላቅ ዩኒቨርስቲዎቻችንና የባህል ማዕከላት አፍሪካዊ ቀለምን የሚያንጸባርቁ፤ አፍሪካውያን ሁሉ ሰፊ ባህላቸውን አንዱ ከሌላው ቀስመው የሚሄዱባቸው ማዕከላት ሊሆኑ ይገባል። በዚህም የአፍሪካ ገጽታና የተጽዕኖ አድማስ እየሰፋ ይሄዳል። በዓለም አቀፍ መድረክም አህጉራችን ተገቢውን ስፍራና ቦታ እንድታገኝ ዕቅም ይፈጥራል።

አፍሪካ እየተሳሰረች ከመጣችና በአንድ ድምጽ የሚናገር ጠንካራና አንድነት ያለው አህጉር መገንባት ከተቻለ፤ በዓለም አቀፍ ግንኙነት ላይ ተገቢውን ተጽዕኖ ማድረግ ትችላለች። በዚህም የተሳሰረች አህጉር በመፍጠር ሂደት፤ በአፍሪካ ውስጥ ትልቅ ታሪካዊ ቦታ ያላት እና የብዙ ዐቅም ባለቤት የሆነች ኢትዮጵያ የላቀ ሚና

ይኖራታል፡፡ የመደመር ትውልድ የሰፋ ምናብ ሊኖረው የሚገባው እነዚህ ሁሉ የትውልዱ ኃላፊነቶች ስለሆኑ ነው፡፡ የነገዪቱ ኢትዮጵያም የአፍሪካ የጥንካሬ፤ የአንድነት፤ የፖሊቲካ፤ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ የስህበት ማዕከል በመሆን ታገለግላለች፡፡ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ድንበር የለሽ ተጽዕኖና ብልጽግና፤ በአፍሪካ ስኬትና ሁለንተናዊ እርነት ውስጥ ተፈጻሚነት ያገኛል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደመር ትውልድ

‹‹እያንዳንዱ ትውልድ የወላጆቹ ጠላት የአያቶቹ
ደግሞ ወዳጅ ለመሆን ይሞክራል፡፡››

~
ሌዊስ ማምፎርድ

‹‹ታሪክን የማያውቅና የሚንቅ ትውልድ -
ትሩፋትም ተስፋም አይኖረውም፡፡››

~
ሮበርት ሄንሌን

# ምዕራፍ ሰባት

## መደመር እንደ ትውልድ ግንባታ ቀመር

### የክሡትነት ብያኔ

‹‹ክሡትነት›› - መገለጥ፣ ማበብ፣ ከፍ ብሎ መታየት፣ መግዘፍ ከሚሉ የአማርኛ ቃላት ጋር ተቀራራቢነት ያለው ትርጉም ሊሰጠው ይችላል፡፡ አንድን አጋጣሚ ወይም ሁኔታ - ‹‹ክሥተት›› ብለን ስንገልፀው ያ አጋጣሚ ወይም

ሁኔታ ተዓምራዊ የሚመስል መገለጥ የታየበት እና ብዙዎች ይሆናል ብለው ከገመቱት እጅግ የገዘፈ ለውጥ የተፈፀመበት እንደሆነ እንረዳለን። በዚህ የለውጥ ሂደት ውስጥ ብዙሃኑ ሰው ክስተት የመሰለውን ሁኔታ ለመገመት ያልቻለበት አንዱ ምክንያት ክሥተቱ እንዲፈጠር ሰበብ የሆኑ ነገሮች ተናጠላዊ ይዘታቸው እጅግ ጥቃቅን በመሆናቸው ነው። በሌላ አገላለፅ ተነጣጥለው ለብቻቸው ሲታዩ ትርጉም ባለው መልኩ የገዘፈ ሕልውና የማይኖራቸው ጥቃቅን አካላት የሚፈጥሩት የተናበበ ግንኙነት አዲስና የገዘፈ የለውጥ ሥርዓትን ወልዶ ማየቱ ለብዙዎች መደነቅን ይፈጥራል። ስለዚህ አንድን ለውጥ ክስጠት የሚያደርገው የለውጥ ሂደቱና ሂደቱን ያጀቡት ንዑሳን የለውጥ ክፍሎት መጨረሻ ከሚገኘው ውጤት ጋር ሲነፃፀሩ እጅግ አነስተኛ በመሆናቸው ነው።

እንደ መደመር ‹‹ክሡትነት›› ስንል ጥቃቅን የሚመስሉና ችላ የተባሉ ዐቅሞች ተጠራቅመውና የተለየ ግንኙነት ፈጥረው እጅግ ግዙፍ ለውጥ መውለድ የሚችበት ሁኔታ ማለታችን ነው። በትንሽ ተጀምሮ፤ ባለው ላይ እየጨመሩ በሚከናወን ያልተቋረጠ የማሳደግና የመጨመር ሂደት ካብቶ የሚፈጠረው ውጤት እጅግ የዳበረና ግዙፍ እውነታ ነው።

መደመር ያስፈለገበት ምክንያት የሰው ልጆች በእለት ተእለት ኑሮአቸው ብቻ መሆን የሚፈጥርባቸውን ጉድለት (የብቸኝነት ጉድለት)፤ ይኽም ሊያስከትልባቸው የሚችለውን የመጥፋት ሥጋት ለማሸነፍ ሲሉ እርስ በእርስ በሚያደርጓቸው መስተጋብሮሽ የጋራ ብልፅግናን ማምጣት ስለሚቻል ነው። ይኽ የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጠው ሁለንተናዊ ብልፅግና የሚፈጠርበት ሂደት ‹‹ክሡትነት›› ይባላል። ለብቻችን የሚኖረንን ተናጠላዊ ማንነት አቀራርበት ኅብራዊ የጋራ ማንነት መፍጠር ስንችል እሱን ተከትሎ ትርጉም ያለው የጋራ ለውጥ እንደሚመጣ የሚጠቁም ጽንሰ ሐሳብ ነው።

የክሡትነት ጽንሰ ሐሳብ በተሻለ ለመረዳት የሚያስችለን የጉንዳን ሥነ-ፍጥረታዊ አኗኗር ነው። ጉንዳን በፍጥረታት ዓለም ከሚገኙ ሌሎች ፍጥረታት ጋር በንጽጽር ስናየው፤ በአካላዊ ጥንካሬውም ይሁን በአእምሯዊ የማሰላሰል ብልኀቱ፤ ከሌሎች ልቆ የሚገኝ አይደለም። ይሁንና የነፍሳት ዝርያ የሆነው ጉንዳን፤ ከመሰሎቹ ጋር በኅብር ለመኖር የሚፈጥረው የተናበበ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማህበር እጅግ የሚደንቅ ነው። ካላቸው አካላዊ ጥንካሬ አኳያ ተነጣጥለው መኖር ለሕልውና አደጋ ስለሚያጋልጣቸው ከመቶዎች እስከ ሚሊዮኖች አባላት ሊይዝ የሚችል ማህበር መሥርተው፣ እንደ ሰብአዊ ፍጡራን የሥራ ድርሻ ተከፋፍለው በመሠማራት የጋራ ማህበረሰባዊ ሕልውናቸውን ማስቀጠልን ይመርጣሉ። የጉንዳን ማህበር የሚፈጥረው የተሠናሰለ ማህበረሰብ ተነጣጥሎ በብቸኝነት ሊታይ የማይችል፤ የጠነከረ የጋራ ሕልውና ያለው፤ አንድ ወጥና ግዙፍ ሕይወት የሚጋራ ፍጥረት፤ ተደርጎ እስከ መወሰድ የሚደርስ ነው።

እንግዲህ በነጠላነት ስንመለከተው በአካልም ይሁን በአእምሮ ብስለት የተለየ ዐቅም የሌለው ጉንዳን፤ ከመሰሎቹ ጋር ተናብቦ በመኖር፤ ልዕለ ፍጥረት ደረጃ የደረሰ ግዙፍ ሥርዓት ፈጥሯል። ጉንዳን በብቸኝነት ያለውን አቅም አስተባባሮ ከመሰሎቹ ጋር መኖር መቻል ብቻ ሳይሆን፤ ሕልውናውንም አረጋግጧል። ከመደመር አንፃር ክሡትነት የሚገልጥልን እውነት ይኽንኑ ነው። ብቻነት በሚፈጥረው ጉድለት የሚመጣውን

የሕልውና አደጋ በማስወገድ፤ በኅብራዊነት የተረጋገጠ፤ ከፍ ያለ የሕልውና ደረጃ ላይ መድረስ እንደሚቻል ይተነትናል፡፡

ይኽ እውነታ ለሰው ልጆችም ይሠራል፡፡ አነስተኛ የሆኑ ልነቶችን ወደ ጎን በመተው፤ የሚያሰባስብና የሚያስተባብራቸውን ሕልም መፍጠር የቻሉ ማህበረሰቦች ሀገር መስርተው፤ ሕልውናቸውን ከውጭ ወረራ ጠብቀው፤ በተናበበ መንገድ በጋራ የተጓዙት የበለፀገ ሀገርና የሠለጠነ ሀገረ መንግስት ለማቆም ችለዋል፡፡በተቃራኒው ደግሞ ልዩነቶቻቸውን ማቻቻል ያቃተቸው፤አብሮ ለመኖርና የጋራ ሕልውናቸውን ለማስጠበቅ የተሳናቸው ልዩነቶቻቸውን እያሰፉ ወደ እርስ በእርስ ጦርነት ገብተዋል፡፡ በእነርሱ መጋጨት ምክንያት የራሳቸውን ፖለቲካዊ ጥቅም ለማሳደድ ለሚራወጡ ባዕዳን መጠቀሚያ ሆነዋል፤ የማያበራ የጦርነት አዙሪት ውስጥም ተዘፍቀው ሀገር አፍርሰዋል፡፡ ሕዝባቸውን ለሞትና ለስደት፤ ማኅበረሰባቸውን ለብተና ዳርገዋል፡፡ የ‹‹ክሡትነት›› ተቃራኒ የሆነው ‹‹ክስመት›› እጣ ፈንታቸው ሆኗል፡፡

ወደ ሀገራችን መለስ ብለን የክሡትነትን ሁነኛ ምሳሌ ስንፈልግ የአድዋን ድል እናገኛለን፡፡ የአድዋ ድል ፈርጀ ብዙ በሆነ መልኩ ልናየው የምንችለው ድል ነው፡፡ አድዋ የነጭ ቅኝ አገዛዝን ለመመከት የተደረገ ፍልሚያ ብቻ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያውያን ተነጣጥለን በብቸኝነት ቆመን ልናረጋግጠው የማንሞክረውን፤ በኅብረት በመሰለፍ ሕልውናችንን ማስጠበቅ መቻላችንን ያሳየ ታሪክ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን የአድዋ ድል ተነጣጥለን ልንደርስባቸው የማንችላቸውን ታላላቅ ግቦች፤ ብሔር፤ ሃይማኖትና አካባቢያዊነት ሳያግደን በአንድነት ከተሰለፍን፤ ማሳካት እንደምንችል ያረጋገጥንበት ነው፡፡ ክሡትነት ማለት ይህ ነው! በብቸኝነት ልናሳካው የማይቻለንን ተናብቦና ተከባብሮ፤ ተደምሮና ተጣምሮ፤ ለአንድ ዓላማ በመሰለፍ፤ በነባራዊ የተናጠል ዐቅማችን ሊታለም የማይችል ድል መቀዳጀት፡፡ ለብቻችን ጎድለን እንድንቆም የሚያደርጉንን አናሳ እሳቤዎች ወደ ጎን ትተን በጋራ ስንሰለፍ የሚፈጠር፤ መግነጢሳዊ የታላቅነት ኃይል ነው፡፡

ተባብሮ በመኖር የሚፈጠረው ኃይል ክሡትነት ሲሆን፤ አለመተባበርና አለመደመር የሚያመጣውን የኃይል ማጣት ደግሞ የብቸኝነት ጉድለት እንለዋለን፡፡ የብቸኝነት ጉድለት እያነሱ መሄድን፤ እያደጉና እያበቡ ካለመሄድ የሚመነጨውን የመክሰም ሥጋት እና የሕልውና እጦት አደጋ ይገልፅልናል፡፡ ማንኛውም ሕዝብ እንደ ማህበረሰብ ሕልውናውን በዘላቂነት አስጠብቆ መቀጠል የሚችለው በክሡትነት ወደ ፊት ሲሄድ ብቻ ነው፡፡ ባለበት የሚረግጥ በጊዜ ሂደት ያለውን እያጣ ወደ መበስበስ ከዚያም ወደ መክሰም ማምራቱ አይቀሬ ነው፡፡ አዲስ የተሰራ ቤት እንኳን በየጊዜው እየተከፈተ የማይጸዳ፤ ግድግዳና ወለሉ የማይታደስ፤ ውስጡ የማይናፈስ ከሆነ ይበላሻል፡፡ ሸረሪት ድሯን ታደራበታለች፡፡ ዝናብና ፀሐዩ፡ ውርጭና ቁሩ፡ ሙቀትና ቅዝቃዜው ቀስ በቀስ ያደክመዋል፤ የተገነባበት ምሦሶ ይበሰብሳል፡፡ ስለዚህ ቤቱ በጊዜ ሂደት ወደ መፍረስ እንዳያመራ ከተፈለገ፤ ተገቢው እንክብካቤ ሊደረግለት ይገባል፡፡ በዚህ ምሳሌ ክሡትነት በየጊዜው እየታደሰ፤ እየተሻሻለና እየተገነባ የሚሄደውን ቤት የሚገልጽ ሲሆን፤ የብቸኝነት ጉድለት ደግሞ፤ ተገንብቶ የቆመውን፡ ጣራና ግድግዳው፡ ብረትና ምሦሶው፡ የሚጠግነው ያጣውን፡ ቆሻሻ የሞላውን፡ ቤት ይመስላል፡፡

በሌላ የታሪክ ምሳሌ እንየው ካልን የዘመነ መሳፍንትዋ ኢትዮጵያ በተወሰነ መልኩ ለብቸኝነት ጉድለት ማሳያ

ይሆናል፡፡ የዘመኑ የጎበዝ አለቆችን የየአካባቢው መኳንንት ኢትዮጵያን ብዙ ቦታ ሸንሽነው እየገዙ በግዛት ይገባኛል እርስ በእርስ የሚራኮቱበት ሁኔታን ለተመለከተ የኢትዮጵያ የምጽአት ጊዜ ይመስል ነበር፡፡ በዚያን ወቅት ጠንካራ ጠላት ቢመጣ ከባድ መከታ ሳይገጥመው እንዳልነበር የማድረግ እድሉ ሰፊ ነበር፡፡

በአንፃሩ በዘመነ አድዋ ሕልውናችንን ሊያሳጣንና አብሮነታችንን ሊያጠፋ የመጣውን የባዕድ ወራሪ፣ በጋራ ክንዳችን ደቁሰን በማሸነፍ፣ ሀገራዊ የመከሠት ፍላጎታችንን በአንፀባራቂ የድል ታሪክ ጽፈናል፡፡ ከእኛ በተቃራኒ ኃይላቸውን አስተባብረው መሰለፍ ያልቻሉ ሌሎች ሕዝቦች፣ መነጣጠላቸው ከፈጠረው የዐቅም ማጣት የተነሳ፣ አንድ በአንድ ለቅኝ ገዢዎች እጃቸውን እንዲሰጡ አስገድዷቸዋል፡፡ በብቸኝነት ጎድለውና ዐቅም አጥተው ስለተገኙ፣ የቆየ ታሪካቸውን አጥተዋል፣ ባህላዊና ትውፊታዊ ማንነታቸውን ተነጥቀዋል፡፡ በአንፃሩ ተባብሮ፣ ዐቅሙን አሰባስቦ፡ የክሡትነት ኃይሉን አጣምሮ፡ ለመጣ የውጭ ወራሪ ተጋላጭ ሆነዋል፡፡ የታሪክ ጠባሳው ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተወራረሰም፣ አሁንም ድረስ የመነጣጠላቸውና እርስ በእርስ የመጋጨታቸው መነሻ ሆኖ ዘልቋል፡፡

# የክሡትነት መነሻ

ተለምዷዊው አመክንዮ እንደሚነግረን አንድን ትልቅ ሥርዓት መረዳት የሚቻለው፣ ለሥርዓቱ መፈጠር መሠረትና መገንቢያ የሆኑትን ንዑሳን ቅንጣቶች በትኖ በማየት ነው፡፡ በዚህም የሥርዓቱን ምንነትና ቀጣይ ሕይወት መረዳት ይቻላል፡፡ በመሠረታዊ የሂሳብ ቀመርም፣ በቢሊዮን የሚቆጠር ነገር የሚገነባው፡ በውስጡ ባሉ መቶ ሺህና መቶ ሚሊዮን ቁጥሮች፣ ወዘተ መሆኑን ነው፡፡ ይኽንን መሠረታዊ አመክንዮ የተከተሉ ሳይንቲስቶች፣ የአንድን ግዙፍ ቁጥር ምንነት ለመረዳት፣ በውስጡ የሚይዛቸውን ትንንሽ መጠን ያላቸውን ቁጥሮች በማወቅና በማስላት፣ በቀላሉ የትልቁን ቁጥር ትርጉም ማግኘት ይቻላል ብለው ያስቡ ነበር፡፡

የዚህ እሳቤ ተከታይ የሆኑ የፊዚክስ ልሂቃን፣ ዩኒቨርስን፣ ፕላኔቶችንና ሌሎች ግዙፍ አካላዊ ቅርፅ ያላቸውን ነገሮች ለማወቅና የወደፊት እንቅስቃሴያቸውን ለመተንበይ፣ ግዙፍ ቁሶችን፣ ፕላኔቶችንና ዐለቶችን፡ ‹‹የሚገነባበትን የቁስ ቅንጣት ወይንም አቶም መረዳት በቂ ነው›› የሚል፣ እውቀትን አቅልሎ መመልከት አዝማሚያ ነበራቸው፡፡ የሥነ-ሕይወት ዐዋቂዎችም፣ በዙሪያችን የሚገኙ ሕይወት ያላቸው ፍጥረታትን አመጣጥና የወደፊት ሕልውና ለመረዳት፣ ለእያንዳንዱ ፍጥረት መሠረት የሆነውን ‹‹የሥነ-ሕይወት ሕዋስ ማወቅ በቂ ነው›› የሚል ሐሳብ ያቀርቡ ነበር፡፡

ሆኖም የኋላ ኋላ የሰው ልጅ ምርምር እያደገና ስለአካባቢውም የበለጠ እየተገነዘበ በመጣበት ወቅት የሚገኙ አዳዲስ ግኝቶች፣ ‹‹ትልቁን ሥርዓት ለመረዳት በውስጡ ያቀፈውን ትናንሽ ሥርዓቶችን ማወቅና፡ ያንን መሠረት አድርጎ ስለትልቁ ሥርዓት መተንበይ ይቻላል›› የሚለው ገዢ እሳቤ እየተሸረሸረ በመሄድ አዲስ እሳቤ መጣ፡፡

በተፈጥሯዊ አካላዊ ቁመናቸው አነስተኛና በማሰላሰል ብልኀታቸውም ከአቻ ፍጥረት እምብዛም የማይልቁ ጥቃቅን ነፍሳት፤ ቀላል የሆኑ የኑሮና የግንኙነት መርሆችን በመከተል ብቻ፤ ተባብረውና ተሠናኝተው የሚፈጥሩት የጋርዮሽ ሥርዓት፤ በአካልና በአእምሮ የሚልቋቸው አቻዎቻቸው ከሚፈጥሩት የሚስተካከል፤ በአንዳንድ ሁኔታዎችም የላቀ ሥርዓት መገንባት መቻላቸው ታየ። በአንፃሩ ደካማ የሆኑ ነፍሳት፤ በአካል የገዘፉና በማሰብ ዐቅማቸው የረቀቁ እንስሳት ሕልውናቸውን አስጠብቀው መዝለቅ በማይችሉባቸው ለኑሮ በማይመቹ ሥነ-ምኅዳሮቹ ውስጥ እንኳ በሰፊው ተንሠራፍተው መኖር እንደሚችሉ ታወቀ።

አካላዊ ብቃትና የአስተሳሰብ መብሰል፤ በፍጥረታት ዓለም ሕልውናን ለማስቀጠል እንደ ቁልፍ ጉዳይ ይታይ ነበረ። ሆኖም አዳዲስ መረጃዎች ነባሩን ዕይታ በመቀየር፤ አነስተኛ ዐቅም ያላቸው ፍጥረታት ተፈጥሮ የለገሠቻቸውን ዐቅም አስተባብረው ከተጋገዙ፤ የጋራ ሕልውናቸውን በላቀ ደረጃ ማስቀጠል የሚችልበት ዕድል እንዳለ አረጋገጡ። በተፈጥሯዊም ይሁን በሰው ሠራሹ ዓለም ሕልውናን አስጠብቆ ለመዝለቅ ቁልፉ ጉዳይ፤ በተፈጥሮ ከሚገኝ አካላዊና አእምሯዊ የበላይነት ይልቅ፤ በኅብረት የሚፈጠር የተደመረ ዐቅም እንደሚሻል ታይቷል። ይኽም ‹‹በተፈጥሮ ከፍተኛ ዐቅም ገንብቶ መገኘት የበላይ ያደርጋል›› የሚለውን ነባሩን ፓራዳይም ያመሳቀለ አዲስ ዕይታ ነበር።

ይኽ የፓራዳይም ለውጥ የቁስ አካላትን አመጣጥ፤ ዑደትና የወደፊት ሁኔታ በሚመረምረው የፊዚክስ ዘርፍም ታይቷል። ከዚህም የተነሳ ‹‹የፕላኔቶችንና የቁስ አካላት ንዑሳን ክፍል የሆኑትን የአቶም ቅንጣቶች በማጥናት፤ አካላዊና ኢ-አካላዊ ነገሮችን መረዳት ይቻላል›› የሚለው እሳቤ እየተለወጠ መጥቷል። ከሚጨበጥ ነገር የማይጨበጠውን፤ ከሚታየው ላይ የማይታየውን፤ ለመረዳት ይቻላል የሚለው አስተሳሰብ ተሸንፏል። ለዚህ ጉልህ ማሳያ የሚሆኑት በሰው ልጅ አእምሮ ላይ ይደረጉ የነበሩ ምርምሮች ናቸው።

የሰው ልጅ አንጎል የተሠራባቸውን የኒውሮን ቅንጣቶች በማጥናት፤ ሐሳብ ማመንጨት፤ ማሰላሰልና ማፍቀር የሚችልን የሰው አእምሮ ማወቅ እንደማይቻል ግልፅ ሆኗል። የሰው ልጅ አእምሮ፤ በተናጠል ሲታዩ ደካማ የሆኑ ሥነ-ሕይወታዊ የኒውሮን ሴሎች ልክ የሙዚቃ መሣሪያዎች ሕብር ሠርተው የሚፈጥሩት ግንኙነት ጥዑም ዜማን እንደሚያስገኝ ሁሉ የኒውሮን ሴሎች በሰው አእምሮ ውስጥ የሚፈጥሩት ስንኝትና የኤሌክትሪክ መልዕክቶች ልውውጥ ሐሳብን ይፈጥራል። ነገር ግን አካላዊ ከሆኑ የኒውሮን ሕዋሳት ጥናት በመነሳት፤ ምጡቁን የሰው ሐሳብ አፍላቂ አካል ምንነት መረዳት እንደማይቻል ታውቋል። በመሆኑም ‹‹ንዑሳን አካላትን ነጥሎ በመመልከት፤ ንዑሳን የሚፈጥሩት ታላቅ ኅብራዊ ሥርዓት መተንበይ ያዳግታል›› የሚለው አመለካከት ቅቡልነቱ ሰፍቷል። ይኽም አዲሱን እውነት የሚያብራራው፡ የክሱትነት ፓራዳይም ተቀባይነት እንዲያገኝ ምክንያት ሆኗል።

# ክሡትነት እንደ እውነት

ክሡትነት ከትንሽነት ተነሥቶ፤ በመደመር ወደሚገኝ ታላቅነት የሚደረግ ጉዞ ብቻ ሳይሆን እውነትንና ዕውቀትንም የምንገልጥበት መንገድ ነው። በክሡትነት እውነትና ዕውቀት ተጉዘን የምንጨርሰው፤ ሄደን

የምንደርስበት መዳረሻ አለመሆኑን እንረዳለን። እውነትን ከሰው ልጆች የአስተሳሰብና የፍላጎት ማዕቀፍ ተነጥሎ የሚገኝ፤ ከተቀመጠበት ሥፍራ በሳይንሳዊ ምርመራ የምንደርስበት ነገር አድርገን አንመለከተውም። ይልቁንም እውነትና እውቀት የሰው ልጆች ሕልውናችንን ለማረጋገጥ በምናደርገው የዕለት ተዕለት ትግል ውስጥ፤ እየተገበርነው የሚሠራ መሆኑን ፈጥነን የምናረጋግጠው ነው። አንገብጋቢ ችግሮቻችንን በተጨባጭ በመፍታት፤ ዐቅሙን እየፈተንን እውነትነቱን የምንመሰክርለት፤ ሂደት ላይ የተመሠረተ ጉዳይ ነው። የክሡትነት ዕውቀት እውነትን በተግባር በማረጋገጥና ሞክረን በመገምገም ሐቁን መርምረን የምናገኝበት ሂደት ነው።

በአንፃሩ እየኖርን ያልፈተሸነው ጥቅል ዕውቀት ምሉዕነት ይጎድለዋል። በተግባር ሳያዩ ‹‹ይኸ ነው›› ብለው ፈርጀው በመነሳት የሚገኝ ዕውቀት አቅላይ ከመሆኑ አያመልጥም። አቅላዮች የነገርን ሁለንተናዊ መነሻ በተግባር ፈትኖ ከመረዳት በተቃራኒ የጉዳዩን ውሱን መልኮች ለይቶ በማላከክ፤ ለሁሉም ነገር መነሻ የተለዩትን ቁንጽል እውነቶች ብቸኛ መሠረት አድርገው ያቀርባሉ። ‹‹ኢኮኖሚው - ለማኅበረ ፖለቲካዊ ግንኙነታችን ወሳኝ ነው›› ብለው የሚያምኑ፤ ኢኮኖሚውን የችግሮች ሁሉ ምንጭ ያደርጉታል። ለኢኮኖሚው ውድቀት ምንጭ መንግስት ነው ብለው የሚነሡ አካላት ደግሞ፤ መንግስት የተዳከመ ሚና እንዲኖረው ማድረግ ብቻ ብልፅግናን ያረጋግጣል ይሉናል። ‹‹በነጻ ገበያ ሥርዓት የግሉን ዘርፍ ማስፋፋት ለፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ጠንቅ ነው›› የሚሉት ደግሞ፤ የመንግስት እጅ የረዘመ እንዲሆን ይመክራሉ።

በክሡትነት ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ቀውሶችን ለመፍታት፤ የችግር ትንተናችንን ሁሉን አቀፍ፤ ዕይታችንም ምሉዕ እንዲሆን ማድረግ አለብን። ቀውሶች በአንድ ሰበብ ወይም ምክንያት ላይ ብቻ አይንጠለጠሉም። ከትንሹ ግለሰባዊ ዋልጌነት አንስቶ፤ እስከ ትላልቆቹ የሥርዓት ጉድለቶች ድረስ፤ የተለያዩ ነገሮች የችግር ምንጮችና መነሻዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ሁሉም በጊዜ ሂደት ዳብረውና ተነባብረው የሚፈጥሩት የቀውስ ክስተት፤ በሂደት ጎልቶ በቀላሉ ለመፍታት የሚያስቸግር ቀውስ ያስከትላል።

በክሡትነት እሳቤ፤ ችግርም ሆነ መፍትሔ የችግሩ ባለቤቶች፤ ችግሩ እንዲፈታላቸው ከመፈለግ በሚመነጭ ቅን መንፈስ ተነሣሥተው በሚያካሂዱት የጋራ ጥረት የሚፈጠር እውነት ነው። ዕውቀት ጥቂት በበራላቸው ልሂቃን በሞኖፖሊ የሚያዝ አይደለም፤ ይልቁንም እያንዳንዱ ማኅበረሰብ በተጨባጭ የሚያጋጥመውን ችግር ለመፍታት በሚያደርገው ተግባራዊ ሙከራ የሚገኝ እንጂ። ዴሞክራሲያዊ በሆነ ሥርዓት በሚደረግ የችግር አፈታት ሂደት በውይይት ሁሉም የጋራ የሚያደርገው ነገር ነው።

ፖለቲካም በዚሁ መልኩ የሚታይ ነው። ፖለቲካ ሰፊው ሕዝብ ተገልሎ፤ ጥቂት ልሂቃን በብቸኝነት የሚዋኙበት ገንዳ አይደለም። ሰፊው ሕዝብ በዴሞክራሲያዊ መጫወቻ ሜዳው የተቀመጡ ሕጎችን ተከትሎ፤ በእኩልነት ድምፁን የሚያሰማበት፡ ያገባኛል ብሎ በሚያስበው የሀገሩ ጉዳይ ላይ በእኩልነት እየተሳተፈ መፍትሔ የሚያፈልቅበት መድረክ ነው።

በዚህ መልኩ ሲቀረጽ ፖለቲካ አዳዲስ አማራጭ ሐሳቦች የሚገኙበት፤ ለችግሮች መፍትሔ የሚፈጠርበት፤ ለአዲስ የፖለቲካ ኢኮኖሚ መከሰትም መደላድል የሚፈጥር ይሆናል። በንዑሳን ቁጥጥር ሥር የሚወድቅ ፖለቲካ፤ አዳዲስ መፍትሔ የማይመነጭበት፤ ባለበት የሚቆም፤ መለወጥ የማይችልና አምባገነናዊ ሥርዓትን

የሚያሰፍን ይሆናል። በዚህም የተነሳ በቀላሉ ለመበስበስ የሚጋለጥ፤ እየተለወጠ በመሄድ ክሡትነትን ማረጋገጥ የማይችል ይሆናል።

# ክሡትነትና የሀገራችን ፖለቲካ

ምንም እንኳን ሀገራችን የቆየ የሀገረ መንግሥትነት ታሪክ ቢኖራትም ከእኛ ያነሰ ታሪካዊ ቆይታ ያላቸው ሀገራት ከሚገኙበት የኢኮኖሚና የፖለቲካ ዕድገት ደረጃ ዝቅ ያለ ሥፍራ ይዛ ትገኛለች። ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካ ሁኔታችንን ለመቀየር የተደረጉ ጥረቶች ባለመሳካታቸው፤ የሀገራችን ጉስቁልና እየከፋ ሄዷል።

ለዚህ ተቀባይነት የሌለው ሁኔታችን በምክንያትነት የሚቀርቡ የተለያዩ ሰበቦች አሉ። የሀገረ መንግስቱ በዘመናዊ መልኩ ከተደራጀበት ጊዜ አንስቶ ያጋጠመውና፤ አሁንም ድረስ ሊፈታ ያልቻለው ሥር የሰደደ የቅቡልነት ጉድለት ግን ዋናው ነው። የቅቡልነት ጉድለት በገጠመው ሀገረ መንግስታችን የተነሣ፤ ‹‹ኮሽ ባለ ቁጥር ሀገር ትፈርስ ይሆን?›› እያሉ መሥጋትን የሠርክ ተግባራችን እንዲሆን አድርጓል። ለዚህ ሁኔታ የዳረገንን ሥር ለማግኘት ሀገረ መንግስታችን በዘመናዊ መልኩ ከተገነባበት ጀምሮ ያለፍንባቸውን የፖለቲካ አካሄዶች መመርመር ያስፈልጋል።

ከዘመናዊ የሀገረ መንግስታችን ምሥረታ ቀደምት የነበሩ የታሪክ ወቅቶች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ሃይማኖታዊና ባህላዊ የትውፊት መሠረት ስለነበራቸው፤ ሕዝቦች የራሳቸውን አካባቢያዊ መንግስታዊ መዋቅር ዘርግተው የሚተዳደሩበት ሥርዓት ነበራቸው። በወቅቱ እነዚህ መንግስታዊ አደረጃጀት የነበራቸው አካባባያዊ አስተዳደሮች፤ በውስጣቸው የባህልና የሃይማኖት ብዝሃነታቸውን የተመጠነ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፤ በተመሠረቱበት ቀጣና የቅቡልነት ችግር እምብዛም የሚስተዋልባቸው አልነበሩም።

ሆኖም ዘመናዊ ሀገረ መንግስቱ ሲስፋፋ ፈተናዎች መታየት ጀመሩ። የሀገረ መንግሥት መስፋፋቱ የተከተላቸው አካሄዶች እና ሲጸናም የተመራባቸው መርሖች፤ ነባራዊውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ አስገብተው የተቃኙ አልነበሩም።

በሀገረ መንግሥት ምሥረታ ወቅት የተለያየ የታሪክ፤ የብሔርና የሃይማኖት ማንነት ያላቸው ሕዝቦች፤ ወደ አንድ አስተዳደራዊ መዋቅር መካተታቸው አይቀሬ መሆኑ ይታመናል። መሠረታዊው ጉዳይ፤ ብዝኃነትን ከሀገረ መንግስት አንድነት ጋር አጣጥሞ እንዴት ይመሠረታል? የሚለው ነው። ብዝኃነት የሕዝቡ ማኅበራዊ ሥሪት ነው። ነገር ግን በሀገረ መንግሥት ምሥረታው ሂደት፤ ብዝኃነቱን ከሀገራዊ አንድነቱ ጋር የሚያጣምርና ሁሉንም ሕዝቦች በእኩልነት በማቀፍ፤ የሀገር ስሜትን የሚያጎለብት ሥርዓት ለማዋቀር አልተቻለም። ለትውልድ የዘለቀ የመገፋት ስሜት የተፈጠረባቸው ማኅበረሰቦች ነበሩ። በዚህ የተነሳ ሀገረ መንግሥቱ በሁሉም የሀገሪቱ ሕዝቦች ዘንድ ተመጣጣኝ ቅቡልነት ሊኖረው አልቻለም።

የቅቡልነት ችግሩን ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶች ሁለት ዓይነት መልክ እንደነበራቸው መመልከት ይቻላል። ቀዳሚው የሀገራችንን ብዝሀነት ለሀገረ መንግስቱ እንደ ችግር ምንጭ አድርጎ የሚያየው አመለካከት ነበር።

ብዝኃነቱን የቅቡልነት ችግር ምንጭ የሚያደርገው ዕይታ እንደ መፍትሔ አስቀምጦ የተንቀሳቀሰው፤ ሕዝቡን የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ማድረግ ነበር። ሆኖም ሙከራው ፈተና ገጠመው። ይኽ ለሺ ዘመናት የቆየውን የኢትዮጵያን የብዝኃነት ጠባይ ለመለወጥ የተነሳው የመፍትሔ መንገድ ብዝኃነትን ለማጥፋት እንጂ ለማቀፍ ባለመሞከሩ የታለመው አንድነትን በአንድ ዓይነትነት የማምጣት ዕቅድ ከሸፈ። ተመሳሳይነትን በመፍጠር በሚገኝ አንድነት፤ የሀገረ መንግስቱን የቅቡልነት ጉድለት የመፍታት ሙከራ፤ ልዩነትን ለሚያጠናክሩ ኃይሎች በሩን ወለል አድርጎ ከፍቶ ሄዷል።

አንድነትን በአንድ ዓይነትነት ለማምጣት የተደረገው አክሳሪ ሙከራ የፈጠራቸውን ምቹ ሁኔታዎች ግብአት አድርጎ፤ የወታደሩን መንግስት ገልብጦ ሌላ ኃይል ወደ ሥልጣን አመጣ። ይኽ ኃይልም የቀደመውን አካሄድ በተቃራኒ አቅጣጫ ገልብጦ ተገበረው። የሀገረ መንግስቱን አደረጃጀት ብዝኃነትን ብቻ መሠረት አድርጎ እንዲዋቀር በማድረግ፤ የቅቡልነት ጉድለቱን እቀርፋለሁ ብሎ ተንቀሳቀሰ። ሆኖም ብዝኃነትን አስጠብቃለሁ ያለው ሥርዓት፤ ከጅመሩ በነበረበት የፍትዊነት ችግር፤ የአንድን ቡድን የበላይነት ወደሚያስጠብቅ የሕዳጣን አምባገነናዊ ሥርዓት ተሸጋገረ። በብዝኃነት ላይ ብቻ በማትኮር፡ ለዘመናት አስተሣሥረው ያቆዩንን የአንድነት ገመዶች በጣጠሳቸው። በዚህም ብዝኃነታችን ለመለያየትና ለመራራቅ ምክንያት የሆነበትን ሥርዓት ገነባ። ተስፋ የተጣለበት ኅብረ ብሔራዊ የፌዴራል ሥርዓትም፤ አንድነትን ከእኩልነት ጋር ደርቦ የማረጋገጥን ሕልም መና አደረገው።

የክሡትነትን የዕይታ ማዕቀፍን መነሻ አድርገን ያለፍንበትን የታሪክ ሂደት ስንቃኝ፤ የቀደመው ሀገር የማትጽናት ሙከራችን ለውድቀት እንዲዳረግ መነሻ የሆኑ ጉዳዮችን እንድናይ ያግዘናል። የሀገራችን የፖለቲካ ችግሮች መነሻቸው ጥልቅና ውስብስብ በመሆኑ፤ ችግሮቻችንን የምናይበት መነጽርም አዙሮ የሚመለከት፤ ሁሉን አቀፍና አሰላሳይ መሆን ይገባዋል። ችግሮቻችን በአንድ ምሽት የመጡ ሳይሆን፤ መዋቅራዊ ቅርፅ ያላቸው፤ ተደራራቢና ውስብስብ፤ ምንጪ-ብዙ ናቸው። የሀገረ መንግስታችን የቅቡልነት እጦት አንኳር ጉዳይ፤ የችግሮች መደራረብና በአንድነት መምጣት የፈጠረው፤ የቀውስ ክሡትነት ነው። ውስብስብ ችግሮቻችንን መፍታት የሚችለውም፤ የተሠናኘ የሁሉንም ትብብር የሚጠይቅ፤ ሕዝብና ልሂቃን በአንድነት በመሰለፍ የሚፈጥሩት መፍትሄ ነው። ይኽ ነው የቀውስ ክሱትነትን ሊያስወግድ የሚችለው።

ሆኖም ከዚህ ቀደም የሞከርናቸው ሁለት የፖለቲካ አቅጣጫዎች፤ የሁሉንም መፍትሔ አመንጪነትና ትብብር የሚያረጋግጡ፤ ከችግሮቻችን በተባበረ ክንድ አምልጠን የምንወጣባቸውና፤ ክሡትነትን የምናረጋግጥባቸው ሊሆኑ አልቻሉም። ውስብስቡን ችግራችንን በቅጡ ከመረዳት ይልቅ፤ ችግሮቻችንን በአንድ ጉዳይ ላይ በማላከክ፤ አቅላይነት የተጠናወተው መፍትሔ ለማምጣት ሮጥን። የብዝኃነት መኖርን በራሱ የሕልውና አደጋ አድርገን ቆጥረን፤ ብዝኃነትን ያጠፋልናል ያልነውን አንድ ዓይነት ማህበረሰብ የመፍጠር ፖሊሲ እንደ መፍትሔ ተከተልን።

አሐዳዊነቱ አልሳካ ሲል ደግሞ፤ የችግሩ ምንጭ አንድ መሆናችን ነው አልን። ከዚያም እንደ ሀገር ለመቀጠል እንድንችል፤ የሚሰበስቡንን ተቋሞቻችንን የሚያፈራርስና ልዩነቶቻችንን የሚያጎላ ሥርዓት ገነባን። በብዝኃነትና

በአንድነት ላይ በተናጠል የተንጠለጠለ አቅላይ የችግር አረዳድ፤ የቀውሱን ውስብስብነትና ትሥሥር በምልዐት እንዳንመለከት ጋረደን። ለፍረጃ የተመቹ አቅላይ ምክንያቶችን ደርድረን፤ ቁንጽል መፍትሔ አመነጨን።

አንዱ ብዝኃነትን በማጥፋት፤ ሌላው ልዩነትን የሙጥኝ በማለት፤ አላካኪ የችግር ትንተና ፈጠርን። በውጤቱም አቅላይ የሆነ የመፍትሔ አማራጭ ተከተልን።

በመደመር የክሡትነት ዕይታ፤ የኢትዮጵያ የዘለቁ ችግሮች፤ በአንዱ ወይም በሌላው ምክንያት ላይ በማላከክ የሚገልፁ አይደሉም። ችግሮችን በምልዐት በመመልከት፤ ተውሰብስበውና ተሣሥረው የፈጠሩትን ቀውሶች በመመርመር፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሻገሩ እንዳይሆኑ በማድረግ፤ ከችግሮቹ በክሡትነት የሚወጣ ማህበረሰብን ለመገንባት የሚችል፤ ምሉዕ ዕይታ መፈጠር ይገባዋል።

የመደመር እሳቤአችን - በውስጧ ባቀፈቻቸው የብሔርና የሃይማኖት ማንነቶች ኅብር ፈክታ የምትወጣ ኢትዮጵያን የሚያልም ነው። በብሔርና በሃይማኖት ማንነታችን ታጥረን ስንታይ ደካሞችና ለታላቅነት የሚያበቃ ዐቅም የሌለን ብንመስልም፤ ተሠናስለን፤ ተከባብረንና፤ ተባብረን ለጋራ ግብ ብንሰለፍ፤ ሁሉንም ነገር መለወጥ እንችላለን። ተነጣጥለን በመቆም፡ በብቸኝነት ኀድለን ልናሳካው የማችለውን ታላቅነት፤ በኅብረት ተደማምጠን፡ ተነጋግረን በምንፈጥረው የተባበረ ክንድ ከታላላቆቹ ተርታ መቆም እንችላለን። መደመር በዚህ መንገድ ክሡትነት ማምጣት እንደምንችል ተስፋ የሚያደርግ ዕይታ ነው።

ስለዚህም የምንፈጥረው የመደመር ትውልድ፤ ልዩነቱን የሚያከብርና አንድነቱን ሚያጠናክር ነው። በግልና በማህበር ያለው ማንነቱ አይጋጭበትም። ልዩነትን የውበትና የዐቅም ምንጭ አድርጎ እንጂ፤ የመበላለጫ ምክንያት አድርጎ አይቆጥረውም። እኩልነትን በአንድ ዓይነት ውስጥ ሳይሆን፤ በመከባበርና አብሮ በማሸነፍ እሴቶቹ ውስጥ የሚያይ ትውልድ ነው።

የመደመር ትውልድ የ‹‹ድር ቢያብር አንበሳ ያስር›› እና የ‹‹ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክም፤ ለሃምሳ ሰው ጌጥ›› ጥበብን በተግባር የተቀበለ ነው። ደስታውን በመጋራት የሚያበዛ፤ ችግሩንም በመካፈል የሚቀንስ አስተሳሰብና ባህልን መፍጠር የሚችል ነው። ፍትሕና ርትዕ የሞላበትን ስርዓት በመፍጠር ያምናል። ራሱን በሌላው ቦታ አድርጎ የማየት ብቃት ስላለው፤ የሌላውን ችግር የመረዳት፤ ከፍተትን የመሙላት፤ ብሎም አብሮ ማሸነፍን የመጀመሪያ ምርጫው አድርጎ የሚንቀሳቀስ ትውልድ ነው። ካለፈው ትውልድ ተምሮ፡ ለመጪው ትውልድ አስቦ፤ የራሱን አሻራ በዘመኑ ላይ የማስቀመጥ ብቃቱ ከፍ ያለ ነው።

የካፒታሊዝምን ውድድርና የስኬት ረሃብ፤ የኮሙኒዝምን ጭቆና ጠልነትና ለተጠቃ አጋዥነት አያጣርስቻውም። ይልቁንም በመደመር እሳቤ ውስጥ፤ አንዱን የሌላው ማሚያ አድርጎ ይቀበላቸዋል። እንዲሟሉ አድርጎም ያጣጥማቸዋል። ይኽ ትውልድ ተግቶ በመሥራት፤ ፈጥሮ በማደግ፤ አካፍሎ በመኖርና ተወያይቶ በሐሳብ ብልጫ በማሸነፍ ያምናል።

ይህ ትውልድ ኢትዮጵያዊነቱን ከአፍሪካዊነቱ፤ አፍሪካዊነቱን ከዓለም አቀፋዊነቱ ያጣመረ ነው። ተፈጥሮን

የሚንከባከብ፤ አካባቢውን የሚጠብቅና ሀገሩን የሚወድድ ትውልድ ነው። በጦርነት ከማሸነፍ ይልቅ በሰላም መኖርን የጀግንነት ምልክት አድርጎ ይቆጥራል። ሀገሩ ካለፈው ትውልድ የተረከባት ብትሆንም፤ ከሚቀጥለው ትውልድ የተዋሳት መሆኗንም ያምናል። ስለዚህም ለሚቀጥለው ትውልድ ሊከፍለው የሚችለው ብቸኛ ወሮታ፤ ከተቀበለበት ሁኔታ የተሻለችና የበለጸገች ሀገርን መፍር እንደሆነ በጥልቅ ያምናል።

ሰፊውን ዕይታ በመጠበቅ በዝርዝር ጉዳዮችዋ ላይ ኃላፊነቱን በየዕከቱ ለመወጣት ይሞክራል። የጊዜን፤ የሥራንና የሐሳብን ዋጋ በተናጠልና በጥምረት ይረዳል። በዓለም ዙሪያ የሚካሄዱ ለውጦችን በቅርበት እየተከታተለና እየተሳተፈ፤ የሀገሩን የመጪ ዘመን ዕጣ ፈንታ በሌሎች ሳይሆን በራሱ ለመወሰን በንቃት ይቆማል።

# ምዕራፍ ስምንት

## አዲሱ መደመር ትውልድ - ባህርያትና መለያ ቀለማት

# አዲሱን ትውልድ መረዳት

እንደ ግለሰቦች ሁሉ እያንዳንዱ ትውልድ የራሱ መልክና መለያ ባህርያት አሉት። በአንድ ትውልድ ውስጥ ያሉ ሰዎች፤ በልጅነትና በወጣትነት እድሜያቸው የሚያልፉበት በጎና ክፉ አጋጣሚዎች፤ እድሎችና ችግሮች ተመሳሳይ በመሆናቸው፤ ባህሪያቸውም ተቀራራቢ ይሆናል። በተጨማሪም አካባቢያዊና፤ ሀገራዊ ዓለም አቀፋዊ ሁነቶችን ተጋርተው ስለሚያልፉ፤ የሕይወት ዕይታቸው ተመሳሳይ ይሆናል። ተፅዕኖ ፈጣሪ ክሥተቶችና ግለሰቦች በትውልድ ቀረፃ ላይ ያላቸው ተፅዕኖም ከፍ ያለ ሊሆን ይችላል።

ከአራት ዓመታት በፊት ለውጡ ሲከሰት፤ እድሜያቸው በአስራዎቹና ከዚያም በታች የነበሩት ታዳጊዎችን የአንድ ዘመን ትውልድ ልንላቸው እንችላለን። ምንም እንኳን ገና የራሳቸውን መንገድ መርጠው፤ የራሳቸውንም ኑሮ ኖረው ጠባያቸውን ባናውቅም፤ ከእነርሱ በፊት ከነበረው ውል አልባው ትውልድ በብዙ እንደሚለዩ አያጠራጥርም። ከለውጡ በፊትና በኋላ ያሉት ጥቂት ዓመታትም፤ ከስድሳ ስድስቱ አብዮትና ከሰማንያ ሦስቱ ለውጥ በላይ ትውልድን የመቅረጽና የመፍጠር ኃይል እንዳለቸው እሙን ነው።

ይኸ ትውልድ ገና ተሠርቶ ያላለቀ እንደመሆኑ መጠን፤ ከእነርሱ ቀድመን ያለን ትውልድ አንዱ ኃላፊነታችን፤ በዚህ ትውልድ ላይ በጎ አሻራችንን ማኖር ነው። በዘመነ መደመር የተፈጠረው አዲስ ትውልድ፤ የኢትዮጵያንና የአፍሪካን መጻኢ ዕጣ ፈንታ የመወሰን እድል ያለው፤ ሀገራችንና አህጉራችን በከፍተኛ የሕልውና ፈተና ውስጥ ባሉበት ታሪካዊ ዘመን የተፈጠረ ነው። ምናልባት ከአሁን ቀደም በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥረው ያለፉትን ትውልዶች ሰይሞ፤ ዐቅዶና ተጨንቆ ተጠብቦ በመኮትኮት ለመቅረፅ ያሰበ የቀደመ ትውልድ ያለ አይመስለኝም።

አዲሱን የመደመር ትውልድ ለመረዳት በከፊልም ቢሆን እያሳየ ያለውን ጠባይና በመደመር እሳቤ በሚገባ ተቀርጾ ሲወጣ ሊያሳይ የሚገባቸውን ባህርያት መመልከት ያስፈልጋል። የትውልዱን መልክና ጠባይ ከሚወስኑ ኃይላት መካከል በመደመር ዘመን የኢትዮጵያችን ቅርጽና መልክ ምን ይመስላል? ወይንም ምን ሊመስል ይገባዋል? የሚለውን ሐሳብ ማጤን ያስፈልጋል።

የአዲሲቱ ኢትዮጵያ ዋነኛ ባለቤት የሆነው የመደመር ትውልድ ከቀደሙ ትውልዶች የተለየ እንደሚሆን እሙን ነው። የመደመር ዘመኗ ኢትዮጵያ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ያለባት፤ የወንድማማችነት እሴት የጸናበት፤ የሲቪክ ባህል የጎለበተባትና ቀጠናዊ ትሥሥር የጠነከረባት ትሆናለች። ኅብረ ብሔራዊ አንድነቷ እውነተኛ ፌዴራሊዝምን ተግባሪ፤ ብዝኃ ማንነትን አቃፊና ብዝኃ ልሳንን አስተናጋጅ ይሆናል። ሌላውን እንደራሱ የሚመለከት፤ ብሔሩንና ሀገራዊ ብሔርተኝነትን ያስታረቀ፤ የትናንቱን በጎ ነገር ይዞ የትናንቱን ሥህተት የሚያርም፤ ትናንትን ከዛሬና ከነገ ያስማማል በእነዚህ ጉዳዮች የልሂቃንን ስምምነት በማምጣት፡ ሀገራዊ መግባባትና እርቅን የሚያሰፍን ትውልድ ይፈጠርባታል።

በስምምነትና በመግባባት የጋራና አስታራቂ ሕጎችን በመፍጠር የሚገነቡ ተቋማት፤ ሰላሟንና ብልፅግናዋን ያረጋግጡላታል። የጎረቤቶቿን ሰላምን ዕድገት እንደ ራስዋ የምትመለከት፤ በጋራ ለማደግ ያለመ አካሄድን

የምትከተል፤ በንግድና በሌሎች ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ለመተሣሠር የምትሻ፤ ቀጣናዊና አህጉራዊ ግንኙነቶቿን በመደመር መር የምትመራ ሀገር ትሆናለች።

አዲሲቷ ኢትዮጵያ ስትፈጠር አብሯት የሚመጣው ትውልድ፤ የሀገሪቱን ሕልም እውን የሚያደርግና፤ የዘመናት ምኞቷ ከማሳካት ጋር የተጣጣመ ይሆናል። የመደመር ትውልድ መለያ ባህርያት ከሆኑት መካከል፤ አዲስ ነገርን ለመማርና ለማወቅ ያለ ጥልቅ ጉጉት፤ በምክንያት በሐሳብ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ጥልቅ የውይይት ባህል፤ ውበትን የማድነቅ ልማድ፤ ለሰብዓዊ ክብር ቅድሚያ የመስጠት አኗኗር፤ በሁለንተናዊ ዐርበኝነት የሚገለጥ የሀገር ፍቅር ስሜት ጎልቶ የሚወጣበት ይሆናል።

የትውልዱን ባህርያት ለመገንባት፤ ካለፈው የተላለፉ አፍራሽ ባህሎችን በመተው፤ ካለፈው የተወረሱትን በጎ ወረቶች ለማስቀጠል ጥረት ይደረጋል። እነዚህም ላመኑበት ዓላማ መስዋዕት መሆን፤ ከፍተኛ ሀገር ወዳድነት፤ ሰፊ የመሠረተ ልማት ሥራዎችና ታላላቅ ፕሮጀክቶችን ደፍሮ የመሥራት ወረቶች ናቸው። የመደመር ትውልድ ዋነኛ ባህርይ ጥበበኝነት ነው። ይህም መልከ ብዙ መገለጫዎችና ከትውልዱ ጋር የሚዋሃድበት ሂደቶች ይኖሩታል።

## ጥበብ እንደ ባህል ኢንዱስትሪ

ባህልን ያጠኑ ሊቃውንት የተለያዩ ትርጓሜዎች ሰጥተውታል። በአጠቃላይ ባህልን ለመተርጎም ከመሞከር ግን የሚይዛቸውን ነገሮች ማሳየት የተሻለ መሆኑን አጥኚዎቹ ይገልጣሉ። ባህል በውሥጡ ቋንቋን፤ አለባበስን፤ የአኗኗር ዘይቤን፤ የጥበብ ዘርፎችን፤ አስተሳሰብን፤ የሥነ-ምግባር ደንቦችን፤ የእምነት ሥርዓቶችን፤ መጠቀሚያ ቁሳቁሶችንና የመሳሰሉትን የሚይዝ የሰው ልጅ የተከማቸ ሀብት ነው።

ከዚህም በመነሳት ባህል የሰው ልጆች የኑሮ ቅርጽ ነው ማለት እንችላለን። መብላት፣ መጠጣት፣ መዝናናት፣ ማሰብ፣ መሥራት፣ መናገር፣ ወዘተ የዕለት ተዕለት የኑሮ ክዋኔዎች፤ በየትኛውም የዓለም ዳርቻ በሰው ልጆች የሚከወኑ ጥቅል የኑሮ ይዘቶች ሲሆኑ፤ እነዚህን የሚከውኑበት ቅርጽና የክዋኔዎቹ ጠባይ ግን ከቦታ ቦታና ከጊዜ ጊዜ ይለያያል። ይኽንን የክዋኔዎቹን ቅርጽና አተገባበር ነው ባህል የምንለው።

አብዛኞቹ ባህልን ያጠኑ ሊቃውንት በሚከተሉት መገለጫዎቹ ይስማማሉ።

- ባህል በተፈጥሮ የሚገኝ ሳይሆን የሚለመድ ሀብት ነው።
- ባህል ግላዊ ሳይሆን ማህበራዊ ነው።
- ባህል ከትውልድ ትውልድ ተወራራሽ ነው።
- ባህል የሰው ልጆችን ማህበራዊ፤ ሃይማኖታዊ፤ ሥነ-ልቦናዊ፤ ሞራላዊ፤ ቁሳዊ፤ ቴክኖሎጂያዊ ፍላጎቶች ማሳኪያ ነው።
- ባህል በብዙሃን ዘንድ የሚጋሩት እንጂ በግል ባለሀብትነት የሚይዙት አይደለም።

- ባህል የሚጠራቀም እንጂ በአንድ ዕለትና በአንድ ዓመት የሚፈጠር አይደለም።
- ባህል የሚሻሻል እንጂ ቆሞ ቀር አይደለም። በፍጥነትም ይሁን በአዝጋሞት እየተሻሻለ ወይም እየተለወጠ ይሄዳል።
- ባህል የተደራጀና ሥርዓት ያለው ነው፤ ወይም በተለያዩ ስርዓቶች የተገነባ አንድ ታላቅ ቀመር ነው።
- ባህል በተለያዩ ትዕምርቶች አማካኝነት የሚገለጥ ነው።
- ባህል ዋና መሣሪያው ቋንቋ ነው።

ባህል የሰው ልጆችን እንቅስቃሴ የሚመራ ማዕቀፍ፤ ንድፍ ወይም ካርታ ነው ማለት እንችላለን። በጂኦግራፊ ዘርፍ ካርታ ወደ አንድ ቦታ ለመድረስ የምንጓዝበትን መንገድ የሚያመለክት ሲሆን፤ ባህል ስንል ደግሞ የሰው ልጆች ተወልደው እስኪሞቱ ድረስ የሚከተሉት የጊዜ ካርታ ነው ማለት እንችላለን። እያንዳንዱ ቅጽበት በሕይወታችን ውስጥ የማናውቀው አዲስ ቦታ እንደ ማለት ነው። አንድ የማናውቀው ጫካ ውስጥ ደርሰን ከጫካው የምንወጣበት ካርታ እንደሚያስፈልገን ሁሉ፤ ባህል ደግሞ የማናውቀው ዛሬን የምናልፍበት ግልፅ የሕይወት ካርታ ነው ማለት እንችላለን። አንድ ሕፃን ለአቅመ አዳም ሲደርስ ወይም ሲጎለምስ፤ ምን ማድረግ እንዳለበት የሚያውቀው ከአሁን በፊት ጎልምሶ ስለሚያውቅ አይደለም። ይልቁንም በየት በኩል መጓዝ እንዳለበት የሚረዳው፤ ባህል የተባለውን ካርታ ይዞ ነው።

የሰው ልጆች የግል የሕይወት መንገድ እንዳላቸው ሁሉ፤ የጋራ የሕይወት መንገድ አላቸው። የግል የሕይወት መንገድ የግለሰብን ማንነት፤ ስብዕና እና ጠባይ የሚቀርፅ ሲሆን፤ የጋራ የሕይወት መንገድ ደግሞ፤ የትውልድን ማንነት ወይም ጠባይ ይቀርፃል። ይሕን የጋራ የሕይወት መንገድ ባህል ይባላል።

ባህል የሰው ልጆችን ቁሳዊና መንፈሳዊ ክዋኔዎችና፡ ግዙፍና ረቂቅ ሀብቶች ሁሉ የሚያጠቃልል ሰፊ ማዕቀፍ ነው። በየዕለቱ የምንገለገልባቸው ቁሳቁሶች፤ የምንመራባቸው ሐሳቦች፤ የምንከውናቸው ሥነ-ሥርዓቶች ሁሉ በባህል ማዕቀፍ ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው። በአጠቃላይ የሰው ልጆች የአኗኗር ቀለም ወይም መልክ፤ የድርጊታቸውና የሐሳባቸው ስልትና ዘይቤ፤ የየዕለት ክንውኖቻቸው ማስፈፀሚያ ካርታ፤ ባህል ነው ለማለት እንችላለን።

ባህል እንዲህ ያለ ሰፊና የሰው ልጆችን የኑሮ መንገድ የሚያመለክት ጉዳይ ቢሆንም በተፅዕኖ አድማሱና በጠባዩ በተለያዩ ዓይነቶች ሊከፋፈል ይችላል። በዚህ አውድ ትኩረት የምንሰጥባቸው የባህል ዓይነቶችን፤ ገጠር ፈጠር ባህል እና ከተማ ፈጠር ባህል ብለን ልንበይናቸው እንችላለን።

ገጠር ፈጠር ባህል በዋናነት ከትላንት ጋር ብቻ የሚተሳሰርነው። ገጠር ከከተማ ገጠሬነትም ከከተሜነት በፊት የተፈጠረ የሰው ልጅ የአኗኗር ዘይቤ ነው። በመሆኑም የአንድን ማህበረሰብ ጥንታዊ ባህል በዋናነት የምናገኘው፤ ወይም በጥንት ቅርፁና ሁኔታው የምናገኘው በገጠር ነው። ገጠር ፈጠር ባህል የትናንትን ስልትና ቀለም ከመጠበቅ ጋር የሚገናኝ የአኗኗር ስልት ነው።

ገጠር ፈጠር ባህል ትናንት የምንጠቀምባቸውን ቁሳቁሶች፤ ሐሳቦች ቴክኖሎጂዎች፤ አለባበሶች፤ አመጋገቦች፤ የመጠቀሚያ ቁሶች፤ እሴቶች፤ የሥነ-ምግባርና የሞራል ሕጎች ጠብቆ የመሄድ ዝንባሌ ያለው የባህል ዓይነት ነው። በባህርይው ቶሎ የመለወጥ አዝማሚያ የሌለው፤ በተፅዕኖ አድማሱም በአንድ ውሱን ሥፍራ ላይ የሚኖር ማህበረሰብን ብቻ የሚያጠቃልል፤ በአመዛኙ ከጥናታዊ አኗኗር ጋር ትሥሥር ያለው ነው። የአካባቢ፤ የቋንቋ፤ የብሔር፤ የሃይማኖት፤ ወዘተ. ማንነቶች በዚህ ገጠር ፈጠር ባህል ምክንያት የሚገነቡ ናቸው።

ከተሞች የሰው ልጅ የሥልጣኔ ውጤቶች ናቸው። የሰው ልጅ ሲሠለጥን አኗኗሩን ለማመቻቸት፤ ስርዓቱን ለማቀላጠፍና የተለያዩ የኑሮ መልኮችን ለማግባባት ሲል ከተሞችን ፈጥሯል። እነዚህ ከተሞች ደግሞ የአስተዳደር፤ የንግድ፤ የእምነት፤ የትምህርትና የኪነ-ጥበብ ማዕከላት ይሆናሉ። እነዚህን ማዕከላት ለመፍጠርና ለመጠቀም ሲሉ የተለያዩ ዓይነት ማህበረሰቦች ከተለያዩ አካባቢዎች ይመጣሉ። በዚህ የተነሳ ከአንድ ማህበረሰብ የተሻገረ ባህል ይፈጥራሉ። ከተማ ፈጠር ባህል የምንለው፤ በአንድ ሀገር ውስጥ ወይም ከዚያም ባሻገር የተፅዕኖ አድማስ ያለው፤ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኘውን አብዛኛውን ህብረተሰብ የሚያስተሳስር የጋራ የሕይወት ስልትና መንገድ ማለት ነው።

ከተማ ፈጠር ባህል ከአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ጋር በእጅጉ የተሳሰረና፤ ገጠር ፈጠር ባህሎችን የተሻገረ የጋራ ባህል ነው። በዋናነትም የመስፋፊያ ማዕከሉ ከተሞች ናቸው። በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ገጠር ፈጠር ባህሎችን የሚከተሉ የአንድ ሀገር ዜጎች፤ ወደ ከተማ መጥተው በጋራ መኖር ሲጀምሩ የሚተገብሩት፤ የጋራ የሕይወት ስልት ወይም ዘይቤ ነው። በዚህም ምክንያት ከተማ ፈጠር ባህል ዋናው መዳወሪያው ከተማ ውስጥ ሆኖ፤ በጥቅሉ ግን የመላውን ሕዝብ የአኗኗር ስልትና ጠባይ የሚወስን ነው። ይህ ባህል ከሀገራት ወሰን ሊያልፍም ይችላል።

ኢትዮጵያ የብዙ ባህሎች መናኸሪያ ሀገር ነች። ብሔሮች፤ አካባቢዎች፤ መልክአ ምድሮች እና ሃይማኖቶች፤ ልዩ ልዩ የአኗኗር ስልቶችና የኑሮ ቀለም የተፈጠሩባት ሀገር ነች። ልዩ ልዩ ማህበረሰቦች ለረጅም ዘመናት ባደረጓቸው የትብብርና የሸኩቻ ግንኙነቶች ምክንያት፤ ባህሎቹ የጋራ ቀለምና እሴት ፈጥረዋል። አዎንታዊ የሆኑት የጋራ ቀለምና እሴቶች፤ በዘመናዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስተጋብሮች ዳብረውና ጎልብተው እንዲወጡ፤ መታረም የሚገባቸው ደግሞ በአግባቡ እየታረሙና በተሻሉ ስልቶችና ዘይቤዎች እየተተኩ እንዲመጡ፤ ብዙ የቤት ሥራዎ ከፊታችን ይጠብቁናል።

ከተማ ፈጠር ባህል በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገቶች እየተቀረፀና እየጎለበተ የሚመጣ በመሆኑ፤ በእነዚ ዘርፎች የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ዘላቂ ሀገራዊ ማንነት ላይ የሚኖራቸው ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ባህል ከኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ባሻገር በውጭ ግንኙነት ሥራዎችና ስልቶች ላይም የሚመሰረት ነው። ስለሆነም በአጠቃለይ በተለያዩ ዘርፎች የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የመጨረሻ መዳረሻቸውና ዘላቂ ዐሻራቸው፤ በባህል አማካኝነት በትውልድ ላይ የሚንፀባረቅ ይሆናል።

ስለሆነም በተለያዩ ዘርፎች የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ከባህል ጋር ያላቸውን ትሥሥር መለየትና፤

ተገቢውን የባህል ግንባታ መንገድ መቀየስ አስፈላጊ ነው። የትውልድ ጠባይና ማንነት የሚቀረጸው በባህል በመሆኑ፤ በባህል ረገድ የምንቀይሳቸው አቅጣጫዎች በትውልድ ላይ ምን ዓይነት ዐሻራ ያሳርፋሉ? የሚለውን አስቀድሞ በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልጋል። ይሕም ከቁሳዊ ነገሮች ባሻገር የትውልድን እሴቶችና አስተሳሰብ የሚገነባ፤ የባህል ግንባታ ስትራቴጂዎች መተግበርን ይጠይቃል።

ባህልና ሥልጣኔ ሁለት የተሳሰሩ ጉዳዮች ናቸው። ሁለቱን ጽንሰ ሐሳቦች እየቀያየሩ መጠቀምም የተለመደ ጉዳይ ነው። ለምሳሌ፦ የአክሱም ስልጣኔ፤ የሐረር ሥልጣኔ፤ የጊቤ ሥልጣኔ፤ የማያ ስልጣኔ፤ የቻይና ሥልጣኔ፤ የአዜቲክ ሥልጣኔ፤ የፋርስ ሥልጣኔ፤ ወዘተ. የሚሉት ገለፃዎች፤ በሌላ አነጋገር የእነዚህ አካባቢዎች ሕዝቦች የኑሮ ቀለምና ቅርጽ የሚያመለክት ነው። ይህም ማለት በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖር ሕዝብ በሌላኛው አካባቢ ከሚኖር ሕዝብ የተለየ፤ የራሱ መለያ የሆነ የአኗኗር ዘይቤ አለው ማለት ነው። ስለሆነም ሥልጣኔ አንዱ የባህል እድገት ማሳያ ሲሆን፤ ከጥቅል የባህል ብያኔ የሚለየውም በቁሳዊና በምናባዊ ይዘቱ የዳበረና የተራቀቀ በመሆኑ ነው።

ሥልጣኔ ባህልን የማሳደጊያ መንገዱ ሲሆን፤ ባህል ደግሞ የሥልጣኔ ግቡ ነው። የሥልጣኔ ግብ የሠለጠነ የዳበረ ባህልን መፍጠር ነው። ባህል በዋናነት እኛ ምን እንደሆንን የሚገልጥ ሲሆን፤ ሥልጣኔ ደግሞ በዋናነት እኛ ምን እንዳለን የሚያሳይ ነው። ባህል ያለ ሥልጣኔ ሊኖርና ሊያድግ ይችላል። ሥልጣኔ ግን ያለ ባህል ሊኖርና ሊያድግ አይችልም።

የሰው ልጆች ኢኮኖሚያዊ፤ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች እየጎለበቱና እየተራቀቁ ሲመጡ፤ እነሱን ተከትሎ የሚፈጠረው የሰው ልጆች የአኗኗር ስልት ወይም ባህል እየተቀየረ ይመጣል። ኢኮኖሚያዊም ሆነ ፖለቲካዊ ዕድገቱ የመጨረሻ ማረፊያውና ዘላቂ ቤቱ ባህል ነው። በባህል ውስጥ ያልሰረፀ እድገትና መራቀቅ ዘላቂነት ስለሌለውና የሕዝብን ጠባይና ማንነት ስለማይቀርጽ፤ ሥልጣኔ ነው ለማለት ያስቸግራል። በመሆኑም ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገቶች በሕዝብ አስተሳሰብ፤ አኗኗር እሴቶች ውስጥ ሠርፀው ዘላቂ ዐሻራቸውን ሲያስቀምጡ፤ የህብረተሰቡን የኑሮ ምቾትና ጥራት ሲያሳድጉ፤ የአንድን ሀገር ወይም የአንድን ህብረተሰብ ሥልጣኔ ያሳያሉ።

በባህል መሠረት ላይ የፀና እድገት በማንኛውም አጋጣሚ ቢንገጫገጭ ተመልሶ የመምጣት እድል ይኖረዋል። ባህል የህብረተሰብ ስብዕና የሚቀረጽበት ነው። ስብዕናው እስካለ ድረስ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገቶችን በማንኛውም የታሪክ ምዕራፍ ላይ መልሶ ማምጣት አይሳነውም። ስለሆነም በትውልድ ቀረጻ ሂደት አንዱና ዋናው ጉዳይ፤ ሀገራዊ ባህልን በመቅረጽና በማጎልበት፤ በትውልድ ጠባይ ላይ ዘላቂ ዐሻራ ማሳረፍ ነው።

የሰው ልጆች የሚፈጥሯቸው ቁሳዊ ሀብቶችና ዕድገቶች ሁሉ የመጨረሻ ዱካቸው የሚታተመው በባህል ላይ ነው። ሰዎች ችግሮቻቸውን የሚፈቱባቸው መንገዶች፤ የቡድን ሕይወታቸውን የሚመሩባቸው ወይም ፖለቲካዊና ማህበራዊ ሕይወታቸውን የሚያስተዳድሩባቸው ስልቶች፤ ግጭቶቻቸውን የሚፈቱባቸው ዘዴዎች፤ ዓለምና የሰው ልጅን የሚረዱባቸው መንገዶች፤ ወዘተ. ቁስ ተሻጋሪ የባህል ዐሻራዎች ናቸው።

አንዳንድ ህብረተሰብ በቶሎ በቁሳዊ ፍላጎቱ ረክቶ ወደ ቁስ ተሻጋሪ እሴቶች ስለሚያድግ፤ ሐሳባዊና መንፈሳዊ ልዕልናው ከቁሳዊ ሀብቱ ይልቃል፡፡ አንዳንድ ህብረተሰብ ደግሞ በቁሳዊ ፍላጎቱ ላይ ረጅም ጊዜ ስለሚያጠፉ ቁሳዊ ሀብቱ ከመንፈሳዊ እሴቶቹ ይልቃል፡፡ በሁለቱም ሁኔታዎች ግን የቁስ ተሻጋሪ እሴቶች መዳበር፤ በቅድሚያ የቁሳዊ ሀብት እድገትንና የቁሳዊ ፍላጎት መርካትን የሚፈልግ ጉዳይ መሆኑን በደምሳሳው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለቁሳዊም ሆነ ለሐሳባዊ መንፈሳዊ ዕድገቱ ግን ዋናው ጉዳይ የእሴት ግንባታ ሂደቱ ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ሕዝብ ከፍ ያለ ዋጋ የሚሰጠው ለምን ጉዳይ ነው? የሚለውን ጥያቄ ሚመልስ ነው፡፡ ለነፃነት ከፍተኛ ዋገ የሚሰጥ የማንነቱ ሥሪትና የስኬቱ መጠን የሚታየውና የሚመዘነው፤ ይህንን እሴቱን ባስከበረበት መጠን ነው፡፡ ለሰላም ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጥ ሕዝብ ባህላዊ ስልቶቹ የሚዳብሩትና የስኬቱ መጠንም ሊመዘን የሚችለው፤ በፈጠረው ሰላማዊ ባህል ወይም ባዳበረው የግጭት መፍቻ መንገድ መጠን ነው፡፡

ለምግብ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጥ ሕዝብ የአኗኗር ስልቶቹና የስኬቱ መጠን የሚቃኑትና የሚመዘኑት ከምግብ ጋር በተያያዙ ባህላዊ ክዋኔዎቹ ልክ ነው፡፡ ስለዚህ ዋናው ጥያቄ ለነገሮች የምንሰጠውን ዋጋ የምንወስነው እንዴት ነው? ወይም እሴቶቻችንን የምንፈጥረው በምን ምክንያት ነው? የሚለው ነው፡፡

ለነገሮች የምንሰጠው ዋጋ ወይም እሴት ለነገሮቹ የምንከፍለውን መሥዋዕትነትና ነገሮቹን ለማግኘት የምናደርገውን ጥረት ያመላክተናል፡፡ አንዳንዱ ሀገር በጦር ዐቅሙ፤ ሌላው በሕንፃ ግንባታ፤ በዜጎች ምቾች፤ ወይንም በአስተዳደር፤ ወዘተ. በተለያዩ ጉዳዮ ዙሪያ የሚኖረው ስኬት፤ ለጉዳዮቹ ሚሰጠውን ዋጋ ወይም እሴት የሚያመላክት ነው፡፡ በግለሰብ ደረጃ ለዕውቀት፤ ለገንዘብ፤ ለሥልጣን፤ ለበጎ አድራጎት፤ ወይንም ለዝና ዋጋ የሚሰጡ፤ ዋጋ በሚሰጡት ነገር ዙሪያ ጥረት እንደሚያደርጉና፤ በዚያ ዙሪያ የስኬት እድል እንዳላቸው የሚያመለክት ነው፡፡ በህብተሰብ ደረጃም የአንድ ሀገር ሕዝብ ለነገሮች የሚሰጠው ዋጋ ወይም እሴት በነገሮቹ ዙሪያ ሚኖረውን ስኬትና ተሞክሮ ያመላክታል፡፡

እሴት የባህል ጭማቂ ነው፡፡ የሰው ልጅ በተደጋጋሚ ሕይወቱ ካገኛቸው ተሞክሮዎች በመነሳት እሴቶቹን ይቀርፃል፡፡ እሴቶች ማህበረሰቡ ተደጋጋፊ፤ ተጣጣሚና ተግባቢ የሆነ ሕይወት እንዲኖረው የሚያስቀምጣቸው ደረጃዎች ናቸው፡፡ እሴቶች በአንድ ማህበረሰብ ዘንድ ትክክል ወይ ትክክል ያልሆነ፤ ተቀባይነት ያለው/የሌለው፤ ጥሩ ወይም መጥፎ፤ የሚፈቀድ ወይም የሚከለከል፤ ቆንጆ ወይም አስቀያሚ፤ ወዘተ. የሚመዘኑበት ሚዛን ነው፡፡

እሴት በአንድ ወይም በተከታታይ ክስተቶችና አጋጣሚዎች ምክንያት ሊፈጠር ይችላል፡፡ የአንድ ፈታኝ ጦርነት መከሰት ወይም በተከታታይ ለጦርነቶች ተጋላጭ መሆን፤ አንድ ሕዝብ የጀግንነት እሴትን እንዲያዳብር ወይም ለጀግንነት ከፍ ያለ ዋጋ እንዲሰጥ ሊያደርገው ይችላል፡፡ የኢኮኖሚ ቀውሶች ወይም ወረርሽኞች ወይም የረሀብ አደጋዎች የሀገራትን እሴት የመወሰን ኃይል አላቸው፡፡ ለወረርሽኞቹ በተደጋጋሚ የተጋለጠ ወይም በአንድ ወረርሽኝ ምክንያት ከባድ ፈተና ውስጥ የገባ ሀገር፤ ለጤና ትልቅ ዋጋ የመስጠት ዝንባሌ ይኖረዋል፡፡ በኢኮኖሚ ቀውስ ወይም በረሃብ የተመታ ሀገር ለኢኮኖሚ ወይም ለምግብ ትልቅ ዋጋ የመስጠት አዝማሚያ

ይኖረዋል።

እሴቶች በእንዲህ ዓይነት ታሪካዊ አጋጣሚዎች እየጎለበቱ ሊመጡ የሚችሉ ቢሆኑም፤ የእሴቶች መፈጠር፤ መጎልበትና መስፋፋት በባህል ለውጥ ላይ የተመሰረተ ነው። ለምሳሌ፡ መጽሃፍት ያሉበት፤ ጸሐፊዎች የበዙበት፤ ቤተ መጻህፍት የበረከቱበት፤ ማንበብ የዕለት ተዕለት የሕይወት ክዋኔ የሆነበት፤ ጋዜጦች የሚነበቡበት፤ የትምህርት ተቋማት የተጠናከሩበት ሀገር ለዕውቀት ከፍ ያለ ዋጋ ሊሰጥ እንደሚችል መገመት ይቻላል። ይህም ማለት ከእውቀት ጋር የሚገናኙ ባህላዊ ክዋኔዎች ሲኖሩ የዕውቀት እሴት ይጎለብታል ማለት ነው።

የስፖርት ትጥቅ በገበያው ላይ ሲበረክትና የስፖርት ትጥቅ መልበስ ፋሽን ሲሆን ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ከፍ ያለ ዋጋ እያገኙ ይመጣሉ። የመዝናኛ ቦታዎች ሲበራከቱና ሲስፋፉ እንዲሁም መዝናኛ ዓይነቶች ቁጥር ሲጨምር የመዝናናት እሴት እየጨመረ ይሄዳል።

በአንጻሩም በቁሳዊም ሆነ ኢቁሳዊ ምርቶቻችን ውስጥ ባህልና እሴት አንዱ አንዱን እየመገበ የሚሄድ መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል። የመዝናናት እሴት ከተፈጠረ በኋላ የመዝናኛ ሥፍራዎች እየበረከቱ መምጣታቸውና የመዝናናት ባህል እየጎለበተ መምጣቱ አይቀሬ ነው። የፍቅር ሙዚቃዎችና ግጥሞች የበዙበት ባህል የፍቅር እሴትን እያጎለበተ እንደሚሄድ ሁሉ፤ የፍቅር እሴት የጎለበተበት ሕዝብ ደግሞ ከፍቅር ጋር የተገናኙ ባህሎችን እየፈጠረና እያስፋፋ መሄዱ የሚጠበቅ ነው።

ይህ የእሴቶችና የባህል ውርርስ የሚነግረን አንዱና ዋናው ቁም ነገር፤ በባህል ግንባታ ላይ የምንሰራቸው ሥራዎች ዘላቂ ተፅዕኖ እንዲኖራቸው ከፈለግን፤ ምን እሴት እየፈጠሩ ነው? የሚለውን ማጤን እንደሚገባ ነው። ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችንና ምርቶቻችን ባህልን እየፈጠሩ ሲመጡ፤ ባህሉ ደግሞ እሴትን እየፈጠረ ይመጣል። ጋዜጦች፤ ቴሌቪዥን፤ ኢንተርኔት ሲስፋፋ የሚፈጥረው የተግባቦት ባህል፤ የነጻነት እሴትን እያጎለበተ እንደሚሄድ መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም ሚዲያዎች ከተስፋፉና የመገናኛ ብዙሃን ባህል ከዳበሩ በኋላ፤ የነፃነት እሴት ሊፈጠር እንደሚችል አስቀድሞ መረዳት አስፈላጊ ነው።

ኢንተርኔት በየዕለት ህይወታችን ውስጥ ሲገባና ኢንተርኔትን መጠቀም ባህላችን ሲሆን፤ በውስጡ የእኛን እሴት እየገነባ እንደሚሄድ መገንዘብ ይቻላል። የፋሽን ልብሶች በብዛት መጠቀም ስንጀምርና የፋሽን ባህል ሲስፋፋ፤ በውስጡ የቅንጦት እሴትን ወይም ከፋሽኖቹ ባህርይ ጋር የተያያዙ ሌሎች እሴቶችን እያሰረፀ ይመጣል።

ምርጫን የፖለቲካ ባህላችን አካል ስናደርግ፤ የምርጫ ባህል የፉክክር እሴትን እያጎለበተ እንደሚሄድ መገንዘብ ይቻላል። ይህም ከኮንፊሺየሳዊው የምሥራቁ የትብብር እሴት ይልቅ፤ ለሶቅራጠሳዊ የምዕራቡ የፉክክር እሴት መዳበር ትልቅ አስተወጽኦ ይኖረዋል።

ጠንካራ የድምጽ ሕግ ወጥቶ ቢተገበርና፤ በየቦታው ሙዚቃዎችን መክፈት ወይም ሃይማኖታዊ ስርዓቶችን ከፍ ባለ ድምጽ ማከናወን ከባህላችን ቢወጣ፤ በህዝቡ ውስጥ ሊፈጥረው የሚችለው እሴት ምንድነው? ብለን

መጠየቅ ይኖርብናል።

እያንዳንዱ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የመጨረሻ መዳረሻውና ዘላቂ ተፅዕኖ የማድረጊያው መንገድ እሴት መፍጠር ነው። በፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች የሚፈጠረው ባህል የመጨረሻ ጽኑ መሠረት ላይ የሚቆመውና ዘላቂ ተጽዕኖ የሚኖረው እሴቶችን መፍጠርና ማስረፅ ሲችል ነው።

ማንኛውም የፖለቲካ ሥርዓት፤ አስተሳሰብ፤ ርዕዮተ ዓለም ወይም ፖሊሲ አድጎ ፍሬ ማፍራት የሚችለው፤ በእሴቶች ላይ ሲበቅል ነው። በኢትዮጵያ ከ1960ዎቹ ጀምሮ የተፈጠረው የፖለቲካ ባህል የእኩልነት እሴትን እያጎለበተ መጥቷል። ይህም የነፃነት እሴትን አብልጦ ለሚፈልገው የሊብራል ዴሞክራሲ እሳቤ ምቹ አይደለም። በአንፃሩ የሊብራል እሴቶች በዳበሩበት ወይም ለነፃነት ትልቅ ዋጋ በሚሰጠው የአሜሪካ ህዝብ ውስጥ፤ ሶሻል ዴሞክራሲን ወይም ሌላ መሰል ርዕዮቶችን ተክሎ ማብቀልና ማሳደግ አስቸጋሪ ነው።

የጉልበትና የመሸናነፍ እሴቶች በጎለበቱበት ህብረተሰብ ውስጥ፤ የምክክርና የድርድር ፖለቲካ ውጤታማነቱ አስቸጋሪ ይሆናል። የመቻቻል እሴት ባልዳበረበት ህብረተሰብ ውስጥ ሰላማዊ የፖለቲካ ምህዳር መፍጠር ወይም ብሄራዊ መግባባት ማስፈን አስቸጋሪ ነው። ግላዊ ስኬት ዋና እሴት በሆነበት ሀገር ውስጥ፤ የሀገርን ኢኮኖሚ የሚያሳድግ ፖለቲካና ማህበራዊ ስርዓት መዘርጋት እጅግ ከባድ ነው። ድብቅነት ትልቅ እሴት በሆነበት ህዝብ ውስጥ፤ ተጠያቂነት ያለበትና በንግግር የሚመራ መንግስታዊ ሥርዓት መዘርጋት ትልቅ ፈተና ነው።

ሀገራችን በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዋ ለስኬት እንድትበቃ፤ እንቅፋት የሆኑትን ባህላዊ መሰረቶች ተመልክቶና መርምሮ በመቀየር፤ ለህልውናዋ ፈተና የሆኑትን እሴቶች በመለወጥ፤ ምንፈልጋትን የበለጸገችና ሰላማዊት ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ የሚያስችሉ እሴቶች በትውልድ ልብ ላይ እንዲጸኑ መደረግ አለባቸው። መጪው ትውልድ የመቻቻል እሴትን ያዳበረ፤ የወንድማማችነት እሴትን የገነባ እና ለዐርበኝነት ትልቅ ዋጋ የሚሰጥ እንዲሆን፤ የባህል ግንባታ ሥራዎቻችን ትልቅ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል። ለኢኮኖሚያዊም ሆነ ለፖለቲካዊ ሥራዎቻችን ስኬት ደግሞ ለማምረት ዋጋ የሚሰጥ፤ ሥራንና ታታሪነትን የሚያስቀድም፤ ለመስጠትና ለማበርከት የሚኖር ትውልድ መገንባት እና በአጠቃላይ አምራችነትን ሀገራዊ እሴት ማድረግ ያስፈልጋል።

መጪው ትውልድ የዳበረ ከተማ ፈጠር ባህል እንዲኖረውና፤ ለሀገራችን ሕልውና መሰረት የሚሆኑ እሴቶችን በትውልዱ ውስጥ ለመገንባት፤ ጥበብ እጅግ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። የአንድ ሀገር ህዝብ የዕለት ዕለት ክዋኔዎች የሚፈጠሩት፤ ልማዶችና አስተሳሰቦች የሚቀረጹት፤ እሴቶች የሚገነቡት፤ በአጠቃላይ ባህል የሚፈጥረው፤ ዜጎች በቁስ፤ በክዋኔ ወይም በሐሳብ ሲማረኩና የኑሮአቸው አካል ሲያደርጉት ነው። ይህንን የመማረክ ሂደት ደግሞ የሚያቀላጥፈው ዋና መንገድ ጥበብ ነው። አንድን ቁስ፤ ክዋኔ፤ ወይም ሐሳብ ሰዎች በቀላሉ የሚቀበሉት፤ ከጉዳዩ አስፈላጊነት ወይም ጥራት አንፃር ብቻ አይደለም። ወይንም ደግሞ ጉዳዮቹ ተደራሽ ሆነው በገበያና በሌላ መንገድ መቅረባቸው ብቻ የባህላችን አካል አያደርጋቸውም። ይልቁንም እነዚን የባህል መገለጫዎች እንድንማረክባቸው ወይም የተለየ ዋጋ እንድንሰጣቸው የሚያደርገን አንድ ቀላልና ፈጣን

የእሴት መፍጠሪያ መንገድ አለ፤ እሱም ጥበብ ነው።

የጥበብ ስራዎች ማለትም ሙዚቃዎች፤ ፊልሞች፤ ሥዕሎች፤ ኪነ-ሕንጻዎች፤ ውዝዋዜዎች፤ ሥነ-ጽሁፎች፤ ሥነ-ቃሎች፤ የተለያዩ ጥበባዊ ኹነቶችና ክዋኔዎች በታዳሚው ዘንድ ያላቸው እሴት የመፍጠር ዐቅም በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ሀገራት በጥበብ ሥራዎች ዘላቂ እሴትና የጋራ ማንነትን ገንብተዋል፤ አስተሳሰብንና የሕይወት ዘይቤን አንፀዋል። በዘላቂነትም የትውልድን እሴቶች በመገንባት ዘላቂ ሀገራዊ መግባባትና መሠናሠል ፈጥረዋል። ከዚያም ሲያልፍ ሀገር ተሻግረውና ባህር አቋርጠው በተለያዩ ሀገራት ላይ የሚጎለብቱ የተለያዩ እሴቶች፤ በጥበብ አማካኝነት የሥርጭትና የተቀባይነት አድማሳቸውን የሚያሰፉ ናቸው።

ጥበብ የአንድን ሀገር ታሪክ፤ አመጋገብ፤ ወግና ሥርዓት በቀላሉ ለሕዝብ ተደራሽና ማራኪ አድርጎ በማቅረብ፤ የሕዝብን አስተሳሰብና ክዋኔዎች የመቅረጽ ኃይል አለው። የብዙ ጀግኖች ገድል፤ የብዙ ወግና ሥርዓቶች ቅደም ተከተልና ክዋኔ፤ የብዙ አስተሳሰቦችንና ትርክቶቻችን ይዘት፤ የእምነት መግለጫ ክዋኔዎቻችን፤ በጥበብና በጥበባውያን ተፅዕኖ ምክንያት የመስረጽ ዐቅሙ ከፍተኛ ነው። ጥበብ የባህል ወኪል ነው። በዚያው ልክ ደግሞ ጥበብ ባህልን ይፈጥራል፤ የተፈጠረውንም ያጎለብታል። ከሁሉም በላይ ጥበብ ለስሜት ቅርብ በመሆኑ፤ በቀላሉ የሰዎችን ባህልና እሴት የመቅረጽ ዐቅም አለው። ጥበብ ብቻ ሳይሆን ጥበበኞችም በግል የሕይወት ዘይቤያቸው ባህልን የመፍጠርና እሴትን የማስረጽ ችሎታ አላቸው። ጥበብና ጥበበኞች የነኩት ነገር በትውልድ ልብና ልማድ ውስጥ ሳይሰረጽ፤ ትኩረት ሳይስብና፤ ሳይለመድ የመቅረት እድሉ ትንሽ ነው።

## ጥበብ ሆይ ምንድነሽ?

ጥበብ የሰው ልጅ የፈጠራና የምናብ ክህሎት መግለጫ ነው። ከመደበኛውና በስፋት ከሚገኘው ይዘት በተለየ ሊታይ ሊሰማ ሊዳሰስ በሚች ቅርፅ ማለትም በስዕል፤ በቅርፃ ቅርፅ፤ በሙዚቃ፤ በስነ-ጽሁፍ ወዘተ ..የሚገለጽ ነው። ደስታን፤ ሀዘንን፤ ግርምትን፤ ንዴትን በምናባዊ ፈጠራ የሚያጋባ ሳቅና እንባን ከስሜት ከረጢት ውስጥ የሚያፈልቅ፤ ሀሳብና እውቀትን በስሜትና መንፈስ ውስጥ አስርጎ የሚያሰርፅ፤ የሰው ልጆች የልብ ወይም የስሜት ምግብ ነው። ሆዳችን የእህል ምግብ እንደሚፈልግ ሁሉ አእምሮአችን የእውቀት ምግብ እንደሚፈልግ ሁሉ መንፈሳችን ወይም ስሜታችን የውበት ምግብ ይፈልጋል። ይህንንም የውበት ምግብ የሚያመርተው እርሻ ደግሞ ጥበብ ነው።

የጥበብ ሚና ምን መሆን አለበት? በሚለው ጉዳይ ዙሪያ የተለያዩ ምልከታዎች ቢኖሩም ሁለት ዋና ዋና ሀሳቦች ዋነኛ መከራከሪያዎች ሆነው ሲቀርቡ ይስተዋላል። አንደኛው መከራከሪያ ጥበብ ለማህበራዊ ዓላማ መዋል አለበት የሚለው ሲሆን፤ ጥበብ የሰው ልጆችን ለማስተማር፤ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ለውጥ ለማምጣት፤ ለመቀስቀስ፤ ወዘተ መዋል አለበት የሚል ነው። በአጠቃላይም ጥበብ የሰው ልጆችን ህይወት ለመቀየር፤ ወይም በሀገር ግንባታ ሂደት ላይ ለውጥ ለማምጣት፤ ተልዕኮ መውሰድ አለበት የሚል ነው።

ሁለተኛው መከራከሪያ ደግሞ ጥበብ ለጥበብነት ዓላማ ብቻ መዋል አለበት የሚል ሲሆን፤ ጥበብ የውበትና

የማዝናናት ተልዕኮን ብቻ መሸከም ይኖርበታል ይላል። የጥበብ ስራዎች የሰው ልጆችን የሥነውበት ፍላጎት ከማርካት ባለፈ ሌላ ተልዕኮ ሊወስዱ አይገባቸውም የሚል ነው። እነዚህ መከራከሪያዎች በሀገራችንም ቀደም ባሉት ጊዜያት የጥበብ ሰዎች ክርክር ያደረጉባቸው ሀሳቦች ናቸው። የእነዚህን መከራከሪያዎች ዋና ቁም ነገር አንጥረን ስንመለከተው ሀሳቦቹ ከጥበብ ብያኔ ጋር የሚያያዙ ናቸው። ጥበብ ለማህበራዊ ወይም ለሀገራዊ ዓላማ የሚለው መከራከሪያ በዋናነት የጥበብን የይዘት ገፅታ ትልቅ ትኩረት ይሰጠዋል። ጥበብ ለጥበብነቱ የሚለው መከራከሪያ ደግሞ፤ በዋናነት የጥበብን የቅርፅ ገፅታ ከፍ ያለ ትኩረት ይሰጠዋል። ሆኖም ይዘትም ሆነ ቅርፅ የጥበብ መሰረታዊ ተፈጥሮዎች ስለሆነ፤ የጥበብን ዓላማ ወደ አንድ ጎን ብቻ መጎተት ጥበብን ራሱን ያጠፋዋል።

በይዘት ላይ ብቻ ያተኮረ ጥበብ ጥበብነቱ ቀርቶ ታሪክ፤ ፍልስፍና ወይም ፖለቲካ እየሆነ ይመጣል። በይዘት ላይ ብቻ በማተኮር ጥበብን ለማህበራዊ ለውጥ ማዋል አለብን የሚለው ዝንባሌ፤ የጥበብን ለዛ በማድረቅ ጥበብ ወደ ፕሮፖጋንዳነት እንዲለወጥ እና የጥበብነት አቅሙን እንዲያጣ የሚያደርግ ነው። በሀገራችን የዘመናዊ ታሪክ ጅማሮዎች ላይ ይቀርቡ የነበሩ የጥበብ ስራዎች፤ በዋናነት በይዘት ላይ ያተኮሩ ነበሩ። በባህሪያቸውም ህብረተሰቡን ግብረገብነት የማስተማር ዝንባሌ ያላቸው ናቸው።

ለምሳሌ አርአያ እና እንደወጣች ቀረች፤ ‹‹ያላቻ ጋብቻ›› የተባለው ቲአትር፤ ‹‹ተማር ልጄ››፤ ‹‹የት ሄደሽ መጣሽ›› እና ‹‹እሁድ የእቁብ ጠላ›› የተሰኙት ሙዚቃዊ ጨዋታዎች፤ ግብረገብነት የማስተማር ዝንባሌን የሚያመላክቱ ናቸው። በመቀጠል የማርክሲስት ርዕዮተ ዓለም መስፋፋትን ተከትሎ ህብረተሰብን ለለውጥ የማነሳሳት ዝንባሌ ያላቸው የጥበብ ስራዎች በሰፊው መታየት ጀምረው ነበር። ‹‹አልወለድም››፤ ‹‹ፖለቲካና ፖለቲከኞች››፤ ‹‹ኦሮማይ›› የተባሉት ልቦለዶች ‹‹በረከተ መርገም›› የተሰኘው ግጥም፤ ፖለቲካዊ መነሳሳትን የማማተር አዝማሚያ ነበራቸው። ግብረገብነት የማስተማሩም ሆነ ለለውጥ የማነሳሳቱ ዝንባሌዎች፤ በጥቅሉ ጥበብን ለማህበራዊ ለውጥ የማዋል ዓላማ ያላቸው ናቸው።

በሌላ በኩል ጥበብን ለቅርፁ ብቻ የሚለው እይታ፤ የሀገረ መንግስትን ጣልቃ ገብነት ለማስቀረትና፤ የጥበብ ሰዎችን ግላዊ ነፃነት የማስጠበቅ ዝንባሌ አለው። ጥበብ ምንም ዓይነት ማህበራዊ እና ሞራላዊ ተልዕኮ መያዝ የለባትም፤ የጥበብ ዋነኛ ዓላማ ሥነውበትን ማላቅና ማዝናናት ነው፤ የሚል ሀሳብ የሚያቀርብ ነው፤ በጥበባዊ ስራዎች ህዝብን ማስተማር ወይም ለለውጥ ማነሳሳት፤ የጥበብ ተልዕኮና ሚና አይደለም የሚል መከራከሪያ ይቀርባል።

በሀገራችን ከአብዮቱ ጊዜ ጀምሮም እንዲህ ዓይነት የማዝናናት ተልዕኮ ያላቸው የጥበብ ስራዎች ባይጠፉም፤ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን እንዲህ ዓይነት ከይዘት ይልቅ ለቅርፅ ሰፊ ትኩረት የመስጠት ዝንባሌዎች በብዙ የጥበብ ስራዎች ላይ ተንፀባርቀዋል። በዚህም ምክንያት የጥበባዊ ስራዎች ዋናው ሚና ትውልድን ማዝናናት ላይ እያተኮረ መምጣቱን መታዘብ ይቻላል።

ጥበብ የህብረተሰብ ህይወት አካል፤ ጥበበኛም የህብረተሰባዊ እንቅስቃሴዎ ውጤት በመሆኑም ጥበብ ከማህበራዊ ዓላማ እርቆ፤ በጥበባዊነቱ ብቻ ወይም በሥነ ውበታዊ ፋይዳው ብቻ መታየት አለበት የሚለው

መከራከሪያ ሩቅ አያስኬድም። የጥበብ ምንነት በይዘትና በቅርፅ የተዋቀረ እንደመሆኑ፤ ቅርፁ ብቻ ትኩረት ሰጥቶ፤ ይዘቱን ችላ ማለት፤ የጥበብን ፋይዳ እንደቁማር ወይም እንደሌላ ዓይነት ቁምነገር አልባ መዝናኛ ብቻ መቁጠር ይሆናል።

በመደመር እይታ መሰረት ጥበብ የህብረተሰብን ባህልና አስተሳሰብ የመቅረፅ ሚና ሊኖረው ይገባል። ነገር ግን ይህ ሚና በሀገረ መንግስት ግፊት ወይም ጫና የሚመጣ ሳይሆን በራሱ በጥበበኛው ትዝብትና ስሜት ላይ መመስረት ይኖርበታል። ጥበበኛው በጥበብ ስራው የታዘበውን ጉዳይ ስሜት በሚሸነቁጥ ቅርጽ ማቅረብ የሚችለው መጀመሪያ የራሱን ስሜት ሲነካ ነው። የሀገረ መንግስቱ ዋንኛ ተልዕኮ ሶስት ለጥበብ መስፋፋት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን መከወን ነው። ለጥበብ መስፋፋት የሚያግዙ ህጎችና ፖሊሲዎችን ማውጣት፤ የትምህርት እና የስልጠና ተቋማትን እንዲስፋፋ ማድረግ፤ የጥበብ መከወኛ ስፍራዎች እንዲገነቡና እንዲስፋፉ ማድረግ ናቸው።

የሀገረ መንግስቱ ሚና ጥበበኛው የህብረተሰቡን ህይወት ሊረዳበት የሚችልበትን መንገድ ማመቻቸት እንጂ ጥበበኛው በተወሰኑ አጀንዳዎች እና አስተሳሰቦች ዙሪያ እንዲጠበብ ግፊት ማድረግ አይደለም። በማንኛውም ዓይነት ሁኔታ በግፊት ላይ ተመስርቶ የሚሰራ የጥበብ ስራ ከጥበብነቱ ይልቅ ፕሮፖጋንዳነቱ ያመዝናል። የፕሮፖጋንዳ ዘዴና ስልትንም በአግባቡ ስለማይከተል፤ ሰዎችን የማሳመን እና የመለወጥ እድል አይኖረውም። በለዛውም ደረቅና ይስሙላ የበዛበት ስለሚሆን ለሰዎች ስሜትና ነፍስ የቀረበ አይሆንም።

በአጠቃላይ ጥበብ የጥበበኛውን ስሜት በሰዎች ላይ የማጋራት ተፈጥሮ አለው ያልነውን አንዱን እና ዋናውን የጥበብ ገፅታ የሚያፈርስ በመሆኑ፤ ጥበብነቱ ፈፅሞ የደበዘዘ ይሆናል። ከመነሻውም ጥበበኞች የጥበብን ስራ የሚሰሩት ከውስጣቸው የሚራወጠውን ስሜት ለመግለፅ በሚያደርጉት ምጥ ውስጥ ስለሆነ፤ ምጡ ከሌለ ልጁ አይኖርም። አንድ ደራሲ የአንዲት ህፃንን የተጎሳቆለ ሁኔታ ተመልክቶ ጽሁፍ ለመጻፍ የሚንደረደረው፤ መጀመሪያ በውስጡ አላስቀምጥ የሚለው የሀዘን ስሜት ሲጎተጉተው ነው። ስለተጎሳቆለችው ሴት እንዲፅፍ ከታዘዘ ግን የሚያጋራው ስሜቱን ሳይሆን እውቀቱን ወይም የተሰጠውን መረጃ ይሆናል። ጥበብ ደግሞ መረጃ ከስሜት ወደ ስሜት የማስተላፍ እንጂ፤ ከአዕምሮ ወደ አዕምሮ የማስተላለፍ ስራ አይደለም። አዕምሮን ማዕከል ያደረገ መልዕክት የሚያስተላልፍ ሰው የሳይንስ ወይም የፍልስፍና አስተማሪ እንጂ፤ ጥበበኛ አይደለም። የጥበብ ስራ ለህብረተሰብ እና ለሀገር ግድ የሌለውና በማዝናናት ላይ ብቻ ያተኮረ ከሆነ ደግሞ፤ የኪነጥበብ አንዱ አምድ የሆነውን የይዘት ተፈጥሮ እየሸረሸረው መምጣቱ አይቀርም። ቅርፁ አምሮና ተውቦ ይዘቱ ግን ብዙ ትርጉም የማይሰጥ ከሆነ ሲያዩትና ሲቀምሱት የሚያሳሳ፤ ሲበሉት ግን የሚያቅር ወይም ሰውነት የማይገነባ ምግብ ይሆናል። ምግብን ምግብ የሚያሰኘው መጣፈጡ ብቻ ሳይሆን በውስጡ የያዘው ንጥረ ነገር ጭምር ነው። የጥበብ ስራዎች ምንም ያህል ስሜትን የሚኮረኩሩ ቢሆኑም ይዘታቸው የሰው ልጆችን ማስተዋል የማይከፍት ከሆነ ሥነ-ውበታዊ ፋይዳቸው ደካማ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

በዚህ የሉዓላዊነት ዘመን የመማሪያም ሆነ የመዝናኛ ዓይነቶች በብዛት ለትውልዱ ቀርበውለታል። ነገር ግን

መረጃዎችንም ሆነ መዝናኛዎችን መርጦ እንዲከታተል፤ ያገኘውን እንዲመረምር፤ የሚበጀውን ለይቶ በቀላሉ እንዲመርጥ፤ የመረጠውን በቀላልና በአዋጭ መንገድ እንዲከታተል፤ የሚያደርግ መላ ሊያገኝ አልቻለም። ስለዚህም የግራ መጋባት መንፈስ በትውልዱ ውስጥ ረብቧል ማለት ይቻላል። በመደመር እይታ መሰረት፤ ጥበብ መጪውን ትውልድ የማንቃት ሚና ሊጫወት ይገባል። ትውልድ በምን መረጃ እና የህይወት ዘይቤ ላይ ማተኮር እንደሚያዋጣውና ነገሮችን እንዴት በቀላሉ እና በፍጥነት መለየት እንዳለበት፤ የማንቃት ስራ የጥበብ ሚና ሊሆን ይገባል።

ንቁ ትውልድ ነገሮችን የሚከታተል፤ አዝማሚያዎችን በቶሎ የሚለይ እና የሚያዋጣውን መንገድ በፍጥነት የሚቀይስ ትውልድ ነው። የመደመር ትውልድ ይህን ንቃት እንዲላበስና፤ ትኩረቱን ከሚበታትኑ በርካታ ነገሮች መካከል ለህይወቱ የሚያዋጣውን ነገር እንዲመርጥ፤ የጥበብ ስራዎች የስሜት ልቀቱን የማዳበር ተልዕኮ መውሰድ ይኖርባቸዋል። ጥበብ ስሜትን በሰዎች ላይ የማጋባት አቅም የተላበሰ፤ በስሜት ላይ የሚሰለጥን የሰው ልጆች ስራ እንደመሆኑ፤ ስሜትን የማላቅና ንቁ ትውልድ የመፍጠር ሚናን በቀላሉ መወጣት ይችላል። ነገሮችን በቶሎ ለመረዳት ከሚያስፈልገው የአመክንዮ አቅም ባሻገር፤ የሰው ልጆች ህይወት በእጅጉ በስሜት ልቀታቸው ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፤ መጪው ትውልድ አደገኛ በሆኑ የስሜት ማዕበሎች የሚነዳ እንዳይሆንና የራሱን እና የሀገሩን ሁኔታ በቀላሉ መረዳት እንዲችል ማንቃት ያስፈልጋል። እርስ በእርስ መተዛዘንን፤ በሰዎች ደስታ መደሰትን፤ የሰዎች ስቃይና ሀዘንን መጋራትን፤ ንዴትና ብስጭትን መቆጣጠርን፤ በፍርሃት ጥፋት እንዳይደርስ ራስን መግዛትን፤ ወዘተ እንዲለማመድ በማድረግ፤ በማይጠቅሙና በማይመለከቱት ጉዳዮች ስሜቱን እንዳያስገዛና ትኩረቱን ምን ላይ ማድረግ እንዳለበት እንዲረዳ ማንቃት ያስፈልጋል።

መጪው ትውልድ ከቁሳዊ ሽኩቻ ተሻግሮ፤ ለህይወት ከፍ ያለ ትርጉም የሚሰጠው ውበትን ማድነቅ ሲችል ነው። አስተዋይና ንቁ ትውልድ እንዲኖር ከጥበብ ጋር የተሳሰረ አስተዳደግና ህይወት ሊኖር ይገባል። በቤቱ፤ በትምህርት ቤቱ፤ በአካባቢው፤ በአጠቃላይ በሚንቀሳቀስባቸው ስፍራዎች ሁሉ ከጥበብ ስራዎች ጋር የሚገናኝበትንና ጥበብን የሚላመድበትን መንገድ መፍጠር አስፈላጊ ነው።

ትውልድ ጠቃሚ እሴቶችን እንዲለይና በመረጃ ብዛት የማይደናበርና በስሜት ማዕበል የማይናጥ እንዲሆን፤ በእያንዳንዱ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ፤ እሴቶችን የሚገነቡ የጥበብ ስራዎች ሊቀርቡለት ይገባል። የወንድማማችነት ጣዕም በየጎዳናዎቻችን፤ በየህንፃዎቻችን፤ በየሰፈሮቻችን በጥበብ ስራዎች አማካኝነት መንፀባረቅ ይኖርባቸዋል። ከቤት እስከ ሀገር ባሉ ተቋሞቻችን እና አካባቢዎቻችን ሁሉ በኪነ-ህንፃው፤ በሥነ-ስዕሉ፤ በሥነ-ፅሁፉ፤ በሥነ-ጥበቡ፤ በሙዚቃው፤ ወዘተ የአርበኝነትና የሀገር ኩራት እሴትን የሚያሰርፁ የጥበብ ስራዎች፤ የህይወቱ አካል መሆን አለባቸው።

መጪው ትውልድ በዳበረ ከተማ ፈጠር ባህል ውስጥ እንዲኖርና፤ በተጨባጭ ህይወቱን የሚለውጡትን እሴቶች እንዲያዳብር በጥበብ ዘርፍ ሶስት ጉዳዮች ላይ ትኩት አድርጎ መስራት ያስፈልጋል። ውበት አድናቂ ትውልድ መገንባት፤ ጥበብ ፈጣሪ ትውልድ መገንባት እና የጥበብ ኢንዱስትሪውን ማሳደግ።

ውበትን አድናቂ ትውልድ ሲፈጠር፤ ጥበበኞች መበርከታቸውና መጎልበታቸው አይቀርም። በሂደትም የነጠሩ የጥበብ ስራዎችን የሚሰራ፤ ብቁ ትውልድ መፈጠሩ አይቀርም። ጥበብ ፈጣሪውና ጥበብ አድናቂው ተመጋጋቢ ናቸው። ጥበብ ፈጣሪው ያለጥበብ አድናቂው ጠንካራ የጥበብ ስራ ሊፈጥር አይችልም።

ትውልዱ ጥበብን ማድነቅ የማይችል ከሆነ፤ ከልብ የፈለቁ የጥበብ ስራዎች ይጠፉና፤ ለታዳሚው የሚመቹ የይድረስ ይድረስ ስራዎች ይበረክታሉ። የታዳሚው ስንፍና ጥበበኛውንም ሰነፍ ያደርገዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ጥበብ ፈጣሪዎች ሰነፍና ብቃት የጎደላቸው ከሆኑ፤ ታዳሚውም ጥበብን ማድነቅ የማይችልና በጥበብ የማይማረክ እየሆነ ይመጣል። በዚህም ከማስተዋል፤ ራስን ከመግዛት እና ከንቁ የህይወት አካሄድ ትውልድ ይናጠባል። በመረጃ ጋጋታ ግራ የሚጋባና የሚሸወድ፤ በስሜት ማዕበል የሚናጥ ትውልድ ይሆናል።

የጥበብ ፈጣሪዎች እንዲጠነክሩ በትህምርት እና ስልጠና ማጎልበት አለብን። ሀገራቸውን እንዲያውቁና ከህዝቧና ከተፈጥሮዋ ጋር በቂ ግንኙነት እንዲኖራቸው፤ ሁኔታዎችን ማመቻት ይገባናል። ግላዊ ነፃነታቸውን ጠብቀን በሀገር ጉዳይ ላይ በቂ መረጃ እንዲያገኙ ማስቻል ይጠበቅብናል። እነዚህን በማድረግ የጥበብ ፈጣሪዎችን ብቃት ማሳደግና በበጎ ጉዳዮች የመነሸጥን እድል ማስፋት ያስፈልጋል።

በሦስተኛ ደረጃ ትኩረት የሚፈልገው ጉዳይ በአጠቃላይ የጥበብ ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የቴክኖሎጂ፤ የገበያ፤ የካፒታል እና የፖሊሲ ድጋፎች በማከናወን ዘርፉ በጥራትም በተደራሽነትም እንዲያድግ ማድረግ ነው። የጥበብ ስራዎቻችን ከሀገራችን አልፈው ወደ ሌሎች ሀገራትም እንዲሻገሩና ተፅዕኖ እንዲፈጥሩ ማድረግ፤ ለኢኮኖሚያዊም ሆነ ለፖለቲካዊ ግቦቻችን መሳካት የሚኖረው ድርሻ በቀላሉ አይታይም። የአሜሪካ ጂንስ፤ የቱርክ ሸሚዝና ጫማዎች፤ በፊልም ኢንዱስትሪዎቻቸው ምክንያት የፈጠሩት ገበያ እና ተፈላጊነት የሚታወቅ ነው። ከገበያው ባሻገር ለሀገሪቱ ገፅታ ግንባታ የሚያደርጉት አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

በሆሊውድ መስኮት ገዝፎ የሚታየን የአሜሪካ ሀገረ መንግስት ስሪት፤ ከተጨባጭ ስራዎች ባሻገር የጥበብ ውጤት እንደሆነ በቀላሉ መገንዘብ እንችላለን። ጥበብ ምናብን የሚቀርፅ፤ እሳትን የሚገነባ፤ ባህልን እየፈጠረና እየሞረደ የሚሄድ መግነጢሳዊ ሃይል አለው።

ከጥበብ የተዛመደ ትውልድ በሀሳብ የበላይነት ማመን ብቻ ሳይሆን በረጋና በሰከነ መንፈስ ምክንያታዊና ህሊናዊ ሆኖ የመወያየት ባህልን ያዳብራል። ከሁሉም በላይ ደግሞ የሰብዓዊነት ክብርን የሚያስቀድም እና በሀገሩ ፍቅር የሚቀጣጠል ትውልድ ሆኖ ይታነፃል። አርበኝነት ያለው የሀገር ፍቅር፤ ከጦረኝነት የተለየ እና የቅርብ ጎረቤቶቹን እና የሩቅ ወዳጆቹን ስኬት እና ብልፅግና የሚመኝ፤ የራሱን ሰብዓዊ ክብር በብሄራዊ ኩራቱና ሉላዊ ማንነቱ በሚፈጥረው ሚዛን ላይ ያስቀምጣል።

# ከስሜት እስከ ስክነት

## የስሜት ብልህነት

ስሜት የህይወት ቀለም ነው፡ ህይወትን ከስሜት ውጭ ለመኖር ብቻ ሳይሆን ለማሰብም ከባድ ነው። ፍቅርና

ፍርሃት፤ ኀዘንና ደስታ፤ ግርምትና ፀፀት፤ ጽያፎትና አድናቆት፤ ቁጣና ፈንጠዝያ የሌለበት ሕይወት፤ በመካነ መቃብር ውስጥ በሞት ከተሸበቡ ሰዎች የተለየ ምን ዓይነት ለዛ ሊፈጥር ይችላል? አፍቅሮ ማግባት፤ ወልዶ መሳም፤ ታግሎ ማሸነፍ፤ አዝኖ መርዳት፤ ተገርሞ መፈንደቅ፤ ተቆጥቶ ለፍትሕ መቆም፤ ፈርቶ መሸሽ ባይኖር፤ ሕይወት ምን ልትመስል ትችል ነበር? ስሜት ተለዋውጦ መልክ ብዙ ባይሆን፤ በአንድ ዓይነት ስሜት ውስጥ ብቻ ሆኖ ለስንት ጊዜ መዝለቅ ይቻላል? በጎዶሎ የስሜት ሕይወት ውስጥስ ለዘመናት መኖር፤ ሕይወትን ምን መልክ ሊሰጠው ይችላል? ስሜት ለሕፃንና ለዐዋቂ፤ ለወንድና ለሴት፤ ለተማረና ላልተማረ ሁሉ የሕይወት ማጣፈጫ ቅመም ብቻ ሳይሆን፤ ብቸኛ የመኖሪያና፤ ክፉና ደጉን አሉታዊና አዎንታዊ አጋጣሚዎችን የመለማመጃ መንገድ ነው፡፡

ስሜት የሕይወት መገለጫ ነው ማለትም ይቻላል፡፡ የስሜትን ምንነትም ሆነ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ያለውን ጉልህ ሚና አለመረዳት በራሱ በሚፈጥረው ጉድለትና ጥፋት እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ለረጅም ዘመናት ገዢ በነበሩ የሰው ልጆች ፍልስፍናዎች ውስጥ፤ ስሜት የብስለት ምልክት ሳይሆን እንቅፋት ተደርጎ መታየቱና፤ በእውቀት ያልበሰሉና ራሳቸውን መግዛት የማይችሉ ሰዎች ደካማ መገለጫ ተደርጎ መወሰዱ፤ በስሜት ላይ አሉታዊ ድባብ የጣለ ዕይታ ነበር፡፡ ይኽም ቢሆን ስሜት ስለገፉትና ስላኮሰሱት ከሰው ሕይወት የሚርቅ አይደለም፡፡ የስሜት ብስለትና ብልሕነት ባልተገነባበት ሕይወት ላይም ቢሆን፤ ወይ የስሜት ድርቀት አልያም ግልብ ስሜታዊነት ጎልቶ መታየቱ አይቀሬ ነው፡፡

በተለምዶ አይ ኪው (IQ) ተብሎ ከሚጠራው የዕውቀት ብልሕነት በተጨማሪ፤ የተለያዩ የብልሕነት ዓይነቶች እንዳሉ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይዘረዝራሉ፡፡ በቁጥራቸው ብዛት ባይስማሙም ከስምንት እስከ አስር የተለያዩ የብልሕነት ዓይነቶች በብዙ ጽሁፎች ላይ ይጠቀሳሉ፡፡ ከእነዚህ ውሰጥም የቀመር፤ የምስል፤ የሙዚቃ፤ የአካላዊ እንቅስቃሴ፤ የፍልስፍናና የማህበራዊ ግንኙነት ብልሕነቶች ይገኛሉ፡፡ አሁን አሁን ደግሞ የሞራልና የመንፈሳዊነት ብልህነትም ሲጠቀሱ ይስተዋላሉ፡፡ እያንዳንዱ ሰው በሁሉም የብልህነት ዓይነቶች ላይ የተለያየ የልህቀት ደረጃን ያሳያል፡፡ ብዙዎቹ የብልህነት ዓይነቶች የተፈጥሮ ተሰጦነት ቢኖራቸውም፤ በሥልጠናና በአስተዳደግ ሊዳብሩ ወይንም ሊኮስሱ እንደሚችሉም ይታወቃል፡፡

በ1990 እ.ኤ.አ አካባቢ በሁለት የዬል ዩኒቨርስቲ የሥነ ልቦና ምሁራን ከወጣው ጥናታዊ ጽሁፍና፤ እርሱን ተከትሎ በ1995 እ.ኤ.አ ለሕዝብ ከተሰራጨው የዳንኤል ጎልማን የስሜት ብልህነት ፋይዳና ብርታት መጽሐፍ በኋላ፤ ስሜት ከፍተኛ የሆነ አትኩሮትን ያገኘ ጉዳይ ሆኗል፡፡ አልፎ ተርፎም የስሜት ብልሕነት በሚል የሚጠራው ይሕ የብልሕነት ዓይነት፤ ስኬትና እርካታ ላለው የግንኙነት ሕይወት የሚሰጠው ፋይዳ ከመቼውም በላይ ጎልቶ የወጣበት ጊዜ ይመስላል፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ጥናቶችና ጽሁፎች፤ የተለያዩ የምርምር ማዕከላትና የማስተማሪያ ተቋማት በየሀገሩ በፍጥነት ተስፋፍተዋል፡፡ ስሜትን እንደ እዳ ሳይሆን እንደ ሀብት፤ እንደ እንቅፋት ሳይሆን እንደስኬት መሰረት ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ በተለይም የሥሜት ብልህነት በሥልጠናና በልምምድ የሚያድግ ከመሆኑም ባሻገር፤ የዕድሜና የትምህርት ደረጃ ውሱንነት ሳይገድበው ማንኛውም ለመለወጥ የተዘጋጀ ሰው ሊያዳብረው የሚችለው ክህሎት መሆኑ፤ ጉዳዩን ይበልጥ ተፈላጊ ሳያደርገው አልቀረም፡፡

በሀገራችን ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎችና ዘመናት የኖሩ ትውልዶች፤ የስሜት ብልህነትን ችላ ያሉ ነበሩ። ባልተገራና ብስለት ባጣ ስሜታዊነት የተነሳም፤ ብዙ ጥፋት መድረሱን ለማየት ከባድ አይደለም። በሀገራችን እንደ ጎርፍ ተምመው ባለፉ የለውጥ ማዕበሎች ውስጥ፤ የመሪዎችና የሕዝብ ስሜት ያደረሰውን ጥፋትና ጉዳት ለመለካት አዳጋች ነው። በዚያው ልክ በደልን ለመቃወምና የሀገር ፍቅርን ለመግለጥ፤ እምነትን ለማክበርና ድልን ለመጋራት የስሜት ድርሻው ከፍተኛ ነበር። ጥላቻና ቁጣ፤ ኩርፊያና ኀዘን፤ ፍርሃትና የበቀል ስሜቶች የፈጠሩት ሀገራዊ ጠባሳ፤ ዛሬም ገና ቁስሉ አልተሻረም። በየቤቱ የታፈኑና የፈነዱ፤ ያልተገለጡና ከቁጥጥር ውጪ ሆነው ለያዡ ለገናዡ ያስቸገሩ ስሜቶችን ሁላችንም እናውቃለን። ይሕ ሁሉ ሲሆን ግን ቤተሰብም ሆነ በትምህርት ቤት፤ በቤተ-እምነትም ሆነ በሚዲያ፤ የስሜትን ምንነትም ሆነ አያያዝ በቅጡ የመማርና የማወቅን እድል አለማግኘታችን ደግሞ፤ ነገሩን ይበልጥ አስገራሚ ያደርገዋል።

በመደመር ትውልድ ዘመን ግን የስሜትን ፋይዳና ዕምቅ ዐቅም እንረዳዋለን። መጪውን ትውልድ በዚ ረገድ የማስተማርና በዚህ ረቂቅ ክህሎት ማብቃት እንዳለብንም እናምናለን። ሀገርን አሁን ካለችበት የስሜት አረንቋ ውስጥ የማውጣት ፋይዳ ብቻ ሳይሆን፤ ወደ ሁለንተናዊ ብልጽግና የማንደርደር አስተዋጽኦውም ከግምት በላይ ነው። በስሜቱ የበሰለና የተገራ ትውልድ፤ ለመደማመጥና ለመረዳዳት፤ የራሱንና የሌላውን ሁኔታ ለመረዳትና እንደ አመጣጡ ለማስተናገድ፤ የተሻለ ብቃት ይኖረዋል። በስሜት ግብታዊነት ከሚደረጉ አጉል ነውጥና ፍሬ ቢስ ድርጊቶች እንዲታቀብ ያስችለዋል። ከወገኖቹ ኢትዮጵያውያን ጋር ብቻ ሳይሆን፤ ከጎረቤት ሀገራት ወንድምና እህቶቹ ጋር ተስማምቶና ተከባብሮ የመኖርንና፤ ያለውን ተጋርቶ የማደርን ጸጋም እንዲጎናፀፍ ይረዳዋል። ፈጠራንና ፈጣን እድገትን፤ ጥበብንና ደስተኝነት የተጎናፀፈ ማህበረሰብ ፈጥሮ ይኖራል። ሌሎችም እንዲኖሩ ይፈቅዳል፤ ይተጋል። የሕይወትን ጸጋ የሚያደንቅ ብቻ ሳይሆን የሚለማመድን ማበረሰብ ለመፍጠር ቁልፍ ግብዓት ይሆናል።

የስሜት ብስለት ማለት በቅድሚያ የራስን፤ በማስከተልም የሌሎችን ስሜት የማወቅ፤ የመረዳትና በተገቢው መንገድ የመምራት ረቂቅ ክህሎት ነው። ለስሜት በቂ ቋንቋ ያለውና ስሜቱን ያለስሜታዊነት የሚገልፅ፤ ለራሱ ስሜት የባለቤትነትን ኃላፊነት የሚወስድ፤ ስሜቱን ተጠቅሞ ግንኙነቶቹንና ኃላፊነቶቹን በብቃት የሚወጣ ትውልድን መፍጠር የስሜት ብስለት ነው። ከመሠረታውያኑ ጀምሮ እስከ ውስብስብ በስሜት ጥልቀቶች ድረስ ያሉትን ደርዞች መረዳትና መጠቀም የስሜት ብስለት መገለጫ ነው። እነዚህ ስሜቶች ሾልከው ከቁጥጥር ውጭ ሳይሆኑ፤ በተገቢው ቋንቋና ባህሪያዊ መንገዶች የመግለጥ ብቃት የስሜት ክህሎት አንዱ ክፍል ነው። የራሱን ስሜት በቅጥ ተረድቶ የገዛ ግለሰብና ትውልድ፤ ለሌሎች ስሜት ዋጋ መስጠትና መረዳት አይከብደውም። ራስን በሌሎች ቦታ አድርጎ የሌሎችን ስሜት መረዳት ደግሞ ከፈራጅነት ያወጣል። የሰዎችን ስሜት እንደነርሱ ሆኖ መረዳት ብቻ ሳይሆን፤ በመተጋገዝ፤ በቀናና በመተዛዘን ስሜት በመተያየት፤ ሁሉንም አሸናፊ የሚያደርገውን ከፍ ያለ ጎዳና ለመጓዝ ሰፊ ምርጫን ይሰጣል።

የመደመር ትውልድ ቁሳዊ ሀብቱን ብቻ ሳይሆን፤ የስሜትና የሐሳብ ረቂቅ ሀብቱ የሚያገናዝብና የሚያሳልጥም ነው። በዚህ ተሳልጦ ከዚህ ቀደም ወዳልደረሰበት የብልጽግናና የሥልጣኔ ማማ ለመውጣት ይችላል። በስሜት የዳበረ ሐሳብ በቂ ጉልበትና ልባዊ መሰጠት ስለሚኖረው፤ ወደ ትክክለኛ ተግባር መምጣቱ

አይቀርም። ሥራና ትምህርት፤ ፈጠራና ግንኙነት፤ ኃላፊነትና ዕድል ሁነኛ ስሜት ሲታከልባቸው፤ ውጤታቸው የላቀ ነው። ቁጣውንና ርካታውን፤ አድናቆቱንና ጭንቀቱን፤ ደስታውንና ኃዘኑን፤ ግርምቱንና መጸየፉን በትክክለኛው መንገድ መረዳትና መግለጥ የቻለ ትውልድ፤ በችግሩና በተገዳዳሪዎቹ ላይ የበላይ ለመሆን ቅርብ ነው። ማንም በሆነ ባልሆነው፤ በመረጃና በአጀንዳው፤ በቀላሉ ሊነዳው አይችልም። ስሜቱ የተገራና የበሰለ ትውልድ ሥልጣኔን የሚፈጥር፤ ስኬትን የሚሸከም፤ ተግዳሮትን የሚጋፈጥ፤ ልዩነትን የሚቀበልና አንድነትን የሚጠብቅ ይሆናል።

## ሚዛን ያለመሳት ትግል

ስሜቶች እንደማንኛውም ነገር ከልክ በታች ሲያንሱም ሆነ ከልክ ሲበዙ ጤናማነታቸው ይጓደላል። በልካቸው ሲሆኑ ግን ሁሉም ስሜቶች የሰው ልጆች ዓለምንና ክሥተቶችን የሚረዱባቸውና የሚመዝኑባቸው መሣሪያዎች ናቸው። ፍርሃት ባይኖር የሰው ልጆች በአደጋ ያልቁ ነበር። ደስታ ባይኖር የሕይወትን ጣዕም ያጡ ነበር። ኀዘን ባይኖር የመለያየትን ጉዳት አይረዱም ነበር። ንዴት ባይኖር አደጋዎቻቸውን አይጋፈጡም ነበር። ሁሉም ስሜቶች የሰው ልጆችን ሕልውና ለማስጠበቅ የሚያገለግሉና፤ ነገሮችን የምንመዝንባቸው ደመ ነፍሳዊ ደወሎች ናቸው። አደጋ ሲኖር ፍርሃት፤ ጥቃት ሲኖር ንዴት፤ ድል ሲኖር ደስታ፤ ጉዳት ሲኖር ሃዘን፤ ወዘተ. የሚጠቁሙንና ዝግጁ እንድንሆን የሚያደርጉን የመላመጃ ስልቶች ናቸው።

ነገር ግን ስሜቶች በአንዳችን ሁኔታ ሲያንሱ ወይም ሲበዙ፤ የሰው ልጅን ሚዛን የሚያስቱ አውሎ ነፋሶች ይሆናሉ። ከቆምንባቸው የሕይወት መርሖችና ከተገነባንበት ስብዕና አናግተው ሚዛናችንን የሚያስቱን ስሜቶች ናቸው። ነፋስ ዛፍን ሊያወዛውዘው ይችላል፤ ያም ለዛፉ ሕይወትም ጥቅምም ነው። ነቅሎ እንዲወስደው ወይም እንዲጥለው ግን መፍቀድ የለበትም። ዋናው ጉዳይ አውሎ ነፋሱን ተቋቁሞ ለሚፈልገው ነገር ማዋል መቻል ነው። እንደጠወለገ ቅጠል በነፋስ የምንወሰድ ሳይሆን፤ እንደዋርካ ባለንበት ጸንተን ነፋሱን የምንጠቀም መሆን አለብን።

ስሜቶችን የሚቋቋምና ወደ ሚዛኑ በቶሎ የሚመልስ የሕይወት ዘይቤ ‹‹ስክነት›› ይባላል። ስክነት የመደፍረስ ተቃራኒ ነው።መደፍረስ አለመርጋትን፤ አለመጽናትን፤ መረበሽን፤ ስፍራ ማጣትን፤ ምንነትን ማጣትን የሚያመላክት ነው። በአንጻሩ ስክነት ነገሮች ወደ ሥፍራቸው መመለሳቸውንና መርጋታቸውን የሚያመለክት ነው። በሕይወታችን ውስጥ የሚከሠቱ ልዩ ልዩ አጋጣሚዎችን ተከትለው ስሜቶቻችን ከሥፍራችን ያነቃንቁናል፤ ከመርሐችን ይንጡናል፤ ከቆምንበት ዓላማ ያዛንፉናል። የተነሳንበትን ግብ ረስተን፤ ሚዛናችንን ስተን፤ ከመሐላችን ርቀን፤ ከእሴቶቻችን ተናጥበን፤ ካደግንበት የማንነት ሥሪት ርቀን፤ ሌላ ዓይነት ዓለም ውስጥ እንገባለን። ብዙዎቻችን ከእንዲህ ዓይነት መንገዳገዶች ተመልሰን ሚዛናችንን መጠበቃችን አይቀርም። ዋናው ጥያቄ ግን መጀመሪያውኑ በነፋሱ ላለመንገዳገድ፤ በማዕበሉ ላለመወሰድ፤ ከዓላማና ከስብዕናችን ላለመራቅ በስክነት መቆም መቻል ነው።ስክነትን ከመደፍረስ  ቡኃላ የሚመጣ ብቻ ሳይሆን፤ በመደፍረስ ጊዜ ማዕበሉን የምናሳልፍበት የማንነታችን አካል ማድረግ ይኖርብናል። የስሜት ነፋሶች እዚህና እዚያ እንዳያላጉን፤ ሥራችንን የሰደድን ዋርካዎች መሆን አለብን።

## ስክነትን ሚያመጣው ምንድነው?

አእምሮ የሚጓዘው አመክንዮና ስሜትን በሁለት ጫፍ አድርጎ ነው፡፡ አመክንዮ ነገሮችን በዕውቀት፤ በሐሳብና፤ በምክንያት፤ በመረጃና በማስረጃ እንድንመዝን የሚያደርግ ነው፡፡ ስሜት ደግሞ ከእኛ በሚወጡ ወይም ወደ እኛ በሚመጡ መረጃዎች፤ ሐሳቦች፤ ምስሎች፤ ወዘተ. ምክንያት የሚፈጠር መናወጥ ነው፡፡ አእምሮ በአመክንዮ ደርቆ የሮቦት ጠባይ እንዳይኖረው፤ ሰብአዊ መንፈስ የሚያጎናጽፈው ስሜት ነው፡፡ ስሜት ማዕበል ሆኖ አእምሮን ይዞት እንዳይነጉድ፤ እንደ መልሕቅ የሚያጸናው ደግሞ አመክንዮ ነው፡፡ ስሜትንና አመክንዮን ማመዛዘን ሲቻል፤ ስክነት ይመጣል፡፡

ሕጻናት፤ በተለይ በገጠር፤ የሚጫወቱበት ወስፈንጥር የሚሉት መሣሪያ አላቸው፡፡ በባላ እንጨት ላይ የሚለጠጥ ቀጭን ላስቲክ ያስራሉ፡፡ በባላው ትክክል ለጠጠር መያዣ የሚሆን ነገር ያያይዙበታል፡፡ ከዚህም ጠጠሩን በመካከል አድርገው ላስቲኩን በመለጠጥ ወፎችን፤ ዝንጀሮዎችንና ጃርቶችን ከማሳ ላይ ለማባረር ይጠቀሙበታል፡፡ የወስፈንጠሩ ላስቲክ ስሜት፤ የወስፈንጠሩ እንጨት ደግሞ አመክንዮ እንበል፡፡ ላስቲኩ ከልክ በላይ እንዳይለጠጥ፤ ከተለጠጠም በኋላ ወደ ቦታው እንዲመለስ የሚያደርገው ባለ ባላው እንጨት ነው፡፡ ባለ ባላው እንጨት ተለጥጦ ጠጠሩን ሊያስወነጭፍ አይችልም፡፡ ይህንን ለማድረግ የሚያስችለው ላስቲኩ ነው፡፡ ስክነት በሁለቱ መካከል የሚገኘው መናበብ ወይም ሚዛን ነው፡፡

መጪው ትውልድ በስሜት ሰክኖ የሚቆይና፤ ከመርህና ከማንነቱ በቀላሉ የማይናጠብ እንዲሆን፤ የኢትዮጵያን የስሜት ታሪኮች መመርመርና ተገቢውን ትምህርት መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች ትውልዶች ያለፉባቸው የስሜት ማዕበሎች፤ ከማንነታቸውና ከዓላማቸው በተቃራኒ እንዲጓዙ ያደረጉባቸውና፤ ብዙ ፀፀት ያተረፉባቸው ናቸው፡፡

## ሦሥቱ የሥሜት ልጓሞች

መጪው ትውልድ ስሜቱን የሚገራና የሰከነ እንዲሆን ቢያንስ ስሜቶቹን የሚቆጣጠርባቸውን ሦሥቱን መንገዶች በአግባቡ መምራት ይኖርበታል፡፡ ንዴት፤ ፍርሃት ደስታ፡፡

## የንዴት ልጓም፤ ሆደ ሰፊነት ወይስ ቂመኝነት?

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በጥቃቅን ጉዳዮች የተጀመሩ ቅራኔዎች የንዴትና የእልህ ነዳጅ እየጠጡ፤ ወደ ትልቅ እሳትነት የተቀየሩባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡ ከቀላል እስከ ከባድ የሚደርሱ ፖለቲካዊ ልዩነቶች በእሰጥ አገባ እየጋሉ ሄደው፤ በመጨረሻም እንደ እሳተ ጎመራ የፈነዱባቸው ክስተቶችን በታሪካችን አልፈናል፡፡ ሽብሮችን በቀለም እየሰየሙ እርስ በእርስ መጨራረስ የቅርብ ጊዜ ትዝታዎቻችን ናቸው፡፡ የንዴትን ፍም

እንዲቆይ የሚያደርገው እልህ ነው፤ የእልህ ፍም ተዳፍኖ እንዲቆይ የሚያደርገው ደግሞ ቂመኝነት ነው። ንዴት ወዲያው ሲገለጽ ግልፍተኝነት ልንለው እንችላለን፤ በቀጣይነት ሲገለጽ እልህ፤ ተዳፍኖ ሲቆይ ደግሞ ቂም ይሆንና በተግባር ሲገለጽ በቀል ተብሎ ይጠራል።

ቂም የንዴት ፍምን አዳፍኖ የማቆየት ሂደት ነው። ከጊዜ በኋላ ፍሙ ከተደበቀበት አመድ ወጥቶ በበቀልነት ጥፋት ማድረሱ አይቀርም። በተጻራሪው ደግሞ ሆደ ሰፊነት ፍሙን ተቋቁሞ የማክሰም ኃይል ነው። ፍምን በውሃ የመያዝ ዐቅም ነው። ንዴትን ቋጥሮ የማቆየት ሳይሆን፤ ከንዴት በላይ እንደሆንን የመረዳት ውጤት ነው። የንዴት ነፋስ የማይበግረን፤ በስሜት ማዕበል የማንናጥ፤ በቂም ረመጥ ተቃጥለን የማናቃጥል፤ ጽኑአንና ብርቱዎች የመሆን ጉልበት ነው። አይቶ ማለፍ፤ ሰምቶ መቻል። ሰዎችን በእነርሱ ጫማ ውስጥ ሆኖ ለመረዳት መሞከር፤ ክስተቶችን በልካቸው ለመገንዘብ መጣር ነው። መጪው ትውልድ ሆደ ሰፊ፤ በንዴት፤ በእህልና በቂም የማይነዳ እንዲሆን፤ ከስሜቶቹ በላይ የሆነ ትውልድ መፍጠር ይኖርብናል።

## የፍርሃት ልጓም፡ ልበ ሙሉነት ወይስ ጭካኔ?

ፍርሃት ከልክ ካነሳ ጀብደኝነትን፤ ከልክ ካለፈ ደግሞ ጭካኔን መውለዱ አይቀርም። ፍርሃት ሲያንስና ድፍረት ሲበዛ፤ ከዐቅም በላይ የሆኑ አደጋዎችን መጋፈጥ እንጀምራለን። ይኽ ደግሞ ውጤቱ ጥፋትና ጉዳት ነው። ፍርሃት ሲበዛ ደግሞ በደመ ነፍስ መውተርተርንና እጠፋለሁ ብሎ በመሥጋት፤ ለሕልውና መፍጨርጨርን ይፈጥራል። ይኽ ደግሞ ጭካኔን ይወልዳል። በሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ ብዙ የጭካኔ ድርጊቶች ፍርሃት የወለዳቸው ነበሩ። ፍርሃት የሕልውና አደጋን አጋንነን እንድናይ ያደርጋል። የፍርሃት ደወል ሲበዛ ሥጋት እንዲጨምር ያደርጋል። በዚህ ጊዜ ሕልውናችንን ለማስጠበቅ ስንል የማንፈነቅለው ድንጋይ አይኖርም። ይኽም ሁኔታ የሞራል ድንበራችንን ጥሰን፤ በሰዎች ላይ የጭካኔ በትር እንድናሳርፍ ያደርገናል።

ሕልውናችን አደጋ ላይ የወደቀ ሲመስለንና፤ ሕልውናችንን ለማትረፍ መጣር የመጨረሻ አማራጫችን እንደሆነ ስናስብ፤ የምናሳልፈው ውሳኔና የምንወስደው እርምጃ ከፍተኛ ጭካኔን ሊወልድ ይችላል። በፖለቲካዊ መጠላለፎችና በጦርነቶች ላይ የምናስተውላቸው የጭካኔ ነውሮች የሚያሳዩት፤ የፍርሃት ጥላ ያረበበባቸውን የታሪክ ገፆቻችንን ነው። በአንጻሩ ፍርሃትን የሚገራውና ከሚዛናችን እንዳንዛነፍና መርሐችንንና ማንነታችንን እንዳንስት የሚያደርገን፤ ትልቁ የፍርሃት ልጓም ልበ ሙሉነት ነው። ልበ ሙሉነት ፍርሃትን ገርቶ በሞገስ የሚያቆመን፤ ሩህሩህነትን የሚያላብሰን፤ ከእሴታችንና ከዓላማችን እንዳንዛነፍና እንዳንደናበር የሚያደርገን የስሜት ልእልና ነው። ልበ ሙሉነት የሚመጣው አመክንዮ ስሜትን በሚገባ መግራት ሲችል ነው።

## የደስታ ልጓም፡ እብሪት ወይስ ቁጥብነት?

ደስታ ምኞትን የማሳካት፤ ድል የማድረግ፤ ያሰቡትን የማግኘት ውጤት ነው። ደስታ በሕይወት ውስጥ ትልቅ ሥፍራ የምንሰጠው የስሜት ዓይነት ቢሆንም፤ በልኩ ካላስተናገድነውና ካልገራነው፤ ያልተፈለገ ውጤትና ጥፋት ሊያስከትል ይችላል። ደስታ ሲበዛ እብሪት ይፈጥራል፤ እብሪት መዘናጋትን ይፈጥራል፤ መዘናጋት ስንፍናን ይፈጥራል፤ ስንፍና ደግሞ ሽንፈትና ውድቀትን ያስከትላል። በታሪካችን ድሎቻችን መዘናጋትን

ፈጥረው ለፈተና ሲዳርጉብን አስተውለናል። በአድዋ ድል ተዘናግተን ለሁለተኛው የጣልያን ጦርነት እንዳንዘጋጅ አድርጎናል።

የደስታ ልጓም ቁጥብነት ነው። ነገሮችን በልካቸው ማየትና መደሰት፤ ከዚያም ለቀጣይ ድልና ስኬት መገስገስ ያስፈልጋል። መጪው ትውልድ ድሉን በልኩ የሚያይ፤ ቁጥብነት የባህርይ መገለጫው የሆነ፤ በደስታ ስካር ውስጥ ገብቶ ያገኘውን ድል የማያጣ፤ ሁሌም ተጨማሪ ከፍታን የሚያማትር መሆን ይኖርበታል።

## የሚያምንና የሚታመን ትውልድ

ማመንና መታመን ከህሊናዊ እምነት የሚቀዱ፤ በማህበራዊ መስተጋብር ሲታይ በመተማመን መልክ የሚገለጡ የድርጊትና የአኗኗር ዘይቤ ሆነው እናገኛቸዋለን። እምነት ቁስ ተሻጋሪ በአካል ሊዳሰስ የማይችል፤ በሰብዓዊ ፍጡራን ህሊና የሚኖር ክስተት ነው። እምነት አካላዊ መልክ አይኑረው እንጂ፤ ለተላበሰው ሰው ድርጊትን የሚመራ፤ ተተግብሮም የሚፈጥረው እውነት ሊዳሰስና ሊጨበጥ የሚችል ውጤትን የሚያስገኝ ነው። የሞራል ልህቀት፤ ለህሊና መገዛት፤ ቃል መጠበቅ፤ መውሰድ ብቻ ሳይሆን መልሶ መስጠት፤ በሀቅ ማገልገልና መሰል ግብረገብ ድርጊቶች የእምነት ምንጮች ናቸው።

አንድ ማህብረሰብ የኑሮን ስንክሳር አሸንፎ ለመዝለቅ፤ ኑሮውን አሻሽሎም የበለፀገ ህይወት ለመገንባት፣ ግላዊና ተናጠላዊ ሩጫው አይበቃም። የተሻሻለ ማህበረሰብና ሀገር ለመገንባት፤ ግለሰቦች ለጋራ ዓላማ ተደምረው ለውጤታማ እንቅስቃሴ የሚሰለፉበት፤ የተባበረ ክንድ ያስፈልጋቸዋል። የተባበረ ክንድ መፍጠር የማይችል ሀገርና ህዝብ፤ ከተናጠላናዊ የግለሰቦች አቅም የዘለለ፤ ታላቅ አላማን ማሳካት አይቻለውም። መተባበር መተማመንን ይጠይቃል። የማይተማመን ህዝብ ድርጊቶቹን ለጋራ ራዕይ የሚያስተባብርበትና፤ አቅሞቹን ለሁሉም ጥቅም ሚያሰልፍበትን፤ የትብብር ግንኙነት መፍጠር የሚቻለው፤ ትብብሩ የሚፈፀምበት ስርዓት በተሳታፊዎቹ እምነት የሚጣልበት ሆኖ ሲገኝ ብቻ ይሆናል።

‹‹የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል›› እንዲሉ፤ መተማመን የሌለው ስብስብ የጋራ ህልሙን ለማሳካት ከመረባረብ፤ እርስ በእርስ ጥርጥር ውስጥ እየገባ ውጤት ማግኘት የማይችል፤ ሁሉም ግላዊ ጥቅሙን በማሳደድ ላይ የሚጠመድበትና ጥቃቅን ስኬቶች ያሉት፤ ነገር ግን የጋራው የደከመ ህብረት የሚፈጥር ይሆናል። መተባበር ሊመጣ የሚችለው፤ እርስ በእርስ መተማመን ሲኖር መሆኑ ግልጽ ነው። መተማመን የሌለው ስብስብ፤ የለፋው እያለ ያልደከመው ውጤቱን የሚሰበስብበት ይሆናል። አበዳሪው ብድሩ ሊመለስ አይችልም ብሎ ስለሚያስብ፤ የገንዘብ አቅም ያለው፡ ሃሳብ ያለውን ለመደገፍ የሚችልበት እድል የሚጠብ ይሆናል።

መተማመንን ያዳበረ ማህበረሰብ፤ ከሌላው ጋር ተደምሮ መስራት፤ ከእርሱ ውስን አቅም የላቀ ውጤት እንደሚያመጣ በሚያምኑ የተሞላ ነው። አበዳሪ ብድሩ አድጎ እንደሚመለስልት እምነት ስላለው፤ ሃሳብ ላለው መያዣ ሳይቀበል ለማበደር የማይቸገርበት ነው። ሃሳብና ካፒታል በቀላሉ የሚሰናኙበት፤ አብሮ ማደግና መለወጥ ቀላል የሚሆንበት አውድ ነው። ቃሉን የሚጠብቅ ፖለቲከኛ የፈጠረ የሚተማመን ማህበረሰብ

የምርጫ ቅስቀሳዎች የሚታጀቡት፤ አማላይ በሆኑ የማይሳኩ ህልሞች ሳይሆን በሚጨበጡ እቅዶች ይሆናል፡፡

ህግንም ህግ የሚያደርገው የሚጣልበት እምነት ነው፡፡ ህግ በሚገዛለት ህዝብ መታመንን ካጣ፤ ህግ መሆኑ ቀርቶ የአምባገነኖች ትዕዛዝ ይሆናል፡፡ የሚገዛለት ያጣ ህግ በምንም አስገዳጅ ኃይል፤ የተግባር ፋይዳ ሊያገኝ ያዳግተዋል፡፡ የህግ መሰረቱ የሚፈፀምበት ኃይል መበራከቱ ሳይሆን፤ በህጉ ገዢነት ላይ ማህበረሰቡ የፈጠረው ከእምነት የመነጨ ቅቡልነት ነው፡፡ በመሆኑም ጥቂቱን ለይቶ ለመጥቀም የሚወጣ ህግ እምነት ስለማይኖረው፤ ተማምኖበት የሚገዛለት አያገኝም፡፡

መተማመን የራሱ ልክና መጠን አለው፡፡ መተማመን ሲጠብና ሲሰፋ ሲበዛና ሲያንስ፤ ጉዳትና ጥቅሙም በዚያው ልክ የሚቀያየር ይሆናል፡፡ የእርስ በእርስ መተማመን ከቤተሰብ፤ ወደ መንደር ከዚያም አልፎ ወደ ሀገር ሲሻገር በረከቱ የበዛ ይሆናል፡፡ መተማመን የሰፋለት ማህበረሰብ የማደግ እድሎቹም እንደዚያው የሰፉ መሆናቸው አይቀርም፡፡ መተማመኑ መተባበርን ይገነቡለታል፤ ታላላቅ ህልሞችን መፍጠርና እውን ማድረግም የሚችል ህዝብ ይፈጥርለታል፡፡

የብዙኃኑ ታላላቅ ህልሞችን ማሳካት የቻሉ አካላት ልምምዶች ተሞክሮም የሚያስረዳን ይኽንን ነባራዊ ሀቅ ነው፡፡ በግዙፍነታቸውና በስኬታቸው ተምሳሌት የሆኑ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች የስኬታቸው ቁልፍ፤ የገነቡት ህንጻ፤ የገጠሙት ቴክኖሎጂ ወይም የቀጠሩት ክህሎት የታደለ የሰው ሀብት አይደለም፡፡ ይልቁንም በሠራተኞቻቸውና በሥራ አስኪያጆቻቸው መካከል መፍጠር የቻሉት፤ ለጋራ ታላቅ ግብ የመሰለፍ ህልም፤ ያንንም ህልም ለማሳካት የሚያስችለውን መተባበር የሚፈጥር፤ የእርስ በእርስ መተማመን፤ መሆኑን ብዙዎቹ ይመሰክራሉ፡፡ በሀገራት ብልፅግናም ሁኔታው ተመሳሳይ ገፅታ የሚታይበት ነው፡፡ ቻይና ለላቀ ከፍታ መምዘግዘግ የቻለችበት ህልም፤ በሚተማመኑ መሪዎቿ የተቀየሱ ናቸው፡፡ ህልሙን ያሳካው ህዝቡም በኮንፊሻን ባህላዊ እምነቱ፤ የአብሮነት መተማመንን የገነባ በመሆኑ ነው፡፡

መተማመን በሁሉም ዘንድ እየሰፋና እያደገ ሲሄድ ትሩፋቱ የማይገደብ የመሆኑን ያህል፤ መተማመን ሲጠብና ማደግ ሲያቆም ጥፋትን ማስተከተሉ አይቀርም፡፡ የምናምነው የዘርና የብሄር ተጋሪያችንን ከሆነ፤ ከዚህ ክበብ ውጭ የሚገኘውን ሰው እንደሌለ ፍጥረት፤ ሰብዓዊ ክብርና ርህራሄ የማይገባው፤ ህሊናዊ የሞራል ድንጋጌዎቻችን የማይፈጽሙበት፤ አድርጎ መቁጠር ይመጣል፡፡ የመተማመን ክበባችን ሲጠብ፤ በክበባችን ጥበት ውስጥ የሚካተተው የብሄር ወይም የዘር ተጋሪ አድርገን ለምናየው ሰው የምንሰጠው ሰብዓዊ ክብርና ርህራሄ፤ ከመተማመን ክበባችን ውጭ ያለው እንዲያገኘው አንፈቅድም፡፡ የእኛ ላልነው መሰላችን የምናሳየው መታመንና መቆርቆር፤ ከመተማመን ማቃፋችን ውጭ ላለው ስለማይሰራ ሌላውን እናገላለን፤ እንገፋለን፤ እንበድላለን፡፡

ብዙ የታሪክ ግፎች የተከሰቱት፤ ከመተማመኛ ክበባችን ውጭ ላለው እንግዳ ሰው ከምንሰጠው የአይታመኔነት እይታ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የአይሁድ ዘርን በጥላቻ ነጥሎ ለማጥፋት ‹‹የመጨረሻውን መፍትሄ›› ያቀደው ህሊና፤ ከራስ ወገን ውጭ ያለውን ለማመን የተቸገረ፤ የመተማመን ጥበት ሰለባ የሆነ አካል ነው፡፡

በዓለም ዙሪያ ብሎም በሀገራችን፤ በጽንፈኝነት ናውዞ ንጹሃንን ለፍጅትና ለመፈናቀል የሚዳርገው የዘረኝነት ልክፍት፤ ሌላውን እንደራስ ተቀብሎና አምኖ በሰብዓዊነት የማየት ፈተና፤ ውጤት መሆኑ እርግጥ ነው። የህዝብን ሀብት የግልን የቤተሰብ ሀብት ይመስል የመዝረፍና የመበዝበዝ በሽታ የተንሰራፋባቸው ታዳጊ ሀገራት፤ ከራስ ወገን አልፎ ማሰብ የማይቻልበት የማመን ግሽፈት የተሰራፋባቸው በመሆናቸው ጭምር ነው። የችግሩ መልክና ስፋት ያከራክር እንደሆነ እንጂ፤ ተመሳሳይ ሁኔታ ለሀገራችን ፖለቲካ መገለጫው ነው።

## የአለመተማመን ዋጋ

ነጋዴውን ገዢው በጥርጣሬ ከተመለከተው፤ ተገልጋዩ አገልጋዩን በአይነ ቁራኛ ካየው፤ ሕዝብ ፖለቲከኞች ላይ እምነት ከአጣ፤ ዳኞች በፍትህ ጠያቂዎች ዘንድ ታምነው ካልታዩ፤ በአንድ ግንባር የተሰለፈ ወታደር እርስ በእርስ ጥርጣሬ ውስጡ ከሰረጸ፤ ወዘተ… እንደ ማህበረሰብ ችግር ውስጥ ነን። ማህበረሰባዊ ሥርዓቶች በአጠቃላይ የተመሰረቱት በእምነት መሰረት ላይ ነው። የእምነት መላላት በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ግንኙነቶች ጤናማነትን ጥያቄ ውስጥ ይከትታል።

ማመንና መታመን የሌለበት ማህበረሰብ ሥርዓቶቹን ማቆየት ይከብደዋል፤ ሌላ መገንባትም አይቻለውም። ማመንና መታመን የጎደለበት ማኅበረሰብ ሕብረትና ጽናቱ እየቀነሰ ስለሚመጣበት፤ የትኛውንም ዓይነት ሥርዓት ለመገንባት አይቻለውም። የማኅበረሰብ አባላት አለመተማመን ሲፈጠርባቸው፤ ሕብረታቸውና አንድነታቸው ይላላል። ለገነቡት ሥርዓት ያላቸው ቁርጠኝነትና ጽናት በዚያው መልኩ እየተነቃነቀ ይመጣል። ማመን መታመን አለመቻል በዋናነት ሕብረትንና አንድነትን ያናጋል። ሰዎች ለጋራ ዓላማና በጋራ ግብ ከመንቀሳቀስ ይልቅ፤ በየፊናቸው የሚደረግ የተናጥል ጉዞን ይመርጣሉ። ለምሳሌ ባደጉት አገራት ለዘመናት በተገባው የዲሞክራሲ ሥርዓታቸው ላይ እምነት በማጣታቸው ለመምረጥ ዳተኛ ሲሆኑ ይስተዋላል።

አለመተማመን በነገሰበት ማህበረሰብ የጋራ ግቦች ቦታ እያጡ፤ ግጭት፤ ግለሰባዊ እና ቡድናዊ ጥቅምን ለማሳካት፡ ዋነኛ መሳሪያ ሆኖ ብቅ ይላል። በጭፍን ጥላቻ ላይ የተመሰረተ አክራሪነት ዋነኛ መገለጫው ነው። በአገራችንም ማኅበረሰባዊ እሴቶች ተሸርሽረውና አለመተማመን ዳብሮ፤ ለብዙ ቀውስ መነሻ ሆኗል። የማመን መታመን መሸርሸር መንስኤዎች የተለያዩ ሲሆን፤ የማኅበራዊ ተቋማት መዳከምና ቦታ እያጡ መምጣት ቀዳሚው ነው።

ማመን መታመንን መገንባት የረጅም ጊዜ ሂደት ውጤት ነው። በማኅበረሰብ ውስጥ እምነት እያዳበረ የሚመጣው፤ በዋናነት ሃይማኖትና ባህል በሚፈጥሩት የጋራ ሥነ ምግባራዊ እሴቶች ውስጥ ነው። በዚህ መልኩ የዳበረ እምነት በጊዜ ሂደት እነዚህን ማህበራዊ መሰረቶች በተለያዩ ጉዳዮች መነቅነቅ ሲጀምር፤ እንዲሁም በድርጊቶችና በክስተቶች ውስጥ እየተሸረሸረ ይመጣል። በዚህም ረገድ ከፍተኛ የጥላቻና የአሉታዊ መረጃዎች ስርጭት የትውልድን እምነት እየሸረሸሩ ካሉ ጉዳዮች መካከል ቀዳሚው ነው።

የሚሰራጩ መረጃዎች የተጫናቸው ጥላቻና አሉታዊ ድባብ፤ ሰዎች በሰዎች ላይ ያላቸው እምነት እንዲሸረሸር አድርጓል። ለምሳሌ ስለግለሰቦች፤ ብሔሮች፤ ሃይማኖቶች የሚሰራጩ ተከታታይ አሉታዊና የጥላቻ

አሉባልታዎች፤ እርስ በእርስ መተማመን እንዲላላና በምትኩ ፍርሐትና ግጭት እንዲነግስ ያደርጋሉ። በአባቶቻችን ዘመን ሰው ፊት የሚቀርብ ነገር የተመረጠ ነበር። ሰው ፊት የሚቀርብ ምግብም ይሁን ሃሳብ ንጹሕና ጥሩ ተመርጦ ነው። ያልጠራ ወሬ ሰው ፊት ተይዞ አይቀረብም። ነገር ግን ይህ ባህል ተሸርሽሮ፤ ፍሬውን ከግርድፉ፤ ውሸቱን ከእውነቱ ሳይለዩ የሚሰራጩ ሃሳቦች ሰው ፊት ለመቅረብ ያልበቁ ወሬዎች፤ ጥርጣሬን የዘመኑ ገዢ እንዲሆን አድርገዋል።

እውነት የእምነት መሰረት ናት። በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚሰራጭ እውነትና የማይታጠፍ ቃል፤ እምነት እየዳበረ እንዲሄድ ያደርጋል። ከዚህም በተቃራኒ የሚሰራጨው የውሸት ብዛት፤ የሚታየውና የሚነገረው በሙሉ በጥርጣሬ የመታየት ግዴታ ውስጥ ከቶታል።

## የጠንካራ እምነት ትውልድ

የመደመር ትውልድ ከእንደዚህ ዓይነት ቀውስ የተላቀቀ እንዲሆን የማመን የመታመንን እሴት፣ ማዳበር አለበት። እምነት እንዲጠነክርና አለመተማመን ቦታ እያጣ እንዲመጣ የሚያስችሉ፤ የትውልድ ቀረጻ ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል። ከዚህም ቀዳሚው ትውልድን በሥነ-ምግባር ሊያንጹ የሚችል ማህበራዊ ተቋማት መጠናከር ነው። እነዚህ ማህበራዊ ተቋማት፤ ህዝብን ሊያንፁ በሚችልበት ቁመና ላይ ሊገኙ ይገባል። የሚያምን የሚታመን ትውልድ ሊፈጠርበት የሚችለው አንደኛው ቦታ ትምህርት ቤት ነው። ትምህርት ቤቶች እውቀትና ክህሎትን ከማስጨበጥ በተጨማሪ፤ ማህበረሰብን በእሴት እንዲበለጽግ ማድረግ ይገባቸዋል።

በመደመር ትውልድ የመተማመን ክበቡ በብሔርና በመንደር ሳይታጠር ሰብአዊነትን ለሁሉም መስጠት የሚችል እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። የመደመር ትውልድ የማንነት ብዝኃነትን የሚቀበልና የሚላበስ ቢሆንም ሰብዓዊ መርሆዎቹን በማንነት እንዲታጠሩ የሚፈቅድ አይደለም። ማንነትን መሠረት የሚያደርጉ ውግንናዎች ያላቸውን የፍትሃዊነት ውክልና ፋይዳ የሚረዳ ቢሆንም፤ ለሰው ልጆች ሰብዓዊ ርህራሄን እንዲነፍግ የሚያደርጉ የልዩነት መሳሪያዎች አይሆኑበትም። የመደመር ትውልድ የሞራል ህሊናን ስንቀርጽ፤ ከራስ ወዳድነት የፀዳ፤ ለሌሎች የሚራራ፤ ኃላፊነት የሚሸክም፤ እውነተኛና የሌላው ህመም የሚያመው ትውልድ እየቀረጽን መሆኑን ከአሁኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

አሁን ላይ የምንመለከተው የሥርቆትና የስግብግብነት፤ የጭካኔና ጥላቻ፤ የስንፍናና የምናገባኝ አኗኗር፤ እንዲሁም ኃላፊነትን ከመውሰድ ይልቅ ጣትን ወደ ሌላው የመጠቆም ልማድ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸረሸር የመጣው የሞራል ዝቅጠትና የሚታመን መጥፋት ውጤት ነው። የትውልድ ግንባታ ሂደታችንን እንደገና ለማደስና ለመስራት ጊዜው አሁን መሆኑንም ይጠቁማል።

ከቤተሰብ እስከ ትምህርት ቤት፤ ከቤተ-እምነት እስከ ማህበረሰባዊ ተቋማት ድረስ የሚታየው የሞራል ድቀት፤ የእምነት ድክመት፤ ሥነ-ምግባራዊ ዝንፈት፤ ሌላውን የማያምን፤ በራሱም የማይታመን ትውልድ ሰጥቶናል።

በመደመር ትውልድ ይህንን የሞራል ቀውስ ተጋፍጠን፤ ትውልዱን ወደ ሞራል ልዕልናው ልንመልሰው

ይገባል። የሚተማመን አድናቆትና ምስጋናን የሚያውቅ ለሥራ ትጋትና ድፍረት ያለው፤ በደልን ይቅር የሚልና ጥላቻን በፍቅር የሚተካ፤ ያለውን የሚያካፍልና ስለሌሎች ራሱን መስዋእት ለማድረግ ፈቀኛ የሆነ፤ ራሱን በመግዛት ልዩነት ተቀብሎ ሚዛናዊ ህይወትን የሚኖር እንዲሆን ማሰልጠን ይኖርብናል። ይህንን የምናደርገው ክፍል ውስጥ አስቀምጦ በመደስኮር ሳይሆን ትውልዱ እንዲሆን የምንፈልገውን በተግባርና በህይወት፤ በእውቀትና በሀሳብ በማሳየትና በመምራት ነው። የመደመር ትውልድ የሞራል ብልሃትን የተላበሰ በሥነ-ምግባራዊ አስተሳሰብና እሴት የታነፀ፤ በግብረ ገባዊ ባህርይ እና አኗኗር የተመሰከረለት እንዲሆን ጠንክረን መስራት አለብን።

ጥላቻን በፍቅር፤ ቂምን በይቅርታ፤ ግጭትን በውይይት፤ ሌብነትን በስራ፤ ስግብግብነትን በማካፈል፤ ጭካኔን በደግነት እንዲለውጥ ተምሳሌት የሚሆኑ የሞራል ልዕልና ያላቸው መሪዎችንና አስተማሪዎችን በፍጥነት ማፍራት ይኖርብናል። ቤተሰብን በጠንካራ መሰረት ላይ መገንባት ሀገርን የሚረከብ ትውልድን ለማዘጋጀት መተኪያ የሌለው ተግባር ነው። የሞራል ማዕከላት የሆኑት ቤተእምነቶች፤ በሥነ-ምግባርና ግብረ ገባዊ ባህርይ የታነጸ ትውልድ ለመፍጠር፤ የራሳቸውን የዘቀጠ ሞራልና የተበላሸ የሥነ-ምግባር ቁመና ሊያስተካክሉ ይገባል። ትውልድ ቀና ብሎ የሚመለከታቸው ተፅእኖ ፈጣሪ ግለሰቦችና የማህበረሰብ መሪዎች የተተኪው ትውልድ ተምሳሌቶች መሆናቸውን በመረዳት ሥነ-ምግባራዊ አስተሳሰባቸውንና ግብረገባዊ አኗኗራቸውን የማስተላለፍ ሃላፊነት አለባቸው።

# በቦታ ያልታጠረ ፡በጊዜ ያልታሰረ ልህቀት

## ምናባዊ ልህቀት

አልፎ አልፎ ሲነገሩ የምንሰማቸው አፈታሪኮች ምናብ ወለድም ይሁኑ እውነተኛ ታሪኮች፤ በውስጣቸው አስተማሪ የሆኑ ቁምነገሮችን ይዘው እናገኛለን። በዓለማችን የህዋ ምርምር እሽቅድምሞሽ ወቅት ከተሰሙ አፈታሪኮች መካከል ቀጥሎ የሚነበበው ታሪክ በዚህ የጽሁፍ ክፍል ለሚነሳው ሃሳብ ጥሩ መነሻና አስተማሪ አድርጎ መውሰድ ይቻላል። ታሪኩ እንዲህ ነው ይላል፤ ብዙ ተመራማሪዎችን ያቀፈ አንድ የጠፈርተኖች ቡድን ወደ ህዋ ላይ በሚያደርጉት ምርምር ውስጥ አንድ ችግር ይገጥማቸዋል። ይህም ከወረቀት ጋር ተገናኝቶ ማስታወሻዎችን ለማስቀረት የሚረዳው ብዕር፤ ያለስበት ሃይል ሊሰራ እንደማይችል ይረዳሉ። ስለዚህም የመሬት ስበት በሌለበት ህዋ ውስጥ ጠፈርተኞች በቆይታቸው ያዩትን መዝገበውና በሥዕል አስቀርተው፤ ወሳኝ የሆኑ የምርምር ነጥቦችን ይዘው መመለስ አልቻሉም። በመሆኑም የገጠማቸውን ችግር ለመፍታት አያሌ ባለሙያ ይሳተፉበትና ከፍተኛ ወጪ የፈሰሰበት የዓመታት ምርምር ተካሂዶ በመጨረሻ የመሬት ስበት

በሌለበት አካባቢ መጻፍ የሚችል ብዕር ተሰራ፡፡ ከዚህ የጠፈርተኞች ቡድን ጋር የሚፎካከር ሌላ የጠፈርተኞች ቡድን ተመሳሳይ ችግር ገጥሞት የነበረ ቢሆንም የቡድኑ አባላት ለችግሩ ያገኙት መፍትሄ የተለየ ነበረ፡፡ ወደ ጠፈር የሚጓዙ ጠፈርተኞቻቸው በብዕር ፋንታ እርሳስ ይዘው ለመሄድ ሲወስኑ ጊዜ አልፈጀባቸውም፡፡ አፈ-ታሪኩ አንድ ነገር ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡ የመጀመሪያዎቹ የጠፈርተኞች ቡድንን ችግር ሲገጥማቸው መፍትሄ አድርገው የወሰዱት ፤ ችግሩ ላይ በማተኮር የብዕሩን አለመፃፍ ችግር መቅረፍ ነው፡፡ በተቃራኒው የሁለተኛው የጠፈርተኛ ቡድን አባላት የብዕሩን አለመፃፍ ችግር ላይ ብዙ ትኩረት ከመስጠት ይልቅ ዓላማው ላይ በማተኮር፤ መፍትሄን ለመመልከት ጥረት አድርገዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ያለድካምና ያለብዙ ወጪ መፍትሄውን አግኝተዋል፡፡ ችግሩን በግልፅ መረዳትና መተንተን መፍትሄውን ለማምጣት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ችግሩ ላይ ከሚገባው በላይ ከተጣድን ግን በችግሩ መወሰዳችን አይቀርም፡፡ ችግሩን ለማጥናት ስንል በችግሩ መንገድ እንሄዳለን ሌሎች መፍትሄዎች ላይ ማማተርና ተሻግሮ መመልከት ያቅተናል፡፡

የሰው ልጅ ችግር ሲገጥመውና ድንገተኛ የህይወቱን ሂደት የሚቀይር ክስተት ሲፈጠር የተለያዩ ምላሾችን በተለያዩ ጊዜ ይሰጣል፡፡ ምላሾቹን የሚሰጥበት መንገድና ምልከታ ለእድገቱ ወሳኝ ነው፡፡ የሰው ልጅ ችግር ሲያጋጥመው የመጀመሪያውና ቅጽበታዊ ምላሹ፤ ችግሩ ወይም ክስተቱ የህይወቱን ሂደት እንዳይቀይርበት እና ተጽእኖ እንዳይፈጥርበት መከላከል ነው፡፡ አንድ ጊዜ ችግሩ ከተከሰተ በኋላ ሁለተኛው ሂደት የሚሆነው ችግሩን መረዳትና ሊያስከትለው የሚችለውን ተጽዕኖ ማስተደደር ይሆናል፡፡ በተፈጠረው አዲስ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ በመላመድ፤ ራሱን አስተካክሎ ህይወት እንዲቀጥል ማድረግ የሰው ልጅ አማራጭ ምላሽ ነው፡፡ እነዚህ የመከላከልና የመላመድ ሂደቶች በችግሩ ዙሪያ የሚያውጠነጥኑ ሲሆኑ ሦስተኛው ከችግሮቹና ከስህተቶቹ በላይ ሆኖ የተፈጠረውን አዲስ ሁኔታ የሚለውጥ መንገድ መቀየስ ነው፡፡ ሦስተኛው መንገድ ምናብ ሲሆን እየተከሰተ ካለውና ከተከሰተው ነገር በሀሳባዊ ዓለም ርቆ፤ ለሁኔታዎችና ለነገሮች አእምሮአዊ ሞዴል የመፍጠር፤ የመቅረፅና የመጠቀም ሂደት ነው፡፡ ይህም አዳዲስ ነገሮችን በመፍጠር አዲስ የእድገት መንገድ ለማግኘት ያስችላል፡፡ የወደፊት ስኬትም የሚመጣው በዚህ መንገድ ነው፡፡

በቁሳዊ ዓለም ውስጥ ያለውን ለመመልከት ከአእምሮ ጋር የተያያዙ ዓይኖች እንዳሉ ሁሉ፤ የሀሳቡን ዓለም ተመልክተን እና ተረድተን ሃሳቡን ወደ እቅድና ምስል መለወጥ የምንችልበት ረቂቅ ክህሎትም ታድለናል፡፡ ይህም ዓይነ ልቦና ወይንም ምናብ ይባላል፡፡ ከህፃናት እቃ እቃ ጨዋት እስከ ሳይንቲስቶች ፈጠራ፤ ከደራሲዎች ልቦለድ እስከ ሰዓሊዎች ስእል ድረስ ዓለም የምናብ ውጤትና ፍሬ ነው፡፡ ዓይነስውር በዓለም ላይ ያለውን ቁስ ለመመልከት እንደማይችል ሁሉ ምናቡ የታሰረ ሰው ደግሞ በሀሳቡ ዓለም የሚገኘውን መጠን የለሽ እድልና ሀብት ሊመለከት አይችልም፡፡ የሀሳቡን ዓለም ለመመልከት ምናቡን ያላሰለጠነ ሰው ደግሞ በአካላዊው ዓለም ምንም ሀብትና እድል ቢኖረው የበላይነት ሊቆናጠጥና ሊጠቀምበት አይችልም፡፡ ለዚህም ነው አካላዊ ዓይኖቻቸው የማያዩ ሰዎችን ዓይነ ስውር የምንላቸው ምክንያቱም አካላዊ ዓይናቸው ቁሳዊ ነገር ማየት ባይችልም ስውሩ ዓይናቸው ግን የሀሳቡን ዓለም ይበልጥ አጥርቶ ያያል፡፡ የምናብ ዓይኑ የታወረ ግን እውር እንጂ ዓይነስውር ሊባል አይችልም፡፡

ሀገርን ጨምሮ ትላልቆቹ የሰው ልጆች ውጤቶች ምናባዊ መነሻ አላቸው፡፡ ሀገር በአንድ የተከለለ ስፍራ፤ በጋራ

አስተዳደር ስር፤ በማህበረሰብ ፈጥሮ የሚኖር የሰዎች ክምችት ነው ሊባል ይችላል፡፡ ሆኖም ግን የሚታየውን ህዝብና ምድር ማህበረሰብና አስተዳደር ሀገር የሚያደርገው ቁልፍ ነገር የማይታየው የገዥ ትርክት ብርታት ነው፡፡ ታሪኩ ሲፈርስ ሀገር ይፈርሳል፡፡ ሲጠብም ይጠባል ከሰፋም እንደዛው ሀገር የትርክት ውጤት ነው፡፡ ትርክት ደግሞ የተቀመረና የተሰባሰበውን ህዝብ መነሻንና መድረሻን የሚቃኝ ሀሳብ ነው፡፡ ሀሳቡ ሲለወጥ ሀሳብን የሚመስል ሀገርና ህዝብ ይፈጠራል፡፡ ምድሩም ቅርፁንና መዋቅሩን ይለውጣል፡፡ ሀሳቡ እንደሆነ ሀገሩ ይሆናል፡፡ ሀሳቡ ሲከፋ ሀገር ይከፋል፤ ሀሳቡ ሲለመልምና ሲበለጽግ ሀገሩም እንደዛው ይበለጽጋል ስለዚህም ሀሳብን የማይረዳ የማያከብርና ከሀሳብ ይልቅ ከቁስ የተጣበቀ ሀገርና ህዝብ ኋላ ቀርና የሁሉ አሽከር መሆን አይቀርም፡፡

ቁስ በአካላዊ ዓለም ተንሰራፍቶ የሚገኝ ከምናቡ ዓለም ለሚመጣ ሀሳብ መገለጫነት የተፈጠረ ተገዥ መሳሪያ ነው፡፡ ወርቅና ድንጋይ፤ ውሃና ነዳጅ፤ እህልና አፈር ሁሉም በሀሳብ ይመራሉ፡፡ ዋጋቸውም በውስጣቸው በተጨመረው የሀሳብ ልክ ይልቃል ወይ ይኮስሳል፡፡ ሰውን ከሌሎች እንስሳት የሚለየው በቁስ ውስጥ ሃሳብን ጨምሮ ከፍ ያለ ነገር በማውጣቱና ሀሳብን ተጠቅሞ ራሱንን ተቋማት የማነጽ፤ ሀገርንና ማህበረሰብን የመፍጠርና የማፍረስ አቅም ያለው መሆኑ ነው፡፡ ሰውና ሀሳብ አንዱ ሌላውን ለመቅረጽ ሲታገሉ የሚኖሩ ሃይላት ናቸው፡፡ የሰው ልጅ በሀሳብ ላይ የበላይነት እንዲኖረው የሚያስችል አእምሮን ታድሏል፡፡ በዚህ አእምሮ ውስጥ ደግሞ የተለያዩ ረቀቅ ክህሎቶችና ክፍሎች አሉት፡፡ በነዚህ ረቂቅ ክህሎቶቹ ተጠቅሞ ደግሞ ራሱን፤ አካባቢውን፤ ሃሳቡንና ሌሎች አእምሮዎችን ይቀርጻል፡፡

ስልጣኔና የበላይነትን የተቆናጠጡ ሀገራትና ድርጅቶች፣ ሰዎችና ትውልድ ብልጫቸው ያለው ኪሳቸው ባለው ገንዘብ ወይንም በከርሰ ምድራቸው ባለው ሃብት ሳይሆን በምናባቸው የማየትና ሀሳብን ወደ ምስል በመቀየር ብቃታቸው ነው፡፡ የአለምን ታሪክ በፈጠራ ስራቸው የቀየሩና ያስደመሙ ሰዎች በምናባቸው ያዩትን መጀመሪያ በወረቀት፤ ከዛም በቁስ ላይ ለመግለጽ በመቻላቸው ነው፡፡ ስልክና አውሮፕላንን ኤሌክትሪክና መንኮራኮርን ፍቅር እስከ መቃብርንና ሞናሊዛን፤ ኮምፒዩተርንና እንጀራን የፈጠረው፤ ሰው ሃሳቡን ቁስ ውስጥ ጨምሮ ለውጥ ለማምጣት በመቻሉ ነው፡፡

የሕፃናት ጉጉነትና የምናብ ኃይል እጅግ አስገራሚና ዕረፍት የለሽ ነው፡፡ የሕፃናት ልብ ትንሽ አይደለም፡፡ ሩቅን መመልከት ይችልበታል፡፡ አሁን ያሉበትን የልጅነት እድሜ ተሻግሮ የወጣትነት፤ ከዚያም በኋላ ያለውን ዕድሜ በምናባቸው መሳልና መመልከት ይችላሉ፡፡ አንድ የአምስት ዓመት ሕንፃ ዶክተር ሆኖ ራሱን ለማስቀመጥ አይቸግረውም፡፡ የስድስት ዓመት ልጅ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጋ ራሷን ታስቀምጣለች፡፡ የልጅነት ጨዋታቸው ጨዋታ ብቻ ሳይሆን የምናባቸው ማሳያ፤ ወደፊት ለሚደርሱበት ደረጃም ትልቅ መነሻ ነው፡፡ በወላጆቻቸው፤ በአስተማሪዎቻቸውና በማህበረሰቡ በአጠቃላይ ተኮትኩቶ ሲያድግ መዳረሻው እውን ይሆናል፡፡

ጥቂት ከፍ ሲሉና ትምህርት ቤት መሄድ ሲጀምሩ ጥያቄዎቻቸው ተገቢ ባልሆነ አያያዝ ምክንያት ይጨናገፉባቸዋል፡፡ ምናባቸው ያንቀላፉና ፈተና አልፈው መኖር የሕይወት ግባቸው ይሆናል፡፡ በዚህም የተነሳ ማህበረሰቡ የጥንት የጠዋቱን ሐሳብ የዛሬ ደንብና ልኬት አድርጎ ይኖራል፡፡ ከመፍጠር መኮረጅን

ይመርጣል። መለወጥ መበጥበጥ ሆኖ ይታየዋል። ባለበት ይረግጣል፤ ችግርን ወደ መፍትሄ ከመቀየር ይልቅ፤ ዕድልን ችግር አድርጎ በማየት የውስጡን ጥሪ እያዳፈነ ይኖራል።

ምናብ ከአሁናዊ ሁኔታና ክስተት ተሻግሮና አርቆ የማየት አቅም ነው። የሰው ልጅ ስፔስ ላይ መድረስ እንዴት ቻለ? መብረርስ እንዴት እውን ሆነ? መኪናስ እንዴት ተፈጠረ? ሰውን ተከተው የሚሠሩ እና የሚያስተውሉ ማሽኖችስ? እያልን ስለ ዓለማችን ትላልቅ ግኝቶች ብንጠየቅ፤ መልሳችንን የምናገኘው በዘመናቸው እንደ እብድ በታዩ ሰዎች አእምሮ ውስጥ ነው። የሰው ልጅ በአህያ እንኳን በቅጡ መጓጓዝ ሳይችል ስለ መኪና በሐሳባቸው በሳሉ፤ በምድር በመጓዝ እጅግ ከባድ በነበረበት ዘመን መብረርን በተለሙ፤ ምድሩን በቅጡ ሳያውቁ ስለ ሕዋ ባውጠነጠኑ ሰዎች ልብ ውስጥ ነው፡ እጅግ ድንቅ የሆኑ የዓለማችን አስደናቂ ፈጠራዎች የተወለዱት።

የሰው ልጅ ከተከሰቱት እና እየተከሰቱ ካሉ ሁኔታዎች ርቆ ነገሮችን በተምኔት የሚመለከትበት መነፅር አለው። ተምኔት መፍጠር ለሚፈልገው ዓለም ሐሳባዊ መነሻ ነው። በ1961 እ.ኤ.አ ዩሪ ጋጋሪ ሕዋን የረገጠ መጀመሪያ ሰው ከመሆኑ ቀድሞ፤ ሰማዩ እና ሰማዩ ላይ የሚታዩትን ከዋክብትና ጨረቃ በምናብ ሲመላለሱባቸው ኖረዋል። የሰው ልጅ በምናቡ ቀድሞ የደረሰበትን ሕዋ፤ ዕቅድ አውጥቶለት፤ ፕሮጀክት ነድፎለት በአካል ደርሷል። ቀድሞ ሕዋን በምናቡ ሲመላለስ እብድ አስብሎት እና የማይሳካ ተብሎ ተንቆ የታለፈ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ያቺ ትንሽ ሐሳብ ለ1961 የዩሪ ጋጋሪ የጠፈር ጉዞ መነሻ ሆነች።

በየዘመናቱ በሚነሡ የምናብ ኃይላቸው በነቃና በሠለጠኑ ጥቂት ሰዎች ጥረት የሚሊዮኖች ችግር ተፈትቷል። የሰው ልጅ ሕይወትም እመርታን አግኝቷል። የብዙ ሥልጣኔ መሰረቱ ምናባቸው የነቃና የበራላቸው ሰዎች በማህበረሰብ ላይ በዘሩት ብርቱ ሐሳብ፤ በፈጠሩት የዕይታና የአስተሳሰብ ለውጥ የተነሳ ነው። ለዚህ የግሪክና ሮም፤ የአክሱምና ላሊበላ ሥልጣኔዎች፤ የመካከለኛው ዘመን ተሃድሶ፤ ያለፈው ክፍል ዘመን የቴክኖሎጂ አብዮቶች ሁሉ ምሳሌዎች ናቸው።

ምናብ ግለሰባዊም፤ ትውልዳዊም ሊሆን ይችላል። የነቃ ትውልድ በተባበረና በተነባበረ ምናብ ሀገርን ብሎም ዓለምን ሊለውጥ የሚችል የሐሳብ ማዕበልን አስነስቶ፤ አዲስ ሥልጣኔን የመፍጠርና የመተግበር ችሎታ አለው። ከተናጠል ምናባዊ ኃይል ይልቅ ትውልዳዊ ጥምር ምናብ፤ የላቀ ነገር ይፈጥራል። ሥልጣኔዎች ሁሉ የትውልዳዊ ጥምር ምናብ ውጤት ናቸው ልንል እንችላለን።

የትውልድ ምናብ ችግሮቹን ተሻግሮ ሲመለከት ታሪክ ይቀይራል። ከእርሱ በኋላ ለሚመጡ ትውልዶችም ብዙ አበርክቶ ይኖረዋል። የፈረንሳይ የአብርሆት ትውልድ ምናብ፤ ከፈረንሳይም አልፎ በዓለም ታሪክ ላይ ዐሻራውን አኑሯል። የአሜሪካን አባቶች አሜሪካንን ሲመሠርቱ የቀረፁበት ምናብ እስከ አሁን ድረስ ላለው ትውልድ አበርክቶው የላቀ ነው። በወቅቱ ሀገራቸው ከቅኝ ግዛት ገና መላቀቋ ቢሆንም፤ የቅርብ ሥጋታቸው የነበረውን ቅኝ ግዛት እንዴት እናስቀር ከሚል መነሻ የአሜሪካን መሠረትን አልጣሉም። ይልቁንም ሕይወት፤ ነፃነት እና የሐሴት መሻት ምሉዕ የሚሆንባት ምናባዊ ምድር ለመፍጠር በማሰብ የአሜሪካን መሠረት አስቀምጡ።

አሜሪካን ለወደፊት ከሚመጣው ሥጋት በተለይም እጅግ በጣም መጥፎ ከሚባለው አምባገነናዊ

የመንግስት ሥርዓት እንዴት እንጠብቅ ብለው ነበር ጉዟቸውን የጀመሩት፡፡ በዘመኑ አሜሪካ የሰው ልጆች ሕይወትና ነፃነት የሚከበርባት፤ ለደስታ ያላቸውም መሻት እውን የሚሆንባት አልነበረችም፡፡ ይልቁንም ከዚያ ብዙ ርቃ የሰው ልጅ ከሰው መሆን ወርዶ፤ ሕይወት እንደ ሌላው ግዑዝ የሚሸጥባትና የሚለወጥባት ነበረች፡፡ እንዲሁም ምርጫን የመሳሰሉ መብቶች ለሴቶች ያልተፈቀዱበት ወቅት ነበር፡፡ የአሜሪካ አባቶች ሊፈጥሩ ካሰቡት ሀገረ መንግስት በእጅጉ የራቀች ነበረች፡፡ ነገር ግን አሜሪካውያን በዘመኑ የነበሩበትን ሁኔታ ተመልክተው ‹‹ይህ ትልም ውሸት ነው››፤ ‹‹በምናባችን ያለምነው ሊደረስበት አይችልም›› ሳይሉ ወደ ምናባቸው ለመዳረስ በመትጋታቸው፤ በ1865 እ.ኤ.አ ባርነት ቆመ፡፡ በ1920 እ.ኤ.አ. ሴቶች መምረጥ ቻሉ፡፡ በኋላም በብዙ ጥረቶች ውስጥ ለምናባቸው የቀረበ ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡

ሰዎች በአንድ ምናብ ላይ ተጋግዘው መሥራት ከቻሉ ለራሳቸው የተሻለ መዳረሻን ይፈጥራሉ፡፡ ሰሜን ጫፍ ያለው በደቡብ ጫፍ ካለው፤ በምሥራቅ ጫፍ ያለው በምዕራብ ጫፍ ካለው ኢትዮጵያዊ ጋር በአካል ተገናኝተው አያውቁም፡፡ ጭራሽ በጥንቱ ዘመን በአንዱ ጫፍ ያለው ኢትዮጵያዊ በሌላኛው ጫፍ ያለው የሚኖርበትን መልክአ ምድር በፎቶም በቴሌቪዥንም አላየንም፡፡ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ከአንዱ ጫፍ ወደ ሌላው ጫፍ አንድ ሆና የቆመችው በልጆቿ ምናብ ነበር፡፡ ይሄ የተጋራነው ምናብ ነው ያስተሳሰረን፡፡ ጣልያን መጣ ሲባል ከሁሉም ጫፍ ተሰብስቦ ወደ ሚያውቀው አካባቢ ዘምቶ ነፃነቱን አስከብሯል፡፡ ማይጨው፤ ካራማራ፤ ባድመ ሲባል፤ ኢትዮጵያ አትደፈርም ብሎ በየዘመኑ የነበረው ትውልድ በአንድ በመቆሙ፤ ነፃነቱን ጠብቆ ሊቆይ ችሏል፡፡ ይሕ የሆነው በየዘመኑ ልዩነት ሳይኖር ዕለታዊ ጉዳዮች ሳያጋጩት አይደለም፡፡ ይልቁንም ምናቡ ከፍ ያለና የተሻገረ ስለነበር ነው፡፡ ለዚያ ምናብ በአንድነትና በህብረት ለመቆም በመምረጡ ነው፡፡

በተለያየ ጊዜ ሲነቃና ሲደበዝዝ የቆየውን ትውልዳዊ ምናብ በዚህ የመደመር ትውልድ ዘመን ልንቀሰቅሰው ይገባል፡፡ ሀገራችንንና አህጉራችንን ለመለወጥ የሚችለው በጥቂቶች የምናብ ጉልበት ሳይሆን፤ በሁላችንም ጥምር ምናብ ብርታት ነው፡፡ ለዚህም የመደመር ትውልድን፤ ምናቡን ከሚያኮላሹ ተቋማዊና ባህላዊ አሰራሮች፤ መታደግ ይኖርብናል፡፡ አዲስ የትምህርት ስርዓትና የትውልዳዊ ምናብ መቀስቀሻ ተቋማትን መፍጠር ይገባናል፡፡ የመፍርጠርና ተብብሮ የመስራትን፤ እየወደቁ እየተነሱ በድፍረት የመሞከርን፤ ከተለመደው  አካባቢያዊና የአሰራር መንገዶች በመውጣት የመስራት ባህልን፤ የመጠየቅና የመሟገት ልማድን እና መሰል ድርጊቶችን ማደፋፈርና ማስፋፋት አስፈላጊ ናቸው፡፡ ትውልዱን በጅምላ ከመንቀፍና በእጦት አስተሳሰብ እንዲጠመድ ከሚያደርጉ እይታዎች መታቀብ ይገባናል፡፡ ለ19ኛው መ/ክ/ዘ ከተቀመረ የትምህርት ስርዓት የተለየ የመማር መንገድ መፍጠር ያሻል፡፡ በክፍፍልና በግጭት ከተወጠረና ከተጠፈረ አመለካከት ነጻ ማድረግ ይገባል፡፡ ወደተባባሪና ሰው በሰውነቱ ወደሚከበርበት፤ ብቃት ዋነኛ መለኪያው ወደሚሆንበት አሰራር ማሻገር ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ በመከወን አዲሱ የመደመር ትውልድ ምናባዊ አብርሆቱን እንዲቀዳጅ ማድረግ ይቻላል፡፡

ምናባቸውን ያላበጁ ትውልዶች አቅጣጫቸውን እንዳልመረጡ መንገደኞች ናቸው፡፡ በእለት አጀንዳ ውስጥ ጉዞአቸው ይናወጣል፡፡ አዲስ ትውልድ ራሱንም ሆነ ሀገሩን የቀደመ ታሪኩንም ሆነ የወደፊት እጣ ፈንታውን

የሚመለከትበት ምናብ ሊኖረው ይገባል። አለም አቀፍ ሂደቶችንና ሁኔታዎችን በመረዳት ብቻ ሳይሆን፤ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲሳተፍ መግፋት ያስፈልጋል።

በቀጣይ ዘመን ሰው ሰራሽ አስተውሎት የሰውን ቦታ ተክቶ፤ በሰው ልጅ ሲሰሩ የነበሩ ስራዎችን ይበልጥ የሚከውንባት ዓለም ትፈጠራለች። በዚህም የሰውን ልጅ ከስራ እያፈናቀለ በመሆኑ ዓለም መተካካቱን መለስ ብሎ እንዲቃኝ ተገድዷል። ብዙ ተመራማሪዎች እንደሚጠቁሙት እየተፈጠረ ባለው ዓለም ውስጥ፤ የሰው ልጅ ከፍተኛ ሚና የሚሆነው፤ በሰው ሰራሽ አስተውሎት በቅርብ ይተካል ተብሎ የማይገመተው፤ የፈጠራ አቅም ነው። የፈጠራ መነሻ አእምሮ ውስጥ የሚፈጠር የሀሳብ ስዕላዊ ቅንብር የሆነው ምናብ ነውና።

ዓለም በፍጥነት ትቀያየራለች፤ በዚህ ፍጥነት ትውልዱ አሻግሮ ማየት ካልቻለ፤ ተከታይ እንጂ መሪ መሆን አይቻልም። የወደፊቱን መቅረጽ ካልቻልን፤ በተቀረጸው ውስጥ ተለማምዶ መኖር አማራጫችን ይሆናል። ሀገር በቀል ሃሳቦች እቅድ ሆነው ሲቀርቡ ከማጣጣልና ሰርቆ ከመውሰድ ከመሞከር፤ በፈጠራቸው ባለምናብ ባለቤትነት እንዲተገበሩ አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ያስፈልጋል። ሀገርን በሰፈርና በራስ ዘር ብቻ ሳይሆን ከዳር እስከ ዳር የሚገነዘብ ትውልድ ከተፈጠረ፤ ለምናቡ ማሳረፊያ ወሰን የለሽ አድማስ ያገኛል። ታሪክን ለጥልና ለግጭት ሳይሆን ምናብን ለመኮርኮሪያና ለመማሪያ ከተጠቀምንበት መጪው ትውልድ የራሱን ሀገር አሳምሮ ሊገነባ ይችላል።

ከሰፈሩ ርቆ ማየትና መተለም የመደመር ትውልድ መገለጫ ነው። ስለነጻነት ሲያስብ ስለራሱና ስለአካባቢው ብቻ ሳይሆን፤ ስለሰው ልጆች መብት ማገናዘብ የሚችል አእምሯዊ ስዕል ሊኖረው ይገባል። እንደዚህ ሲሆን ለራሱ የጠየቀው መብት ለሌሎች እንደሚገባ፤ ለአጠቃላይ የሰው ልጆች እንደሚያስፈልጋቸውም ያምናል። ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጆች ሁሉ ክብርና ነፃነት የሚቆረቆር ትውልዳዊ ምናብ ሲፈጠር መከባበር ይነግሳል፤ ሰላምም ይሰፍናል። እንዲህ ሲሆን የራሱን መብት የሚጠይቅ፤ የሌሎችን አይነካም። የሌሎች መብት ተጥሶ ሲመለከት አካባቢዬ፤ መንደሬ፤ ሀገሬ ሳይል በሰብዓዊነት ተሻጋሪ ምናብ ከተበዳዮች ጎን ይቆማል።

ቼ/ጉቬራን ከሌሎች የነፃነት ታጋዮች አስበልጦ የሚያስወድሰው፤ የተለየ የትግል ስልት ወይም ጀግንነት ስለተላበሰ አልነበረም። ስለነፃነት ያለው የተሻገረ ምልከታ ነው። ነጻነት ለሰው ልጆች ሁሉ እንደሚገባው አምኖ ከራሱና ከአነስተኛ መንደሩ ተሻግሮ የሰው ልጆችን ከቀኝ አገዛዝና ከጭቆና ነጻ ለማውጣት ሀገርንና አህጉርን አልፎ በቁርጠኝነት በመታገሉ ነው። ምናብ ከቦታ ሲሻገር የህብረት፤ የእድገትና የጥንካሬ መሰረት ነው። በቦታ ሳይገደቡ ስለሰው ልጆች የጋራ መዳረሻ እንዲተልሙ ያደርጋል። የሰው ልጆችን ሁሉ የሚያግባቡ ጀግኖች የሚፈጠሩትን በዚህ ምናባዊ ልህቀት ውስጥ ነው።

የመደመር ትወልድ በቦታ ብቻ ሳይሆን ከዛሬ አሻግሮ ነገን የሚመለከት ተሻጋሪ ምናብ ሊኖረው ይገባል። የትውልድ እሳቤው ዛሬ ላይ ብቻ የታጠረ መሆን የለበትም። ትናንትን የሚማርበት፤ ዛሬን ለነገው ምናቡ የሚወጣጣበት መሰላሉ ማድረግ አለበት። የኢትዮጵያን የትላንት ታሪክ ብቻ እየዘከረ ወይም እያማረረ የሚኖር መሆን የለበትም። ዛሬ ብቻ አያስጨንቀውም፤ አያስደስተውም።

የመደመር ትውልድ ነገን የሚተልምበት፤ ከትናንት ዝክርና ምሬት፤ ዛሬ ጭንቀትና ደስታ የተሻገረ ምናብ ሊኖረው ይገባል። የዛሬን ችግርም ይሁን ስኬት የሚመረምርበትን የከፍታ ትልም ሰንቆ የሚጓዝ መሆን አለበት። እንደዚያ ሲሆን የዛሬ ችግር ተስፋ አያስቆርጠውም፤ ስኬቱን አያዘናጋውም፤ ምናቡ ከዛሬ በላይ ነውና። በችግር ውስጥም አዳዲስ እድሎችን ለመመልከት ይቻለዋል።

ኢትዮጵያ ብዙ ችግር እንዳሉባት ባያጠራጥርም፤ ከችግሮቿ ተሻግሮ መመልከት ካልተቻለ፤ በሰፊ ምናብ ላይ ተቀምጦ ለሀሳብ እውን መሆን ካልተሰራ፤ ወደከፍታ መድረስ አይቻልም። ኢትዮጵያን ከችግር ለማላቀቅ ችግሯ ውስጥ ከተጠመድን መፍትሄው እንደሰማይ ይርቀናል። ነገር ግን እንደሰማይ ከራቀ ከፍታ ላይ ሆነን ችግሮቻችንን ማየት ብንችል፤ መሬት ላይ እንዳለች ጠጠር ችግሩ አንሶ ይታየናል። ችግርን የምመለከተው ከስር ነው ከላይ? የሚለው ለመፍትሄ ወሳኝ ነው። የውጭ ድጋፍ በመቀዛቀዙና ሌሎች ኮሮናን ተከትለው የተፈጠሩ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት የተከተልው ስልት ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው። ይህንን ችግር ለመፍታት የተጠቀምነው ፈጠራ የታከለበት መፍትሄ፤ ጥገኝነትን አሽቀንጥሮ ለመጣል በሚደረገው ጥረት ታሪክ ቀያሪ ሆኗል። ይኸም ነገ ላይ ለትውልዱ ከፍተኛ አበርክቶ ያለው ነው።

ኮሮናን ተከትሎ የተፈጠረ የድጋፍ መቀዛቀዝ፤ ሀገራችንን ጨምሮ ከእርዳታ ባልተላቀቁ ሀገራት ላይ ጫና ፈጥሯል። ሀገራችን በደረሰባት ተጨማሪ የውጭ ጫና፤ የድጋፍ መቀዛቀዙ ከሌሎች ሀገራትም ከፍ ያለ ነው። ድጋፉ መቀዛቀዙ በሀገራችን ላይ ጫና የሚፈጥር ስለሆነ፤ የመጀመሪያው ምላሽ ድጋፉ እንዳይቀር ለመከላከል የሚደረግ ጥረት ነበር። ነገር ግን ይህን የመከላከል ጥረት የመጀመሪያው ደረጃ እንጂ ሙሉ ለሙሉ የሚያዋጣው መንገድ አልነበረም። ድጋፉ እንዳይቀር መከላከል ሳይቻል ሲቀር፤ ችግሩን በመረዳት የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ አማራጭ የገቢ ምንጮችን በመፈለግና ወጪ መቆጠብ ሌላኛው ደረጃ ነበር። ይህም ግን አዲስ እድልንና አዲስ መንገድን የሚቀይስ ስላልሆነ ዘላቂ አልነበረም።

ችግሩን ለመፍታት የሄድንበት መንገድ ችግሩን የፈጠረውን የድጋፍ መቋረጥ ሁኔታ ከማውጠንጠን ከፍ ብሎ የመጓዝ አካሄድ ነው። ስንዴ ከውጭ አናስገባም ብለን በዓመት ሶስት ጊዜ ማምረት ጀመርን። ያልታረሱ መሬቶችን ማልማት ያዝን። አንድም መሬት ጾም እንዳያድር ለማድረግ ቆርጠን ተነሳን። በዚህም ለዘላቂ ችግራችን ጊዜያዊ መፍትሄ ከሚሰጠው ነባሩ አካሄድ ተላቀቅን፤ አዲስ የመፍትሄ መንገድ ቀየስን። አካሄዳችን ችግሩን ወዲያውኑ የሚፈታ ባይሆንም ዘላቂና የስንዴ እርዳታ ጥገኝነት እውነታን ላይመለስ የሚለውጥ ነው። ድጋፍ ለምን ቀረብን? እንዳይቀርብን ምን እናድርግ? ከሚለው በችግሩ ዙሪያ ከሚያውጠነጥን የመፍትሄ ምልከታ ተሻግረን ችግሩ ሊፈጥረው የሚችለውን እድል ለመጠቀም የሚችል መንገድን መረጥን።

መጪው ትውልድ በሞራል ተኮትኩቶ፤ በእውቀት በልፅጎና በኪነጥበብ ተነቃቅቶ ከተቀረፀ ምናቡ መንቃቱ አይቀርም። የመደመርን እሳቤ በመረዳትና በመተግበር ከተቃኘ በስንኝት፤ በጉድኝት፤ በጥምረት በህብረትና በቅንጅት በሚፈጠረው የጋራ ምናብ አማካኝነት ሊያልማትና ሊፈጥራት የሚችላት ኢትዮጵያ አስደናቂ ናት። ምናልባትም አፍሪካን ወደ ብልፅግና መምራትና ማብቃት የሚችል ትውልድ ሊፈጠር ይችላል። መጪውን

ዘመን ቀድሞ ማየትም የሚቻለው በምናብ ሃይል ነው። ምናቡ የበራለትና በቀና የተቃኘለት ትውልድ መፍጠር ከቻልን፤ የሀገራችን የወደፊት እጣ ፈንታ የበራ ሊሆን እንደሚችል እሙን ነው። ዛሬ በጥቃቅን ደረጃ የተጀመሩ ሀሳቦች የፈጣሪዎቻቸው ምናብና ልምድ ሲሰፋ፤ አለም አቀፍ ተፅዕኖ ያላቸው መሪ ተቋማት ሊሆኑ ይችላሉ። ምናባዊ ሃይሉ ከፍ ያለ ትውልድ የፈጠረች ሀገር፤ ሀገራዊ ቁመናዋ ከፍ እንደሚል አያጠራጥርም።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የመደመር ትውልድ ሥሪት -

## ብልሐትና ስልት

### ባለቤት አልባ አድማስ

ታህሳስ 4 ቀን 1953 ዓ.ም ንጉሰ ነገስታት ኃይለ ስላስ ከመኳንቶቻቸው ጋር ለይፋዊ ጉብኝት ብራዚል

ይሄዳሉ። ለረዥም ጊዜ መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ ሲያውጠነጥኑ ለነበሩት የንዋይ ወንድማማቾች (ግርማሜ ንዋይና መንግስቱ ንዋይ) እንዲሁም ሌሎች ባለስልጣናት ንጉሱን ለመጣል ምቹ አጋጣሚ ተፈጠረላቸው። በመሆኑም የንጉሱን መውጣት ተከትሎ፤ የሚገድሉትን ገድለው እና የሚያስሩትን አስረው፤ ቤተ መንግስቱንና የሬዲዮ ጣቢያውን ተቆጣጠሩ።

ከተቆጣጠሩት የሬዲዮ ጣቢያ በተሠራጨው የአልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን መልእክት፤ የኢትዮጵያ ኋላ ቀርነት በማንሳት፤ ችግሮችን ለማስተካከል ሲባል ንጉሱ ከስልጣን መውረዳቸውን ገለጹ። ንጉሰ ነገስት ኃይለ ስላሴን በመተካት ልጃቸው አስፋው ወሰን መንበሩን ተቆጣጥረው፤ አዲስ መንግስት እንደተመረጠ ለሕዝብ ተነገረ ይኽ ከሆነ በኋላ ነገሮች የንዋይ ወንድማማቾች እንዳሰቡት አልሆነም። መፈንቅለ መንግስቱም እንደሚገባቸው ተቀናጅቶ በመስራቱ፤ መፈንቅለ መንግስቱ በቀላሉ ተቀልብሶ ንጉሱ ወደ ሃገራቸው ተመለሱ።

ንጉሰ ነገስቱ ወደ ሃገራቸው ሲመለሱ ከወሰዱት ቀዳሚ የማስተካከያ እርምጃ መካከል፤ የመውደቃቸው ዜና ለሕዝብ የተሰራጨበትን መንገድ ሊቆጣጠር የሚችል ተቋም ማቋቋም ነው። መፈንቅለ መንግስት በተካሄደው በጥቂት ጊዜያት ውስጥ፤ ሕዝቡ ንጉሱ ወርደዋል የሚለውን ዜና የሰማበትን የተግባቦት መንገድ ለመግራት ትኩረት አድርገው ሰርተዋል።

የመፈንቅለ መንግስቱ አጋጣሚ ንጉሱ የመገናኛ ብዙሃን ያለውን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያው ተፅዕኖ በተግባር ተገንዝበው፤ የሕዝብ ግንኙነት እና መገናኛ ብዙሃንን ለመከታተል ትኩረት አደረጉ። ለዚህም የማስታወቂያ ሚኒስቴር ተቋቁሞ የሚሰራጩ መረጃዎችን ለመቆጣጠር ኃላፊነት ተሰጠው።

በዘመኑ የሚዲያ ተደራሽነት አነስተኛ ቢሆንም፤ ሬዲዮ በሚያዳምጠው የተወሰነው ሕዝብ ዘንድም ቢሆን፣ ዜናው ግራ የመጋባት፣ የመደናገጥ፣ የመሸበር ወይም የመደሰት ስሜትን መፍጠሩ አይቀሬ ነው። ንጉሱ እንዲወርዱ ሲጠባበቁ ለነበሩት ደስታን ፈጠረ። ሀገሪቷ በቀጣይ ምን ትሆናለች? በሚል የደኅንነቱ ነገር ያሰጋው ተደናገጠ። አብዛኛው ሕዝብ ደግሞ ግራ ተጋባ። መረጃው በወቅቱ ቀዳሚ የሕዝብ መነጋገሪያ አጀንዳ መሆኑ አያጠራጥርም።

የሕዝብ የውይይት አድማስ፤ ባለቤት እና የአጀንዳ ወሰን የለውም። ሕዝብን ``ዛሬ ይኽንን ተነጋገር``፤ ``ነገ ይኽንን ትወያያለህ`` ብሎ የሚቆጣጠረው አካል ሊኖር አይችልም። በመሆኑም የሕዝብን የመወያያ አጀንዳዎች የሚወስኑትና የሚቀርጹት፤ ብዙሃኑን የሚደርሱ በሚዲያ የሚቀርቡ መረጃዎችንና ሃሳቦች ናቸው። ሚዲያ የተግባቦት መሳሪያ ሲሆን፤ ከቀደሙት የተግባቦት መንገዶች በበለጠ በቅጽበት ውስጥ ብዙኃኑን ይደርሳል። የስሜት ለውጥን በፍጥነት ያመጣል። የሕዝቡን የውይይት አጀንዳ በመቅረጽም የተፅዕኖ አድማሱ የሰፋ ነው። ተጽፈው የምናነባቸው፣ ተቀድተው የምናዳምጣቸውና ተቀርፀው የምናያቸው መረጃዎችና ሐሳቦች፤ በሕዝብ ዘንድ የመቀየርና የመቅረጽ ዐቅም አላቸው። ይኽንን ተከትሎ ድርጊታችንን በመቃኘት ጉልህ ጫና የሚሰራጨው መረጃና መልእክት ነው። ስሜትን የመቆጣጠርና ቀልብን የመግዛት ዐቅም ያለው ሚዲያ ሕዝብን ለመልካምም ይሁን ለክፋት የማስተባበር ከፍተኛ ዐቅም አለው። ሕዝብን ለአንድ ዓላማ በማሰለፍ ከሚፈጠር ጠንካራ የሀገር ግንባታና የፖለቲካ ስርዓት ጀርባ ሚዲያዎች አሉ። ዴሞክራሲን መገንባት በቻሉ

ሃገራት ዘንድ፤ ሚዲያው ዴሞክራሲን ያፀና ኃይል ነው። በተቃራኒው ከሕዝብ እልቂትና ከሃገር መፍረስ ጀርባ ሚዲያዎች አሉ። በዮጎዝላቪያ መፈራረስ ውስጥ ልዩነት በማስመር ረገድ፤ ሚዲያዎች የገዘፈ ሚና ነበራቸው። የኢንተርሐምዌይ ድምፆች በሩዋንዳ ጭፍጨፋ ውስጥ ስለትን ያቀብሉ ነበር። በበጎውም ይሁን በጥፋቱ፡ አብዮቶችን እና ለውጦችን ለማቀጣጠል የሚያስችሉ መረጃዎች ከጫፍ ቻፍ እንዲደርሱ በማድረግ ሚዲያዎች የአብዮቶችና የለውጥ ሂደት አካል ናቸው።

ሚዲያ በአዎንታዊ ሚናው የማሕበረሰብ ክፍተቶችን ነቅሶ በማውጣት እንዲታረም የሚያደርግ ነው። የማህበረሰብ ክፍተቶችን እና የአመለካከት መካረሮችን የማረም ሚና መጫወት እንዲችሉ፤ ሚዲያዎች ርካሽ ተወዳጅነትን ከሚያስነኙ የማሕበራዊ ሚዲያ አስተያየቶች ይልቅ፤ ለእውነትና ለሕዝብ አገልጋይነት ትኩረት መስጠት አለባቸው። አጉል ተወዳጅነት ለማግኘት የሚሰሩ ከሆነ፤ በማኅበረሰቡ ዘንድ የአመለካከት ለውጥን አያመጡም፤ አያነቁምም። ማኅበረሰቡንም በመረጃ አይመሩትም። ከዚህ ይልቅ የተለየ ለውጥ እና ሐሳብ የማያስተጋቡና፤ የማህበረሰቡ ተከታዮች ይሆናሉ።

ጠንካራ የሚዲያ ሥርዓት ለመፍጠር፤ ሚዲያዎችና የሚዲያ ባለሙያዎች ሙያዊ፣ ሞራላዊና ማኅበራዊ ልኬት ሊኖራቸው ይገባል። የሚያቀርቡት ፕሮግራም ሙያዊ ደረጃውን የጠበቀ፤ የተሟላ የሞራል ኃላፊነት ያለበት፤ ማኅበረሰቡን ሊያሳውቅ፣ ሊያስተምርና ሊያዝናና የሚችል፤ መሆኑ ሁሌም ከግንዛቤ ሊገባ ይገባል። በዚህ መልኩ ሲሰራ ለሃገራዊ ለውጥ እና ዕድገት፤ እንዲሁም ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ውጤታማነት አስተዋጽዖ ማበርከት ይችላል።

ብዝሃንነት ባለባቸው ሃገሮች በሚዲያ የሚተላለፉ ይዘቶችና ውይይቶች፤ ብዝኀነት ተኮር ውዝግብንና ሥርዓት አልበኝነትን የሚያበረታቱና የሚፈጥሩ መሆን የለባቸውም። ሚዲያዎች የተለያዩ ድምፆች የሚተላለፉባቸው መሆናቸው እንዳለ ሆኖ፤ ግልጽነትንና ለጋራ ዓላማ መቆምን ለሕዝቡ የሚያሳዩ መሆን አለባቸው። በዴሞክራሲያዊነት የተለያዩ ድምፆችና መልእክቶችን ሊያስተላልፉ ቢችሉም፤ የተወሰነ ወገንን ለመጥቀም አልያም ለመጉዳት፤ በፈለጉት መንገድ መረጃዎችን ጠምዝዘው እና ያልሆነ ቅርጽ ሰጥተው ሲያቀርቡ፤ ከባድ ችግር ይፈጥራሉ። የሚዲያዎች ወገንተኝነት ብዝኀነት በሌለበት ሀገር ውስጥም ቢሆን፤ ችግር መፈጠሩ አይቀርም። በመሆኑም ሀገራዊ ጠቅምና የሚዲያ ነፃነት በሚዛን ሊስተናገዱ ይገባል።

ለሚዲያ ነጻነትና ገለልተኝነት የመንግስት ሚና ወሳኝ ቢሆንም፤ በዘመናችን በተፈጠረው የሚዲያ መስፋፋት፤ መንግስት በብቸኝነት ይዞት የቆየውን የሚዲያ የበላይነት አጥቷል። በዚህም ገለልተኝነትን የማረጋገጥ ኃላፊነት የሁሉም ኃላፊነት ሆኗል። የሚዲያ ባለቤቶች፣ የሚዲያ አስተዳደሩ እና ጋዜጠኞች ሁሉ፤ ነጻነትንና ገለልተኝነትን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። በመሆኑም ሚዲያዎች በጋራና በግል አሰራራቸው የሀገርን ጥቅም የሚያከብሩና የሚያስከብሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል። ለዚህም መንግስት ተገቢውን ሚና መጫወት አለበት። በሌላ በኩል ደግሞ የሃሳብ ብዝኃነትን ማረጋገጥ እንዲቻል የሚዲያዎች ነጻነት መከበር አለበት፤ ለዚህም መንግስትም ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል።

በሚዲያ ነጻነት ሚና ዙሪያ የተለዩ ምልከታዎች አሉ። አንዱና ቀዳሚው ``እውነት ሁሉም ቦታ የለም፤ የሚገኘው በጥቂቶች እጅ ነው፤ እነዚህ ጥቂቶች ሕዝብን በእውነት መንገድ መምራት አለባቸው``፤ ከሚል የሚነሳ ነው። ጥቂቶች (መንግስት)፤ አላዋቂውን የተቀረውን ሕዝብ፤ በማንኪያ እየመጠኑ እውነትን ማጉረስ አለባቸው፤ በመሆኑም መንግስት ለሕዝብ የሚነገረውን በሙሉ መቆጣጠር አለበት፤ የሚል አመለካከት ነው።

ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ፤ ``እውነት ሁሉም ቦታ እና በሁሉም እጅ ሊገኝ ይችላል``፤ ብሎ የሚያምን አለ። ስለሆነም አንድ ሐሳብ ለሕዝብ ቀርቦ የመረጠውን ይውሰድ ይላል በመሆኑም የሚዲያው ሚና ሁሉም ሐሳቦች በተለያየ ዓይነት መልክ እዲነገሩ ማድረግ ነው የሚለው የዚህ አመለካት ማዕከል ነው።

በሌላ በኩል `` እውነትና ዕውቀት ለሕዝብ ተጨባጭ ውጤት የሚያመጣ መሆን አለበት`` የሚል እሳቤም አለ። በዚህ እሳቤ መሠረት ሚዲያዎች ማኅበራዊ ኃላፊነትን የሚወጡ፤ ለማኅበረሰብ ዕድገትና ለውጥ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ መሆን አለቸባው። በመሆኑም የሚያገኙትን መረጃ ኃላፊነት በተሞላበት መልኩ የማስተላለፍ ግዴታ አለባቸው የሚለውን ገዢ ሐሳብ ያራምዳል።

# ሚዲያና ፖለቲካ በኢትዮጵያ

ሚዲያ ማለት ሐሳቦችን፣ ዜናዎችን፣ ሙዚቃዎችን፣ ፊልሞችን፣ መልዕክቶችን፣ ፕሮግራሞችን፣ ለብዙኀን የምናደርስበት የተግባቦት መሳሪያ እንደ መሆኑ፤ ሚዲያ ለፖለቲካ ሠርዓቶች ጥንካሬና ድክመት ትልቅ ሚና አለው። በመሆም ፖለቲካ ሚዲያን የመቆጣጠርም የማስተዳደር ትልቅ ፍላጎት አለው። በሃገራችን ሚዲያ ቀደም ብሎ የተጀመረ ቢሆንም፤ ፖለቲካዊ ተፅዕኖው ጎልቶ የወጣው፤ በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ላይ በተቃጣው የ1953ቱ መፈንቅለ መንግስት ወቅት ነው። በዚህም የተነሳ ንጉሱ ሚዲያን ለመቆጣጠር ከፍ ያለ ፍላጎት አሳይተዋል።

በሃገራችን ሚዲያ የተመሰረተው ማስታወቂያ ሚኒስቴር ከመቋቋሙ ቀደም ብሎ ሃሳባቸውን ለማዳረስ በፈለጉ የውጪ ዜጎች ነው። ሕዝቡን ለመድረስ የሚዲያ ጥቅም የጎላ መሆኑን የተገነዘቡ የውጭ ዜጎች፤ ከሃገራቸው ተሻግረው በሃገራችን ቀዳሚዎቹን ሚዲያዎች አቋቁመዋል። ሕዝቡን ለማግኘት እና ሐሳባቸውን ለማስረጽ እንደ ትልቅ አማራጭ በመጠቀማቸው በሃገራችን የሚድያ ስርጭት መጀመርና መስፋፋት ላይ ከፍ ያለ ድርሻ ተጫውተዋል። ኢትዮጵያውያን ሃሳባቸውን ለማስረጽ የመገናኛ በዙኀንን መጠቀም የጀመሩት ከውጪዎቹ በኋላ ነው።

በዘመናዊ የትህትመት ሚዲያ ታሪክ በሃገራችን በጉልህ የሚጠቀሰው ጋዜጣ "አእምሮ የሚሰኘው ሲሆን፤ በንጉሱ ዘመን በዘውዱ ዙሪያና ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሳምንታዊ ዘገባዎችና ሀተታዎችን በማሰናዳት በጥቂት ቅጅዎች ይሰራጭ ነበር። በኋላም የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ ከዚያም የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን እውን እየሆኑ መተዋል። የሚዲያዎች አይነት ሲጨምር፤ የውጭ ሚድያዎች ወኪሎች ሲበዙ፤ ያስከተሉትን ተፅዕኖ በመመልከት፤ በሀገራችን ሚዲያን ለመቆጣጠር የሚያስችል ተቋም ተመስርቷል። ይኸ ሚዲያን የሚቆጣጠር የሚያስተዳድር አካል በፖለቲካውና በሚዲያ መካከል የሚኖርን ግንኙነት ይወስናል። ለሚዲያው

መስመሩ ከምን ድረስ እንደሆነ ያሰምራል። ለፖለቲካውም ሚዲያው ላይ ሚናው ምን ድረስ እንደሆነ ይነግረቸዋል። የመጀመሪያው ሚዲያን የሚቆጣጠር ተቋም ሲቋቋም፤ ይኽንን ግንኙነት የመወሰን ኃላፊነት ይዞ የተነሳ ነበር። ከዚህም በኋላ በየዘመናቱ ሚዲያዎችና ፖለቲካው የተለያየ መልክና ቀለም ሲይዙ ቆይተዋል።

የመገናኛ ብዙሃን ሥርዓቱ ለረዥም ዘመናት “ከአንድ ምንጭ፤ በአንድ ጊዜ ብዙኀኑን መድረስ” በሚል መርሕ የተቃኘ ነበር። በዚህ መርሕ በሚዲያና በመንግስት መካከል ያለው ግንኙነት የመረጃ ምንጭና ማሰራጫውን ለመቆጣጠር በሚኖር ፍላጎት የተመረጠ ነው። መንግስት በአንድ በኩል የመረጃና የማስራጫ የበላይነቱን መቆጣጠር ሲፈልግ ሚዲያ ከፍተኛ ነጻነት ይፈልጋል።

በቀዳማዊ ንጉሱ ነገስታት ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሚዲያው መለስተኛ ነጻነት ስለነበረው፤ የብዙ ሐሳቦች የመወያያ መድረክ መሆን ጀምሮ ነበር የመንግስት፤ የግልና የሐይማኖት ሚዲያዎች ነበሩ። ደርግ ሲመጣ ሁሉን ወርሶ የሶሻሊስታ ሐሳብዊ ሃሳብ ማሰራጨት አደረጋው። ከደርግ መውደቅ በኋላም “ልማታዊ ሚዲያ” በሚል ፖለቲካ ውስጥ ተጨፈለቀ። ዓላማቸውም አንድን ሐሳብ ከአንድ ምንጭ ቀድቶ ማሰራጨት ሆነ።

በዚህ ሚዲያው በታፈነበት ዘመን፤ ሁለት ወቅቶች የተሻሉ የሚዲያ ነጻነት የታየባቸው ነበሩ። ከንጉሱ መውደቅ በኋላ የነበሩት ጥቂት ጊዜያትና የደርግ መንግስት ከወደቀ በኋላ የነበሩት ጥቂት አመታት። ነገር ግን ነጻነቱ እያደር እየመነመነ በመሄዱ፤ የፖለቲካ ሃይሎችና ሌሎች ሐሳቦች ድምፃቸውን የሚያሰሙበት አማራጭ እንዲፈልጉ አስገደዳቸው። ይኽም ከሃገር ውጭ የሚሰራጩ የትግል ሚዲያዎች እንዲስፋፉ አደረገ። እነዚህ የትግል የሚዲያዎች በዋናነት ትግላቸው ሥርዓቱን ለማዳከምና ለመጣል በመሆኑ፤ የሚዲያ ጥራትን የሚያሟላ አልነበሩም።

ማኅበራዊ ሚዲያዎች የመጡበት ወቅትም ከመንግስት ተቃራኒ የሆኑ ሐሳቦችን ለማስተላለፍ አማራጭ ሚዲያ በሚፈለግበት ጊዜ ነበር። ይኽም ለተቃውሞ ጎራው ትልቅ እድል የፈጠረ ሆኗል። ማህበራዊ ሚዲያ ከቀደመው የሚዲያ እሳቤ እና ሥርዓት የተለየ ጠባይ ይዞ የመጣ ነው። በአብዛኛው ዋና ማዕከሉ ከሀገር ውጭ እንደመሆኑ፤ ለመንግስት ቁጥጥር አስቸጋሪ ነው። የሕግ አካሄዶችን አይጠብቅም። በእያንዳንዱ ግለሰብ ሊከወን የሚችል በወጪም ርካሽ እና ሰፊ ተደራሽነትም ያለው ነው።

በእነዚህ ምክንያቶች የተነሳ በፖለቲካ ሥርዓቶች ላይ ማህበራዊ ሚዲያው አዲስ ጫናን ፈጠረ። በእኛ ሃገር ደግሞ ሁለት ነገሮች ገጠሙ። የትግል ስሜት የተጫነው የሚዲያ ፍላጎትና ባህል፡ በአንድ በኩል፤ ያልሰለጠነ የፖቲካ ባህል፡ በሌላ በኩል። የእነዚህ ሁለት ነገሮች ጫና እንዲያሳድር አድርጎታል።

ከሰፊ ምንጭ ሰፊ መረጃ የሚሰራጭበት ማህበራዊ ሚዲያ፤ ፖለቲካን እና ሥርዓቶችን በከፍተኛ ተፅዕኖዎች ውስጥ ከትቷቸዋል። የመረጃና የሚዲያ የበላይነትን ከጥቂቶቹ ወደ ብዙሃኑ ማሸጋገሩ መልካም ውጤት

ቢሆንም፤ ለማስተዳደር ምቹ አለመሆኑ ትልቅ ክፍተት ፈጥሯል፡፡

መደበኛው ሚዲያ ከሞላ ጎደል ከፍ ያሉ የሕዝብ ፍላጎቶችንና ጉዳዮችን የሚያቀርብና የሚያወያይ ነው፡፡ ማህበራዊ ሚዲያው ግን በአንድ ሰው ተነሳሽነት እና ተናጠላዊ ምልከታ ላይ የተንጠለጠሉ፤ ምንም ዓይነት የኤዲቶርያል ሂደትን ያላለፉ፤ ባለቤት አልባ መረጃዎችንና ሐሳቦችን ያሰራጫል፡፡ ይኽ ግለሰባዊ የሆነ መረጃን የማጋራት ሂደት የሀሳብ ብዝኀንነትን ለመፍጠር መልካም ቢሆንም፤ በግለሰባዊ ፍላጎት ዙሪያ የሚያውጠነጥን፤ ምንም ዓይመነት ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሌለበት በመሆኑ ልቅነት፣ ስሜታዊነት ስሕተት የሚበዛበት ሆኗል፡፡

# ቀጣይ የሚድያ ሚና ለትውልድ ግንባታ

የሚዲያ ፍልሰቶችን ሚዲያዎች ነጻ መሆን እንዳለባቸው የሚያምን፤ ነገር ግን ውሃውንም መርዙንም የሚያስተላለፉ ቱባዎች እንዳይሆኑ የሚከታተል ነው፡፡ ሚዲያዎች ነጻነትን ከኃላፊነት ጋር አዛምደው የሚጓዙ መሆን አለባቸው፡፡ ኃላፊነታቸው ለሕዝብ ትክክለኛውን መረጃ በመስጠት፤ ብሔራዊ ጥቅምን ዐውቀው በመጠበቅና በማስጠበቅ፤ የሕፃናትን፣ የሴቶችን፣ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ወገኖችን፣ የሕዝቦችንና የግለሰቦችን መብት በማክበርና በማስከበር የሚገለጥ ነው፡፡ ነፃነታቸው ደግሞ በሕግ የተፈቀደላቸውን ሐሳብን በጸነት የመግለጥ መብት በመጠቀም የሚገለጥ ነው፡፡ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን የሚያጠናክሩ፤ መንግስትን የሚቆጣጠሩ የሕዝብ ድምፆች እንጂ፤ በዴሞክራሲና በነጻነት ስም፤ የሀገር ሕልውናን የሚፈታተኑ እና ሉዓላዊነትን ጥያቄ ውስጥ የሚከቱ መሆን የለባቸውም፡፡ ዜጎች የዲሞክራሲን ባህልና ነፃ ውይይትን የሚማሩባቸው፤ የነጠረ ሐሳብ የሚወጣባቸው መድረኮች ሆነው፤ ትውልድን በመገንባት ሀገራዊ ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

ተግባቦት ሁሌም የሕዝብን እሳቤና ግንኙነት በመቅረጽ ረገድ ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡ ብዙሃኑን መድረስ የሚችል ሚዲያም ትርክትን ይገነባል፡፡ በሃገራችን የኀብረ ብሄራዊ አንድነት ትርክት ገዥ እሳቤ ሆኖ እንዲወጣ፤ ሚዲያዎች ወንድማማችነትንና ብዝኀንነትን የሚያስተጋቡ ድምፆች መሆን አለባቸው፡፡

በመደመር ትውልድ ግንባታ ውስጥ ሚዲያ በሚኖረው ሚና ላይ የተደቀነ ዋነኛው ፈተና፤ ከብዙ አማራጮች የሚሰራጩ አሉታዊ መረጃዎችን ተቆጣጥሮ፤ ኀብረ ብሔራዊ አንድነትን፣ ውበትና የሀገር ፍቅር ስሜትን ማሥረጽ መቻል ነው፡፡ ሚዲያው ለትኩረት ግንባታ የሚኖረውን ሚና ተጠቅሞ የህብረ ብሔራዊ አንድነትና የወንድማማችነት ትርክት፤ በሕዝብ ውስጥ እንዲቀረጽ ማድረግ አለበት፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፤ በሚዲያ የሚሰራጨውን የጥላቻ ትርክት መግራትና መቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ ሕዝብ መደመርንና የአንድነትን እሳቤ እንዲሁም የልዩነትና የጥላቻን ተረት ተረት የሚሰማው ከሚዲያ ነው፡፡ ፖለቲከኛው ተዋደዱም ሲል ተገዳደሉም ሲል በጋዜጦች ጽፎ፤ በሬድዮ ተናግሮ፣ በቴሌቪዥን እና በማህበራዊ ሚዲያ ምስል ከድምጽ አሰራጭቶ ነው፡፡

ሀገር ገንቢ ትርክትን ለማጠናከር ከተፈለገ፤ ዘርፈ ብዙ ጥላቻ ጠንሳሽና አፍራሽ ትርክቶችን መቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ ይኽን ለማድረግም፡ በረዥም ጊዜ ሃገር በቀል ማህበራዊ ሚዲያ ማበልፀግ ዋናው ትኩረታችን

መሆን አለበት። በአጭር ጊዜ ደግሞ፤ ማኅበራዊ ሚዲያውን ለመግራት እንዲያስችል ማኅበራዊ ሚዲያውን የሚገዛ የሕግና የአስተዳደር ሥርዓት መንደፍ ያስፈልጋል። በማህበራዊ ሚዲያ መረጃን ማሰራጨት መብት እንደሆነው ሁሉ፤  የጥላቻ መልዕክትና የተሳሳተ መረጃን ማስተላለፍ ወንጀል ሆኖ ተጠያቂነትን ማስከተል አለበት። በዚህ ረገድ ፀድቀው ወደ ሥራ የገቡ የሕግ ማዕቀፎች ቢኖሩም፤ ከይዘትና ከአፈጻጸም አንጻር የሚኖሩ ክፍተቶችን በመሙላት፤ ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል። የቴክኖሎጂው ባለቤትነት ከኛ ቁጥጥር ውጭ እንደ መሆኑ፤ የሚፈለገውን ተጠያቂነት ለማጣትና ማኅበራዊ ሚዲያውን ለመግዛት፤ ከባለቤት ተቋማቱ ጋር መሥራትና የቴክኖሎጂ ዐቅምን ማሳደግ ወሳኝ ይሆናል።

ከዚህም በተጨማሪ ሕዝብ መረጃዎችን አላምጦ መዋጥ እዲችል፤ በማኀበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምና በመረጃ ጉዳይ ላይ፤ ከታች ጀምሮ በትምህርትና በሥልጠና መልክ፤ ተማሪዎችን ማንቃትና ማብቃት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ሲንጋፖር ዜጎችን በማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ዙሪያ በማንቃት፤ ትልቅ ለውጥ ለማምጣት ችላለች። ቀድሞ የነቃ እና ያወቀ ትውልድ፤ በማኅበራዊ ሚዲያ ምክንያት ሊመጣ የሚችልን መደናገርን ይቀንሳል።

መደበኛ ሚዲያው ከማኅበራዊ ሚዲያው የተነሳ የፉክክር ተግዳሮች ተደቅኖበታል። በዚህም ምክንያት ይሱን ቀለም ከመያዝ የማኅበራዊ ሚዲያ ዓይነት ባህሪ ሊላበስና፤ በማኅበራዊ ሚዲያው ሲመራ ይታያል። መደበኛ ሚዲያው ከማኅበራዊ ሚዲያው ጋር መፎካከርን ትቶ የሱን መልክ በመያዝ፤ ማኅበራዊ ሚዲያው ሊከውናቸው የማችላቸውን ሥራዎች መስራት አለበት። መደበኛው ሚዲያ የሙያ ብቃትን የተላበሰ፤ በማስረጃና በአመክንዮ የሚመዝን፤ በሕዝባዊ ክርክሮች ውስጥ ጠንካራ ሐሳቦች እንዲፈልቁ የሚያደርግ መሆን አለበት። ለዚህም የጋዜጠኝነትን ሥነ ምግባር የተላበሱ ብቁ ባለሙያዎችን ማፍራት ያስፈለግጋል። ለዚህ ሰደሞ የሚዲያ ተቋማትና ማኅበራት ተገቢውን ሚናቸውን በብቃት እንዲወጡ አመራር፤ ድጋፍና ክትትል ያስፈልጋል።

ሁሉም ሚዲያዎች በአንድ አጀንዳ ላይ በመራኮት፤ ሌሎች የሕዝብ አጀንዳዎች ሳይዳሰሱና ትኩረት ሳያገኙ የሚቀሩበት ሁኔታም እየተፈጠረ ነው። ይኽንን የሚፈጥረው ገበያና ተከታይ መር መሆን ነው። ከሃገር አቀፍ ሚዲያዎች በተጨማሪም አካባቢያዊ አጀንዳዎች ለውይይት የሚቀርቡባቸው፤ አካባቢያዊ ተደራሽነት ያላቸው የማኅበረሰብ ሚዲያዎች ሊስፋፉ ይገባል። ዜጎች አካባቢያዊ ችግሮቻቸውን በመወያየት መፍትሔ እንዲያመጡ ማድረግ የእነዚህ ሚዲያዎች ኃላፊነት ነው። የማኅበረሰብ ሚዲያዎች ተደራሽነታቸው የተገደበ፤ የአጀንዳ አድማሳቸውንም በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ በማድረግ የሚሰሩ ናቸው።

በሚዲያ ትውልድ በመገንባት የሚደረገው ጥረት ከሥር መሰረት መጀመር አለበት። በዕድሜ ከፍ ያለውን ሕዝብ መቅረጽና መምራት ብቻ ሳይሆን "እኔ እንትና ነኝ"፤ "እንትና እንዳያደርገው" በሚልው የሕጻናት ንግግር ውስጥ፤ ልጆችን ከልጅነታቸው እያረሙና እየቀረፁ በሀሳብ የሚያበለጽጉ ሚዲያዎች ውስጥ ሕፃናት ያላቸውን ቦታ መመልከትም እጅግ አስፈላጊ ነው።

በሕፃናት ዕይታ ውስጥ የታተመ ምስል የጋራ ትዝታ መሆኑ አይቀርም። ለምሳሌ አባባ ተስፋዬ ከዘመኑ ትውልድ ዘንድ ምን ዓይነት የጋራ ትውስታ እንደፈጠሩ ብዙ ሰው የሚረዳው ነው። "ተነሱ ልጆች"፤ "በሉ

ተቀመጡ” እያሉ ለልጆች ያስተማሩት ታላቅን በማክበር ባህል፤ በትውልዱ ልጆች” ልብ ውስጥ ተቀርጾ የቀረ ነው። “ደህና ሁኑ ልጆች፤ የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች” ሲሉ “ቻው እያሉ በሚቀጥለው ሳምንት ፕሮግራማቸውን እስኪመጣ በጉጉት የሚጠብቁ፤ እሳቸው በፈጠሩት የጋራ ትውስታ ውስጥ የሚግባቡ ትውልዶች ተፈጥረዋል።

ይሁንና በአጠቃላይ በሀገራችን በሚዲያዎች ለሕፃናት የሚሰጠው ቦታ እጅግ አናሳ ነው። በዚህም ምክንያት ሕፃናት በራሳችን ሚዲያዎች ለዕድሜያቸው የማይመጥን ፕሮግራሞችን እንዲከታተሉ ይደረጋሉ። ይኽን ካልፈለጉ ደግሞ የውጭ የሕፃናት ሚዲያዎችንና ፕሮግራሞችን ይከታተላሉ። በዚህም ሕፃናት በሚከታተሏቸው የውጭ ፕሮግራሞች ተፅዕኖ፤ የውጭ ባህልን እየለመዱ ያድጋሉ። ይኽም በትውልድ ግንባታ ሂደት ላይ ከፍተኛ ክፍተትን ስለሚፈጥር፤ የሕፃናት ፕሮግራሞችን ሚዲያዎች የሚበረታቱበትና የሚታገዙበት የተለየ አሰራርን መዘርጋት ያስፈልገናል። ይኽ መሆን ሲችል የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች መሆናቸው አይቀሬ ነው።

በሌላ በኩል ሃገር አቀፍ ሚዲያዎች የትኩረት አድማሳቸው በሃገር ውስጥ ብቻ ታጥሮ ሊቀር አይገባም። ሚዲያ፤ ሃገር ዓለም አቀፍ ተፅዕኖዋን የምታሻግርበት፤ ገር ኃይል ነው። ለጠንካራ ሃገራት፡ ሚዲያ ከሃገር ተሻግሮ በዓለም ላይ ተፅዕኗቸውን ሚያሰፉበት፤ አንድ የዓለም አቀፍ ግንኙነት መሳሪያቸው ነው። ሀገራችንም ሚዲያዋ ከውስጥ ጉዳይ ተሻግሮ የተፅዕኖ ወሰኑን በማስፋት፤ አፍሪካዊነትንም የሚቀርጽበትንና፤ ዓለም አቀፋዊ ተደራሽነቱን የሚያሰፋበት ዕድል መፍጠር ይገባል። የታዳሚ ምልከታዎችን በሀገር ውስጥ ያለውን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ ሊሆን ይገባል።

# ከአምጡነት ወደ እንኩነት፡ የአበርክቶት በረከቶች

“መብቴ ነው - “መብት” የየቀኑ ጥያቄና የዘመኑ ፋሽን ነው። ሁሉም መብቴን አትንኩ መብቴን አምጡ ባይ ነው። ይኽም ትውልድ መብቱን አበክሮ የሚጠይቅ፤ ለመብቱ መከራከር የሚታገል፤ ስለ መብቱ አጥብቆ የሚያስብና የሚያሰላስል ብቻ ሳይሆን፤ የሕይወቱን ትኩረት መብቱን በማስጠበቅ ዙሪያ ላይ ያደረገ ነው። የሚዲያዎችም ትንተና፣ ክርክር፣ ውይይትና ቅስቀሳ፤ በዋናነት በመብት ዙሪያ ያጠነጥናል። ማህበራዊ አንቂዎችን ፖለቲከኞችም ለተከታዮቻቸው የሚሰጡት የተስፋ ምግብ መፍለቂያ፤ መብትን ማስከበርና ማደል ይመስላል። እርምጃውን ሁሉ “መብቴ ነው” በሚል ቃልና ስሜት እያጀበ የሚኖር፤ መብቱን ለማስከበር የሚተጋ ትውልድ ተፈጥሯል።

በእርግጥ ለመብት መሟገት፤ የተረጋጋና በፍትሕ የተሞላ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሥርዓት እንዲፈጠር ያግዛል፤ የሚጠይቅና እርምት እንዲደረግ የሚያስገድድ ትውልድ ያፈራል፤ በደልንና ግፍን የማይሸከም ጫንቃ ይፈጥራል። መብትን መሻት መንግስት በአግባቡ ሥራውን እንዲሰራ፣ ብልሹ አሰራሮች እንዲስተካከሉና ሥርዓቶችን እየታረሙ እንዲሄዱ ያደርጋል። ሆኖም መብትን በመሻት ላይ ብቻ ሰፊውን

ትኩረት ማድረግ፤ በሆነው ባልሆነው ቱግ የሚልና መቀበልን ብቻ የሚወድ ትውልድ ሊፈጠር ይችላል። በሌላ አገላለጽ መብትን ብቻ ማቀንቀን፤ ሌሎችን ተጠያቂ የሚያደርግና ከሌሎች ጠባቂ የሆነ ትውልድን ይፈጥራል።

ጠባቂነት መንግስትንና ተቋማትን የሚያነቃ በመሆኑ መልካም አስተዋፅዖ ሲኖረው፤ ጠባቂነት ግን ከሌሎች የመቀበልና የራስ ሚና አለመወጣትን ያመላክታል። ሀገርና ሕዝብ ወደ ብልጽግና እንዲያመሩ መብቱን ብቻ ሳይሆን ግዴታውንና ኃላፊነቱን የሚወጣ፤ ጠያቂነትን ብቻ ሳይሆን ተጠያቂነትን የሚያውቅ፤ መቀበልን ብቻ ሳይሆን መስጠትን የተለማመደ ትውልድ መሆን ይገባዋል።

መቀበልን ብቻ ማዕከል ያደረገ ሰው፤ በቻለው መንገድ ሁሉ ከሃገር ከሕዝብ እየተቀበለ ይኖራል እንጂ የሚያበረክተው አይኖረውም። ሁሌም ይኽ ያስፈልገኛል እንጂ ይኽ ይጠበቅብኛል ብሎ ለማሰብ ይቸገራል። እንዴት ማግኘት እንደሚችል ብቻ እንጂ እንዴት መስጠት እንደሚችል አይጨነቅም። የጥረቱ ማጠንጠኛ ስለሚያበረክተው አስተዋጽዖ አይደለም። የሕይወቱን ስኬት ሚለካው በተቀበለው ነገር ብዛት እንጂ በሰጠውና ባበረከተው ነገር መጠን አይደለም። ይኽ ዓይነት ሕይወት መንገድ አይደለም።

የሰው ልጆች ዘላቂ ደስታንና የሕይወት ርካታን የሚያገኙት ትርጉም ያለው ሕይወት ሲኖር ነው። ትርጉም ያለው ሕይወት ስንል፤ በሕይወታችን ምን ማሳካትና ምን ነገር አበርክተን ማለፍ እንዳለብን ዐውቀንና፤ ራሳችንን ለዚያ ዓላማ አስገዝተን፤ የምንኖረው ሕይወት ነው። ሰዎች የራሳቸውን ግለሰባዊ ሕልውና ለማረጋገጥ ብቻ የተፈጠሩ አይደሉምና።

ማንኛውም ግለሰብ የተፈጠረው ለሰው ልጆች ሕልውናና ደስታ ሚና እንዲጫወት ነው። የሰው ሕልውናና ደስታ የሚወሰነው ለሰው ልጆች ሁሉ ሕልውናና ደስታ በሚሰራው ሥራና፡ በሚደርስበት ስኬት መጠን ነው። ለሰው ልጆች ሕይወት መለወጥና መሳካት ኃላፊነትን የማይወስድ ግለሰብ፤ ለሕይወቱ ትርጉም እያጣ መምጣቱ አይቀርም። በልቶ፣ ጠጥቶና የሚፈልገውን ነገር አግኝቶ፤ ውስጡ ግን ጥያቄውን አያቆምም። ሲመኘውና ሲያስሰው የነበረውነገር ሁሌ በእጁ ሲገባ ትርጉም ያጣበታል። በድብርት፣ በመቅበዝበዝና ሕይወትን በመጥላት ሁለንተናው ይናጣል። በመጨረሻም የሕይወትን ትርጉም ፍለጋ አላስፈላጊ ወንጀሎችንና መጥፎ ልማዶች ውስጥ ራሱን ተነክሮ ያገኘዋል።

የሕይወት ትርጉም የሚያገኘው ለዓላማ ከመኖር ነው፤ ብዙ ነገር አበርክቶ ለማለፍ ከሚደረግ ጥረት ነው። ለማበርከት የማይተጋ ሰው ደስተኛ ኑሮና የሕይወት እርካታ ሊኖረው አይችልም። ቢያገኝም ድሃ ነው፤ ቢቀበልም ጎደሎ ነው፤ ቢበላም ይርበዋል፤ ቢማርም አያውቅም። ማንም ሰው በተቀበለው ነገር ብቻ ዘላቂ የሆነ ደስተኛ ሕይወት ሊኖረው አይችልም፤ ማበርከትም ሲችል እንጂ። በእርግጥ የሰው ልጅ ለመስጠትም መቀበል ይኖርበታል፤ ለመደሰትም ጉድለቱን በመቀበል መሙላት አለበት። ዘላቂ ደስታን ለማግኘት ትርጉም ያለው ሕይወትን መኖር አለበት፤ በማንኛውም ጨለማ ውስጥ ሆነን የሆነ ነገር አበርክቶ የማለፍ ሕልም ካለን፤ ተስፋና የሕይወት ትርጉምን ማግኘታችን አይቀርም። የማበርከት ሕልም ያለው ሰው፤ ፈተናዎችንና ተግዳሮቶችን ሁሉ የመቋቋም ዐቅምን ማዳበሩ አይቀርም።

መጪው ትውልድ የሚሰጥ፤ የሚያገለግልና የሚያበረክት እንዲሆን ከመብቱ ባሻገር ግዴታውንና ኃላፊነቱን እንዲያውቅ ማድረግ ያስፈልጋል። ሀገራችን የሌላትን አምጪ ብሎ የሚያስጨንቃት፤ በመቀነቷ የቋጠረችውን አራግፎ የሚወስድ፤ ሞሰብ ገልባጭ የሆነ፤ ባልገነባቸው ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ፤ ከጎደለ መሶብ ውስጥ ሁሉን ድርሻ ለኔ የሚልን ልጅ የሚሸከም ጫንቃ የላትም። ከመሶቡ ሊቆርስ እጁን እንደሚዘረጋው ሁሉ፡ ጎጆውን ለመስራት ወገቡን የሚያጎብጥ፤ መውሰድ ስለሚገባው ብቻ ሳይሆን፡ ማበርከት ስላለበትም የሚጨነቅ ልጅ ነው የሚያስፈልጋት። ለዚህ ደግሞ ከመብት ባሻር፤ ግዴታንና ኃላፊነትን ማወቅና መወጣት ያስፈልጋል።

ግዴታና ኃላፊነት ተቀራራቢ ነገር ግን የተለያየ ትርጉም ያላቸው ጉዳዮች ናቸው። ግዴታ ማለት ሕጋዊ፣ ማኅበራዊና ሞራላዊ ድንጋጌዎችን አክብሮ መንቀሳቀስ ማለት ነው። ኃላፊነት ማለት ግን ድንጋጌዎችን ከማክበር ባለፈ ለጉዳዩ ሙሉ የተጠያቂነት ስሜት መያዝና፤ ስለሌሎች ሰዎች ድርጊትና ደኅንነት ዋና ባለ ጉዳዩ መሆን ማለት ነው። ለምሳሌ፣ "መንገድ ላይ ቆሻሻ መጣል ክልክል ነው" ሲባል ይኽንን ደንብ ማክበር ወይንም መንገድ ላይ ቆሻሻ አለመጣል ግዴታ ነው። በአንጻሩ "መንገዱ ንጹሕ እንዲሆን ኃላፊነት አለብን" ስንል አካባቢው ንጹሕ እንዲሆን ማድረግ የእኔ ሥራ ነው ብሎ፤ በአካባቢው የቆሻሻ መጣያ ማስቀመጥ፣ ቆሻሻ እንዳይጣል ቁጥጥር ማድረግ፣ ወይም አካባቢውን የማጽዳት ሥራ መሥራትን ያመለክታል።

የመደመር ትውልድ ሕግና ደንብን በማክበር የሚጠበቅበትን ትንሹን ነገር ሟሟላትነና በመፈጸም፤ ግዴታውን ከመወጣት ባሻገር ስለ ጉዳዩ የሚመለከተኝ እኔን ነው፤ የጉዳዩ ባለቤት እኔ ነኝ ብሎ የሚያስብና ሙሉ ኃላፊነትን የሚወስድ ትውልድ ነው።

# መገልገልና ማገልገል

መጪው ትውልድ ግዴታና ኃላፊነቱን ጠንቅቆ የሚያውቅ እንዲሆንና፤ በሀገሩና በሕዝቡ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ስሜት እንዲፈጠርበት፤ ለሀገርና ለሕዝቡ አገልግሎት የሚሰጥባቸውን መንገዶች መቀየስ አስፈላጊ ነው። መገልገል ብቻ ሳይሆን የማገልገልን፤ መቀበል ብቻ ሳይሆን መስጠትን፤ መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታንና ኃላፊነትን፣ መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ማበርከትን እንዲያውቅ፤ አገልግሎት መለማመድ ይኖርበታል። ዜጎች አገልግሎት ማግኘትን የሚሹ ከሆኑ፤ እነርሱም አገልግሎት ለመስጠት መዘጋጀት አለባቸው። አገልጋዮች ከሌሉ አገልግሎት ሊኖር አይችልም። አገልጋዮች በበዙበት ሀገር፤ ሁላችንም የምንፈልገውን አገልግሎት በቀላሉ ማግኘት እንችላለን።

የሰው ልጆች ተወልደው አድገው ለፍሬ የሚበቁት ከተፈጥሮና ከህብረተሰቡ በሚያገኙት አገልግሎት ነው። አንድ ሰው ብቻውን ምንም ነው። በአካልም በአእምሮም ምንም ከማያውቅና በአካሉም ከደቀቀ የራስነት ደረጃ ተነስቶ፡ ብዙ ነገሮችን ወደ ሚያውቅ ግዙፍ ሰውነት የሚደርሰው፤ ከሌሎች በተሰጠው አገልግሎት ነው። አንድ ሰው ብቻውን ሕልውናን ሊያረጋግጥ አይችልም። የሰው ልጅ ሕልውናቸውን ማረጋገጥ የሚችሉት በጋራ ነው። አንደኛው እህል ሲያመርት ሌላኛው ሕክምና እየሰጠው፣ ሌላኛው ልጅ እየተንከባከበ፣ ሌላኛው ምግብ እያበሰለ፣ ሌላኛው ከብት እያረባ፤ ሌላኛው እሰሸመነ...አንዱ የአንዱን እየተጠቀመ፤ አንዱ ሌላውን እያገለገለ

ነው የሰው ልጆች ሕልውናቸውን የሚያረጋግጡት። ተወልደው የሚያድጉት፤ ጎርምሰው የሚጎለምሱት፤ አርጅተው የሚጦሩት በሌሎች የአበርክቶ ጥላ ሥር ነው።

በቻሉት መጠን እየመገቡና እያለበሱ ያሳደጉን ወላጆች ስላሉን ነው ጤናማ ሕይወት የምንመራው። መምህራን ስላሉን ነው ፊደል የቆጠርነው፤ የገሰጹንና የመከሩን ቤተሰብና ጎረቤት ስላለን ነው፡ ግብረ ገብነት ያለው ሰው የሆንነው። እያለማመዱንና እያረሙ ያስተማሩን ሰዎች ስላሉ ነው ጥሩ ባለሙያ የሆንነው። እንቅልፍ አጥተው ሕክምና እየሰጡን ያሉ ሃኪሞች ስላሉ ነው ከበሽታና ከሞት የተረፍመው።

በሕይወታችን በእያንዳንዱ እርምጃችን እየተገለልን እንደምንኖር መገንዘብ፤ እኛስ ምን ያህል እያሰገለገል ነው? ብለን ራሳችንን ለመጠየቅ ይጠቅመናል። ሳያገለግሉ መገልገል፤ አገልጋዮች እየቀነሱ፡ ተገልጋዮች እየጨመሩ እንዲመጡ ስለሚያደርግ፤ አገልግሎት እየተመናመነ ይመጣል። ሀገርና ሕዝብ ወደ ብልጽግና እንዲያመሩና ሕልውናቸውን በዘላቂነት ማረጋገጥ እንዲችሉ ለማድረግ፤ አግልጋይነት ትውልድ መፈጠር ይኖርበታል።

ትውልድ አገልግሎትን መስጠት እንዲለምድ፤ ሀገሩንና ሕዝቡን እንዲወድ፤ ለሀገሩና ለሕዝቡ መሻሻል ዋጋ ለመክፈል የተዘጋጀ ልብ እንዲኖረው፤ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችልባቸውን አቅጣጫዎች መቀየስ ይኖርብናል። የአገልጋይ ትውልድ መፍጠር መንገዶችን ተግባራዊ በማድረግ፤ ትውልድ ኃላፊነቱን የተረዳ፤ የሀገር ፍቅር ያለው ኢትዮጵያን ጠንቅቆ የሚያውቅ፤ በትርጉምና በዓላማ የተቀነበበ ኑሮ የሚኖር፤ ደስተኛና በሕይወቱ እርካታ ያለው እንዲሆን፤ መልካም አጋጣሚን መፍጠር ይገባል።

አገልጋይ ትውልን ለመፍጠር ሀገራዊ አገልግሎት፤ ማኅበራዊ ኃላፊነትና በጎ ፈቃደኝነትን ማስፋፋትና በትውልዱ ውስጥ ማሥረጽ አስፈላጊ ነው። ሀገራዊ አገልግሎት፡ በመንግስት ደረጃ የሚዘረጋና፤ ዜጎች በመደበኛ ፕሮግራም ለሀገራቸው በጊዜ የተገደበ አገልግሎት የሚሰጡት መንገድ ነው። ማህበራዊ ኃላፊነት፡ እንደ ድርጅት ወይም እንደ ግለሰብ፤ በየዕለት እንቅስቃሴያችን በኅብረተሰቡ ውስጥ የምንመለከታቸውን ችግሮች ለመፍታት የምናደርገውን ጥረትና፤ በሥራዎቻችን ሂደት ኅብረተሰቡን የሚጎዳ ነገር አለመሥራታችንን የማረጋገጥ የሞራል ተጠያቂነት ነው። በጎ ፈቃደኝነት፡ ግለሰቦች በራሳቸው ተነሳሽነት አስተዋጽዖ ለማበርከት በሚፈልጉት ጉዳይ ላይ የሚሰሩበት፤ ወይም መፍታት የሚፈልጉበትን ማኅበራዊ ችግር ለመጋፈጥ ጊዜያቸውንና ትኩረታቸውን አሳልፈው ለበጎነት የሚሰጡበት ሂደት ነው።

የመደመር ትውልድ ሀገራዊ አገልግሎትን እንደ ግዴታውና ኃላፊነቱ የሚቆጥር፤ ከሀገር ፍቅር በመነጨ ትጋት ታታሪነት፤ በስፋትና በጥራት ሀገሩን የሚያገለግል ትውልድ ነው። በግልም ሁን በተደራጀ መልኩ የማኅበረሰቡን ችግሮች የሚፈታ፤ በሚሰራው ስራ ሁሉ ማኅበረሰቡ አለመጎዳቱን የሚያረጋግጥና፤ ለሕልውናው መሰረት የሆነውን ማኅበረሰብ ዝቅ ብሎ በማገልገል ማህበራዊ ኃላፊነቱን የሚወጣ ትውልድ ነው። የተለያዩ የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎቶችን የሚፈጥር፤ ሃብትን አሰባስቦ የማኅበራዊ ችግሮችን የሚጋፈጥ፤ የሌሎችን ችግር እንደራሱ አድርጎ የሚቀጥር፤ የአረጋውያንና የሕፃናት መራብና መጠማትን አምርሮ የሚታገል፤ ጧሪ ቀባሪ የሆነ ትውልድ ነው።

# አስኳለ እና አስኳል

የጽሑፍ መጀመር በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ትልቁን ለውጥ ያመጣ አብዮት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ጽሑፍ የሰው ልጆች ሐሳቦቻቸውን፤ ታሪካቸውን፣ ሥርዓታቸውን፣ እምነታቸውን፣ ሕጎቻቸውንና ሁሉ ነገራቸውን ለቀጣይ ትውልድ እንዲያስተላልፍፉ አስችሏቸዋል፡፡ ቀጣዩም ትውልድ ትናንት የነበሩ ሐሳቦችን፣ ምልከታዎችንና ክስተቶችን በመገንዘብ፤ ከዛሬ ጋር ራሱን እንዲያነጻጽር፤ እንዲሁም ስለ ነገ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ግምት እንዲኖረው ረድቶታል፡፡ የጽሑፍ መጀመሪያ በአንድ ትውልድ አባላትና በትውልዶች መካከል የተፈጠረ መግባባት እና መማማር፤ በሂደት በትምህርት መስፋፋት ጎልቶ፤ ብዙ ለውጦችን አስከትሏል፡፡

ጽሑፍ ሐሳቦችና መረጃዎች ሳይበረዙና ሳይጠፉ ዘመናትን ተሻግረው ሰዎች እንዲቀስሟቸው ማድረግ ዐቅም አለው፡፤ በመሆኑም የጽሑፍ መጀመር ከትውል ወደ ትውልድ ዕውቀትን ለማሸጋገር ዕድል ሰጥቷል፡፡ የመማር ዕድል እንዲሰፉ አድርጓል፡፡ መማማር ዕውቀት መቅሰም እና አዳዲስ ልማዶችን ማዳበር የሂይወት ዘመን ሂደት ነው፡፡ ሰዎች በየትኛውም ዘመን ተምረዋል፤ ዕውቀት ቀስመዋል አዲስ ልምድ አዳብረዋል፡፡ ዘመናዊ ትምርት እነዚህ በየዘመናቱ በጽሑፍ እና በተለያየ ዓይነት መንገድ የተከማቹ ዕውቀቶች፤ ወጥነት ባለው መልኩ ተቀርጸውና ተከትበው፤ ትውልድን የሚሰሩበት መንገድ ነው፡፡

ትምህር በዕውቀት፣ በክህሎት እና በእሴት ትውልድን ይወልዳል፡፡ ትውልድ አስኳል ነው፡፡ በትምህርት ውስጥ ጠንክሮና አድጎ ይወለዳል፤ ወይም በትመምህርት ውስጥ ቀጭጮና በስብሶ ይሞታል፡፡ አስኳል በሀገርችን ትውልድ የማዋለድ አደራን ተረክቦ የተመሰረተና የተስፋፋ ዘመናዊ ትምህርት ነው፡፡ ትውልድ፡ የሀገር አስኳል፡ ጫጩት ሆኖ እንዲፈለፈል፤ ከዕንቁላልነት ነፍስ ወዳለው ጫጩትነት የተቀየረ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ፣ ዘመናዊነትን እንዲቀስም፤ በቀሰመውም ሀገር እንዲለወጥ የሚያደርግ ነው፡፡

ትምግርት የባህሪይን ለውጥ በማምጣት፤ የገበሬውን ሞፈርና ቀንበር የሚቀይር፤ ልዩነትን ማቀራረብ የሚችል፤ የሚታመመውን ሕዝብ ጤናን የሚጠብቅ፤ መንገዶችን የሚሰራ፤ ደሳሳ ገጎጆውን ወደ ምቹ መኖሪያ የሚቀይር፤ በፈጠራ የተካነ አዳዲስ ሐሳቦችን የሚያፈልቅ፤ ችግር ፈቺ ትውልድ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲፈጠር የሚያደርግ ነው፡፡

በሀገራችን ``ችግር ፈቺ ትውል`` የሚለው ሐረግ ተደጋግሞ የሚነሳና ኢትዮጵያ የምትናፍቀው ሕልም ነው፡፡ ይኽንን ትውለድ መፍጠር፤ ከትምህርት ዋነኛ ዓላመዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ትምህር የሰው ልጆች ዕውቀትን፣ ክህሎትን፣ ሐሳቦችና እሴቶችን በመተዋወቅና በመቅሰም የባህሪ ለውጥ የሚያመጡበት መንገድ ነው፡፡ እንዲሁም ያላቸውን ዕውቀት ተጠቅመው በሰው ልጆችና በሀገር ዕድገትና ለውጥ ሂደት ውስጥ፤ አስተዋጽዖ የሚያበረክቱበት ሁነኛ መሳሪያ ነው፡፤ ከልጅነት ጀምሮ በሚቀሰሙ ዕውቀቶችና ልምዶች፤ እንዲሁም እሱን ተከትለው በሚመጡ የባህሪ ለውጦች፤ አዳዲስ ነገሮችን ማድረግና መፍጠር፤ እንዲሁም ከአካባቢ ተስማምቶና አካባቢን ተቆጣጥሮ መኖር የሚያስችል ዐቅም ይገኛል፡፡

ሃገርን ለመገንባት እና ለውጥ ለማምጣት፤ ከትምዕር በላይ ዐቅም ሊሰጥ የሚችል የሰው ልጆች መሳሪያ

የለም። ትምህርት ትናንትን ለማስታወስ፣ ዛሬን ለመገንዘብ እና ነገን ለመመልከት የሚያስችል ዐቅም ይሰጣል። በሀገር ግንባታ ሂደትም ፤ የትናንት ስሕተቶችንና ወረቶችን አስታውሶ የጋራ ትውስታ መፍጠር፤ የዛሬ ጥንካሬዎችንና ድክመቶችን፤ የነገ ተስፋና ሥጋቶችን በማስገንዘብ፤ የጋራ ትልምን የመፍጠር ዐቅም አለው። ሀገር መምሰል የምትፈልገውን እና ማምጣት የምትፈልገውን ለውጥ ለመፍጠር፤ ከልጅነት ዕድሜ ጀመሮ የሚከተብ ትምህር፤ ከሁሉም የገዘፈ አስተዋፅዖ አለው።

በሃገራች ዘመናዊ ትምህርት መስፋፋትን ተከትሎ፤ የትምህርት ሥርዓቱ የተለያዩ ግቦችን አንግቦ፤ ለሀገር ግንባታ ሂደቱ አስተዋጽዖ እንዲያደርግና በየዘመናቱ የነበረውን ትውልድ እንዲቀርጽ ጥረቶች ተደርገዋል። በሀገራችን ከሃይማኖታዊ የትምህርት ሥርዓት እስከ ዘመናዊ ትምህርት ያሉት ሁሉ፤ በየዘመኑ በነበሩት ትውልዶች ጠባይ ላይ ተፅዕኖ አሳርፈዋል።

በሃገራችን ቀዳሚ የሆኑ አብርሃማዊ ሃይማኖቶች፤ ኢትዮጵያውያን በዚህ መልክ እንዲያስቡ ባህሪያቸውን ከሃይማኖቶቹ ጋር አስተካክለው ለአስተምህሮዎቹ መርሖች ተገዥ እንዲሆኑ አድርገዋቸዋል። ስለ ሀገርና ስለ መሪዎቻቸው ባለው እሳቤ፤ መሪዎቻቸውን ከሰማይ የተቀቡ አድርገው የሚመለከቱ ናቸው። ዘግይቶ በሀገራችን የተጀመረውን ዘመናዊ ትምህርት እንደዚሁ በየትውልዱ ባህሪይ ላይ ለውጥ አምጥቷል። ስለ ዓለም፣ ስለ ተፈጥሮ፣ ስለ ሀገር እና ስለ መሪዎቻቸውን ያለንን ምልከታ ለውጧል።

ዘመናዊ ትምህርት በሀገራችን ሲጀመር፤ እንዲሁም ኢትዮጵያውያን በውጭ ሀገር ዕውቀትን ቀስመው ወደ ሀገር ሲመለሱ፤ ዋነኛው ፍላጎት ኢትዮጵያን የማዘመን ትልም ነው። በዚህም በመጀመሪያዎቹ ትምህርት በተስፋፋባቸው ወቅቶች፤ የውጭ ቋንቋዎችን ማወቅና መናገር፣ የውጭ ሀገር አለባበስን መልበስ፣ ሀገር በቀል የሆኑ ነገሮችን መናቅና መተቸት፣ የመማር ምልክት ተደርጎ ይወሰድ ነበር የውጭ እውቀቶችን የቀሰመውና ልምዶቻቸውን ተካፍሎ የመጣው ቀደምት የተማረው ትውልድ፤ ካገኛቸው ልምዶችና ዕውቀቶች በመነሳት፤ ኢትዮጵን ያዘምናሉ ያላቸውን መንገዶች አቅርቧል።

``ኢትዮጵያ እንዴት ትዘምን?`` የሚል ጥያቄ በተማረው ዘመን ተጭሯል። በተማረበት መሥመር መፍትሔ ለማጣት ጥረቶች አድጓል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በውጭ ትምህርት ቀስሞ የተመለሰው ወግ አጥባቂው ትውልድ፤ የጃፓንን ታሪክ አንብቦና ቀስሞ ሀገሩን የጃፓን ዓይነት ለውጥ እንድታመጣ ጥረት አድግጓል። በሌላ በኩል ሕልመኛው ትውልድ ኢትዮጵያን የማዘመን ምልከታው ከሞላ ጎደል በማርክሲዝም ሌኒንዝም ርዕዮት የተቃኘ ነበር።

የዩኒቨርሲቲዮችን መስፋፋት ተከትሎ የተፈጠረው ዘመናዊ ልሂቅ፤ ኢትዮጵያን በአዲስ መልክ ለመረዳት በመሞከር፤ አዳዲስ ትርጓሜ እንዲኖራት አድግጓል። የራሱን የዘመናዊነት ጥያቄዎችን ይዞም ብቅ ብሏል። በዋናነት ``የመሬት ባለቤትነት``፤ የማንነት መከበርና እኩልነት`` እና ``ዴሞክራሲያዊ መብት`` የሚሉ ጉዳዮችን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የፊት ለፊት አጀንዳ በመሆን፤ ሀገር መንግስት ግንባታ ሂደትን አቅጣጫ ያስቀየረ ሐሳብ ሆኖ እስካሁን ድረስ ዘልቋል።

በየዘመናቱ የተፈጠረው የትምህር መስፋፋት በየትውልዱ ውስጥ ተፅዕኖ አሳድሯል። የተለየ ባህሪይ በየትውልዱ ውስጥ ለመፍጠርም ችሏል። ከጊዜ ወደ ጊዜ የተፈጠረው የትምህር መስፋፋት፤ ብዙኃኑን ሕዝብ ማንበብና መጻፍ እንዲችል ቢያደርግም፤ የትምህርት ጥራት በመዳከሙ ``አይመለከተኝም`` የሚል ትውልድ አፍርቷል፤ ሀገር አዳክሟል። ስርቆትን፤ ሀገር ፍቅር ስሜቱ የመነመነ እና በሀገር ጉዳይ ላይ ባይተዋር የሆነ ትውልድ በመፍጠር፤ ኢትዮጵያ አደጋ ውስጥ ከትቷል። አሁን ላይ የተፈጠሩ ችግሮች ባለፉት ዓመታት የታየው የትምህር ጥራት ችግር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠያቂ ይሆናል።

በትምህርት ስርዓቱ ላይ ጥያቄ መነሳት የጀመረው ኢትዮጵያ ውስጥ የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት ከጀመረበት ጊዜ ነው። ዘመናዊ ትምህርት ኢትዮጵያ ውስጥ ሲጀምር እና ሲስፋፋ፤ የቀደመውን ሀገር በቀል ትምህር የሚተካ ተደርጎ የቀረበ እንጂ፤ ከሀገር በቀል ትምህርት ጋር ተሰናስሎ የቀረበ አይደለም። ነባሩን ሀገር በቀል ዕውቀትና የዕውቀት ማግኛ መንገድ ወደ ጎን በመተው፤ ከአውሮፓ የተኮረጀው ብቻውን እንዲስፋፋ ተደርጓል።

ዘመናዊ ትምህርት ከነባሩ ተፋትቶ መጀመሩ ሶስት ችግሮችን አመጣ። በትምህርትና በዕውቀት ዘርፍ ከዚያ በፊት የተሰራውን ሀሉሉ እንዳልተሰራ ቆጠረው። ከመሰረቱ የተነቀለ፤ ሀገሩን የሚያውቅ ትውልድ ተፈጠረ። በአውሮፓ ነባራዊ ሁኔታ የተቃኘ፤ ለአውሮፓውያን የተቀረፀን ዕውቀት የሚያነበንብ ትውልድ ተፈጠረ። ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን ያላገናዘበ በመሆኑ፤ የኢትዮጵያን ችግር በአውሮፓ መነጽር በመመልት ለብዙ ችግሮች መፈጠር ምክንያት ሆኗል።

ይኽ ዘመናዊ ትምህርት ያመጣውን አሉታዊ ለውጥ በመጥቀስ የመታረሚያ ሐሳብ ያቀረቡ ሁለት ዓይነት ሊቃውንት መጥተዋል። የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያ መማር ያለባት ሀገር በቀሉን ዕውቀት ነው የሚሉ ናቸው። በአውሮፓ ነባራዊ ሁኔታ ለአውሮፓውያን የተቀረጸን ትምህርት ሳይሆን፤ ሀገር በቀሉን ዕውቀትና ክህሎት መማር፤ የሀገራችንን ችግር ይፈታል ይላሉ። ይኽን ሐሳብ የሚሰነዝሩ አጥኚዎች የዕውቀትን አካባቢያዊነት በመጥቀስ፤ ለማህበረሰቡ ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው፤ ማኅበረሰቡን በመገንዘብ የተቃኘው ሀገር በቀሉ ትምህር እንደሆነ ይናገራሉ።

ሁለተኛዎቹ ደግሞ ሀገር በቀሉን ዕውቀት ከአውሮፓዊው ዕውቀት አዛምደን ማስተማር አለብን የሚሉ ናቸው። እነዚህ ሊቃውንት የዕውቀትን አንድነት በመጥቀስ፤ እንዲሁም ዝመናን ለማምጣት ከኛ ቀድመው የዘመኑ ሃገራትን መንገድና እሳቤ መከተል እንዳለብን በመግለጽ፤ ከባህላዊ ትምህርት የሚያስፈልገንን ወስደን፤ ከዘመናዊው የአውሮፓ ትምህርት የሚያስፈልገንን መርጠን፤ አዛምደን መማር አለብን የሚሉ ናቸው።

ሀገር በቀል ዕውቀትን ያገለለው እና ከሀገሪቱ፤ ማኅበረሰብ እና ኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር ያልተገናዘበው ዘመናዊ ትምህር፤ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ብዙም ቦታ የማይሰጠው ሀገር በቀል ትምህርት ክፍተት ያለባቸው ናቸው። ዘመናዊ ትምህርት ሀገር በቀሉን ተክቶ ለበርካታ ዓመታት በተግባር ላይ ውሏል፤ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጎኖቹንም ባለፉት ትውልዶች በሚገባ አይተናቸዋል። በመሆኑም የትምህር ተሐድሶን ለማምጣት ነገሩን በሚዛን መመልከት ያስፈልገናል። ሀገርን እና ሀገራዊ እሳቤን በቅጡ የሚረዳና የሚገነዘብ፤ ያለውን ሠፍሮና

ቆጥሮ የሚያውቅ፤ የሌለውን ከሌሎች አዛምዶ የሚቀበል፤ በኢትዮጵያ መልክና ቃና የተቃኘ ዘመናዊ ትምህርት አዋጪውና ለውጥ አምጪው አካሄድ ነው፡፡

የትምህርት ስርዓታችን ትውልድን መቅረጽና ለሀገራዊ ችግሮች መፍትሄ ማምጣት የሚችል መሆን አለበት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዓለም ከደረሰበት ደረጃ መድረስ የሚያስችል ዕውቀትን፤ ክህሎትንና እሴትን ሊያስጨብጡን ይገባል፡፡ በመሆኑም የመደመር ትውልድ በኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣ በሀገር ፍቅር በወንድማማችነት፣ በሥነ ውበት፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በዓለም አቀፋዊ እሴቶችና ክህሎቶች የተቃኘ እንዲሆን፤ የትምህርት ስርዓቱ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ ይኸም እንዲሳካ ሀገራዊውን ነገር ዕውቀት፤ ክህሎትና ጥበብ፤ ከዓለም አቀፋዊው ዕውቀትና ክህሎት ጋር ማስተሳሰር ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም ባለፈ ባለፉት ዓመታት ጉልህ ጉድፍ ሆኖ የታየው የትምህርት ጥራት ችግር መታረም አለበት፡፡

የትምህርት ጥራት ሲባል የትምህርት ግብን ለመምታት የሚችል ዕውቀትንና ክህሎትን በሰው ልጆች ውስጥ የሚሰረጽ ዐቅም ነው፡፡ ትምህርት ጥራቱ ሲጓደል፤ አንድም የሚሰጠው ትምህርት የባህርይ ለውጥ የማምጣት ዐቅም አይኖረውም ወይም ይዳከማል፡፡ ሌላም የሚማረው ተማሪም በትምህርት የማይለወጥና የተማረውን ተግባራዊ ማድረግ የማይችል ይሆናል፡፡

የትምህርት ጥራት ሲጓደል መካኒክነት ተምሮ የቴክኒክ ነገሮችን የማያውቅ፤ ሕክምና ተምሮ በትክክል ማከም የማይችል፤ ኢኮኖሚን ተምሮ የኢኮኖሚ ሥርዓቱን ለመረዳት የሚቸግረው፤ ለመሠረታዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ባዕድ የሆነ፤ የራሱን ሕይወት ከተማረ ሰው ጠባይ በተቃራኒው የሚኖር፤ ማኅበረሰቡን ለመቀየር ምንም ዓይነት ዓቅምም ጥረትም የሌለው፤ ራሱን ቤቱንና አካባቢውን ለማሻሻል የማይነሳ “የተማረ ሰው” ይፈጥራል፡፡ መሰረታዊ የስነ ምግባር ክፍተት ያለበት፤ ማመዛዘንና አመክንዮ ከሐሳቦቹ የጎደሉ፤ ጥናትና ምርምር ባህሉ ያልሆነ ትውልድ መፍጠር፤ የትምህር ጥራት መጓደል ውጤቶች ናቸው፡፡

የትምህርት ጥራት መለኪያዎች የሚባሉ ስድስት ነገሮች አሉ፤ መምህራን የትምህቱ ይዘት፣ የትምህርት ስነ ዘዴ፣ የማመሪያ አካባቢው፣ የትምህር ቤት አመራሩ፣ የቅበላ ሥርዓቱ እና የትምህርት በጀትና አደረጃጀቱ ናቸው፡፡ ይዘት ማለት በየትምህር ደረጃው ተማሪዎች መማር ያለባቸው የትምህርት ዓይነቶችን፤ በዓይነቶቹ ውስጥ የሚካተቱትን ነገሮች፤ እንዲሁም በመማሪያ መጻሕፍትና በተዘጋጁ የትምህርት ሞጁሎች የሰፈረው ሐሳብ ነው፡፡ የሰፈሩት ሐሳቦች ተማሪዎች ተገቢውን ዕውቀትና ክህሎት በትክክለኛው ዕድሜ እንዲጨብጡ የማድረግ ዐቅድ አላቸው ወይ? የሚለው የትምህርት ጥራትን ይወስናል፡፡

የሰፈረውን ይዘት ተማሪዎች በሚገባ ተረድተው በዕውቀት፣ በክህሎት እና በእሴት እንዲዳብሩ የሚያደርጉት መምህራንና የማስተማሪያ ዘዴዎቻቸው ናቸው፡፡ መምህራን በየትምህርት ደረጃው እና በየዕድሜ ክልሉ ተማሪዎች በአግባቡ ትምህርት እንዲቀስሙ ለማድረግ የዕውቀት ደረጃቸው ከፍ ያለ፤ የማስተማር ክህሎታቸውና ዘዴዎቻቸው የላቁ፤ እንዲሁም በስነ ምግባር ታንጾ ለተማሪዎች አርአያ የሚሆኑ መሆን አለባቸው፡፡ የትምህርት ስነ ዘዴ ማለት መምህራን እንዲያስተምሩ፤ ተማሪዎችም እንዲማሩ የሚያስችላቸው የትምህርት መርሕ፣ ሥርዓት ትምህርቶችና ስልቶች (የአመራር ስትራቴጂዎች) ናቸው፡፡ የትምህርት ሥነ ዘዴ

የሚወሰነው በትምህርት ዓላማዎች፤ በምንከተለው የትምህርት ፍልስፍና፣ በትምህርት ክፍሉ የብዝሃንነት ጠባይ፣ በትምህርት ዓነቱና በትምህርት ቤቱ ተልዕኮ ነው፡፡ ለዚህ መሳካት ደግሞ ከመምህራን ክህሎት እና ዕውቅ በተጨማሪ፤ የትምህርት ማዕከላት የትምህርት መርጃና የተግባር ሙከራ መሳሪያዎች መሟላት አለባቸው፡፡

ለትምህርት ጥራት ተማሪዎች የሚማሩበት ከባቢ ወሳኝ ነው፡፡ የትምህርት ከባቢ ሲባል የትምህርት ክፍሉ ምቾትና ጥራት፤ የትምህርት አካባቢው ሰላምና ተስማሚነት፤ በትምህርት አካባቢው ተማሪው የሚኖሩት እንቅስቃሴዎችና ሥራዎች፤ የስራና የትምህርት ባህሉ፤ እና የመሳሰሉትን የሚመለከት ነው፡፡ የትምህርት ከባቢ የተማሪውን የመማር ተነሳሽነት፤ በትምህርት ላይ የሚያሳልፈውን የጊዜ መጠን፤ ተሳትፎ፤ የምዘና ውጤቱንና ባህሪውን የሚወስን ነው፡፡

በሀገራችን መፍታት ከሚገቡን ችግሮች አንዱ ትምህርት ቤቶቻችን፤ ቢያንስ ዝቅተኛውን የትህርት ቤት መመዘኛ መስፈርትን እንዲሟሉ ማድረግ፡፡ በዳስና በዛፍ ስር በፈራረሱ ግድግዳዎችና በሚያፈሱ ጣሪያዎች፤ መቀመጫና ሰሌዳ በተሰባበረባቸው ክፍሎች የሚማሩ ተማሪዎች እስካሉን ድረስ፤ የትምህርት ጥራትን እናሳካም፡፡ ትምህርት ቤቶቻን ቢያንስ ዝቅተኛውን የአንድ ትምህርት ቤት መመዘኛ እንዲያሟላ ማድረግ፤ የመደመር ትውልድን የመፍጠር ጥረት የመጀመሪያው ተግባራችን መሆን አለበት፡፡

መምህራን፤ የትምህርት ይዘት የትምህርት ሥነ ዘዴና የመማሪያ ከባቢ ተቀናጅተው የትምህርት ጥራት እንዲያመጡ፤ የትምህርት አመራር ብቃት አስፈላጊ ነው፡፡ የትምህርት ቤት አመራር ማለት መምህራንን፣ የትምህርት ይዘትን፣ ሥነ ዘዴን፣ ተማሪዎችን፣ ትምህርት ቤትንና ወላጆችን አቀናጅቶ፤ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ትምህርትን የሚማር አካል ነው፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚታቀዱት ትምህርትን የሚመለከቱ ነገሮች ሁሉ ፍሬ የሚያፈሩት፤ ጥራት ያው የትምህርት ቤት አመራር ካፈራን ብቻ ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ በትክክል እየተመራ መሆኑን፤ ብሔራዊ ዕቅድና መመሪያ እየተተገበረ መሆኑን፤ የትምህርት ቤት ዕለታዊ ተግባር በሚገባ መቀናጀቱን፣ ነገሮች፣ ተማሪዎች፣ የአካባቢው ሰላምና ምቹነት መሟላቱን የሚያረጋግጠውና እንዲሳካም የሚያደርገው የትምህርት ቤት አመራር ነው፡፡

የትምህርት ቅበላ ለትምህርት ጥራት መፈጠር ሌላው ወሳኝ ነገር ነው፡፡ ምን ዓይነት ተማሪዎችን ነው የተቀበልነው? እንዴት ነው የምንቀበለው? ተማሪዊች የሚመጡበት ዳራ ምን ምን ይመስላል ከየትኛው የማህበረሰብ ክፍል ይመጣሉ? ምን ዓይነት ተግዳሮት አልፈው ይመጣሉ? ምን ዓይነት ድጋፍ ይፈልጋሉ? በቂ ምግብ ያገኛሉ? የትምህርት መሳሪያዎችን ለማሟላት ይችላሉ? በቤት ውስጥ የስራ ጫና አለባቸው ከትምህርት ቤትና በአካባቢያቸው መካከል የቋንቋ ልዩነት አለ? የመኖሪያ አካባቢያቸው ከትምህርት ቤቱ ምን ያህል ይርቃል? የእነዚህ ጥያቄዎች መልሶች በተማሮዎች የትምህርት አቀባበል ላይ እጅግ ወሳኝ ነገሮች ናቸው፡፡

ትምህርት ቤቶቻችን የሚቀበሏቸውን ተማሪዎች ማንነት ዐውቀው፤ ልዩነቶችን ለማጣጣም የሚያስችል ሥራ እንዲሰሩ ማድረግ አለብን፡፡ የተማሪዎች ምገባና ለተማሪዎች የትምህርት መሳሪያዎችን ማሟላት እንደ

ኢትዮጵያ ያሉ ሀገሮች ቅንጦት አይደለም። ትምህርት የሚያቋርጡ ተማሪዎችን በእጅጉ የሚቀንስ ነው። ትምህርትን ለማኅብረተሰቡ በአቅራቢያቸው ለማዳረስ የምናደርገው ጥረት፤ ተማሪዎች ረዥም ርቀት ተጉዘው ከመምጣት የሚታደጋቸው ብቻ ሳይሆን፤ ትምህርትን በድካም መንፈስ እንዳይቀበሉ የሚያደርጋቸውም ነው።

የትምህርት በጀትና አደረጃጀቱ ስንል፤ በብሔራዊ ደረጃ ለትምህርት የሚሰጠው በጀትና፤ በአጠቀላይ የትምህርት ሥርዓቱ የተደራጀበት መንገድ ማለታችን ነው። ይኽ ነገር በአመዛኙ የፌደራል መንግስት የሚመለከት ነው። የመደመርን ትውልድ ለመፍጠር እንድንችል መፍታት ከሚገቡን ነገሮች አንዱ ለትምህርት ሥርዓቱ በቂ የሆነ በጀት መመደብ ማቻል ነው። በቂ በጀት ከመመደብ ጋር አብሮ የሚያያዘውም የተመደበውን በጀት በቁጠባ መጠቀምና፤ አካባቢያዊ ዕድሎችን ለመፍጠር መቻል ነው። ማኅበረሰቡ በትምህርት ቤት ግንባታዎች እንዲሳተፍ ማድረግ። በተለያዩ አካባቢዎች በሚኖሩ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ጊዜ የሚሰሩ የመኖሪያ ካምፖች በጥራት ቀድመው ተሠርተው ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ትምህርት ቤቶች እንዲሆኑ ማድረግ፣ ተቋማት በማኅበራዊ ኃላፊነት ትምህርት ቤቶችን እንዲገነቡና እንዲያሟሉ ማትጋት ይጠበቅብናል።

ከትምህርት ሚኒስቴር ጀምሮ እስከ ትህርት ቤቶች ድረስ መዋቀሮች፤ በተገቢ ባለሙያዎች እንዲያዙ ማድረግ አለብን። ትምህርት ቤቶች ሲከፈቱ በተገቢው መመዘኛ እንዲያልፉ፤ በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግባቸው፤ የመምህራን ማሰልጠኛዎች ብቁ ባለሙያዎችን እንዲያፈሩ፤ የመምህራን መብቶችና ጥቅሞች እንዲከበሩ፤ በየጊዜው የትምህርት ጥራት መመዘኛዎች እየተካሄዱ ማስተካከያዎች እንዲደረጉ ማስቻል፤ ለትምህርት ጥራት እጅግ ወሳኝ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

በዚህ አኳያ በሀገራችን የነበረውን የትምህርት ጥራት ስንመዝነው በብዙ መመዘኛ ዝቅ ያለ ሆኖ ይገኛል። የጥራት ችግር አሁን ላይ ለሚታዩት የትውልድ ግራ መጋባትና ለሀገራዊ መናጋት፤ አንዱ ተጠቃሽ ምክንያት ነው። የትምህርት ጥራት የሚለካው በፈጠረው ዜጋና ትውልድ ነውና። በትውልዱ ላይ የሚታየው የመግባባት ችግር፤ የሞራል እሴቶች መዛባት፤ እንዲሁም ለሀገራዊ ችግሮች ያለው የመፍትሔ ዐቅም መዳከም፤ የጥራት ችግሩ መገለጫ ናቸው።

ዋነኛው የትምህርት ጥራት ችግር ዘርፉን እና ሙያውያን ካለማክበርና፤ ቁጥር ላይ ብቻ መሰረት ካደረገ አካሄድ የመነጨ ነው። ይኽም ብቁ የሆነ ዜጋ በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ ክፍተት እንዲፈጠር አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪ ለትምህርት ጥራት ችግር አንዱ ምክንያት ተደርጎ የሚጠቀሰው፤ አካዳሚያዊ ነጻነት መጣሱና መገደቡ ነው። ዩኒቨርሲቲዎችና የትምህርት ማዕከላት በነጻነት እውቀትና ክህሎት የሚበለጽግባቸው ሳይሆኑ፤ የፓርቲ ግብ ማስፈጸሚያ አንድ ክንፍ ተደርጓል። በዚህም የተነሳ በነጻነት የማሰላሰል እና ዕውቀት የማፍራት መብታቸው ተገድቧል። ይኽም በትምህርት አማካኝነት መሳካት የሚገባቸው ግቦች እንዲኳደሉ አድርጓል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተኳደለ የመጣው አካዳሚያዊ ነጻነትን ከአካዳሚያዊ ነጻነት እና እየበዛ የሄደው ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት፤ በትምህርት ሥርዓቱ ከታዩ ጉዳዮች መካከል የሚመደብ ነው፣፤ በመሆኑም በትምህርት ተሐድሶ አካዳሚያዊ ነጻነት እንዲረጋገጥ በማስቻል፤ ነጻነቱንና ኃላፊነቱን በሚዛን የሚረዳ ከፍተኛ የትምህርት

ተቋም መፍጠር ይገባል፡፡

በአካዳሚው አካባቢ አካዳሚያዊ ነጻነትን ከአካዳሚያዊ ነጻ ሀገር ጋር አምታትቶ፤ የመመልከት ዝንባሌ መኖሩ አይካድም፡፡ የትምህርት ማዕከላት እና አካዳሚውያን ዕውቀትን የማበልጸግና የማሳደግ ነፃነት ቢኖራቸውም፤ ከተቀረው ሕዝብ የተነጠሉ ነፃ ሀገራት ግን አይደሉም፡፡ የትምህርት ማዕከላት ከኅብረተሰቡ ተነጥለው፤ ዕውቀትን ለዕውቀት ግብ እና፤ ለምሁራዊ ፍጹማዊነት ብቻ የሚሰሩ አይደሉም፡፡ ከኅብረተሰቡና ከባለ ድርሻ አካላት፤ በዋናነትም ከምንግስተ ጋር በትምህርት ዓላማና በብሔራዊ ጥቅም ጉዳዮች ተሰናስለው፤ ችግር ፈቺ ሐሳቦችን የሚያበረክቱ መሆን አለባቸው፡፡

ከመንግስት ጋር በመሰናሰል የኅብረተሰቡን ፍላጎት ተንተርሰን ይስሩ ሲባል፤ ተቋማቱን ተለጣፊ ሆነው አካዳሚያዊ ነጻነት እንዳይፋለስ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አካዳሚዎች ነጻ ሀገራት እንደሆኑ አድረጎ መገንዘብም ሆነ፤ አካዳሚዎች ከሌሎች ባለ ድርሻ ጋር ተጣጥመው የፖሊሲ ፍላጎት ብቻ ለማሳካት የተቋቋመ ተቋማት እንደሆኑ መመልከት፤ መሰረታዊ ችግሮች ናቸው፡፡ ወደ አንድ ጎን ብቻ ያዘመኑ ከሆኑ ሙሉውን የትምህርት ግብ ለማሳካት ይቸግራቸዋል፡፡ ምሁራዊ ፍጹምነትን ብቻ ማዕከል ያደረጉ ከሆኑ፤ የኢትዮጵያንን ፍላጎት ማሟላት የማይችሉ እና ማኅበረሰባዊ ዕድገትና ለውጥን እውን ማያደርጉ ይሆናሉ፡፡ በሌላ በኩል የኅብረተሰብን ፍላጎት ለማሳካት ብቻ የሚሰሩ፤ ይኽንንም ተከትሎ በተቀመጠ አቅጣጫ ላይ ብቻ የሚጓዙ ከሆነ ደግሞ፤ የሰው ልጆችን የማሰላሰል ነጻነት እና የዕውቀት ዕድገትን የሚገድብ ይሆናል፡፡

ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶችን ለማሳካት በሚያስችል መልኩ፤ ትምህርትን በጥንቃቄ ገቢያ መር በሆነ መንገድ መምራት፤ አንዱ ልናበረታታው የሚገባ ነው፡፡ የምሥራቅ እስያ ሀገሮች የትምህርት ሥርዓታቸው በሳይንስና ቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት እንዲያደርግ በማስቻል፤ ለሚፈልጉት ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ቁልፍ መሰረት እንዲሆን ያደረጉት በዚሁ መንገድ መተግበር ይገባል፡፡ በተለወጠ ዓላማዊና ሀገራዊ ሁኔታ ውስጥ ተወዳዳሪ ሆኖ የሚወጣ ትውልድ ለመፍጠር፤ ኢኮኖሚውን መሰረት ያደረጉ ዕውቀት እና ክህሎቶችን የሚያመርት የትምህርት ሥርዓት ዝርጋታ ያስፈልጋል፡፡

በቅርብ ዓመታት ሰባ በመቶ ለተፈጥሮ ሳይንስ፤ ሰላሳ በመቶ ለማህበራዊ ሳይንስ የሚል መርሕ ተጀምሮ ነበር፡፡ ይኽ መርሕ ትኩረቱን ያደረገው ኢኮኖሚያዊ ሁኔዎችን መሰረት አድርጎ ነው ቢባልም፤ ከብዙ ክፍተቶች የጸዳ አይደለም፡፡ የሳንስና ቴክኖሎጂ አስፈላጊነት አያጠራጥርም፡፡ ነገር ግን አካሄዱ ማኅበራዊ ሳይንስ ለሃገር እድገት ያለውን አበርክቶ በእጅጉ የዘነጋ ነው፡፡ ከዚህም በላይ የሳይንስና የቴክኖለፐጂ ትምህርት የሚያስፈልገው ከፍተኛ በጀት፤ የሰው ኃይልና የትምህርት መርጃ መሳሪያ ሳያሟላ ለመተግበር የተነሳም ነው፡፡ ትምህርቱም ተግባር ያልተደገፈና ብዙዎቹ ተመርቀው እንዲቀመጡ የተገደዱበት መሆኑ፤ እውን ፖሊሲው ከኢኮኖሚው ጋር በሚገባ የተቀናጀ ነበር? የሚል ጥያቄን ያስነሳል፡፡

በመሆኑም የመደመር ትውለድን ለመቅረጽ መሠረቱ የሚጣለው፤ ክፍተቶች ያሉበትን የትምህርት ሥርዓት በማደስ ላይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውብ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የበለጸገች አሰላሳይ ሊቃውንት የበዙባት፣ የሀሳብ

ልዕልና ወሳኝ ቦታ የሚይዝባት፣ ጥናትና ምርምር ባህል የሆነባት፣ እንዲሁም እውነተኛ ነጻነቷን ማስከበር የምትችል ሀገር እንድትሆን፤ የትምህርት ሥርዓቱ ላይ ያሉበትን ችግሮች ማረም ቀዳሚው ተግባር ነው። የትምህርት ሥርዓቱን ማረም የመንግስትን ትልቅ ሥራ የሚጠይቅ ቢሆንም የግሉ ዘርፍም በኋላፊነት ስሜት በመንቀሳቀስ ወሳኝ ሚናን ይጫወታል።

የትምህርት ተሃድሶ አካታችና ሁለንተናዊ የሆነ የትምህርት ዓላማ በሚዛን ያነገበ ሊሆም ይገባል። የተትምህር ሥርዓቱን ሀገራዊ ዓላማ ሊያሳካ በሚችል መልኩ መቀረጽ አለበት። ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታን ከግምት በማስገባት፤ የትውልድ ለውጥን በማጣጣም፤ ሀገራዊ ዕድገት እና ብልጽግናን ለማምጣት በሚያስችል መልኩ፤ የትምህርት ሥርዓቱን ሊታደስ ይገባል። በዚህም ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን የሚያደንቅ እና የሚያከብር፤ በራሱ የሚተማመን እና ሀገራዊ ኩራት የሚሰማው፤ ለሀገሩ ኩራት የሚሆን፤ በዕውቀት የታነጸ ፤ ሙያዊ ብቃት ያለው፤ በዓለም አቀፍ ገቢያ ተወዳዳሪ የሆነና በመልካም ሥነ ምግባት የታነጸ፤ የወንድማማችነት እሴትን ሥልጠና፣ የትምህርት ከባቢ፣ የተማሪ ቅበላ የትምህርት አስተዳደርና በጀት የትምህርት ቤት አመራር የስራ ዘዴዎች ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል።

ባለንበት ዘመን በቀደመው መደበኛ ትምህረት ይዘት እና ንድፈ ሐሳብ ላይ ብቻ የተመሠረት ሥነ ዘዴ መከተል፤ ትውልድን በሥነ ምግባር የታነጸ፤ ምክንያታዊ፣ ተወዳዳሪና ችግር ፈቺ አያደርገውም። በመሆኑም የሥነ ምግባር የትምህርቶች እና የ21ኛው መክዘ የማወቅ፣ የመከወንና የመኖር ክህሎቶችን በማስተማር ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን። ከዚህ በተጨማሪም የትምርት ሥርዓቱ በተግባር ተኮር ሥነ ዘዴዎች የታገዘ መሆን ይገባዋል።

በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ትልቁን ለውጥ ለማምጣት፤ ከከፍተኛ ትምህርት ባላነሰ ለለጋ ዕድሜ ዕድገት ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። በለጋ ዕድሜያቸው በሚሰጥ ትምህርት በልጆች ላይ መልካም መሰረት ከተጣለ፤ ቀጣይ ሥራዎች ቀላል ይሆናሉ። ቅድመ መደበኛ ትምህርት ለሕፃናት የተስተካከለ ዕድገት እጅግ ወሳኝ ነው። ተማሪዎች እንዴት ጥሩ ተማሪ መሆን እንደሚችሉ ይማሩበታል፤ ማኅበራዊ ክህሎት ያዳብሩበታል። ራሱን የማወቅና ራሱን የመምራት ዐቅም ያዳብሩበታል። መሠረተ ትምህርትን ያገኙበታል። የውሳኔ አሰጣጥ ክህሎትን ያገኙበታል። ኃላፊነትና መብትን ይለዩበታል። አንዱ ስለ ሌላው ማሰብና መከባከብን ይማሩበታል። የአእምሮ እድገታቸው በሥርዓት የተቃኘ እንዲሆን ያደርጋቸዋል። መካኒካዊ ክህሎትን ያዳብሩበታል። ሕግ፣ ሥርዓትና የሞራል ደንቦችን ያውቁበታል። ለዚህም ነው የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጉዳይ ወሳኝ የሚሆነው።

በለጋ ዕድሜው ያልተቀረጸውን ከፍ ባለበት ዕድሜ ለማስተካከለል መሞከር፤ መሠረቱ የተበላሸን ሕንጻ በልስን ለማስተካከል እንደመሞከር ነው። "ሆድን በጎመን ቢደልሉት ጉልበት ዳገት ይለግማል" እንደሚባለው ይሆናል። በመሆኑም የትምህርት ተሐድሷችን ትኩረት፤ ከሥር መሠረቱ ከማጠናከር የሚጀምር ነው። በለጋ ዕድሜያቸው ተማሪዎች ትምህርት ሊወዱና ዝንባሌያቸውን ለይቶ ሊያሳድጓቸው በሚችሉ ዕውቀቶች፤ ስነ ዘዴዎች፣ መምህራን፣ መሳሪያዎች እና የትምህርት ከባቢዮች መማሪየዎች ትልቅ ውጤት የሚያመጣ

ይሆናል።

ይህንን ለማድረግ መምህራን አካዳሚያዊ ብቃት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ፤ በሥነ ምግባር ምሳሌ መሆን የሚችሉ መሆን አለባቸው። ልጆች "ልክ የሚሉት " እና ልክ አደለም ብለው ለጉዳዮች ብያኔ የሚሰጡባቸው መለኪያዎች፤ ከወላጆቻቸው ቀጥለው መምህሮቻቸው ናቸው። መምህራን ለልጆች የመልካም ባህሪይ አርአያ ሊሆኑ ይገባል።

ለትምህርት የሚሰጠው ክብርና ዋጋ፤ ሀገር ለመምህራን በምትሰጠው ፍቅርና ክብር ይለካል። ስለዘህም ትምህርት በእርግጥም ትውልድን እንዲያሳድግ፤ ለመምህራን ምልመላና ብቃት፣ መብትና ጥቅም የሚሰጠው ትኩረት መለወጥ አለበት። ይኸም ከቅድመ መደበኛ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ማዕከላት ድረስ መሰራት አለበት።

ከፍተኛ ትምህርት መምህራን እና ተቋማት ለሀገር የሚጠቅሙ ምርምሮችን የሚያበረክቱ የአዳዲስ አሳቦች መፍለቂያ ሊሆን ይገባል። ሀገር ለሕመሟ ፈዋሽ የሆኑ መድኃኒት ሐሳቦች፤ ከከፍተኛ የትምህርት ማዕከሎቿ የሚወጡ መሆን አለባቸው። ይኽ እንዲሆን ግን ተቋማቱ በሀገር ውስጥ ከሀገር ርቀው የተቀመጡ መሆን የለባቸውም። ማኅበረሰባቸውን በቅጡ የሚረዱና፤ ስብራቱ ተሰምቷቸው ለመጠገን የሚችል ሃሳብ የሚያቀርቡ ሊሆን ይገባል።

የመደመር ትውልድ ዕውቀት ከምንጊዜውም በላይ ለሀገር የሕልውና ጉዳይ እየሆነ እንደሚመጣ ተገንዝቦ፤ ካለው ትውልድ የተላለፉ ቱሩፋቶችንና ተግዳሮቶችን በሚገባ በማጤን፤ ዘርፉን የማያቋርጥ የኢትዮጵያ ተስፋዎች መፍለቂያ ለማድረግ መሥራት ይኖርበታል። ከዚህም ባለፈ፡ የሀገራችንንና የአህጉራችንን ችግሮች ለመፍታት ትኩረት ያደረጉ ምርምሮችና ምርቶች በስፋት የሚከወኑበት፤ በውጤቶቹም መላውን ዓለም የሚጠቅም ዘርፍ፤ እንዲሆን አድርጎ መቅረጽ ይጠበቅበታል።

# ምዕራፍ አሥር

## መካከለኛው ምሥራቅ ለመደመር ትውልድ

## ዕድል ወይስ እክል?

# የጂኦፖለቲካ ዕይታ ለውጥ

ውስጣዊ ጉዳዮች ለሀገር ጥንካሬ እጅግ ቁልፍ ሚና አላቸው ። ቢሆንም ሀገር ተነጥላ መኖር ስለማትችል፤ከውጭው ዓለም ጋር የሚኖራት ግንኙነት በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ጫና ማድረጋቸው አይቀርም። በዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርሱ ተዋንያን ጋር የሚኖር ግንኙነት፤ በአንድ ሀገር ጉዳይ ውስጥ እንዲሁም በትውልዱ ላይ ዐሻራ ማሳረፍ አይቀርም ። ስለዚህም ትውልዱ አካባቢውን መቃኘትና አዳዲስ ለውጦችን መመልከት አለበት ። ቀጣዩ ትውልድ ሊመለከታቸው ከሚገባቸው አዳዲስ ለውጦችና ዓለም አቀፍ ተዋንያን መካከል፤ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት እና ጂኦፖለቲካው አንዱ ነው ።

መካከለኛው ምስራቅ የሚባለው ጂኦፖለቲካዊ ቀጣና፤ ከፋርስ (ኢራን) እስከ ቱርክ ምዕራባዊ ድንበር ያለውን ቦታ የሚሸፍን ነው። በውስጡ ሳዑዲ ዓረቢያን፤ ቱርክን፤ ግብጽን፤ እሥራኤልን፣ ዮርዳኖስን፣ ሊባኖስን፣ ሶሪያን፣ ኢራንን፣ ኢራቅን፣ ቆጵሮስ፣ ኩዌት፣ ባሕሬን፣ ኦማን፣ ኳታር፣ የተባበሩት የዐረብ ኤምሬቶች እና የመንን ይይዛል። ኢየሩስሌምን፣መካን፣መዲናን፣ የዮርዳኖስ ወንዝና የዘምዘም ምንጭን የመሳሰሉ፤ በአማኞች ዘንድ ከፍተኛ ትርጉም ያላቸው ቅዱሳት መካናት ያቀፈ አካባቢ ነው። የትኛውም ሃይማኖተኛ ሰው እነዚህን ሥፍራዎች በሕይወት ዘመኑ መጎብኘትና በረከት መቋደስን ይመኛል። ይኸንንም ተከትሎ እነዚህ ቅዱሳት መካናት የሚገኙባቸው ሀገራት፤ በሃይማኖተኞች ዘንድ በልዩ ቦታነት የሚታዩ እንደ መሆናቸው፤ መካከለኛው ምስራቅ በብዙኀን ዘንድ ትኩረትን የሚስብ አካባቢ ነው። ከሃይማቶች መስፋፋት አስቀድሞ አካባቢው በዓለማችን ቀደምት የሚባሉ ሥልጣኔዎች የበቀሉበት ነው። የግብጽ፣የሜሶፖታምያ፣የፋርስ፣የባቢሎን፣የሱሜርያውያን፣የአሦራውያን ሥልጣኔዎች ተገኝተውበታል ። መካከለኛው ምሥራቅ በጥንቱ ዘመን ከፋሪስ ወዲያ ማዶ የነበረው ምሥራቁ ዓለምና፤ ከእሥራኤል ወዲህ ማዶ ያለው ምዕራቡ ዓለም የሚገናኙበት ሥፍራ ነው። ሦስቱ ከጥንት የታወቁት አህጉራት ማለትም አፍሪካ፣አውሮፓና እስያ የሚገናኙትም በመካከለኛው ምሥራቅ በኩል ነበር። በዚህም ምክንያት የሕዝብ ንቅናቄ፣የንግድ፣የባህል ልውውጥና የወታደራዊ እንቅስቃሴዎች ዋና ማዕከል ነበር። ሦስቱ የዓለም ታላላቅ ሃይማኖቶች (ይሁዲነት፣ክርስትናና እስልምና ) መነሻቸው መካከለኛው ምሥራቅ ነው።

በጥንቱ ወታደረዊ አስተሳሰብ መካከለኛው ምሥራቅን የተቆጣጠረ፤ ዓለምን እንደተቆጣጠረ ይቆጠር ነበር። በዚህም የተነሣ አካባቢው ዋና የጦርነት ቀጣና ሆኖ ኖሯል። አሦራውያን፤ ባቢሎናውያን፣ ግሪካውያን፣ ሮማውያን፣ ሞንጎላውያን፣ ፋርሶች፣ አረቦች፣ ቱርኮች፣ ፖርቱጋሎች፣ ስፔኖች፣ ፈረንሳዮች፣ እንግሊዞች በየዘመናቸው መካከለኛው ምሥራቅን ለመያዝ ብርቱ ጥረት አድርገዋል።

እነዚህ የተለያዩ ሥልጣኔዎችና ባህሎች የአካባቢውን ፖለቲካ በመቅረጽ ረገድ አስተዋጽዖ አደርገዋል። አሁን ያለውን አካባቢያዊ ቅርጽና ፖለቲካ መልክ እየያዘ የመጣው ግን፤ በዋናነት ከኦቶማን ቱርክ ግዛት መውደቅ በኋላ በተፈጠሩ ክሥተቶች ነው። ይኽ አካባቢ ላለንበት የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና እጅግ ቅርብ፤ለአውሮፓ፣ለእሰያ እና ለአፍሪካ መተላለፊያ እና መገናኛ የሆነ ስትራቴጂካዊ ቀጣና ነው።

የመካከለኛው ምሥራቅ ተፈላጊነት ይበልጥ እየጎላ የመጣው፤በአካባቢው ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ በተከሠቱ ሦስት ታላላቅ ክሥተቶች የተነሣ ነው። ኦቶማኖቹን ተክተው አካባቢውን የተቆጣጠሩት አውሮፓውያን አካባቢውን ለቅቀው ሲሄዱ የፈጠሯቸው የግዛት አከላለሎች፣ አሁን ያሉትን የመካከለኛ ምሥራቅ ሀገራት ፈጥረዋል ። በ1948 እ.ኤ.አ. እሥራኤላውያን ወደ አከባቢ ተመልሰው ሀገር መመሥረታቸው ፤የአካባቢውን ፖለቲካዊ ሁኔታ ቀይሮታል። ከዚህ በተጨማሪ የነዳጅ በአካባቢው መገኘትና ተፈለጊነቱን መጨመር ፤ ኃያላን ሀገሮች በአካባቢው ላይ ተፅዕኗቸው ከባድ እንዲሆን አድርጎታል።

በዘመናዊው የመካከለኛው ምሥራቅ ታሪክ ውስጥ የተከሠቱ ኹነቶችና ለውጦች ፤ ብዙ ኃይላት በአካባበው ላይ ትኩረት በማድረግ ውድድር ውስጥ እንዲገቡ አደርጓቸዋል ። ነገር ግን በአካባቢው ዘመናዊ ታሪክ ውስጥ ዋና ተፅዕኖ ፈጣሪ ሆኖ መውጣት የቻለችው አሜሪካ ናት ። አሜሪካ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ፤ በአካባቢው ዋነኛዋ የደኅንነት አስጠበቂ ኃይል እና የነዳጅ ኢኮኖሚ ዋነኛዋ ተዋናይ ሆና ቆይታለች ።

በአካባቢው ሶሻሊስታዊና ሃይማኖታዊ እሳቤ መስፋፋቱ ፀረ አሜሪካ ኃይላት እንዲፈጠሩ ቢያደርግም ፤ አሜሪካን የአካባቢው ዋነኛ ተፅዕኖ ፈጠሪ ሀገር ከመሆን አልከለከላትም ። ከተወሰኑ ሀገራት ውጭ ፤ ከአካባቢው ዋና ዋና ኃይላት ጋር ግንኙነቷ አሁንም እጅግ ጠንካራ ነው ከእነዚህ አሜሪካን አጋር ሀገራትም ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ በዋናነት በአሜሪካ ላይ ጥገኛ ናቸው ። በተለይም ከቀዝቃዛው ጦርነት በኃላ በነበሩት የመጀመሪያ ሃያ ዓመታት ፤ አሜሪካ ያለ ምንም ተገዳዳሪ በአካባቢው ዋነኛ የደኅንነት ተዋናይ ሆና ቆይታለች ።

የነዳጅ መገኘት የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራትን ሕዝቦችን ከአርብቶ አደርነት ፤ ከሢራራ ነጋዴነትና ከአርሶ አደርነት ፤ ወደ ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ እንዲሸጋገሩ አድርጓቸዋል ። የነዳጅ መገኘት የአካባቢው ጂኦፖለቲካዊ ተፈላጊነት ከመሠረቱ ቢለውጠውም ፤ የአካባቢው ሀገራት ግን ግዙፍ ዓለም አቀፋዊ ኃይል ሆነው ሊወጡ አልቻሉም ።

ብዙዎቹ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች (ከሶሪያ ፤ ከኢራንና ከየመን በስተቀር ) ባለ አንድ ዋልታ በሆነው የዓለም ሥርዓት ውስጥ ፤ የምዕራቡ ዓለም ሁነኛ አጋር ሆነው ቆይተዋል ። በመሆኑም የሚያደርጉት ጂኦፖለቲካዊ እና ደኅንነታዊ እንቅስቃሴ ፤ ምዕራቡ ዓለም በአካባቢው ከነበረው ጂኦፖለቲካዊ ፍላጎት ሥር የሚንቀሳቀስ ነበር ።

ከቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ ተገዳዳሪ አልባ የነበረውን የዓለም ሥርዓት ፤ የሚነቀንቁ ኃይላት ብቅ አሉ ። ዓለም አቀፍ ፖለቲካ በአንድ ዋልታ ጥላ ስር ሊቆይ እንደማይችል እየታየ መጣ ። ዓለም ባለብዙ ዋልታነት አዝማሚያ በማጋደሏ ፤ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት በምዕራቡ ካባ ሥር ከመሸፈን እየወጡ ፤ በራሳቸው የሚቆሙ ኃይሎች መሆነቸውን ማሳየት ጀምረዋል ።

የቻይና እና የሌሎች የእስያ ሀገራት መነሣሣትና የተገዳዳሪ ኃይሎች መፈጠር ፤ የምዕራቡን ጂኦፖለቲካዊ ትኩረት ከመካከለኛው ምሥራቅ ወደ ሩቅ ምሥራቅ እንዲያጋድል አደርጎታል ። በተጨማሪም በመካከለኛው ምሥራቅ ላይ ያለው የነዳጅ ጥገኝነት እየቀነሰ መምጣት ፤ በመካከለኛው ምሥራቅ የነበረው የምዕራቡ

ኃይልና ዐቅም፤ ትኩረቱን ወደ ምሥራቅ በማዞሩ በአካባቢው የኃይል ክፍተት እንዲፈጠር አደርጓል ፡፡

የአሜሪካ በመካከለኛው ምሥራቅ እና በአዋሳኝ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ላይ ያላት ፍላጎት እና እንቅስቃሴ እየቀነሰ መምጣት ፤ የኃይል ክፍተት ፈጥሯል ፡፡ ይኸም የአካባቢው ሀገራት ጎልተው እንዲንቀሳቀሱ በር የከፈተ ነው ፡፡ ሀገራቱ የኃይል ክፍተቱን ለመድፈን እና ደኅንነታቸውን ለማስጠበቅ መስራት ጀምረዋል ፡፡ እንዲሁም በተፈጠረው ክፍተት ውስጥ የአካባው መሪ ሆኖ ለመውጣት እና የኃይል ሚዛኑን ለመጠበቅ እርስ በእርስ እየተፎካከሩ ይገኛሉ ፡፡ ከዚህ አልፈው በዙሪያ ገባው ወታደራዊ ካምፖችን የመመሥረትና ኃይላቸውን የማስቀመጥ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተዋል ፡፡ ይኸም የአካባቢውን ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታ በፍጥነት እየቀያየረው ነው ፡፡

ግጭት በሰፊው  በሚታይበት መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ፤ አንዳንድ ሀገራት ከውጪያዊ ግፊትና ከውስጣዊ ሽኩቻ የተነሣ ፤ ደካማ የመሆንና የመፈራረስ አደጋ አጋጥሟቸዋል ፡፡ በየመን ፣በሶሪያና በኢራቅ የደረሰው ለዚህ ማሳያ ነው ፡፡ ሌሎቹ ሀገራት ደግሞ ስትራቴጂካዊ የነዳጅ ዐቅማቸውን ወደ ዘርፈ ብዙ ኃይል በመቀየር ፤ በዓለም ላይ ተፅዕኖ ከሚፈጥሩ ሀገራት መካከል ሆነዋል ፡፡ ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ ዐቅም ወደ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ኃይል በመመንዘር ፤ የተፅዕኖን አድማሳቸውን ማስፋት ችለዋል ፡፡ የተከማቸው የውጭ ምንዛሬቸው ፖለቲካዊ ተፅዕኖን ለማሳረፊያ ወሳኝ መሣሪያ ሆኗቸዋል ፡፡ ከፍተኛ የመጠባበቂያ ክምችት ፤ ብዙ ሀገራትን የሚያማልልና ከሀገራቱ ጋር ግንኙነትን ለመመሥረት የሚያጓጓ ነው፡፡

በነዳጅ የበለጸገ ሀብታቸውን በመጠቀም ሀገራቱ ጠጣርና ገር ኃይላቸውን አዳብረዋል ፡፡ በዚህ ረገድ ዋነኛው ተጠቃሽ የሚሆነው ሀገራቱ ራሳቸውን በወታደራዊ ኃይል ለማጠናከር የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው ፡፡ የፈጠሩት ከፍተኛ የጦር መሣሪያ ፍላጎት ፤ በመሣሪያ ሻጭ ሀገራት ዘንድ ከፍተኛ ፉክክር እንዲፈጠር አድርጓል ፡፡ በወታደራዊ ረገድ ራሳቸውን የማጠናከርና ደኅንነታቸውን የማስጠበቅ ጥረት ፤ መሣሪያ በመታጠቅ ላይ የተመሠረተ ብቻ ሳይሆን ፤ ከሀገራቸው ተሻግረው ወታደራዊ ሠፈሮችንም እስከ መመሥረት የደረሰ ነው ፡፡ ከዚህም ተጨማሪ  በተለያዩ አካባቢዎች ወደቦችን በማልማት ፤ ስትራቴጂካዊ ቦታዎችን ለመቆጣጠር ችለዋል ፡፡

በንግድ እና በገር ኃይል ረገድ ለመፍጠር የሞከሩት ተፅዕኖም ዋነኛው ዐቅማቸውን ማሳያ ነው ፡፡ በረሃን ወደ ታላላቅ የንግድና የቱሪስት መዳረሻ በመቀየር ፤ ከዓለም ቀዳሚዎቹ የንግድና የቱሪስት ማዕከላት ለመሆን በቅተዋል ፡፡ ከዚህም ውጭ የራሳቸውን ትርክት የሚያስተጋቡበት የሚዲያ ኃይል በእጃቸው አድርገው ፤ በብዙኃኑ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር እየጣሩ ነው ፡፡ ብዙ ገንዘብ በማፍሰስ በአውሮፓ ውስጥ ታዋቂ የሆኑ የእግር ኳስ ክለቦችን ይገዛሉ ፡፡ ታላላቅ ውድድሮችን በማስተናገድ ተሰሚነታቸውን ከፍ ለማድረግ ይሠራሉ ፡፡

በአሜሪካ ጥላ ሥር ከቆየ ጂኦፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ወጥተው ዋነኛ ዓለም አቀፍ ተዋናይ እየሆኑ መምጣታቸው ፤ እየተለወጠ በመጣው የዓለም ኃይል ሚዛን ውስጥ የሚኖረው ድርሻ እጅግ የገዘፈ ነው ፡፡ ዓለም አሁንም ከነዳጅ ጥገኝነት አልተላቀቀም ፡፡

የዩክሬኑን ጦርነት ተከትሎ ምዕራባውያኑ እና ሩስያ የነዳጅ ፍሰትን መቆጣጠር ፤ የኃይል የበላይነትን ለመያዝ

የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለዚህ ማሳያ ነው ። በዚህ ውስጥ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራትን ከጎናቸው ለማሰለፍ የሚያደርጉት ጥረት ሲታይ ፤ ሀገራቱ በዓለም አቀፉ የኃይል ሚዛን እጅግ ተፈላጊ ተዋንያን መሆነቸውን መገንዘብ ይችላል ።

የገንዘብ ዐቅማቸውን በመጠቀም ፡ጠጣር እና ገር ኃይላቸውን ለማጠናከር የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ፤ በቀጣይም ሀገራቱ ኃይላቸው እየተጠናከረ እንደሚሄድ ማሳያ ነው ። ይኽ ኃይል እየገዘፈ ሲሄድ በዓለም ፖለቲካ ላይ ያላቸው ተደማጭነትም እየገዘፈ ይመጣል ። እየተለወጠ ባለው ባለብዙ ዋልታ የዓለም ሥርዓት ውስጥ ፤ ፈርጣማ ተዋንይ ሆነው እንደሚወጡ ከዚህ እንቅስቃሴያቸው መገመት አያዳግትም ።

# በሁለት የውሃ አካላት ሥር

የአፍሪካ ቀንድ ለመካከለኛው ምሥራቅ መካከለኛው ምሥራቅ ለአፍሪካ ቀንድ እጅግ አስፈላጊ አካባቢ ናቸው ። በታሪክም ሁለቱ አካባቢዎች በህዝቦች እንቅስቃሴ ፣በንግድ ፣በወታደራዊ ቅናቁ፣በሃይማኖትና በባህል ሲገናኙ ኖረዋል ። አሁንም በሁለቱ አካባኪ ሀገራት መካከል ያለው ግነኙነት እየሰፋና እየተጠናከረ መጥቷል ። ከዚሁም በኋላ በሚኖሩ ትውልዶች ዘንድ ፤ በሁለቱ አካባቢዎች ሀገራት መካከል የሚኖረው ግነኙነት ፤ በአሉታም ይሁን በአዎንታ እጅግ የገዘፈ ተፅዕኖ ይኖረዋል ። ይኽህ ግንኙነት በብልሐት ከተያዘ ሊጠቅም የሚችል ፤ እንዲሁም አያያዙ ከተበላሸ ብዙ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ሊያስከትል የሚችል ነው ። ስለዚህም ግንኙነቱ ሊፈጥረው ከሚችለው ዕድልም ይሁን አደጋ አንፃር ፤ በነባራዊ እንዲሁም በቀጣይ ዘመናት በቀንዱ እጅግ ትኩረት ከሚፈልጉ ግንኙነቶች መካከል ነው ።

የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት የተፅዕኖ እንቅስቃሴና ደኅንነታቸውን ለማስጠበቅ ትኩረት ካደረጉባቸው አካባቢዎች ዓይናቸው በዋናነት ያረፈው ፤ ወደ ሌላኛው የቀይ ባሕር ዳርቻ ፤ የአፍሪካ ቀንድ ነው ። ይኽ ባሕርን ተሻግሮ ተፅዕኖን የማስፋት ፍላጎት አሁን የተጀመረ ሳይሆን ፤ በየዘመኑ በሁለቱም ዳርቻ የነበሩ ሀገራት ትኩረት ያደርጉበት የዘመናት ስትራቴጂ ነው ።

ከጥንት ጀምሮ በቀይ ባሕር ሁለት ጫፍ ያሉ ሀገራት ፤ ባሕርን ተሻግርው ሌላኛውን የቀይ ባሕር ወሰን ለመቆጣጠርና ግንኙነት ለመፍጠር የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነበረ ። ይኽም በአንደኛው የቀይ ባሕር በኩል የሚፈጠር አደጋም ሆነ ዕድል ፤ በሌላኛው የቀይ ባሕር በኩል ተፅዕኖ እንደሚያደርስ ከመገነዘብ የሚመነጭ ነው ። በአክሱም ሥልጣኔ ዘመን ፤ የእኛው ዐፄ ካሌብ ቀይ ባሕር ተሻግሮ ደቡብ ዓረቢያን ለመቆጣጠር ችሎ ነበር ። ዓረቦች የአካባቢው ኃያላን ሆነው በተነሡበት ከ8ኛው እስከ 14ኛው መክዘ በነበረው ጊዜ ፤ ቀይ ባሕር ተሻግረው የአፍሪካን ቀንድ ለመያዝ ሞክረው ነበር።

የአፍሪካ ቀንድ ፡ አዋሳኝ ከሆኑ የሰሜን አፍሪካ ሀገራትና ባሕር ተሻግሮ ከሚገኙት የባሕረ ሰላጤው ሀገራት ጋር ፤ ከፍተኛ መልክአ ምድራዊ ቅርርብ አለው ። ከአህጉራችን ውጭ ለሀገራችን እንደ መካከለኛው ምሥራቅ የሚቀርብ አካባቢ የለም ። አካባቢዎቹ ከፍተኛ የንግድ መተላለፊያ የሆነውንና ሰፊ ወታደራዊ ጠቀሜታ ያለውን ቀይ ባሕርን ከመጋራት ባለፈ ፤ በዓለም ታሪክ ታዋቂ ከሆኑት ወንዞች ማለትም ዓባይ ፤ ኤፍራጥስና

ጤግሮስ ጋር የተሳሰሩ ናቸው ፡፡

በመካከለኛው ምሥራቅ  ከተፈጠሩ ታላላቅ ሥልጣኔዎች መከካል አንዱ የግብጽ ሥልጣኔ ነው ፡፡ ለዚህ ሥልጣኔ መሠረት የሆነውን  የዓባይ ወንዝ መነሻ  ለማወቅ ፤ ግብጻውያን ብቻ ሳይሆኑ ቀደምት የአውሮፓና የመካከለኛው ምሥራቅ አጥኚዎች ሁሉ ሲፈልጉት ነበር ፡፡ ግብጻውያን ግን በተለየ ሁኔታ የዓባይን መነሻ ማስጠበቅና መቆጣጠር የዘመናት ፍላጎታቸው ሆኖ ኖሯል ፡፡ ኢትዮጵያውያንም የዓባይን ውሃ እንደሚገባ አለመጠቀም የዘመናት ቁጭታቸው ነበር ፡፡

ከዛሬ 700 ዓመታት በፊት የኖሩት ኢትዮጵያዊው ዐፄ ይሰሐቅ ዐባይን ለመገደብ ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው ፡፡ ከዘመኑ የሰሜን ምሥራቅ ስፔን ኃይል መንግሥት ከአራጎን የውሃ ባለሙያዎችን ለማስመጣት ፤ አልጣብሪዚ በተባለ ሰው የሚመራ የሉኡካን ቡድን ወደ አልፎንዞ 5ኛ በ1420  ዓ.ም ልኮ ነበር ፡፡ የሉኡካን ቡድኑ ወደ መካከለኛ ምስራቅ ሄዶ 13 ባለሙያዎችን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ጉዞ ጀመረ ፡፡ ነገሩን ሲከታተሉ የነበሩት ግብጾች አልጣብሪዚንና ባለሙያዎቹን የካቲት 20 ቀን 1421 ዓ.ም በግብጾች በኩል ሲያልፉ ይዘው ገደሏቸው ፡፡ የኢትዮጵያውያን በዓባይ ውሃ የመጠቀም ዕቅድ በየዘመናቱ በዚህ መልኩ ሲከሽፍ ኖሯል ፡፡

ከዓባይ ውሃ በተጨማሪ በቀጣናችን እና በመካከለኛው ምሥራቅ መካከል መልከአ ምድራዊ ትሥሥርን የሚፈጥረው ቀይ ባሕር ነው ፡፡ ቀይ ባሕር ለሁለቱም አካባቢዎች የንግድ መገናኛ መሥመር ነው ፡፡ የቀይ ባሕር ዳርቻዎችን መቆጣጠር እና ንግዳቸውን ማሳለጥ ለቀደምት ሥልጣኔዎች ቀዳሚ አጀንዳ ነበር ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወደ ሕንድና ቻይና ይደረጉ የነበሩ ንግዶችና ጉዞዎች የሚካሄዱት በቀይ ባሕር በኩል ወደ ሕንድ ውቅያኖስ በመሻገር ነበር ፡፡ በአጠቃላይ እጅግ ዘርፈ ብዙ አስፈለጊነት ባላቸው መልከአ ምድራዊ አካላት መተሣሠራቸው ፤ ትብብርንም ይሁን ሥጋትን እንዲካፈሉ ፤ አንደኛው ሌላኛውን በመልካም ዕይታም ይሁን በዓይነ ቁራኛ እንዲመለከቱ አደርጓቸዋል ፡፡

በውሃ አካላቱ ላይ ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስከበር ዲፕሎማሲያዊ መንገድን ፣ግጭትን እና ጦርነትን ይጠቀማሉ ፡፡ የዐፄ ካሌብ ባሕርን ተሻግሮ የፋርስ ባሕረ ሰላጤ አካባቢዎችን መቆጣጠር የዚህ ሙከራ አንዱ ማሳያ ነበር ፡፡ እንዲሁም በዘመናዊ ታሪክ  ውስጥ የቀይ ባሕርና የዓባይን ውሃ ለመቆጣጠር የተደጉ የኃይል ፣ የማባበል እና የማታለል እንቅስቃሴዎች፤ ተደጋጋሚ የቀጥታና የእጅ አዙር ጦርነቶችና፤ ውስጣዊ ግጭቶችን በመለኮስና በማቀጣጠል ሀገር የማዳከም ጥረቶች፤ ጥቅምን ለማስከበር የሚደረጉ ሙከራዎች ማሳያዎች ናቸው ፡፡ የዓባይ ውሃን በበላይነት ለመቆጣጠር የተፈረሙ የቅኝ ግዛት ውሎችና በተለያዩ ወቅቶች የተደረጉ ጦርነቶች ዓላማቸው የምንጩን ውሃ መቆጣጠር ነበር፡፡

መልክአ ምድራዊ ቅርበትና መተሣሠር ዘመናትን የተሻገረ የሕዝብ ንቅናቄን አስተናግዷል፡፡ ከመካከለኛው ምሥራቅ ተነስቶ ወደ ምስራቅ አፍሪካ፤ ከምሥራቅ አፍሪካ ተነስቶ ወደ መካከለኛው  ምሥራቅ ለመጓዝ፤ የባብኤል ወሸመጥ ዋነኛው መተላለፊያ ነበረ ፡፡ ሌላኛው አማራጭ በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ በኩል የሚገኘውን የሲና በርሃን ማቋረጥ ነው፡፡ አያሌ ሕዝቦች ከመካከለኛው ምሥራቅ ተነስተው ወደ ምሥራቅ አፍሪካ መጥተዋል፤ ከአፍሪካም ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ተጉዘዋል፡፡ በሁለቱ የቀይ  ባሕር ዳርቻዎች

የተደረጉ የአርኬዎሎጂ ምርምሮችም፤ ተመሳሳይ ሥልጣኔዎችን፣ ቋንቋዎችንና ባህሎችን አሳይተዋል፡፡

ከዚህ ሕዝብ ንቅናቄ ጋር በተያያዘ በባሕርሩ ወዲያና ወዲህ የሃይማኖት፣ የባህልና የቋንቋ ተዛምዶ ተፍጥሯል፡፡ ይኽም የንግድ ግንኙነት እንዲጀመር አስችሏል፡፡ በሁለቱ አካባቢ ሥልጣኔዎች መካከል፤ በዓለማችን ቀዳሚ የንግድ ልውውጦች ይካሄዱ ነበር፡፡ በሀገራችን ቀደምት ሥልጣኔዎችና በመካከለኛው ምሥራቅ በተፈጠሩ ሥልጣኔዎች መካከል፤ መልክአ ምድራዊ ቅርበትን ተከትሎ በተፈጠረ ውድድርና ትብብር ውስጥ፤ የሥልጣኔ መወራረስ ተፈጥሯል፡፡ በቅርሶች እና በአፈ ታሪኮች ውስጥ በሁለቱም አካባቢዎች ተመሳሳይ የቋንቋ አጠቃቀም ይታያል፤ መቀራረብ ያላቸው ትርክቶች ይደመጣሉ፡፡ የሳባ ፊደልና ቋንቋ ዐሻራዎች፣ የንግሥተ ሳባ ትርክቶችና ሌሎች የሥልጣኔ መወራረሶች፤ በሁለቱም የባሕር ጫፎች የነበሩ ሥልጣኔዎች ጥለዋቸው ባለፉት ቅርሶች ላይ ይታያሉ ፡፡

የሃይማኖት መስፋፋት በግንኙነቱ ላይ ተጨማሪ ደረጃን ጨምሮበት፤ አዳዲስ መልክ ያላቸው ግንኙነቶች እንዲፈጠሩ አደርጓል፡፡ የሃይማኖት መምህራን ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው ተጉዘዋል፡፡ የሃይማኖት ስደተኞች ፈተናቸውን ለማለፍ ከአንዱ ወደ ሌላው ሸሽተዋል፡፡ ሃይማኖተኞች ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም ከአንዱ አካባቢ ወደ ሌላው ይጓዙ ነበር፡፡ ይኽ በየዘመኑ በነበሩ የሀገራችን ነገሥታት ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት ሲሰጠው ነበር ፡፡

ሃይማኖታዊ ተጓዦች ሁለት መሠመሮችን ሲከተሉ ኖረዋል፡፡ ዋናዎቹ መዳረሻዎቻቸው ኢየሩሳሌም፤ መካና መዲና ናቸው ፡፡ ወደነዚህ ቦታዎች ለመደረስ አንደኛው መሥመር የባብኤል ወሸመጥን ተሻግሮ ወደ ዓረቢያን መጓዝ ነው፡፡ በዚህ ወደ መካና መዲና የሚሄዱትና ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄዱት ይለያያሉ፡፡ ወደ መካና መዲና የሚሄዱት ወደ ሳዑዲ ሲዘልቁ፤ ወደ ኢየሩሳሌም የሚያመሩት የባሕሩን ዳርቻ ይዘው ወደ ሰሜን ያቀናሉ፡፡

ሁለተኛው መሥመር ደግሞ በሱዳን በኩል ወደ ግብጽ በመዝለቅ፤ በግብጽ በሲና በኩል መሻገር ነው ፡፡ በዚህ መሥመር የሚጓዙትም ሲና ሲደርሱ የመካና መዲና ተሳላሚዎች ወደ ደቡብ ሲወርዱ፤የኢየሩሳሌም ተሳላሚዎች ወደ ሰሜን ያቀናሉ፡፡ ሁለቱም ተጓዦች ግብጽ ውስጥ የሚሳለሟቸው መካናት አሏቸው፡፡ ሙስሊም ተሳላሚዎች ከመካና መዲና አልፈው እስከ ባግዳድ ይዘልቁ ነበር ፡፡ ክርስቲያኖቹም በታናሽ እስያ(ቱርክ) አልፈው እስከ ስፔንና ፖርቹጋል ይጓዙ ነበር፡፡

አንዳንድ ኢትጵያውያንም በሀገራቸው ሰዎችና ከባሕር ማዶ በሚመጡ ባሪያ ፈንጋዩች ተሸጠው ቀይ ባሕርን ይሻገሩ ነበር፡፡ እነዚህ ኢትዮጵያን እስክ ቻይናና ሕንድ ድረስ ተጉዘዋል ፡፡ ከእነዚህ መካከል እጅግ የታወቀው ማሊክ አምባር ነው፡፡ በ1540 ዓ.ም. አካባቢ በሐረር ሡልጣኔት ውስጥ የተወለደው ማሊክ አምባረ፤ በትውልድ አካባቢው ዋቆ ወይም ቻፑ ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡ መጀመሪያ ወደ የመን ተሻገር፤ ከዚያም ወደ ሕንድ ሄደ ፡፡ በሕንድ 50 ሺ ሰዎችን ከኋላው ያሰለፈ የጦር መሪ ሆኖ ነበር፡፡ በሕንድ የነበረው የአህመድናጋር ሡልጣኔት ጠቅላይ ሚኒስትር እስክ መሆንም ደርሶ ነበር፡፡ በአካባቢው የሽምቅ ውጊያ ስልትን የጀመረው እርሱ መሆኑ ይነገራል፡፡ በሕንድ ታሪክ ውስጥ የጦር ስልት ዐዋቂና፤ የመንግሥት ግብር አሰባሰብ ሥርዓትን

የዘረጋ፡ በመሆኑ ይታወቃል።

ከኢትዮጵያ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ የሚደረገው ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ፤ ከሁለት ሺ አመታት በላይ ሲከናወን የኖረ ነው። በየአካባቢዎቹ በሚፈጠር የጥቅምና የፖለቲካ ግጭት ምክንያት ፈተና ሲገጥመውም፤ አያሌ ኢትዮጵያውያን ለመካራ ተዳርገዋል። በመንገድ ላይ ይሞታሉ፤ ይራባሉ፤በባሪያ ፈንጋዮች ይሸጣሉ፤ ለግዳጅ የጉልበት ሥራ ይዳረጋሉ። አካባቢውን ለመቆጣጠር የሚነሡ ኃይሎች የንግድና የጉዞ መሥመሮችን ሲዘጓቸው፤ መንገደኞቹ ከሀገራቸውና ከመንግሥታቸው ይነጠላሉ፤ ግፍና ሰቃይም ይደርስባቸዋል ። ኢትዮጵያዊያን በኢየሩሳሌም የነበሯቸው ብዙዎቹን ቦታዎች የተነጠቁት፤ በዚህ የመከራ ሁኔታ ውስጥ ነው።

ቅዱስ ላሊበላ ለሃይማኖታዊ ጉዞ ወደ እያሩሳሌም ተጉዞ ነበር። በዚህ ጉዞው በተሳላሚዎች ላይ የሚደርሰውን እንግልት ተመልክቶታል። ረዥም መንገድን የሚጓዙ መንገደኞች የሚደርስባቸውን እንግልት ለመግታት፤ ኢየሩሳሌም እዚሁ መፍጠር የተሻለ ነው በማለት፤ የሮሐን ከተማ በኢያሩሳሌም ዲዛይን መሠረት ገነባ፤ የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት አቀማመጥና ዲዛይን የተሠራበት መሠራተ ሐሳብም ይሄው ነው። ንጉሥ አባ ጂፋር የሐጅ መንገደኞች ደኅነታቸው ተጠብቆ የሚያርፋበትን ሕንጻ በሳዑዲ ገዝተው ነበር።

ጥንት የነበረው ሌላው ትልቅ ሃይማኖታዊ ፍላጎት የሃይማኖት አባቶችን ማሰመጣት ነበር። ክርስትናም ሆነ እስልምና በኢትዮጵያ ሲሰበክ፤ በመካከለኛው ምሥራቅ የነበሩ የሓይማኖት አባቶች ተፈላጊነታቸው ጨምሮ ነበር። በተለይም የክርስቲያን ሥርወ መንግሥት እና የሙስሊም ሥርወ መንግሥት በነበራቸው ሽኩቻ ውስጥ የበላይነትን ለመቆጣጠር፤ የሃይማኖት መሥመርን ተከትሎ የሚደረግ እንቅስቃሴ ብዙ ነበር። ኢትዮጵያ ጳጳሳትን የምታስመጣው ከግብጽ ስለነበር፤ ግብጾች ይኽንን ዕድል ለፖለቲካ መጠቀሚያ ለማዋል በብርቱ ታግለዋል። የዓባይን ውሃ ለመቆጣጠር በነበራቸው ፍላጎት የተነሣ ጳጳሳትን እንደ መያዣ ይጠቀሙ ነበር። የሙስሊሙን ስርወ መንግሥትና የክርሥቲያኑን ሥርወ መንግሥት በማጋጨት፤ የኢትዮጵያን ዐቅም ለማደከምም ሠርተዋል።

መካከለኛው ምሥራቅ ለመቆጣጠር የሚፈልጉ የውጭ ኃይሎች የመሻኮቻ ሜዳ ካደረጓቸው ሀገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ነበረች። እነዚህ ውጫዊ ኃይሎች ከኢትዮጵያ ጋር ሊያደርጉት በሚፈልጉት ግንኙነት ምክንያት፤ ኢትዮጵያውያን ተጓዦች በመካከለኛው ምሥራቅ ፈተና ይገጥማቸው ነበር። በ1518 ዓ.ም. ኢያሩሳሌምን ለመሳለም ከተጓዙት 348 ኢትዮጵያውያን መካከል በሕይወት የተረፉት 15ቱ ብቻ ነበሩ ። አልቫሬዝ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ምጽዋ ላይ እነዚህን ተሳላሚዎች አግኝቷቸው ነበር። ተሳላሚዎቹ // ይኽ ሁሉ መከራ ያጋጠመን በእናንተ ወዳጅነት ምክንያት ነው // ሲሉ እንዳማረሩት ይናገራል። ይኽም የውጭ ኃይሎች ለራሳቸው ጥቅምት ሲሉ የሚያደርጉት ግንኙነት፤ ይፈጥር የነበረውን ችግር የሚያሳይ ነው ።

ሮማውያንና ግሪኮች በመካከለኛው ምስራቅ በነበራቸው ግዛት ኢትዮጵያን ከጎናቸው ለማሰለፍ ታግለዋል። በኋላም ቱርኮችና ፖርቹጋሎች ቀይ ባሕርንና አካባቢውን ለመቆጣጠር በነበራቸው ሽኩቻ ኢትዮጵያን ከጎናቸው ለማድረግ ጥረዋል። በ16ኛው መከዘ መጀመሪያ በክርስቲያኑና በሙስሊሙ ሥርው መንግስታት መካከል የነበረው ጦርነት የዚህ ውጤት ነው። ፖርቹጋል ክርስቲያኑን፤ ቱርክ ደግሞ ሙስሊሙን ሥርወ መንግስት

ደግፈው ተዋግተዋል። በዘመናዊ ታሪክ ውስጥም እንግሊዝ፣ግብፅ፣ፈረንሳይ፣ጀርመን፣አሜሪካና ሩሲያ ተመሳሳይ ታሪክ ፈጽመዋል።

በሀገራችን እንዲሁም በአጠቃላይ በአፍሪካ ቀንድና በመካከለኛው ምሥራቅ ለተፈጠረው ግንኙነት ታሪካዊ መነሻ የሆኑ ጉዳዮች " ታሪክ ብቻ ናቸው" ተብለው የሚጣሉ አይደሉም። አሁንም እጅግ አስፈላጊ የግንኙነት ነጥቦች ናቸው። ነባራዊም ይሁን ቀጣይ ግንኙነቶቻችን፤ በአዳዲስ ለውጦች እየተቃኙ፤ታሪካዊ መሠረት በተባሉት ግንኙነቶች ላይ የሚወጠኑ ናቸውና።

# ነባር ፍላጎቶች፡ በአዲስ መልክ

በመልክአ ምድራዊ መቀራረብ እና ግንኙነት ምክንያት፡ ከጥንት ጀምሮ በሁለቱ አካባቢዎች መካከል የነበረው የሃይማኖት፣የባህል፣የቋንቋ፣የሥልጣኔና የንግድ ግንኙነት፤ በአዳዲስ ለውጦች ምክንያት የተለየ ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና የደኅንነት መልክ እየያዘ፤ፍጥነቱና ትኩሳቱ እያጨመረ መጥቷል። በዚያው ልክ ለሁለቱም ወገኖች ይዟቸው የሚመጣው ዕድሎችና አደጋዎች አድገዋል። ከቀይ ባሕር በሰተ ምሥራቅ ያሉት ኃያላን የነዳጅ ሀብትና የያዙት ስቲራቴጂካዊ ቦታ የሰጣቸውን ዐቅም ተጠቅመው፤ የተለያዩ ፍላጎቶቻቸውን በመያዝ ወደ አፍሪካ ቀንድ እየመጡ ነው። እስካሁን በዘመናዊው ታሪክ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ወደ አፍሪካ ቀንድ መጡ እንጂ፤ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ኃይልና ዐቅም ይዘው ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ተሻግረው አልሄዱም ።

ምዕራባዊያን በመካከለኛው ምሥራቅና በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያላቸው ፍላጎት እየቀነሰ ነው። በአካባቢው ከነበራቸው የበላይነት ሚና ገሸሽ ማለታቸው፤ ለመካከለኛው ምሥራቅ አዲስ የፖለቲካና የደኅንነት ዕድል ፈጥሯል። የአሜሪካ ከአካባቢው የደኅንነት ሥርዓት እየተላቀቀች መምጣት፤ የአካባቢው ሀገራት ደኅንነታቸው ለማስጠበቅ በራሳቸው ክንድ ላይ ወደ መተማመን አሸጋግሯቸዋል።

በሌላ በኩል የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት፤ የምዕራባዊያን በአካባቢው ያላቸው እንቅስቃሴ እየተቀነሰ መምጣቱ ሊፈጥር የሚችለውን የድጋፍ መቀዛቀዝ ለመተካት፤ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት እንደ ጥሩ አማራጭ ሆነዋቸዋል። በመሆኑም የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ይዘውት የመጡትን ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ድጋፍ እና ሌሎች ትብብሮች፤ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት እጃቸውን ዘርግተው እንዲቀበሏቸው እያደረገ ነው።

በሽብር ቡድኖች እንቅስቃሴ፣በእርስ በእርስ ግጭት እና በሀገራት መካከል በሚደረጉ ጦርነቶች፤ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት የሰላም እና የደኅንነት ሁኔታቸው እየተፈተነ ነው። ስለዚህም ደኅንነታቸውን ለማስጠበቅ፤ ከራሳቸው አካባቢ በመቀጠል ትኩረት የሚያደርጉበት አካባቢ፤ የአፍሪካ ቀንድ ነው። የአፍሪካ ቀንድ መካከለኛው ምሥራቅ የነዳጅ ኃይል ለሚተላለፍበት መሥመር አዋሳኝ እንደ መሆኑ፤ የቀንዱ ሁኔታ ለአጠቃላይ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖለቲካ ትልቅ ተፅዕኖ አለው። ስለዚህም ደኅንነተቸውን ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ትኩረት ቀዳሚ ማዕከላቸው የአፍሪካ ቀንድ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በመካከለኛው ምሥራቅ የሚከሠት ማንኛውም አለመረጋገት፤ በአፍሪካ ቀንድ ጂኦፖለቲካ

ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳርፋል። በመሆኑም አንዱ አካባቢ ለሌላቸው አካባቢ ደኅንነት አስፈላጊ ነው። ምንም እንኳን የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዐቅም ፈጥረው፡ ባሕር ተሻግረው ወታደራዊ እንቅስቃሴ ባያደርጉም፤ ዐቅሙ ያላቸው የመካከለኛ ምሥራቅ ሀገራ፤ የአፍሪካ ቀንድ የባሕር ዳርቻዎች ወታደራዊ መሣፈሪያዎቻቸው ሆነዋል። በቀንዱ ያሉ ወደቦችም በእነዚሁ ሀገራት ቁጥጥር ሥር እያዋሉ ነው።

በጂኦፖለቲካ የተሣሠሩ አካባቢዎች በመሆናቸው፤ በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ከደኅንነት ሥጋት አንጻር ይታያሉ። ለዚህም ነው ፍጹም ኢኮኖሚያዊ የሆነውና ከልማት ፍላጎት የሚነሣው የሕዳሴ ግድብ፤ እንደ ደንኅነት ሥጋት ተቆጥሮ፤ በአፍሪካ ቀንድ ለተፈጠረው ፈጣን እንቅስቃሴ ምክንያት የሆነው ። የሕደሴ ግድብ በጠንካራ ጥረት ወደ ጥሩ አፈጻጸም መግባቱ ፤ በአካባቢያችን ከተፈጠሩ አዳዲስ ሁኔታዎች ጋር ተደምሮ ፤ በአፍሪካ ቀንድ እና በመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ላይ ትልቅ ለውጥ አስከትሏል ። ይኽንን ተከትሎ በቀጣናችን ሰፊ ወታደራዊና የደኅንነት እንቅስቃሴ እንዲሁም ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ለማሳረፍ የሚደርጉ ጥረቶች ተበርክተዋል።

መካከለኛው ምሥራቅ በአብዛኛው በርሃማ ነው። እንደ ሳዑዲ ዓረቢያ ያሉ ሀገሮች ምንም ዓይነት ወንዝ የላቸውም። በመካካለኛው ምሥራቅ ሦስት የውሃ ቀጣናዎች አሉ። የዓባይ፣የዩርዳኖስ፣የኤፍራጥስና የጤግሮስ። ዓባይ፡ ከኢትዮጵያ እስከ ግብጽ፤ ኤፍራጥስና ጤግሮስ፡ ሶሪያ፣ ኢራቅና ኢራን፤ ዮርዳኖስ ደግሞ እሥራኤልና ዮርዳኖስን ያዳርሳሉ። በዚህም የተነሣ የውሃ ፖለቲካ የመካከለኛው ምሥራቅ ዋናው ፖለቲካ እንዲሆን አድርጎታል።

በሦስቱ ዉሃ ቀጣናዎች የሚፈሱ ወንዞች፤ በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ግብርናን ለማልማት ዕድል ሰጥቷቸዋል። ጥንታዊ የሆነው የግብርና ሥራም የተወጠነው በእነዚህ አካባቢዎች ነው የሰው ልጅ ዘመናዊ አኗኗር የውሃን ፍጆታ ጨምሮታል። በዚህም የተነሣ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች ለዘመናዊ አኗኗርና ለግብርና በቂ የሆነ ውሃ ማግኘት አልቻሉም። አብዛኛው አካባቢም በተፈጥሮው የንጹሕ ዉሃ እና የለም መሬት እጥረት አለበት ። ይኽም በአካባቢው የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ትልቅ ዕንቅፋት ሆኗል።

ሀገራቱ አብዛኛውን የምግብ ፍላጎቶቻቸውን የሚያሟሉት ከሌሎች ሀገራት በማስገባት ነው። ይሁንና የዓለም የምግብ ዋጋ አለመረጋጋት፤ በአብዛኛው በውጭ ሀገራት የምግብ ምርት ላይ ለተንጠለጠሉት የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ሥጋትን ፈጥሯል። በመሆኑም የምግብ ዋስትና ጥያቄዎቻቸውን ለመመለስ፤ ከፍተኛ የግብርና ዐቅም ወዳለበትና ቅርባቸው ወደሆነው፤ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ እንዲሳቡ አድርጓቸዋል።

በሁለቱም አካባቢዎች የምግብ ዋስትና ጉዳይ ትልቅ ጥያቄ ነው ። አንደኛው በተፈጠሮ ምክንያት ምግብን ለማምረት እጅግ አዳጋች ሆኖበታል፤ ሌላኛው ተፈጥሮ ቢያድለውም ተፈጥሮን ለመጠቀም ዐቅም ባለመፍጠሩ ተቸግሯል። በሁለቱም አካባቢዎች የምግብ ዋስትና ጥያቄ ኢኮኖሚያዊ የደኅንነት ጉዳይ ነው።

ሀገራችንን ጨምሮ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት፤ ባንጠቀምበትም ፤ ብዙ ሊታረስና ሊለማ የሚችል የግብርና አቅም ያለው መሬት አለን። ኢትዮጵያ የአፍሪካ የውሃ ማማ ናት፤ ወንዞች ፣ሐይቆች፣ጅረቶችና ምንጮች በብዛት አሏት። አራት ዓይነት የአየር ንብረት ታድላለች። ሊታረስ የሚችል አያሌ መሬት አላት። በዚህም በመካከለኛው

ምሥራቅ ያለውን የምግብ እና የንጹሕ ውሃ ፍላጎት ለማሟላት፤ የአፍሪካ ቀንድ ጥሩ አማራጭ ነው። ሀገራቱም ወደ አፍሪካ ቀንድ ከሚያማትሩበት አንደኛው ምክንያት ለግብርና ተስማሚ የሆነ ተፈጥሯልዊ ዐቅም ፍለጋ እንደመሆኑ፤በምግብ ራሳቸውን ለመቻል በግብርና ላይ እያሌ መዋዕለ ነዋይ ለማፍሰስ ይንቀሳቀሳሉ ፤ይኽም በቀጠናዎቱ መካከል የንግድና የኢንቨስትመንት ልውውጥን እያሰፋ ለመሄድ የሚያስችል ትልቁ ዕድል ነው።

በአፍሪካ ቀንድ እያደገ ያለው ኢኮኖሚ፣ሊለማ የሚችል ዕምቅ ኢኮኖሚያዊ ዐቅም እና ሰፊ የሕዝቦች ቁጥር፤ ለመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ሰፊ የገበያ አማራጭ፤ የኢንቨስትመንት ዕድል እና ከፍተኛ የሰራተኞች የሰው ኃይል ምንጭ ነው። ለሀገራችን እና ለአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ምርታቸውን ወደ ዓለም አቀፍ ገበያ ለማድረስ፤ ቅርቡና ጥሩው አማራጭ መካከለኛው ምሥራቅ ነው። ዱባይ እና አቡዳቢን የመሳሰሉት ከተሞች የብዙ ሀገራት ምርት መዳረሻዎችና፤ብዙ ሕዝብ ለመገበያየት የሚከትምባቸው ከተሞች ናቸው።

የሀገራችን ምርቶች ዓለም አቀፍ ገበያን ዘልቀው ገብተው ተወዳደሪ እንዲሆኑ፤ በቅርብ ርቀት ያሉት ዱባይን የመሳሰሉት የንግድ ከተሞች መውጫ በሮች ናቸው።

የመካከለኛው ምሥራቅ የንግድና የቱሪስት ከተሞች፤ ሀገርችንን ለማስተዋወቅ ትልቅ ዕድልን የሚስጡ ፤እንዲሁም ለሀገራችን የተለያዩ የገቢ ምርቶች በቅርብ ርቀት የሚገኙ መነሻዎች ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪ መካከለኛው ምሥራቅ ለሀገራችን እና ለቀንዱ ሀገራት ከውጭ ለሚላክ ገንዘብ (Remittance) አንዱ ምንጭ ነው ። በፍጥነት እያደገ ያለ የሕዝብ ቁጥር ያለበት የአፍሪካ ቀንድ፤ብዙ የሰው ኃይል ፍላጎት ላለበት መካከለኛው ምሥራቅ የሠራተኛ ኃይል ፍላጎት ምንጭ ነው። ኢትዮጵያውያን እና የቀንዱ ሀገራት ዜጎች ፤ለሥራ ፍለጋ የስደታቸው መዳረሻ ከሚያደርጉት አካባቢ መካከለኛው ምሥራቅ አንዱና ቀዳሚው ነው። ወደ አካባቢው የተሰደደው እጅግ ብዙ ሕዝብ፤ ለባሕረ ሰላጤው ቀላል የማይባል የሠራተኛ ኃይል ይሸፍናል። በመሆኑም ይኽ የአፍሪካ ቀንድን መነሻው የደረገ ከፍተኛ የሰው ኃይል ለተነሣባቸው ሀገራት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ነው። ነገር ግን በአብዛኛው ይኽ የሰው ኃይል በሕገ ወጥ መንገድ የተሰደደና ያልሠለጠነ ነው። በዚህም የተነሣ በአንስተኛ ከፍያ የሚሠራ ሲሆን፤ለብዙ ስቃይና እንግልት የሚዳረግ ነው።

በባሕረ ስላጤው ሀገራት የተሰደደው ሕዝብ ለተለያዩ ውዝግቦች ምንጭም ነው። በአብዛኛው በሕገ ወጥ መልኩ የተሰደደ እንደመሆኑ ለተሰደደባቸው ሀገራት ሥጋት መሆኑ አይቀርም። ይኽን እና ሌሎች ጉዳዮን ተከትሎ የሚደርስበት ስቃይ ደግሞ፤ የስደት መነሻ በሆኑ ሀገራት መንግሥትና ሕዝብ ዘንድ ቅሬታን፤ አለፍ ሲልም ብሄራዊ ውርደትን የሚፈጥር ነው።ከዚህም በተጨማሪ በሀገራችን ላይ ተፅዕኖ ለማድረግ እንደ መሳሪያ ሲጠቀሙበት ይስተዋላል።

ይኽ ሠራተኛ የሰው ኃይል በስደት ብዙ ችግሮች የሚስተዋሉበት ቢሆንም፤ ለአፍሪካ ቀንድ ሀገራትም ይሁን ለመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ብዙ አበርከቶ አለው። በሥርዓት ከተያዘ ደግሞ፤ ችግሮችን በመቀነስ አበርክቶው ከዚህም በላይ ከፍ ሊል ይችላል።

የባሕረ ሰላሌው ሀገራት፤ ከተወላጁ ይልቅ በስደት የመጣው ህዝብ ቁጥር የሚበልጥባቸው፤ በስደተኞች የተገነቡ ናቸው ማለት ይቻላል። እንደ ሕንድ የመሳሰሉ ሀገርት የሠለጠነ የሰው ኃይላቸውን በመላክ፤ ለሀገራቱ ግንባታ ትልቅ አስተዋጽዖን አድርገዋል። ለራሳቸውም ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አግኝተዋል። በመሆኑም የሰው ኃይሉን መልክና ቅርጽ ማስያዝ ቢቻል፤ ለሁለቱም አካባቢዎች ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ አበርክቶ ያለው ጠንካራ የግንኙነት መሥመር መሆን ይችላል።

# ሽሚያ ከአፍሪካ ቀንድ ሳሕን

በመካከለኛው ምሥራቅና በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት፤ በአንዱ አካባቢ የሚታይ የእሳቤ፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ፣ ወዘተ. ልዩነቶችና መከፋፈሎች፤ ይኽንንም ተከትሎ የሚመጣው ሽኩቻ፤ በሌላኛው የቀይ ባሕር ዳርቻ ላይ ይንጸባረቃል። በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ ያለው ሃይማታዊ መከፋፈል፣ መሥመሩን ጥብቆ በቀጣናችን ላይ ተፅዕኖውን ያሳድራል።

በመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት መካከል፤ ሃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ መልክን የቀላለቀለ የእሳቤ ልዩነትና ውድድር አለ። ይኽም የዓለም የፖለቲካ ሥርዓት የኃይል ሚዛን ሽግግር ውስጥ መግባቱን ተከትሎ የበላይነትን ለማያዝ ወደ ለየለት ግጭት እና ጦርነት ገብቷል ። ሀገራቱ በቀንዱ ኢኮኖሚያዊና ደህንነትን የማስጠበቅ ፡ ውድድራዊ መልክ የተላበስ፡ ፍለጎቶች አሏቸው። በሃይማኖታዊና በፖለቲካዊ እሳቤ ክፍፍል ሳቢያ በመካከለኛው ምሥራቅ ጠርቶ ያልወጣ የኃይል ሚዛን ፉክክር አለ። በዚህ ፉክክር የአንደኛው መስፋፋት፤ ሌላኛው በቀንዱ ውስጥ የርዕዮተ ዓለም መሠረት፣ የፖለቲካ ድጋፍና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዳይኖረው በመከላከል ላይ፡ የተመሠረተ ነው።

ይኽ አይነቱ በውድድር ላይ የተመሠረተ መስፋፋት፤ የቀንዱን ሀገራት በውድድሩ ጎራ ውስጥ በመክተት የመከፋፈል አዝማሚያ አለው። ይኽም ብቻ ሳይሆን በሀገራት ውስጥ ባሉ የፖለቲካ ስንጥቆች ዘልቆ በመግባት፤ ስንጥቆቹ እንዲሰፋ በር የሚከፍት ሆኗል። በነዳጅ ሀብት ዐቅማቸውን ያፈረጠሙት ሀገራት፤ ወደ ቀንዱ ይዘውት የሚመጡት ረብጣ ዶላር፤ በፋይናንስ እጥረት ለሚሰቃዩት የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ብዙ ችግሮችን ለመቅረት የሚያስችል፤ ጥሩ የፋይናንስ አማራጭ ነው። ይኽ በውድድር ይዘውት የሚመጠት ድጋፍ፤ በቀንዱ ሀገራት መካከል ያልተገባ ፉክክርና ውጥረትን ሲፈጥር ይታያል። ቀንዱን የፉክክራቸው ቅጥያ ሜዳ እና የእጅ አዙር መፋለሚያ በማድረግ፣ ውጥረት ውስጥ እየከተቱት ነው።

በመሆኑም እነዚህ ከታሪክ የሚወራረሱ የግንኙነት መሥመሮችና አዳዲስ ፖለቲካዊ ለውጦች፤ መልክአ ምድራዊ ቅርበት ያላቸውን ሁለቱን አካባቢዎች፤ ይበልጥ ፖለቲካዊ በሆነ መንገድ በማቀራረብ ጂኦፖለቲካዊ አሐድ አድርጓቸዋል። በሁለቱ የቀይ ባሕር ዳርቻዎች ባሉ ሀገራት መካከል፤ ከምንም ጊዜም የበለጠ ጂኦፖለቲካዊ ትሥሥር እንዲፈጠር አድርጎታል። የቀይ ባሕር ሁለት ጫፎች እንደ አንድ ጂኦፖለቲካዊ ቀጣና እንጂ፤ እንደ ተለያየ ጆኦፖለቲካ የሚታይ አይደለም። ቀይ ባሕር የአፍሪካ ቀንድ መጨረሻ እና የመካከለኛው ምሥራቅ መጀመሪያ ተደርጎ ብቻ የሚታይ አይደለም። ቀይ ባሕርን ተሻግሮ በአፍሪካ ቀንድና በመካከለኛው

ምሥራቅ መካከል እጀግ እየጨመረ የመጣ ጂኦፖለቲካዊ ቅርበትና ትሥሥር ተፈጥሯል፡፡ ቀይ ባሕር የሁለት ክፍላተ አህጉራት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ የደኅንነት እና የመሰል ጉዳዮች መገናኛ እና መተላለፊያ መንገድ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታው በየአንዳንዱ ሀገር ውስጥ፤ እንዲሁም በሀገራት መካከል የሚለዋወጡ ፖለቲካዊ ኹነቶች በአጠቃላይ፤ ጀኦፖለቲካዊ ሁኔታው ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ፡፡ ስለዚህም በዚህ አካባቢ የሚፈጠሩ እያንዳንዳቸው ጉዳዮች ተናጠላዊ ተደርገው የሚታዩ ሳይሆን፤ ከሁለተናዊ ጂኦፖለቲካዊ ተለዋዋጭነት ጋር የሚኖራቸው ሚና ምንድን ነው? ተብሎ የሚቃኝ ነው፡፡

# የትውልድን ትኩረት የሚሻ አካባቢ

ትውልዱ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት መመልከቻ መነጽሩ በሦስት ተያያዥነት ባላቸው ነጥቦች ላይ የሚቃኝ ነው ፡፡ የመጀመሪያው ለሀገራችን ባለው ቅርበት ነው፡፡ በዚህ መልክአ ምድራዊ ቅርበትና ግንኙነት የተነሣ የሃይማኖት፤ የባህል እና የሥልጣኔ መወራረስ ተፈጥሯል፡፡ በአንዱ አካባቢ የተፈጠረ ነገር በሌላው አካባቢ አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ ተፅዕኖ ኖሮታል፡፡ ሁለተኛው ያለው መቀራረብ በአዳዲስ ለውጦችንና ክሥተቶች ታጅቦ፤ ይበልጥ እርስ በእርስ እየተሳሰረ የመጣ ጂኦፖለቲካ መፈጠሩ ነው፡፡ በዚህም ውስጥ በጋራ ልንሠራባቸው ወይም የልዩነት ነጥብ ሊሆን የሚችሉ፤ እኛም እነርሱ ላይ፡ እነርሱም እኛ ላይ የተለያዩ ፍላጎቶች ያለን መሆኑ ነው፡፡ ሦስተኛው ደግሞ እየተለወጠ ባለው ዓለም ውስጥ፤ ካካበቱት ዐቅም የተነሣ ይበልጥ የተጠናከረ ዓለም አቀፍ ኃይል ሆነው የመውጣት ዕድል ያላቸው መሆኑ፡፡ በአፍሪካ ቀንድና በመካከለኛው መሥራቅ በተሳሰረ ጂኦፖለቲካ ውስጥ፤ ጠንካራ አካባቢያዊ ኃይል መኖሩን የሚገነዘብ ነው፡፡

በዚህ መነጽር ውስጥ ትውልዱ ከአካባቢያችን ውጭ፤ በሁለት የተሣሠሩ ጀኦፖለቲካዊ ከባቢዎች ውስጥ የሚንቀሳቀሱ፤ ጠንካራ ተገዳዳሪ ኃይላት መኖራቸውን መገነዘብ አለበት፡፡ ከአካባቢዎቹ መተሣሠር ሊመጣ የሚችለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስና፤ በሚያግባቡ ጉዳዮች ላይ አብሮ ለመሥራት መንቀሳቀስ ይገባል፡፡ ይህንንም ለማድረግ በቅድሚያ ለነባራዊ ሁኔታ እና ከጠንካራ ተገዳዳሪ ኃይል ጋር ለመደራደር የሚያስችል፤ የመደራደሪያ ዐቅም መፍጠር አለብን ፡፡

ትውልዱ የማካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት በአፍሪካ ቀንድ ላይ ያላቸውን ተሳትፎና ተፅዕኖ የሚወልደውን ጥቅምና አደጋ ሊዘነጋው አይገባም፡፡ እየተለወጠ ባለው ዓለም አቀፍ ሥርዓትም ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለው ቦታ ቀላል ስለማይሆን፤ በትውልዱ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ ቁልፍ ሥፍራን የሚይዙ ናቸው፡፡ በመሆኑም ተፈላጊውን ሀገራዊ ጥንካሬ ለማረጋገጥ፤ የሀገራቱን የግንኙነት ሂደት በመመልከት፤ በቀጣይ ሊኖር የሚችል ዕድልን ለመጠቀምና አደጋን ለመከላከል የሚያችል ሥራ መሥራት አለበት፡፡ ከእነዚህ ሀገራት ጋር በእኩል ለመደራደር የሚያስችል ጂኦፖለቲካዊ ዐቅም መፍጠር ያስፈልጋል

እየሰፋና እያደገ የመጣው ዐቅማቸው እንዲሁም ከአፍሪካ ቀንድ ጋር ያላቸው ግንኙነት፤ ለቀጣይ ትውልድ ከሀገራቱ ጋር የሚኖረው ግንኙነት አማራጭ ሳይሆን፤የግድ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሀገራቱ ለሀገራችን የመልማት ዕድልን የሚፈጥሩ ሰፊ የገንዘብ ዐቅም ያላቸው ናቸው፡፡ የንግድ ልውውጥን

ሊያሰፋ የሚችል የገበያ መዳረሻ በሀገራችንና በመካከለችው ምሥራቅ ሀገራት ዘንድ መኖሩ ለግንኙነቱ ትልቅ ዕድል ነው። በሀገራችን ያለው ሰፊ የሕዝብ ቁጥርና፤እያደገ የመጣው ኢኮኖሚ የሚፈጥረው የገበያ ዐቅምና፤ በመካከለኛው ምሥራቅ ያለው ከፍተኛ የፍጆታ ፍላጎት፤ የንግድ ልውውጥን የመሚያጠናክር ነው።

በዚህ የግንኙነት ትሥሥር ረገድ አንደኛው ትኩራታችን ሊሆን የሚችለው፤የግብርና ዐቅምን ማሳደግ ነው። የግብርና ዐቅምን ማሳደግ በአንድ በኩል ራሳችንን በምግብ በማስቻል፤ ምግብን ተንተርሶ የሚቃጣብንን ዓለም አቀፍ ተፅዕኖ ለመመከት ያስችለናል። በሌላ በኩል ደግሞ የግብርና ምርቶችን በሰፊው ከሚያስገቡት ሀገራት ጋር ግንኙነትን ለማጠናከር ሁነኛ መሣሪያ ይሆነናል። የተለያዩ ሀገራት የግብርና ምርታቸውን ከመካለኛው ምሥራቅ ፍላጎት አንጻር ሠርተው አትራፊ ሲሆኑ ታይቷል። ጥራት ያለው፣ደኅንነቱ የተጠበቀና በሥርዓቱ የታሸገ ምርት ይዞ መቅረብ፤ በተጠቃሚዎች ዘንድ እምነትን በመፍጠር፤በምግብ  ገበያው ውስጥ ዘልቆ ለመግባት ያስችላል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር በቀጣይ ዓመታት በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ መምጣቱ አይቀርም የሕዝብ ቁጥር ማደግ ብቻ ሳይሆን፤ ካለው ሕዝብ መካከል አብዛኛውን ድርሻ የሚወስድው፡ ኢኮኖሚያዊ ዐቅም የሆነው ወጣቱ ነው። ይህም በመሆኑ በሀገር ውስጥ ሊፈጠር ከሚችለው ኢኮኖሚያዊ እሴት በተጨማሪ፤ በሌሎች ሀገራት የሥራ ገበያ ውስጥ ተሠማርቶ ተጨማሪ ሀብትን ሊያመጣ ይችላል። ነገር ግን ይህን እሴት ለማግኘት ትውልዱ ተገቢውን ትምህርት እንዲቀሰምና፤ በተለያዩ ሙያዎቸ እንዲሠለጥን ማድረግ ይገባናል። የሠለጠነ የሰው ኃይል በብዛት ማውጣት መቻል፤ከሀገር ውስጥ የሥራ ገበያ በተጨማሪ፤ በመካከለኛው ምሥራቅ የሥራ ገበያ ውስጥ አትራፊ ሆኖ ለመውጣት ያስችላል። ከዚህም ጋር የሕገ ወጥ ስደትን ጉዳይ መልከ ማስያዝ ያስፈልጋል።

ከመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ጋር የሚኖር ግንኙነት የሚፈጥረው ብዙ እድል አለ። ነገር ግን የሀገራቱ በአፍሪካ ቀንድ የባሕር ዳርቻዎች አካባቢ መብዛታቸው፤ በወደብ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ተፅዕኖ የሚፈጥር የደኅንነት ሥጋት ነው። ከዚህም አልፎ የሀገራቱ ሽኩቻ በአካባቢያችን ሊፈጥረው የሚችለው ሥጋት፡ እንዲሁም በመካከለኛው ምሥራቅ የሚነሡ ግጭቶች በሀገራችንና በቀንዱ ላይ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ፤ በትኩረት ሊጤን የሚገባው ነው።

የሀገራቱ በቀጣናችን መስፋፋት የባሕር በር አልባ የሆነችውን ሀገራችን የወደብ አገልግሎት፤ በተዘዋዋሪ በእነዚህ ሀገራት ሥር እንዲወድቅ የሚያደርግ ነው። በመሆኑም ሀገራችን የወደብ አማራጭን ለመፈለግ የምታደርገውን ጥረት በማጠናከር፤ ሊደርስባት የሚችለውን ተፅዕኖ መቀነስ አለባት። ከዚህም በተጨማሪ በቀጣናው እና በባሕር አካባቢ እየሰፋ በመጣው ወታደራዊ  እንቅስቃሴ የሚፈጠረውን ሥጋት ፤ለመቀነስ ብሔራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ የሚያስችል ተገዳዳሪ ኃይል ሆኖ ለመውጣት፤ ትልቅ ዐቅም መፍጠር ያስፈልጋል ። ከዚህ ጋር ተያይዞም ሁለንተናዊ ወታደራዊ ዐቅም መገንባትና የባሕር ኃይል ግንባታን በልዩነት መጠናከር አስፈገላጊ ነው። በተጨማሪም  በዲፕሎማሲ ረገድ ባልጠራው የሀገራት ውድድር መካከል፤ ለአንድ ወገን በማድላት ሊመጣ ከሚችለው ተፅዕኖ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ዲፕሎማሲያዊ ሚዛንን

በመጠበቅ ሊያግባቡን በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ከሁሉም ኃይል ጋር ለመሥራት ዝግጁ መሆነ ውጤትን ያመጣል።

# መውጫ

# //ከትውልድ ወደ ትውልድ//

የቀደመው ትውልድ ላይ ይንጸባረቁ የነበሩ እሴቶች ፣አመለካከቶችና የኑሮ ዘይቤዎች ቀጥሎ በሚመጣው ትውልድ ላይ አሻራቸው ይገኛል ።በተጠናም ይሁን ባልተጠና መንገድ የቀደመው ትውልድ ያለፈባቸው ሁኔታዎች፣ክስተቶችና አጋጣሚዎች ለመጪው ትውልድ ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጽዎ ያበረክታሉ። አዝጋሚ የሆኑ ስነ-ህይወታዊ ለውጦች እንደተጠበቁ ሆነው ፣ትውልዶች የሚያልፉበት መንገድ ከእነሱ በኋላ የሚመጡ ማህበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ኹነቶችን ቅርጽ ያስይዛሉ። የእነዚህ ኹነቶች መቀያየር ከግዜና ከሥፍራ መለያየት ጋር ተደማምሮ ትውልዶች የተለያየ ጠባይና ባህሪያት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ ።በ19ኛው መክዘ መጨረሻ አውሮፓ የነበረው ትውልድ ኑሮውን የሚመራው በፋብሪካዎች ተቀጥሮ በሚያገኘው ገንዘብ ሲሆን ፣በአንጻራዊነት ከሌላው አለም በተሻለ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማረ ፣የመብት ጥያቄዎችን የሚያቀነቅን፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ ለውጦች እንዲመጡ የሚታገል ነበር ።በአንጻሩ በአፍሪካ የነበረው ህዝብ በቅኝ ግዛት ቀንበር ስር ፣በእስያ የነበረው (ከጃፓን በቀር) በፊውዳል ስርዓት ውስጥ ፣በደቡብ አሜሪካ የነበረው በሰፋፊ የጥጥና የሸንኮራ አገዳ አምራቾች የጉልብት ብዝበዛ ውስጥ አልፏል። በ20ኛው መክዘ የመጀመሪያው አጋማሽ በአውሮፓ ሁለቱን የአለም ጦርነቶችን ፣በአፍሪካ የጸረ ቀኝ ግዛት ትግሎችን ፣በአሜሪካ የሲቪል መብት እንቅስቃሴዎችን ፣በእሲያና በደቡብ አፍሪካ ሶሻሊስታዊና አብዮታዊ እርምጃዎች የተቀጣጠሉበት ወቅት ስለነበር የትውልዱ ጠባይና ባህርይም ከእነዚያ ዋና ዋና ማህበራዊ ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ኹነቶች የተቀዳ ነበር። በሃገራችን ባለፉት አንድ መቶ አመታት የነበሩ ትውልዶችን የቀረጹ የተለያዩ ኹነቶች አጋጥመዋል። ጦርነቶች ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያው ለውጦች ፣የአለም የሃይል አሰላለፎች ፣ቴክኖሎጂ ወለድ መቀያየሮች እና ሌሎችም ለትውልዱ ማንነት ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። ከአድዋ ማግስት የተፈጠረው ትውልድ በአገራዊ ፍቅር የነደደና ጀብደኝነትን የሉዓላዊነታችን መጠበቂያ መሳሪያ አድርጎ ተመለክቷል ፤በአንጻሩ የዳግም የጣሊያን ወረራ ትውልዱ የዝመናን አስፈላጊነት፣የትምህርትና በቴክኒካዊ እውቀት የዳበረ ትውልድ ለሃገር የግንባታ ወሳኝ እንደሆነ እንዲያምን አድርጎታል ።ከዚያ በኋላ በነበረው ዘመን እንደ ሰደድ እሳት በመላው አለም የተስፋፋው የሶሻሊስታዊ አይዲዮሎጂ በእኛም ሀገር ትውልዱ የሚተከተክለት አጀንዳ ሆኖ // ህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ወይም ሞት // የሚሉ መፍክሮች ተስተጋብተውበታል ። እሱን ተከትሎ የመጣው ትውልድም የእኩልነት ጥያቄዎችን ለጥጦ በመውሰድ //እስከ መገንጠል// በሚደርሱ የትጥቅ ትግሎች ውስጥ ያለፈ ነው ።

ተከታትለው የመጡ የዘመናዊት ኢትዮጵያ የመጀመሪያ ሶስት ትውልዶች ላይ ጉልህ የሆኑ ሁለት ድክመቶችን እናገኛለን ።የመጀመሪያው ድክመት ትውልዶቹ ከውጫዊ ተጽኖዎች ያላመለጡ መሆናቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የጥቂት ልሒቃን የበላይነት የሚስተዋልባቸው መሆናችው ነው ። በወግ አጥባቂው ትውልድ ወቅት የሃጋራችን ህዝቦች መሰረታዊ የአስተዳደርና የስርዓት ለውጥ እንዲደረግላቸው በመፈለግ ህዝባዊ አመጾችን ማድረጋቸው መሬት ላይ ያለ እውነታ ቢሆንም ፣በትውልዱ ዋና ዋና ልሒቃን ዘንድ ይስተዋል የነበረው ከባህር ማዶ የቀዷቸውን የለውጥ ሃሳቦች ከመኳንቱ ፍላጎት ጋር በማይጻረር መልኩ የመተግበርና ጥገናዊ ለውጥ የማምጣት አዝማሚያ ነበር። አብዮታዊ ለውጥ የማምጣት ውጥን የነበራቸው የህልመኛው ትውልድ አባላት የሆኑ ጥቂት ሊሂቃንም መሬት ላይ ካለው የህዝብ ፍላጎት ይልቅ ፣ከውጪ ያገኙት ርዕዮተ አለምን ሙጥኝ ማለትን የመረጡ ነበሩ ።ልክ እንደ //ህልመኛው ትውልድ// ሁሉ //ውል አልባው ትውልድም// ለለውጥ

ንቅናቄዎቹ መነሻ ያደረጋቸው ሃሳቦች፣የትግል ስልቶችና የመፍትሄ ሞዴሎች ወደ ውስጥ ከመመልከት ይልቅ ወደ ውጪ ያማተሩ ነበሩ።

የመደመር ትውልድን የፈጠረው አብዩት አይደለም።ጥቂት ግለሰቦች ወይም የለውጥ ተዋንያን ሃሳብና ፍላጎቶቻቸውን በጉልበት ጭነውበት የተፈጠረም አይደለም።በግዜ ሂደት ትውልዱ ክፉና ደጉን ተመለክቶ፣የሚጠቅመውን መንገድ ለመምረጥ በሚያደርገው መውተርተር ውስጥ የወለደው የጋራ ጠባይና የኑሮ ዘይቤ ነው።ይኼ በህዝብ ገፊነትና በብዙሃኑ ልሂቃን ትብብር በታሪክ ሂደት የተፈጠረ የህብረተሰብ የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ፍጹም ነው አንልም፤ብዙዎችን ወደ የሚያግባባና ይኼ ነው ተብሎ ወደ ተበየነ ግብ ለመጓዝ የሚያስችለውን ትክክለኛ አቅጣጫ ገና በመፈለግ ላይ መሆኑም አይካድም ። እንደቀደሙት ለውጦች ያለፈውን በዜሮ አባዝቶና አማራጭ ምዕራፎችን ዘግቶ እንደአዲስ ከመጀመር ይልቅ፥ ቀስበቀስ ሪፎርም እያደረጉ መጓዝን የመረጠ ነው ። በዚህ ምክንያት ዙሪያውን በወንዞች ተደርድረው እንደሚያጠጡትና የዘርሩበትን እንደሚያበቅል ለም መሬት ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል። በአግባቡ ከተያዘ መሬቱ ለብሩህ ዘመን መነሻ የሚሆን ትልቅ የለውጥ ስንቅ ነው ።

የልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን ተስፋ የሚወሰነው የዛሬ ትውልድ አባላት እጅ ውስጥ ባለ ዘር ነው። ተስፋ የሚያለመልመውና ትውልዱ እንዲፋፋ የሚረዳው መልካም ሰብል የሚበቅለው ዘር ተዘርቶ ነው። በተመሳሳይ የተስፋችን ተክል ፍሬ ከማፍራቱ በፊት እንዲቀነጭር የሚያደርገውና አንቆ የሚገድለው አረምም ዘር አለው። ሁለቱም ዘር እንደ ለም አፈር በቆጠርነው የዛሬ ትውልድ ላይ ብንዘራው መብቀሉ አይቀርም። መልካም ዘር ያልነው በብዛት እንዲያፈራ ብዙ ጥንቃቄና እንክብካቤ ይፈልጋል። በአንጻሩ አረሙ እንኳንስ ሆን ብለን ዘርተነው ይቅርና ፤ትላንት ጥቂት የነበረው አረም ያለ እንክብካቤ መስፋፋና መብዛት ይችላል ። በፖለቲካችን ውስጥ ትላንትን እንደቀልድ የተዘሩና ችላ ተብለው የታለፉ አረምና አሜኬላዎች ሰፍተውና ገዝፈው ዛሬ ላይ የጋራ ጠብን ችግሮችን ምን ያህል ህይወታችንን እንዳወሳሰቡብን ሁላችንም እናውቃለን ።

የዛሬ ትውልድ አባላት ለሚመጣው ትውልድ የተሻለች ኢትዮጵያን ለማውረስ መልካም ዘር መዝራት ብቻ በቂ አይሆንም፤ከዚህ ቀደም የበቀሉ አረሞች ወደ ነገ እንዳይስፉፉ የማድረግ ድርብ ሃላፊነትም አለበት ።